አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር

# የሴት ቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክ እና ቅኔያት ይዘት ትንተና

በ

እቴነሽ ዋለልኝ

ሰኔ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሴት ቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክ እና ቅኔያት ይዘት ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር

ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ.ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት

በ

እቴነሽ ዋለልኝ

አማካሪ

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር)

ሰኔ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ  ዩኒቨርሲቲ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድኅረ-ምረቃ መርሐ ግብር**

# የሴት ቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክ እና ቅኔያት ይዘት ትንተና

**በ**

**እቴነሽ ዋለልኝ**

**የፈተና ቦርድ አባላት**

| | |
|---|---|
| **የአማካሪ ስም** | **ፊርማ** |
| _______________________________ | ____________________ |
| **የውስጥ ፈታኝ ስም** | |
| _______________________________ | ____________________ |
| **የውጭ ፈታኝ ስም** | |
| _______________________________ | ____________________ |

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ እስከዚች ሰዓት ድረስ ለጠበቀኝ እና እዚህ ላደረሰኝ ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በመቀጠልም የትምህርት ዕድሉን ለሰጠኝና ይህን ጥናት እንዳደርግ በመፍቀድ በተለያዩ ጉዳዮች የደገፈኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምስጋናዬ ይድረሰው።

መምህሬና አማካሪየ የወንድወሰን አውላቸው(ዶ/ር) ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ አቅጣጫ በማሳየት፣ ጽሑፉን በማስተካከል፣ጠንካራና ገንቢ አስተያየትን በመስጠት ጥናቱ ለዚህ እንዲበቃ ስላደረክ እጅግ አድርጌ አመሰግንሃለሁ። አክብሮቴም ከፍ ያለ ነው።

ከጥናቱ ጅማሬ እስከፍጻሜ ድረስ ሳትታክቱ ጥያቄዎቼን ሁሉ በፍቅርና በትህትና ያለስስት ለመለሳችሁልኝና መረጃ ለሰጣችሁኝ እማሆይ አመተ ማርያም እና እማሆይ ኅሪት ደባስ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው።ብዙ የምታገለግሉበትን እድሜ እና ጤና አምላክ ሊቃውንት ያድላችሁ።

ቅኔያቱን በመተርጎምና የተለያዩ ግድፈቶችን በማረም ላገዙኝ የብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተክርስትያን መርጌታ ዳንኤል ኢሳይያስ እና ጥናቱን በማረም ለረዳሽኝ ለክፍል ጓደኛዬ ኤልሳቤጥ ሽመልስ  እጅግ አድርጌ አመሰግናችኃለሁ።

ወንድሜ በመሆንህ ሁሌም ደስ የሚለኝ (ተሜ) አንተን ለማመስገን ምን ቃል ይበቃ ይሆን?!ግን በቃ ፈጣሪ ዘመንህን ይባርከው።

## ማውጫ


ምስጋና ........ i

መግለጫዎች ........ v

አጠቃሎ ........ vi

ምዕራፍ አንድ ........ 1

1. መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 4

1.4. የምርምር ጥያቄዎች ........ 5

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 5

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 6

1.7. የጥናቱ ዘዴ ........ 6

1.7.1. የመረጃ ምንጮችና መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 6

1.7.2 የመረጃ መተንተኛ ስነዘዴ ........ 8

1.8. በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 9

1.9 የጥናቱ አደረጃጀት ........ 9

ምዕራፍ ሁለት ........ 10

2. ክለሳ ድርሳን ........ 10

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 10

2.2 ጽንሰ ሐሳብ ........ 18

2.2.1 የቃል ግጥም ምንነት ........ 18

2.2.2 የቃል ግጥም ባህርያት ........ 19

2.2.3 ቃል ግጥምና የግዕዝ ቅኔ ........ 19

2.2.4 የግዕዝ ቅኔ ምንነት ........ 20

2.2.5 የግዕዝ ቅኔ አጀማመር ........ 22

2.2.6 የቅኔ የሐሳብ ምንጭ ........ 23

2.2.7 አርእስተ ቅኔ ........ 24

2.2.8 የግዕዝ ቅኔ መንገዶች ........ 29

2.3 ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ........ 33

2.3.1 ግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ (Personal narrative theory) ........ 33

2.3.2 ነገረ ፍካሬ....36
2.3.3 የሁለቱ ንድፈ ሐሳቦች ትስስር....38
ምዕራፍ ሦስት....40
3. የቅኔ መምህራኑ የህይወት ታሪክ....40
3.1 የእማሆይ አመተ ማርያም የህይወት ታሪክ....40
3.2 የእማሆይ ኀሪት ደባስ የህይወት ታሪክ....50
ምዕራፍ አራት....57
4. የቅኔ ትንተና....57
4.1 ማህበራዊ ጉዳይ....57
4.1.1 ስለምክር....58
4.1.2 ስለስንፍና....62
4.1.3 ስለሰው ልጅ ከዳተኝነት....64
4.1.4 ስለቅጣት....65
4.1.5 ስለእድሜ....67
4.1.6 ስለዕውቀት....68
4.1.7 ስለሚዜ ክቡርነት....69
4.1.8 ስለኢትዮጵያ....70
4.1.9 ስለሴትነት....72
4.2 ፍልስፍና....80
4.2.1ስለሰው ልጅ ፍላጎት....81
4.2.2 ስለሞት....82
4.2.3 የአምላክን ፍርድ የሚሞግት....86
4.3 ሃይማኖታዊ ጉዳይ....87
4.3.1 ህያውነትን የሚገልጹ....88
4.3.2 ስለትንሳኤ....89
4.3.3 የአምላክ ትንሳኤ ለቅዱሳት አንስት መገለጥ....89
4.3.4 ስለዕርገት....91
4.3.5 ስለአማላጅነት....92
4.3.6 ስለቅዱሳን ተዓምር....93
4.3.7 ሄሮድስ ስላስፈጃቸው የኢየሩሳሌም ህጻናት....94
4.3.8 ስለሰው ተፈጥሮ....95

4.3.9 ስለንጢያት ........ 96
4.3.10 ስለጿጉሜ ........ 97
ምዕራፍ አምስት ........ 99
5. ማጠቃለያ ........ 99
ዋቢ ጽሑፎች ........ 103
አባሪዎች ........ 108
አባሪ አንድ ........ 108
አባሪ ሁለት ........ 130
አባሪ ሦስት ........ 132

## መግለጫዎች

ምስል 1. የእማሆይ አመተማርያም ተማሪዎች ቅኔ ሲቀኙ

ምስል 2. የእማሆይ ጎሪት ተማሪዎች በትምህርት ላይ

ምስል 3. ሴት የዳዊት ተማሪዎች

ምስል 4. እማሆይ አመተማርያም ከቅኔ ተማሪዎች ጋር ቅኔ ሲነግሩ

ምስል 5. ተማሪ ልሳነ ቅኔ ሲዘርፉ

ምስል 6. አጥኝዋ ቃለ መጠይቅ ስታደርግ

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት የሴት ቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክ እና ቅኔያት ይዘት ትንተና በሚል ርእስ የተሰራ ነው። ጥናቱ የግለተረክ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም የሁለት ቅኔ መምህራንን የህይወት ታሪክ ዳሷል። በዚህም ከውልደት እስከ እድገት የነበራቸው ሁኔታ ምን ይመስላል?፤የቅኔ ትምህርቱን የት የት ተማሩ?፤የቤተሰብና የማህበረሰብ ድጋፍ ምን ይመስላል?፤አሁን ያሉበት የማስተማር ሁኔታ እንዴት ነው?፤ የሚሉ ጉዳዮች ተብራርተው ቀርበዋል። ቅኔዎቹንም በመሰብሰብ በማህበራዊ አስራ ስምንት፣ፍልስፍናዊ አምስት እና በሃይማኖታዊ አስር በጥቅሉ ሠላሳ ሦስት ቅኔያት ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር ተመርጠው ተተንትነዋል። ጥናቱ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል። ቀዳማይ መረጃዎች ከባለታሪኮቹና ከተማሪዎቻቸው በመስክ ቆይታ የተሰበሰቡ ሲሆን ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ከቤተ-መጻህፍት ተሰብስበዋል።ጥናታዊ ምርምሩ ቀደምት ተመራማሪዎች ያላነሱትን የሁለቱን ሴት የቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክና ቅኔያቶች በማጥናት በመስኩ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ታልሞ የተካሄደ ነው። በመምህራኑ የህይወት ታሪክ ውስጥ በዋናነት መቼና የት ተወለዱ፣ አስተዳደጋቸው ምን ይመስላል፣ወደ ቅኔው ትምህርት እንዴት ገቡ፣የቅኔውን ትምህርት የትና ከማን ተማሩት፣በትምህርት ወቅት የማህበረሰቡ ድጋፍ እንዴት ነበር፣አሁን ያሉበት የማስተማር ሙያ በምን አይነት ሁኔታ ላይ ይገኛል የሚሉ ታሪኮች የተነሱ ሲሆን በዚህ ታሪክም የቅኔ መምህራኑን ታሪክ፣ ገጠመኞች፣የቅኔ ቤት ህይወት፣የቅኔ ተማሪ የሚያልፍበት ውጣ ውረድ፣ የማህበረሰቡ ድጋፍ ምን እንደሚመስል ተገልጾበታል።ቅኔያቱም በፍካሬ ስልት ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን በትንተናውም ማህበራዊ፣ፍልስፍናዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያነሱ ቅኔያት ቀርበዋል። ማህበራዊ ጉዳዮቹ ማህበረሰባዊ ትችትን፣ምክርን፣አድሎአዊ ፍርድን፣ ስንፍናንና ንቅጣትን፣ሴትነትና እናትነትን የሚያሳዩ ሲሆኑ ፍልስፍናዊ ጉዳዮቹ ደግሞ ሠብዓዊ ምኞትን እና ፍላጎትናን፣ ሞትን የሚሞግቱና የሚያነሱ፣የአምላክን ፍርድ የሚጠይቁ ሲሆን በቅደም ተከተል ቀርበዋል። ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያነሱት ቅኔዎች በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ያሉ በዓላትን፣ዘላለማዊነትን፣የቅዱሳን አማላጅነትን፣ የቅዱሳንን ገድልና ተዓምራት፣የዘመን አቆጣጠር፣ የሚገልጹ ሆነው ተገኝተዋል። የመምህራኑ ታሪክ በዘርፉ ላሉ አካላት እንዲሁም የአብነት ትምህርት ለሚሰጡ ገዳምና አድባራት አስተማሪ ሲሆን የቅኔ ቤትን ውጣ ውረድ ለመረዳት፤የማህበረሰቡን ልማድና አመለካከት የሚያሳይ ሆኖ ታይቷል። ቅኔያቱም በሃይማኖትም ሆነ በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ታላላቅ ዕሳቤዎችን የሚገልጹ መሆናቸው ተስተውሏል።*

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚገለጹባቸው ቃላዊና ጽሑፋዊ የሆኑ ጥበባት ያሏት ሀገር ናት። እነዚህ ሰዋዊ ጉዳዮች ከሚገለጹባቸው የሥነ-ጥበብ ዘርፎች ውስጥ አንዱ የቃል ግጥም ነው። የቃል ግጥም አፈጣጠሩም ሆነ መተላለፊያው ቃላዊ የሆነ በውስጡም በርካታ ጥበቦችን የያዘ መኾኑን ሰለሞን እንዲህ በማለት ይገልጻሉ።"በቃል ግጥም ስር የሚመደቡ ጥበቦች በአብዛኛው በቃል ተደርሰው በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በግለሰብም ሆነ በቡድን የሚቀርብ ጥበብ ነው።"(2007፣129)። ይህ የቃል ግጥም የትላንቱን ፣ የዛሬውንና የነገውን እንዲሁም አጠቃላይ የትውልድን የማንነት ሽግግር የሚያሳይ በመኾኑ የሰው ልጆች ሁለንተናዊ ሀብት ነው ማለት ይቻላል። ፈቃደ "ቃል ግጥም ማለት አደራረሱ፣ አከዋወኑ፣ተስተላልፎው እና አቀራረቡ ብዙ ጊዜ በቃልና በመዜም የሆነ፣በዘፈን ፣በሙሾ፣ በእንጉርጉሮና በሌሎች ተመሳሳይ ዜማዊ ቅርጾች ውስጥ የሚገኝ ህዝባዊ ግጥም ነው"(1991፣ 86) በማለት ይገልጹታል። ከነዚህ ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው ቃል ግጥም በቃል የሚፈጠር ፣በቃል የሚነገር ወይም የሚተላለፍ፣ በየትኛውም ስፍራ፣ ዘመን፣ ማህበረሰብ እና ሁኔታ ሊገኝ የሚችል የህዝብ ሀብት ነው ማለት ይቻላል። ቃል ግጥም ከስፍራ፣ ከዘመንና ከሁኔታዎች አልፎ ለመነገርና ለመሰማት አቅም ያለው የሰዎች የአመለካከት፣ የስሜት እና የፍላጎት መገለጫ ነው።

ከቃላዊ ጥበብ ውስጥ የግዕዝን ቅኔ እናገኛለን። የግዕዝ ቅኔ ሊቃውንቱ ምስጋናውን፣ ነቀፌታውን፣ ተቃውሞና ድጋፋቸውን፣ ስለተፈጥሮና ስለማህበረሰቡ ያላቸውን አተያይና ዕሳቤ ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ በቃል የሚደርሱት ጥበብ ነው። የግዕዝ ቅኔ በቃል ተደርሶ በቃል የሚባል ቢሆንም ጉባኤ ተዘርግቶለት ደረጃ በደረጃ የሚማሩት የጥበብ ዘርፍ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በአብነት ትምህርት ቤቶቿ በርካታ ሊቃውንትን አፍርታለች አሁንም እያፈራች ትገኛለች። በእነዚህ የአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪው ደረጃ በደረጃ የሚያልፍባቸው ጉባኤ ቤቶች አሉ። እነዚህም ንባብ ቤት፣ዜማ ቤት ፣ቅኔ ቤት እና መጻሐፍት ቤት ናቸው። ተማሪው ቅኔ ለመማርና ለመቀኘት ከንባብ በመጀመር በተለያዩ ጉባኤ ቤቶች በመሄድ ከተለያዩ መምህራን ይማራል። ለዚህ ጥናት የተመረጠው ቅኔ ቤት የሚለው ነው። የቅኔ ትምህርት ተማሪውን

እንዲመራመር አዳዲስ ሀሳቦችን እንዲያፈልቅ የማድረግ ሀይል ያለው ድርሰት በመሆኑ ከሌሎቹ ትምህርቶች ልዩ ያደርገዋል።፡

የቅኔ ዕውቀትም ሆነ ትምህርት ሲነሳ አብረው የሚነሱት ወንዶች ናቸው።በዚህ የጥበብ መስክ ሴቶች ብዙ የተለመዱ ባይሆንም አልፎ አልፎ ብቅ ማለታቸው ግን አልቀረም። ከነዚህ በቀዳሚነት የሚነሱት እማሆይ ገላነሽ ነበሩ። በአሁኑ ሰዓትም በውስን ጉባኤ ቤቶች ቅኔ የሚያስተምሩ ሴት መምህራን ቢኖሩም  በዋናነት በአክሱም ፣በባህር ዳርና በታላቁ ገዳም በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያሉት ሦስት ሴቶች ይታወቃሉ። ከጊዜና ከቦታ ውስንነት አንጻር የዚህ ጥናት ትኩረት በሁለቱ ሴት የቅኔ መምህራን በባህር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል እና በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ጉባኤ ዘርግተው ቅኔ የሚያስተምሩትን መምህራን  የእማሆይ ዓመተ ማርያም አሰፋን እና የእማሆይ ኅሪት ደባስን የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸው ሲሆኑ ጥናቱም በአምስት ምዕራፍ ተከፋፍሎ ቀርቧል። ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን፣በምዕራፍ ሦስት የባለቅኔዎቹ የህይወት ታሪክ፣በምዕራፍ አራት የቅኔያቶቹ ትንተና እና ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ነው።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቅኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ከሚሰጡ ትምህርቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የተማሪውን ምርምር የሚጠይቅና የፈጠራ ችሎታን የሚያዳብር ነው። ቅኔ የማይዳስሰው ጉዳይ እንደሌለ ማርዬ ሲገልጹ"ቅኔ ለምርምር ገደብ የለውም ። በመሆኑም ቅኔ ምድራዊ ንጉስን ቀርቶ እግዚአብሔርን እንኳ ይሞግታል። በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን እውነተኛ የሚባሉ ነገሮችን ይፈትናል።ያለገደብ አዳዲስ አመለካከቶችንም ያፈልቃል።"(2006፣91) ባለቅኔዎች በማህበረ ባህሉ አይነኬ የሆኑ እሳቤዎችን፣ እምነቶችን፣መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ትዕዛዛትን ሳይቀር  ይሞግታሉ። ለአብነትም የአለቃ ገብረ ሐና ጉባኤ ቃና፦

ኮንኖ ኃጥኣን ኵሎሙ ኢይደልወከ ምንት፣<br>
አፍቅሩ ጸላዕትክሙ እንዘ ትብል አንተ።

ትርጉም፦-

ጠላቶቻችሁን አፍቅሩ የምትል አንተ<br>
ኃጥኣንን በገሀነም ለምን ትቀጣለህ?<br>
(ማርዬ፣92፣2006)

አለቃ ገብረ ሐና በዚህ ቅኔ አምላክን አንተ የማታደርገውን ለምን እኛን አድርጉ ትላለህ፤አንተ ትዕዛዝህን በማፍረስ የበደሉህን ይቅር ሳትል እኛን የበደሏችሁን ይቅር በሉ ትላለህ በማለት ሲሞግቱ ይታያሉ። በመሆኑም ቅኔ ሀይማኖታዊ፣ፖለቲካዊ፣ማህበራዊ እንዲሁም ዕረቂቅ የሆኑ እሳቤዎች ሁሉ የሚቀርቡበት ፈጠራዊ ድርሰት ነው። በአጠቃላይ ቅኔ ሊቃውንት የሚፈተኑበትና የሚመሰገኑበት ዕውቀት የሚራቀቅበት የባለቅኔዎቹን አዕምሮ በተመስጦ የሚያመራምር ተቀድቶ የማያልቅ የጥበብ ባህር ነው። በቅኔ ሊቃውንቱ ከፈጣሪ እስከ ፍጥረታት ይጠይቁበታል፣ ይሞገሱበታል፣ ነገስታት ሲበድሉና ፍርድ ሲያጎድሉ ይነቀፉበታል፣ ተፈጥሮ ይመረመርበታል፣ ሀሳብ ይመሰጠርበታል አይነኬ የተባሉ ጉዳዮች ይነገሩበታል።

ይህ የጥበብ መስክ ብዙውን ጊዜ ትምህርቱን በመማርም ሆነ ቅኔ በመቀኘት የሚታወቁት ወንዶች ቢሆኑም አልፈው አልፈው ብቅ የሚሉ ሴቶችም እንደነበሩ ኪዳነ ማርያም ጥንታዊው የቆሎ ተማሪ በተሰኘው መጽሐፋቸው "ባለፉት አያሌ ዘመናት ቅኔ የሚያስተምሩ ወንዶች ብቻ አልነበሩም ቁጥራቸው የተመጠነ ይሁን እንጂ የቅኔ መምህራን ሴቶች ነበሩ፤ እነዚህም ወይዘሮ መሰለች፣ ወይዘሮ አበባ፣ ወይዘሮ ሀይመት፣እማሆይ ለኪደሉ እና እማሆይ ገላነሽ ናቸው። ቀደም ያሉትን ሴቶች የቅኔ መምህራን ታሪክ ማወቅ አልተቻለንም አሁን በቅርብ ጊዜ ያረፉት እማሆይ ገላነሽ በጎጃም ክፍለ ሀገር ለሃምሳ (50) ዓመታት ቅኔ አስተምረዋል።"(1980፣39-40) በማለት ይገልጻሉ። እንግዲህ በዚህ የዕውቀት ዘርፍ የሚታወቁት ወንዶች ቢሆኑም አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉ ሴቶችም እንደነበሩ መረዳት ይቻላል። ነገር ግን እነዚህ ሴት የቅኔ ሊቃውንት ከእማሆይ ገላነሽ በስተቀር በቅኔው ሙያ ሴቶች መኖራቸው ብዙም የታወቀ አይደለም። እነዚህ የቅኔ መምህራን ሙያውን ተምረው ሌሎችን ለማስተማር ጉባኤ ዘርግተው በሙያው ተተኪን እያፈሩ ቢሆንም በዘርፉ እያበረከቱ ያለው አስተዋጽኦ በሰፊው የታወቀ አይደለም። ይህ የሆነበት ምክንያትም በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ትኩረት ወንዶቹ ላይና የቅኔው ሙያ ላይ በመሆኑ በዘርፉ ያሉትን ሴቶች ትኩረት በመስጠት ጥናት ባለመካሄዱ ነው።

በሰፊውና ጥንታዊው የቅኔ ሙያ ላይ በቂ ጥናትና ምርምር ተደርጓል ለማለት ባያስደፍርም አበረታች የሆኑ ጅምሮች ግን አሉ ማለት ይቻላል። ጥናታዊ ስራዎቹ ትኩረት የሚያደርጉት የቅኔን ሰምና ወርቅ እሳቤ፣ አወቃቀሩን፣ ሰዋሰውን ለአንባቢ ማሳየት፤ የግዕዝ ቅኔ ከየት መጣነት ላይ ትንታኔ መስጠት፤ የግዕዝ ቅኔ ውስጥ ሴቶች በምን አይነት መልኩ ተስለዋል የሚለውን የሚያሳዩ፤ የጉባኤ ቤቶችን ባህልና የቅኔን አፈጣጠር የሚያስተዋውቁ፤ የቅኔን ይዘት፣ቅርጽና ታሪካዊ እድገቱን የሚያስቃኙ እንዲሁም ቅኔ ከሀይማኖቱ ባሻገር ማህበራዊና

ፖለቲካዊ እሳቤዎች እንደሚቀርቡበት የሚያሳዩ ጥናቶች ናቸው:: በዚህ ጥናት ዳሰሳ ለማድረግ እንደተሞከረው ጥናቶቹ ትኩረት ያደረጉት ቅኔው ላይና ወንዶች ላይ በመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት በጣም አነስተኛ የሴት የቅኔ መምህራን እና ቅኔ አዋቂዎች ላይ ከአንድ ጥናት በቀር  አልገጠመኝም:: በመሆኑም ቅኔን ጉዳያቸው አድርገው ያጠኑ ተመራማሪዎች በስፋት ያላዩትን የሴት የቅኔ መምህራን ቅኔዎቻቸውን ከሕይወት ታሪካቸው ጋር በማቅረብ በዘርፉ ያለውን ክፍተት ለመሙላት እና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ተመስርቼ ይህንን ጥናት አድርጌያለሁ::

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማጥናት ያነሳሱኝ ምክንያቶች በ2011 ዓ.ም የሥነ ጽሑፍና የፎክሎር ጥናቶችን በምማርበት ወቅት ቃላዊ የሆነው የግዕዝ ቅኔ ሰፊ የዕውቀት መስክ እንደኾነ በመረዳቴ ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ የሊቃውንት መፍለቂያ፣የዕውቀት ማስመስከሪያ የሆነው ታላቁ ገዳም ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ለአካባቢዬ ቅርብ በመሆኑ እና በገዳሙ ሴቶች እና ወንዶች  ስፍራ ለይተው ጉባኤ ዘርግተው ቅኔ የሚማሩበት በመሆኑ ነው:: በተለይም በገዳሙ ሴት የቅኔ መምህር በመኖራቸውና እሳቸውም በሌሎች ጉባኤ ቤት ካላቸው ገዳምና አድባራት በተለየ ሴቶችን ለይተው ሲያስተምሩ በመመልከቴ እንዲሁም በዚሁ በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ለረጅም ጊዜ የቅኔ ትምህርታቸውን ተከታትለው በአሁኑ ወቅት በባህር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ቅኔ በማስተማር ላይ ያሉትን የእማሆይ አመተ ማርያም አሰፋን ታሪክ በመስማቴ ሲሆን በእነዚህ ሴት የቅኔ መምህራን ላይ ግን የተጠና ጥናት ባለመኖሩ የሁለቱንም የቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን በማጥናት በሙያው ያሉትን ሴቶች ከማስተዋወቅ አንጻር ፋይዳ ይኖረዋል በሚል ነው:: ሌላው ምክንያት የተሰሩ ጥናቶችን ዳሰሳ ባደረኩበት ወቅት በሴት የቅኔ መምህራን እና በነሱ እውቀት ላይ የተደረገ ሰፊ ጥናት ባለመኖሩ የነዚህን ሴት ቅኔ አዋቂ የህይወት ታሪካቸውንና የቅኔ ሀብታቸውን ባጠና በቅኔው ሙያ ሴቶች ያላቸውን የቅኔ ዕውቀት ሀብትና የማስተማር ልምድ ለሌሎች ጉባኤ ቤቶች ከማስተዋወቅ አንጻር ያለውን ፋይዳ በማሰብ ነው::

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ አንድ ዓብይ አላማ እና አራት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት:: የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ የእማሆይ ኀሪት ደባስን እና የእማሆይ አመተ ማርያም አሰፋን የህይወት ታሪካቸውን

ማጥናትና የሚቀኟቸውን ቅኔዎች ይዘት በፍካሬ ስልት መፈከር ነው። ከዓቢይ ዓላማው ጋር የተሰናኙ አራት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

- ሁለቱ የሴት ቅኔ መምህራን በሴቶች ብዙ ያልተለመደውን ቅኔ የመቀኘት ዕውቀት ከየትና እንዴት ተማሩት የሚለውን ጥያቄ ከህይወት ታሪካቸው ጋር በማያያዝ መግለጽ
- ባለቅኔዎቹ በቅኔያቱ ውስጥ የሚያነሱትን ታላላቅ ዕሳቤዎች ማሳየት
- በባለቅኔያቶቹ ቅኔያቶች አማካኝነት የግዕዝን ቅኔ ጥበባዊነት ማመላከት
- ቅኔያቱን ከሴቶች አተያይ አንጻር መፈከር
- ምን ያህል የቅኔ ሀብት እንዳላቸው መሰነድ

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

- የቅኔ መምህራኑ የቅኔ ዕውቀት ለሥነ-ጽሑፉ ዘርፍ ያለውን አስተዋጽዎ ምንድን ነው?
- በቅኔያቱ የሚንጸባረቁት ዕሳቤዎች እንዴት ተገለጹ ?
- የባለቅኔዎቹ የሴትነት ዕሳቤዎችና አቀራረባቸው ምን ይመስላል?
- መምራኑ በቅኔያቱ ውስጥ የሚያነሷቸው ሒሶች ተጠየቃዊ ዘላቂነታቸው እስከምን ድረስ ነው?
- ለቅኔያቶቹ መደረስ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል።

- ሴት የቅኔ ሊቃውንቱን እና የቅኔ ሀብታቸውን ያስተዋውቃል።
- ቅኔያቱ መጠናታቸው ለመስኩ ወይም ለትምህርት ክፍሉ በሴቶች የቅኔ ዕውቀት ላይ ያለውን የጥናት ክፍተት በመሙላት በተወሰነ መልኩ ድርሻውን በመወጣት አስተዋጾ ያበረክታል።
- የግዕዝ ቅኔ ከሃይማኖት ባሻገር ያሉ ዕሳቤዎች የሚገለጡበት መሆኑን ያሳያል።
- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ በተለይም በሴቶች የቅኔ ዕውቀት ላይ ምርምር ማድረግ ለሚሹ ሰዎች እንደመነሻ በመሆን ያገለግላል።

- ሴቶች በቅኔ ደራሲነት እንዲሁም ቅኔ በማስተማር ረገድ ያላቸውን ሚና በማሳየት በዘርፉ መነቃቃትን ይፈጥራል ።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ በርካታ ጉባኤ ቤት ያላቸው ገዳማት እና አድባራት በወንዶች ብቻ ሳይወሰኑ ሴቶችምን ቅኔ ማስተማር እንዳለባቸው ጥቆማን ይሰጣል።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከጊዜና ከቦታ ውስንነት አንጻር በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም እና በባህር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል በቅኔ መምህርነት በሚያገለግሉት እማሆይ ኅሪት ደባስ እና እማሆይ አመተ ማርያም አሰፋ የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን በማጥናት ላይ ያተኮረ ነው። የባለቅኔዎቹን ቅኔያቶች ምስጢራዊ ጽንሰ ሀሳቡን ይፈክራል እንጂ ስለ ቅኔ ቆጠራ፣ነገራ፣ዘረፋ፣ ስለቅኔ መቀኘት እና ስለ ቅኔ አቀራረብ አይመለከትም።

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

### 1.7.1. የመረጃ ምንጮችና መሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀዳማይና ከካላዓይ የመረጃ ምንጮች ነው። ከካላዓይ የመረጃ ምንጮች መጽሐፎች፣መጽሄቶችና ሌሎች ጥናታዊ ጽሑፎች እንደ አስፈላጊነታቸው ተመርጠው ጥቅም ላይ ውለዋል። ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የሆኑት በቀዳሚነት የታሪኩ ባለቤት የቅኔ መምህራኑ እማሆይ ኅሪት እና እማሆይ አመተ ማርያም ሲሆኑ እንደአስፈላጊነቱ የቅኔ ተማሪዎቻቸውንና በገዳሙ ዙሪያ ያሉት ሰዎች ናቸው። በመሆኑም ጥናቱ ወደ መስክ በመውጣት ተካሂዷል። የመስክ ምርምር በሶስት መንገድ ሊካሄድ እንደሚችል ፈቃደ ይገልጻሉ። እነዚህ ሶስት መንገዶች ምልከታ (observations)፣ ኢንተርቪው (interview) እና መጠይቅ (questionnaire) ናቸው።(1991፣ 90) ከነዚህ መንገዶች መረጃ ለመሰብሰብም ሁለቱን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም ምልከታና ቃለ መጠይቅ ተመርጠው ጥቅም ላይ ውለዋል።

የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን መጠቀም ምልዑ የሆነ መረጃ እንድናገኝ ከማድረጉም በተጨማሪ የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይረዳል። በመሆኑም ይህን ጥናት የተሟላ ለማድረግ ምልከታና ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በተደጋጋፊነት በመጠቀም

መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል:: ከዚህ ቀጥሎም ሁለቱን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተለያዩ ምሁራን ያነሱትን ሀሳብ በማምጣት በአጭሩ እገልጻለሁ::

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀምኩበት ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው:: ይህ ዘዴ ለጥናት የሚረዱኝን መረጃዎች ስለሚጠናው ጉዳይ ዕውቀት ካላቸው ሰዎች በመጠየቅ መረጃዎች የሚሰበሰቡበት ዘዴ ነው::የቃለ መጠይቅን ዘዴ የምንጠቀመው በሁለት መንገድ መሆኑን Khotari ሲገልጹ "ይህን ዘዴ በሁለት ዓይነት መንገድ እንጠቀመዋለን አንደኛ ተጠያቂውን በአካል አግኝተን ፊት ለፊት በመሆን ጥያቄዎችን የምንጠይቅበት ነው::ሁለተኛው ደግሞ በአካል በማንገኝበት ሁኔታ ያሉንን ጥያቄዎች በስልክ የምንጠይቅበትና ምላሽ የምናገኝበት መንገድ ነው:: (1990, 97-100)::

የዚህ ጥናት ትኩረት የእማሆይ ኅሪት ደባስ እና እማሆይ አመተ ማርያም አሰፋ የህይወት ታሪክ እና ቅኔዎቻቸው በመኾኑ ቦታው ድረስ በመሄድ ከባለታሪኮቹ ጋር በአካል በመገናኘት ጥናቱን ሙሉ የሚያደርጉ መረጃዎችን በሚያስገኝ መልኩ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት እና በመጠየቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ትችሏል::አንድ አጥኚ ለጥናቱ የሚሆኑትን መረጃዎች ለማግኘት መጠይቆችን በሚያዘጋጅበት ጊዜ ሁለት ዓይነት መንገዶችን መከተል እንዳለበት ፈቃደ ያስረዳሉ:: አንደኛው ክፍት ጥያቄ(open questions) ሲሆን ይህ የቃለመጠይቅ ዓይነት ተጠያቂው አካል ሳይወሰን የራሱን አመለካከትና ስሜት እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን ጨምሮ ከተለያየ አንጻር የሚመልስበት እና ተጠያቂው በነጻነት ስሜት የሚናገርበት ነው :: ሁለተኛው ደግሞ ዝግ ጥያቄ (closed questions) ነው:: ይህ የቃለመጠይቅ ዓይነት መረጃ ሰጪው አካል አጭር የሆነ ምላሽ እንዲሰጠን የምንጠይቅበት ስልት ነው::(1991፣101-102) በዚህ ጥናት ሁለቱም የቃለመጠይቅ ዓይነቶች አግልግሎት ላይ ውለዋል :: ምክንያቱም ከባለታሪኮቹ አጭርና ቁርጥ ያለ መልስ የሚሹ ጥያቄዎች ስለነበሩ በዝግ የቃለመጠይቅ ዓይነት መረጃው ተሰብስቧል:: በሌላ በኩል ደግሞ የተጠኚዎችን ሰፊ ማብራሪያና አስተያየት የሚፈልጉ ጥያቄዎችን ክፍት የቃለ መጠይቅ ዓይነት በማዘጋጀት መረጃዎችን ለማግኘት ተችሏል:: ሌላው ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋለው ምልከታ ነው::

ምልከታ የምናጠናው ጉዳይ በትክክል እየተከናወነ መሆኑን፤በአሁኑ ሰዓት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በግልጽ ለመረዳት እንደሚያስችል Khotari ሲገልጽ“The main advantage of this method is that subjective bias is eliminated,if observation is done accurately,secondly,the information obtained under this method relates to what is currently happening.(1990, 96)”ይህ ጥናትም

የእማሆይ ኀሪትን እና እማሆይ አመተ ማርያምን የቅኔ ሀብትና የህይወት ታሪክ ያጠና በመሆኑ በጉባኤው ውስጥ የቅኔ መምህራኑን የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ፣ የተማሪዎቻቸውን ብዛት፣የሚማሩበትን ሁኔታ ከአውዱ ለማየትና ለማሳየት ምልከታ ተግባር ላይ ውሏል። ጥናቱ ከምልከታ አይነቶች ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታን በመጠቀም የቅኔ መምህራኑ ደቀመዝሙርቶቻቸውን ሲያስተምሩ በመቅረጸ ምስል (photograph)፣በመቅረጸ ድምጽ(recorder)፣ በመቅረጸ ድምጽና ምስል (video) መረጃዎችን ለመያዝ ተጠቅሜበታለሁ።

በአጠቃላይ ጥናቱን ለማካኼድ መረጃዎቹ ከቀዳማይ እና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆን በዚህ መሰረት ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ከሆኑት እማሆይ ኀሪት እና እማሆይ አመተ ማርያም የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን በተመለከተ በቃለ መጠይቅና በምልከታ መረጃዎቹ ተሰብስበዋል። ከካልዓይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ በዚህ ርዕስ ዙሪያ የተሰሩ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ እና የሦስተኛ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሁፎችን እና በቤተ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ጽንሰ ሀሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ መረጃዎች ለጥናቱ በግብዓትነት ተገልግዬባቸዋለሁ።መረጃዎችም እንደ አመችነታቸው በምስል፣በድምጽ፣በፎቶግራፍ እና በማስታወሻዎች ተጠናቅረዋል።

### 1.7.2. የመረጃ መተንተኛ ስነዘዴ

በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑት በዐይነታዊ የምርምር ስልት ነው። ዐይነታዊ ምርምር ማለት በቁጥር የማይገለጹ እንደ ልቦለድ፣ሥነ-ግጥም ያሉ ሥራዎች፤ በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች የሚተነተኑበት ዘዴ ነው።በዚህ ጥናትም የቅኔ መምህራኑን የህይወት ታሪክና የሚቀኟቸው ቅኔዎች በዚሁ የአተናተን ስልት ቀርበዋል።ይህ ጥናት የህይወት ታሪክን እና የባለታሪኮቹን ቅኔዎች ያጠና በመሆኑ የህይወት ታሪኩን የግለ ታሪክ መንገሪያ በሆነው ግለተረክ ንድፈ ሐሳብን በመጠቀም ያቀረብኩ ሲሆን። የዚህ ጥናት አንድ ክፍል የሆነው የእማሆይ ኀሪት እና እማሆይ አመተ ማርያም የህይወት ታሪክ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ያካበቱትን ልምድ እና ዕውቀት በኑሯቸውና በተለይም በመምህርነታቸው ወቅት ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር ጠቃሚና ትርጉም ያለው በመሆኑ ይህንን ታሪክ ለሌሎች ሰዎች አስተማሪና መረጃ ሰጪ በኾነ መልኩ ቀርቧል።ሌላው የጥናቱ ዋና አካል የሆነው የመምህራኑ ቅኔያቶች ሲሆኑ እነዚህን ቅኔያቶች በግዕዝ ቋንቋ የቀረቡ በመሆናቸው ወደ አማርኛ የተረጎሚቸው ባለቅኔዎቹ እና በተለያየ ደብር ቅኔ የሚያስተምሩ መርጌቶች ናቸው።እነዚህ የሁለቱም መምህራን ቅኔያቶች እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተከፋፍለው በፍካሬ ስልት ተተንትነው ቀርበዋል።

## 1.8. በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

ይህ ጥናት ወደመስክ ተወጥቶ በቃለ መጠይቅና በምልከታ መረጃ የሚሰበሰብበት እንደመሆኑ ወደ ስራ በሚገባበት ወቅት ሁሉም ነገሮች የተመቻቹ አልነበሩም። ይኸውም አንደኛ የቅኔ መምህራኑ የሚገኙት ገዳም ውስጥ በመሆኑ ወደእነሱ ከመሄዴ በፊት የገዳማቱን አስተዳዳሪ መጠየቅና ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅብኛል። ገዳማት ላይ እንደሌሎች ቦታዎች በቶሎ ፈቃድ ለማግኘት በሩ ክፍት ላይሆን ይችላል። ኹለተኛ ከገዳሙ ፈቃድ ቢገኝ እንኳ የቅኔ መምህራኑ በሙሉ እምነት የጥናቱን ተገቢነትና ጠቀሜታ ተገንዝበው መረጃ ይሰጣሉ ወይ የሚል ነው። ምክንያቱም በገዳማት ዙሪያ የሚኖሩ የዕምነት ሰዎች ለጥናት የመጣን አካል በጥርጣሬ አይን ማየትና የሐይማኖቱን ዶግማና ቀኖና የሚጥስ ነው ብለው በማሰብ መረጃን ከመስጠት ይቆጠባሉ። ለእነዚህ ችግሮች እንደመፍትሄ የወሰድኩት ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም እኔ ባደኩበት አቅራቢያ የሚገኝና ዘመድ ያለበት በመሆኑ በአካባቢው ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን በመያዝ የመጣሁበትን በጎ አላማ በማስረዳት አመኔታ እንዲኖራችው በማድረግ እና መልካም ቅርርብን በመፍጠር ነው። ይህ ከእማሆይ ኅሪት ጋር የተፈጠረው መቀራረብ አብረዋቸው የተማሩትን ጓደኛቸውን የባህር ዳሯን እማሆይ አመተ ማርያምን በቀላሉ ለመግባባትና ጉዳዬን ለማስረዳት ጠቅሞኛል። በተጨማሪም እማሆይ አመተ ማርያም የመደበኛውን ትምህርት የተማሩና ጥናትም ያጠኑ በመሆናቸው ለዚህ ስራ ቀና ተባባሪ ሆነዋል።

## 1.9 የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ተዋቅሮ የቀረበ ሲሆን። በምዕራፍ አንድ በመግቢያ ስር በሚገኙ ንዑሳን ክፍሎች ተደራጅተዋል። እነሱም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣የጥናቱ ዓላማዎች፣የምርምር ጥያቄዎች፣የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ ምንጮችና መሰብሰቢያ ዘዴ፣ እንዲሁም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የሚወሰዱ መፍትሄዎች ናቸው። በምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚመለከት ነው። በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የመምህራኑ የህይወት ታሪክ ተብራርቶ የቀረበበት ክፍል ነው። በምዕራፍ አራት የቅኔዎቻቸው ይዘት የተተነተነበት ሲሆን በምዕራፍ አምስት ጥናቱ የደረሰባቸው ግኝቶች የተጠቆሙበት ሆኗል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ሶስት ክፍሎች ቀርበዋል:: የመጀመሪያው ክፍል ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የምርምር ስራዎች የተቃኙበት የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ሲሆን በዚህ ክፍል ቅኔን ርዕሰ ጉዳይ አድርገው የተካሄዱ ሰባት የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለት የሁለተኛ ዲግሪና አንድ የዶክትሬት ዲግሪ በድምሩ አስር ያህል ጥናታዊ ስራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳሳይነት፣ልዩነት፣የጥናቶቹ ዓላማ፣ የጥናቶቹ ድክመትና ጥንካሬ የቀረበበት ነው:: ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለቃል ግጥም ምንነት፣ ስለቃል ግጥምና ስለግዕዝ ቅኔ፣ ስለቅኔ ምንነት፣ አጀማመር፣ ስለቅኔ ዓይነትና መንገድ የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ያነሷቸው ሃሳቦች ተብራርተው ቀርበዋል:: ሶስተኛው ክፍል ደግሞ ጥናቱ ግብ ይመታ ዘንድ ከጥናት መስኩ የተመረጡት ንድፈ ሀሳቦች ግለ ተረክ እና ፍካሬ ሲሆኑ ምሁራኑ ያነሷቸውን ጽንሰ ሀሳቦች እና በዚህ ጥናት ውስጥ እንዴት እገለገልባቸዋለሁ የሚለው ጉዳይ ተገጿል::

## 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል የቀረቡት ጥናቶች በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት እንዲሁም በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት የተሰሩ ሆነው በርዕሰ ጉዳይ ተመሳስሎ ያለን ናቸው:: እነዚህ ጥናቶች በግዕዝ ቅኔያት ላይ የተሰሩ ሰባት የመጀመሪያ ፣ ሁለት የሁለተኛ እና አንድ የሶስተኛ ዲግሪ በድምሩ አስር ያህል የዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ተቃኝተዋል፤ ልዩነታቸው እና ተመሳስሏቸው ተብራርቶ ቀርቧል:: እነዚህ ቅኝት የተደረገባቸው ጥናቶች እጅጉን የሚቀራረቡና በሩቁ የሚጠራሩ ናቸው:: በመጀመሪያ የሚቀርቡት ከዚህ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው ሲሆኑ እነዚህን ተከትለው የሚመጡት ደግሞ ቅኔን ጉዳያቸው ያደረጉና ይዘቱን የተመለከቱ ጥናቶች ናቸው::

ሰለሞን ሐዲስ "የእማሆይ ገላነሽ ሐዲስ ዘጽላሎ አማኑኤል የህይወት ታሪክና ስራዎቻቸው" በሚል ርዕስ (1992) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን ትኩረቱም በእማሆይ ገላነሽ የህይወት ታሪክ እና የቅኔ ሀብታቸው ላይ ነው:: ጥናታዊ ስራውን ለመስራት ዓቢይ አላማ ያደረገው የእማሆይ ገላነሽ ሐዲስ ዘጽላሎ አማኑኤል የህይወት ታሪክና ስራዎቻቸውን ዘርዝሮ በመተርጎምና በመመስጠር

አቅርቦ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ማሳየት የሚል ነው፡፡ በዚህ መነሻነትም ሴቶች በጥንታዊው የቆሎ ትምህርት ቤት የት ደርሰው እንደነበር የእማሆይ ገላነሽን ታሪክና ስራዎቻቸውን በማቅረብ አሳይቷል፡፡ ሰለሞን የቅኔ መምህሯን የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን በማጥናቱ ከዚህ ስራ ጋር ያዛምደዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ልዩ የሚያደርገው አሁን በህይወት ያሉ ሁለት ሴት የቅኔ መምህራንን የሚመለከት መሆኑ ነው፡፡ ሰለሞን በህይወት የሌሉትን እውቋን የቅኔ ሊቅ የእማሆይ ገላነሽን የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን ከዘመዶቻቸው፣ከአብሮ አደግ ሰዎች እንዲሁም ከተለያዩ ጽሁፎች መረጃዎችን በመሰብሰብ ጥናቱን ያደረገ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የቅኔ መምህራኑ በህይወት ያሉና መረጃውም ከነሱ የተሰበሰበ ነው፡፡ ሰለሞን በጥናቱ ዘዴ ላይ ለጥናቱ መረጃ ሰጪ የሆኑ አካላት እነማን እንደሆኑና እንዴት እንደመረጣቸው በግልጽ ማስፈሩ፤ የእማሆይ ገላነሽን የህይወት ታሪክ ከልደት እስከሞት ያለውን ታሪካቸውን እንዲሁም ያከናወኑትን ተግባር በተቀናጀ መልኩ ማቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን የባለታሪኳን ቅኔዎች ሚስጥር በሚገባ ተንትኖ አለማቅረቡ ፣እማሆይ ገላነሽ የአማርኛ መወድስ ቅኔ በብዛት ይቀኛሉ ቢልም በቂ የሆነ ማሳያ ቅኔዎችን አለማቅረቡ እንደ ደካማ ጎን የሚታይ ነው፡፡ ጥናቱ በህይወት የሌሉትን ሴት የቅኔ ሊቅ ታሪካቸውንና ስራቸውን ማጥናቱ በተለይም ሴት የቅኔ መምህራን ላይ ለማጥናት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

ይኩኖ አምላክ መዝገቡ "በግዕዝ ቅኔ ሰም ውስጥ የሴት ገጸባህርያት ገለጻ" በሚል ርዕስ (1997) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ሲሆን ትኩረት ያደረገውም የግዕዝ ቅኔያት ይዘት ሐይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆችን አጠቃላይ ዕሳቤ እንደሚያሳይ ማመልከት ነው፡፡ ጥናቱ በግዕዝ ቅኔ ውስጥ ሴቶች እንዴት ተገልጸዋል የሚለውን ለማሳየት በመጻሕፍት ከታተሙና በዘመኑ ካሉ የቅኔ መምህራን የተወሰዱ የሴቷን ሰናይና ዕኩይ ባህሪ የሚያሳዩ ቅኔዎችን ሰማዊ ክፍላቸውን መተንተንን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ይህንን ለማሳካትም በሰማዊ ክፍላቸው ሴቷን የሚመለከቱ ማህበረሰቡ ለሴቶች ያለውን አወንታዊም ይሁን አሉታዊ አመለካከት የሚገልጹ ቅኔዎችን ሰብስቦ በሚገባ ተንትኗል፡፡ ይኩኖ አምላክ በዚህ ጥናት የግዕዝ ቅኔ ሐይማኖታዊና አምልኳዊ ጉዳዮችን ብቻ የሚመለከት የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት የህይወት ጉዞ የማይመለከት ሰዋዊ የሆኑ ጉዳዮችን ያገለለ ተደርጎ የሚቆጠረውን የተሳሳተ ግንዛቤ በመተቸት የግዕዝ ቅኔ ሐይማኖታዊ ብቻ እንዳልሆነ የማህበረሰቡ አንድ አካል የሆኑት ሴቶች በቅኔ ውስጥ የተሳሉበትን ሰናይና እኩይ ባህሪ አሳይቷል፡፡የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ ሴቶች በቅኔው ውስጥ

እንዴት ተሳሉ ሳይሆን ቅኔ የሚቀኙ እና የሚያስተምሩ ሁለት ሴት የቅኔ መምህራንን የህይወት ታሪካቸውን ማጥናትና ቅኔዎቻቸውን መመርመር ነው።ይኩኖ አምላክ ለጥናቱ ተስማሚ የሆኑ ቅኔያትን ከተለያዩ መጻህፍትና ከቅኔ መምህራን በመሰብሰብ ሠሙን ብቻ ነጥሎ አሳይቷል። ይህ ጥናት ግን የቅኔ መምህራኑን ቅኔዎች ሚስጥራዊ ሐሳቡንም በመመርመሩ ከይኩኖ አምላክ ጥናት ይለያል። ይኩኖ አምላክ በጥናቱ በግዕዝ ቅኔ ውስጥ ሴቶች እንዴት ይገለጻሉ የሚለውን ለማሳየት ቅኔዎችን በመሰብሰብ እና ሰፊ ትንተና በማድረግ ማሳየቱ፣ለጥናቱ የሚሆኑ ቅኔዎችን ቀድሞ ከነበሩ ሊቃውንት ተሰብስበው ከታተሙና በዘመኑ ካሉ የቅኔ መምህራን አቀላቅሎ መጠቀሙ አሁን ያለውንም ሆነ የበፊቱን የሴቷን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላትን ቦታ እና በቅኔው ውስጥ እንዴት እንደምትገለጽ ለማየት በማስቻሉ እንደጠንካራ የሚወሰድ ሲሆን በጥናቱ ዘዴ ላይ ለጥናቱ የመረጣቸውን ቅኔዎች በመጻህፍት ከታተሙና በዘመኑ ካሉ መምህራን እንደሚወስድ ይግልጻል እንጂ ምን ያህል ቅኔ ከማን እንደወሰደ አይገልጽም።በህይወት ካሉ መምህራንም ቅኔዎችን በምዓይነት መልኩ እንደሚወስድ የጠቀሰው ነገር የለም ።ነገር ግን ሴቶችን የሚመለከቱ ቅኔያቶችን ብቻ በመምረጥ እንዴት ተገልጸዋል የሚለውን ጉዳይ ነጥሎ ማየቱ በግዕዝ ቅኔ ሴትነት በምን አይነት መልኩ እንደሚገለጽ መጠነኛ የሆነ መረጃን ይሰጣል።

ላዕከ ማርያም ብርሀኑ "ጉዳያቸውን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት ይዘታዊ ትንተና" በሚል ርዕስ (2010) ዓ.ም ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ሲሆን በመጽሐፍ ከታተሙ ቅኔዎች ውስጥ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ቅኔዎች በፍካሬ ስልት መተንተንን ዓላማው አድርጓል። በጥናቱም በቀደምት የቅኔ ሊቃውንት ከተዘጋጁ የቅኔ መጻህፍት የወቅቱን ሐይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚያሳዩ ቅኔዎችን በመምረጥና በፍካሬ ስልት በመመርመር የግዕዝ ቅኔያት ጥበባዊ ዋጋቸው ከፍ ያለ፣ታሪክን መንገሪያ እንዲሁም የዘመንን መንፈስ ማሳያ መሆናቸውን ባቀረባቸው የሊቃውንቱ ቅኔ በመረመረበት የጥናቱ ክፍል አሳይቷል። የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በቅኔው ሙያ ብዙም ባልተለመዱት ሴት የቅኔ መምህራን ላይ ሲሆን  የህይወት ታሪካቸውን ማጥናትና የቅኔዎቻቸውን ይዘት መፈከር ነው። ላዕከማርያም ሰባት የሚደርሱ በቅኔ ሊቃውንት ከተዘጋጁ የቅኔ መጻህፍት ውስጥ ለጥናቱ ተስማዊ የሆኑትን በመምረጥ የቅኔያቱን ሚስጥር መርምሮ በማቅረቡ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው።

የሚለይበት ደግሞ  በቅኔ ሙያ ከሚታወቁ የቅኔ ሊቃውንት የተዘጋጁ የቅኔ መጻህፍት ላይ ያሉ ቅኔዎችን መመርመር ሲሆን ይህ ጥናት ግን ለጥናቱ በተመረጡ ሁለት ሴት የቅኔ መምህራን ላይ በማተኮር የመምህራኑን የህይወት ታሪክ እና የቅኔዎቻቸውን ይዘት የሚያጠና መሆኑ ነው። ሌላው ደግሞ ላዕከ ማርያም ጥናቱን በቤተ መጻህፍት ውስጥ ያከናወነ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ወደመስክ በመውጣት ከተጠኚ አካላት መረጃ በመሰብሰብ የተከናወነ ነው። ላዕከ ማርያም ለጥናቱ የመረጣቸው በ1960ዎቹ የቅኔ ሊቃውንት ያሳተሟቸውን ቅኔያቶች ሲሆን ይህ ጥናት ግን በዚህ ዘመን ካሉ የቅኔ ሊቃውንት ላይ ያተኮረ መሆኑ ከላዕከ ማርያም ጥናት የሚለይ ይሆናል። ጥናቱ ቅኔያት ለታሪክ ምርምር መነሻ፣ የዘመንን መንፈስ ማሳያ፣ ፖለቲካዊ ዕሳቤዎችን መንገሪያ ጥበብ መሆናቸውን አሳይቷል።

ፍቅሩ ደመቀ "ሥነ-ቃልን ሠም ያደረጉ የግዕዝ ቅኔዎች ይዘታዊ ትንታኔያቸው" በሚል ርዕስ (1995) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን ትኩረት ያደረገውም ሥነ-ቃልን ሠም ያደረጉ የግዕዝ ቅኔዎችን ከነትርጉማቸውና ምስጢራቸው ለአንባቢያን ማሳወቅ እንዲሁም የቅኔንና የሥነ-ቃልን ምንነት ባጭሩ ማሳየት ላይ ነው። ጥናታዊ ስራውን ለመስራት ዐብይ ዓላማ ያደረገው ሥነ-ቃልን መሰረት የሚያደርግ የግዕዝ ቅኔ ይዘት ለአንባቢ ለማስተዋወቅ እንዲሁም የቅኔውን ምንነት፣ ውበቱንና ምስጢሩን ማወቅ ለሚፈልጉ ምሁራን አብራርቶ መግለጥ የሚል ነው። ፍቅሩ ሠማዊ ክፍላቸውን ሥነ-ቃል ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያቶች ላይ በማተኮር ጥናቱን አቅርቧል። ፍቅሩ የቅኔያቱን ሠማዊ ክፍል ማሳየት ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ቢቀራረብም በይዘቱ ፣በአቀራረቡና በዓላማው ግን የተለያየ ነው። ፍቅሩ ሠማዊ ክፍላቸው ስነ-ቃል የሆኑ ቅኔያቶችን ከተማሪዎች፣ ከቅኔ መምህራን እና ከመጻህፍት በመሰብሰብ ትርጉማቸውን ለማሳየት ሞክሯል። ይህ ጥናታዊ ስራ ግን ሴት የቅኔ መምህራን ላይ በማተኮር የመምህራኑን የህይወት ታሪክና የቅኔዎቻቸውን ይዘት መተንተን ነው። ፍቅሩ የግዕዝ ቅኔ የማህበረሰቡ የአስተሳሰብ ማሳያ በመሆኑ ስነ-ቃላዊ ጉዳዮችን በውስጡ እንደሚይዝ ይህም በቅኔው ሰማዊ ክፍል ጎልቶ እንደሚታይ አስረጅዎችን በማምጣት ያሳየበት የጥናቱ ክፍል ጠንካራ የሚባል ነው። ነገር ግን ለጥናቱ የሚሆኑ ቅኔዎች ከቅኔ መምህርና ከተማሪዎች እንደተሰበሰቡ ቢግልጽም ምን ያህል ቅኔ እንደሰበሰበ፣ የትኞቹን ቅኔዎች ከመምህር የትኞቹን ደግሞ ከተማሪዎች እንደሆነ አይገልጽም በተጨማሪም በትንተና ክፍል የቀረቡት ቅኔዎች በደንብ

ተብራርተው አልተገለጹም። የተለያዩ የሥነ-ቃሎች አይነቶች በግዕዝ ቅኔ ውስጥ እንደሚገቡ ማሳየቱ ለዘርፉ እንግዳ ለሆኑ አካላት አዲስ መረጃን ይሰጣል።

ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርቡት ደግሞ ዓላማቸው የተለያየም ቢሆን የቅኔውን ይዘትም ስለሚመለከቱ ቅኝት ያደረኩባቸው ናቸው።

ስርግው ገላው "Historical Development of Geez Qene in Different Periods" **በሚል ርዕስ** (2009 ) በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ በቅኔ ላይ የተደረገ ጥናታዊ ምርምር ነው። ትኩረቱም በግዕዝ ቅኔ ይዘት፣ቅርጽ እና ታሪካዊ ዕድገት ላይ አድርጎ ሰፊ ጉዳዮችን የዳሰሰ ሲሆን በጥናቱ የግዕዝ ቅኔ ግጥማዊ የሆነ ቃላዊ ሥነ-ጽሑፍ እንደሆነ ተገልጿል።ይኽ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የግዕዝ ቅኔ ከሃይማኖት ይዘቱ ባሻገር ሰዋዊ የሆኑ እሳቤዎችን የሚገልጽ ሥነ-ጽሑፋዊ ዋጋው ከፍ ያለ ጥበብ እንደሆነ መግለጻቸው ነው። የስርግው ጥናት የግዕዝ ቅኔ ታሪካዊ ዕድገት ላይ ያተኮረ በመሆኑ እና በርካታ ጉዳዮችን የሚመለከት በመሆኑ ከእኔ ጥናት ይለያል። ታሪካዊ እድገቱንም ሲያጠኑ በየዘመናቱ በመከፋፈል ሰፊ የሆነ የታሪክ ጊዜ ተዳሷል። ይኽ ጥናት ግን የሁለት ሴት የቅኔ መምህራንን የሕይወት ታሪክና የቅኔዎቻቸውን ይዘት በማጥናት ላይ የተወሰነ በመሆኑ የቅኔን ታሪካዊ ዕድገት ስለማይመለከት ከስርግው ጥናት ጋር ይለያያል።ሌላው የስርግው ጥናት ትኩረት የድጓ ትምህርት ቤት እና ለድጓ ቅኔዎች እንዲሁም የድጓ ቅኔዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ በመግለጽ በድጓ እና በቅኔ መኻል ያለውን የጠበቀ ቁርኝት ማሳየት ላይ ነው። ስርግው የግዕዝ ቅኔ ከመካከለኛው ዘመን እስከ ዘመናዊው የቅኔ ዘመን ያመጣውን የቅርፅና የይዘት ለውጥ የየዘመናቱን ቅኔ በመመደብ ጥናት አድርገዋል። ስርግው ጥናታዊ ምርምሩን በመስክ እና በቤተ መጻሕፍት ላይ በማድረጋቸው ከዚህ ጥናት ጋር በመረጃ መሰብሰቢያ ሥነ-ዘዴ ተመሳስሎ አለን። ስርግው በጥናታቸው የቅኔን ታሪካዊ ሂደቱን በማየት ማጥናታቸው፣ ምን ዓይነት ለውጥ አመጥቷል የሚለውን በማስረጃ ማቅረባቸው፣የድጓና የቅኔን ቁርኝት ማሳየት መቻላቸው እንዲሁም ኢትዮጵያዊው የግዕዝ ቅኔ ከየትኛው የሥነ-ጽሑፍ ጎራ ይመደባል የሚለውን ማሳየታቸው ለዘርፉ አዲስ ዕውቀትን ጨምረዋል ማለት ይቻላል።

ይኄይስ ኃይለ ሚካኤል "የግዕዝ መወድስ ቅኔ"በሚል ርዕስ (1975) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን ከግዕዝ ቅኔያት መካከል አንዱ የሆነውን የመወድስ ቅኔን ለማሳየት የተሞከረበት ነው። ትኩረት ያደረገውም የመወድስ ቅኔን ቅርጽ እና ይዘት ለአንባቢ ማስተዋወቅ ላይ ነው።

ጥናታዊ ስራው ከቅኔ አይነቶች መካከል አንዱ የሆነውን የመወድስ ቅኔን በማንሳት ምንነቱን እና ይዘቱን ማሳየቱ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። ልዩነቱ ደግሞ ይሄይስ የመወድስ ቅኔን ብቻ በማንሳት ቅርጹንና ይዘቱን ማሳየት ላይ በማተኮሩ ነው። የዚህ ጥናት ዓላማ ግን የሴት ቅኔ መምህራንን የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን ይዘት መተንተን ሲሆን ቅኔያቱ ከሃይማኖት ባሻገር ያላቸውን ጭብጥ ይመረምራል ስለሆነም ከይኄይስ ጥናት ልዩ ያደርገዋል። አጥኚው የመወድስ ቅኔን ምንነት ታሪካዊ አመጣጡን ቅርጽና ይዘቱን እንዲሁም አቀራረቡን በቅኔ ሊቃውንት ዘንድ ያለውን ተወዳጅነት በትንተናው ማሳየቱ እንዲሁም ለአስረጂነት ያቀረባቸው የመወድስ ቅኔዎች ሀይማኖታዊው ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይወሰኑ ማህበራዊውንም ፖለቲካውንም የሚያሳዩ ቅኔዎችን ማቅረቡ እንደጠንካራ ጎን ይወሰዳል። ቢሆንም የመወድስ ቅኔ ከሌሎች የግዕዝ ቅኔ አይነቶች የሚለይበትን መሰረታዊ ጉዳይ አላሳየም። ከሱ ጥናት ቀደም ብለው በግዕዝ ቅኔ ላይ የተሰሩ ስራዎችን ለማቅረብ አልሞከረም። አጥኚው የመወድስን ቅኔ ቅርጽና ይዘት ከሥነ ግጥም አንጻር ምን ዐይነት ተመሳሳይነት እንዳለው ማሳየቱ ለዘርፉ አዲስ ለሆነ ሰው መረጃን ይሰጣል ።

ፍቅረ ድንግል "ቅኔ መቀኘትና ቅኔ መቁጠር በግዕዝ" በሚል ርዕስ (1963) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን ስለ ቅኔ መንገዶች በስፋት በመዳሰስ ስለቅኔ መቀኘትና መቁጠር ላይ አትኩሯል። የጥናቱ ዓላማ የቅኔን ሚስጥር ከስርዓተ ግጥም አንጻር ለዘመኑ ተመራማሪ እንዲመች አድርጎ ማቅረብ ነው።አጥኚው ስለግዕዝ የንባብ አይነቶች፣ ስለቅኔ አይነቶች እንዲሁም ስለቅኔ ዜማ በማንሳት ገለጻ አድርጓል። ይህ ጥናታዊ ስራ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቅኔን ጉዳዩ አድርጎ ማቅረቡ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ የቅኔን ምስጢር ከስርዓተ ግጥም አንጻር ለዘመኑ ተመራማሪ ማቅረብን ዓላማው በማድረጉ ነው። ይህ ጥናታዊ ስራ ግን ዋና ዓላማው በሀገራችን ካሉ ውስን ሴት የቅኔ መምህራን ውስጥ የሁለቱን የህይወት ታሪክና የቅኔዎቻቸውን ይዘት መፈከር ነው። በመሆኑም በዓላማ የተለያየ ነው። ፍቅረ ድንግል ቅኔ መቀኘትና ቅኔ መቁጠር ምን ማለት እንደሆነ በማብራራት በቅኔ መቀኘት ውስጥ ያሉትን ሰምና ወርቅ የገለጸበት መንገድ እንዲሁም የቅኔን መንገዶች እና አይነቶች ምሳሌ እያመጣ መግለጹ እንደጠንካራ ጎን የሚወሰድ ነው። በጥናቱ ግብም ከግጥም አንጻር ቅኔን ማጥናት እንደሚቻል አሳይቷል።ጥናቱ ግን በግልጽ የሰፈረ ዓላማም ሆነ የጥናቱ ጥያቄዎች የሉትም።

ጽጌ አባተ "ቅኔያዊ ውርስ"በሚል ርዕስ (1972) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን ዓላማ አድርጎ የተነሳው የቅኔ ትርጓሜና የት መጣነት ሳይንሳዊ ትንተና ለአንባብያን ማቅረብ ነው። ትኩረቱም የግዕዝን ቅኔ ለአንባብያን ማስተዋወቅ ነው። የጽጌ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የግዕዝ ቅኔ ላይ አተኩሮ መስራቱ እና የተወሰኑ ቅኔዎችን በማቅረቡ ነው። ልዩነቱ ደግሞ ስለቅኔ ትምህርት ቤት፣ ስለቅኔ ዘረፋና ቆጠራ የሚሉ ጉዳዮችን በማንሳቱ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የሚመለከተው የሴት ቅኔ መምህራንን የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን ነው። የጽጌ ዓላማ የግዕዝ ቅኔን ትርጓሜና አመጣጥ ለአንባቢ ማስተዋወቅ ስለሆነ በዓላማ የተለየ ነው። ጥናታዊ ስራው የግዕዝን ቅኔ ከየት መጣነት ሳይንሳዊ ትንታኔ ለመስጠት ያደረገው ጥረት በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው።ነገር ግን ለአስረጂነት ካቀረባቸው ቅኔዎች ውጪ ለተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች የሚሰጣቸው ብያኔዎችና ማብራሪያዎች ምንጫቸው ከየት እንደሆነ በማይታወቅ መልኩ በራሱ ሀሳብ ጀምሮ በራሱ ግንዛቤ ይደመድማል። በጥናቱ ውስጥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ግጥሞቻቸው ከግዕዝ ቅኔ የወረሱት ቅኔያዊ ግጥም አላቸው በማለት ይገልጽና እንደአስረጂ የሚያመጣው ግን የአማርኛን ግጥም ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ሀሳቡን ሙሉ አያደርገውም ምክንያቱም ወይ የአማርኛ ቋንቋ ብሎ ወስኖ መነሳት ነበረበት አልያም የሌሎች ቋንቋዎችን ግጥሞች እንደማሳያ ማምጣት ነበረበት።

አበበ ከበደ"የመልአከ መልአክ ተስፋ የዋሻራ ውስጠ ዘ የግዕዝ ቅኔና ቅኔው ከሌሎች ቅኔዎች የሚለይባቸው ባህርያት" ሚል ርዕስ (1993) ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን ትኩረቱም ከቅኔ መንገዶች አንዱ የሆነው "ውስጠ ዘ ቅኔ ላይ ነው። የጥናታዊ ስራው አብይ ዓላማም የውስጠ ዘ ቅኔ የራሱ የሆነ አቀራረብ፣ቴክኒክና ስልት ያለው ቢሆንም በአብዛኛው የቅኔን ውበትና ሚስጥር እንዲሁም ምጣኔ ለመመርመር በሚፈልጉ ምሁራን ዘንድ አይታወቅም በመሆኑም የቅኔውን ምንነት፣ ባህርያቱንና ስልቱን ለአንባብያን ማሳየት ላይ ነው። አጥኚው በአንድ የቅኔ ስልት ላይ በማተኮር የሰራ ሲሆን የውስጠ ዘ ቅኔ መነሻው ጎጃም እንደሆነም ገልጿል። ይህ ጥናታዊ ስራ ከቅኔ አይነቶች መካከል አንዱን በማንሳት የቅኔያቱን ትርጉምና ምስጢር በማቅረቡ ከዚህ ጥናታዊ ስራ ጋር ዝምድና ቢኖረውም በዓላማው፣ በይዘቱ እና በአቀራረቡ ግን የተለያየ ነው። አበበ ዓላማ አድርጎ የተነሳው የውስጠ ዘ ቅኔን ባህርያት ለአንባቢ ማስተዋወቅ ሲሆን ሀይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን የውስጠ ዘ ቅኔዎችንም በትንታኔ መልክ ለማቅረብ ሞክሯል።

የዚህ ጥናታዊ ስራ ግን የሴት ቅኔ መምህራንን የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን ማጥናት ነው። አበበ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ምልከታና ቃለመጠይቅ እንደተጠቀመ በመግለጽ መረጃውን ከማን እና በምን አይነት መንገድ እንደሰበሰበው በግልጽ ማስፈሩ፤ የውስጠ ዘ ቅኔን በብዙሀኑ ዘንድ ከሚታወቀው ከሰምና ወርቅ ቅኔ ጋር በማነጻጸር ያቀረበበት መንገድ እና የውስጠ ዘ ቅኔን ልዩ ባህሪ ዘርዝሮ ማሳየቱ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን መግቢያ አለመኖሩ እንዲሁም አበበ የውስጠ ዘ ቅኔ ከሀይማኖታዊ ጉዳዮች ባሻገር ማህበራዊም ሆነ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ይመለከታል ብሎ ቢገልጽም በጥናቱ ውስጥ የተተነተኑት ቅኔዎች ግን ሀይማኖታዊ ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው። ከሀይማኖቱ ባሻገር ያሉ ጉዳዮችን የሚያሳዩ ቅኔዎችን ማሳየት አለመቻሉ እንደክፍተት ይታያል።

በላይነህ ደሴ "የቅኔ ቆጠራ፣ነገራና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ" በሚል ርዕስ (1999) ዓ.ም ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዓቢይ ዓላማም በቅኔ ጉባኤዎች ውስጥ ያለውን የትምህርት አቀራረብና በትምህርቱ ዙሪያ፣ በመምህራንና በተማሪዎች የሚከናወኑ ተግባራት ለተተኪው ትውልድ አስተማሪና ጠቃሚ በሆነ መልኩ በጽሁፍና በምስል ቀርጾ ማስቀመጥ ነው። ትኩረት ያደረገውም በተመረጡ የጎጃም አካባቢ የቅኔ ጉባኤዎች መነሻነት ስለሚከናወኑ የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ እና ሌሎች የሚከናወኑ ስርዓቶች ላይ ነው። አጥኚው ቅኔያዊ ጉዳይ ማንሳቱና እንደ አስረጂም ቅኔዎችን መዳሰሱ ከዚህ ጥናት ጋር ያዛምደዋል።ነገር ግን ይህ ጥናት በሀገራችን ካሉ ውስን ሴት የቅኔ መምህራን የህይወት ታሪካቸውንና ቅኔዎቻቸውን ይዘት የሚመረምር እንጂ ስለቅኔ ጉባኤ ቤቶች አጠቃላይ ስርዓት የሚያጠና ባለመሆኑ ከበላይነህ ጥናት ይለያል። በላይነህ በጥናቱ በግዕዝ ቅኔ ጉባኤ ቤቶች የትምህርት ስርዓት እና የቅኔውን አፈጣጠር ሂደት ያየ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ቅኔያቶቹ የሚያነሱትን የተለያዩ ጉዳዮች መፈከር ነው። በላይነህ በጉባኤ ቤት ያለውን ባህል፣የግዕዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ስርዓቶችን የተመለከተበት እንዲሁም የቅኔን አፈጣጠር ሂደት ቦታው ድረስ በመሄድ መረጃዎችን ሰብስቦ የገለጸበት መንገድ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው። ነገር ግን ጥናቱ ምንም አይነት ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የለውም፣ነገር ግን ጥናቱ በቅኔ ቤት የሚከናወኑ ስርዓቶችን መግለጹ ለዘርፉ እንግዳ ለሆነ አካል ፍንጭ የሚሰጥ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ቅኝት የተደረገባቸው ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ የቀረቡ ጥናታዊ ስራዎች በግዕዝ ቅኔ ላይ ትኩረት በማድረጋቸው ከዚህ ጥናታዊ ምርምር ጋር ተመስሳይነት አላቸው። ነገር ግን እነዚህ ጥናቶች ስለ ቅኔ መቀኘትና መቁጠር፤ ስለቅኔ

ታሪካዊ አመጣጥ፣ ስለቅርጹ፤ ስለ ዋሽራ ውስጠ ዘ ቅኔ ባህርያትና ይዘት፤ስለ ሴት የቅኔ መምህርት የህይወት ታሪክና ስራዎቻቸው፣ ስለቅኔ ቆጠራና ነገራ የቅኔን ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚገልጹ እንዲሁም የግዕዝ ቅኔ በተለያዩ ክፍለ ዘመናት ያሳየውን እድገት የሚያስቃኙ ጥናቶች ናቸው፡፡ ይህ ጥናታዊ ስራ ግን በአሁኑ ሰዓት ጉባኤ ዘርግተው ቅኔ የሚያስተምሩትን የሴት ቅኔ መምህራንን የሕይወት ታሪክ እና የቅኔዎቻቸውን ይዘት የሚያጠና ነው፡፡

## 2.2 ጽንሰ ሐሳብ

### 2.2.1 የቃል ግጥም ምንነት

ቃል ግጥም በቃል ተደርሶ በቃል እየተነገረ ቃላዊ በሆነ መልኩ ማህበረሰቡ በእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴው ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለውና በብዙ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ሐይማኖታዊ ፣ ፍልስፍናዊ ጉዳዮች የሚገለጡበት ጥበባዊ ሀብት ነው፡፡ ሰለሞን ስለ ቃልግጥም ሲገልጹ "ቃልግጥም የማህበረሰቡን ባህል መሰረት በማድረግ የተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ በግለሰብም ሆነ በቡድን የሚቀርብ ጥበብ ነው፡፡(2007፣129) ቃል ግጥም በተለያዩ አጋጣሚዎች ለተለያዩ ፋይዳዎች ማህበረሰቡ የፈጠራቸው ቃላዊ የሆኑ የጥበብ ውጤቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ቃል ግጥምን ቃላዊ ጥበብ ያሰኘው አደራረሱም ሆነ መተላለፊያ መንገዱ ቃላዊ በመሆኑ ነው፡፡ Finnegan ስለ ቃል ግጥም ቃላዊነት ስትገልጽ"በቃል ግጥም ውስጥ ቃላዊነት የሚለው ቃል አሻሚ ነው፡፡ አንዳንዴ በጽሁፍ ከሚገኙ ስራዎች ጋር ጉልህ ልዩነት ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡ ሆኖም ቃላዊነት በአንድ በኩል የተጻፉ በቃል ከሚገኙ ለመለየት እንደአንድ መስፈርት እንጠቀምበታለን፡፡ ቃላዊነቱን መሰረት አድርገን ደግሞ ሶስት መስፈርቶችን በማስቀመጥ የልዩነት ድንበር ማበጀት ይቻላል፡፡ ይህም አደራረሱ፣ስርጭቱና ክዋኔው ነው፡፡(1977፣17) የቃል ግጥም አደራረስ ቅጽበተዊ በሆነ መልኩ ሊደረስ ይችላል፤ በቃል አጥንቶ በመሸምደድ ወይም ደግሞ ቀድሞ በሰማው ላይ ማሻሻያ በማድረግ ሊደረስ ይችላል፡፡ ይህ በቃል ተደርሶ በቃል የሚነገር ጥበብ የተለያዩ የሰው ልጆችን የህይወት ክስተት ተከትሎ የሚደረስ በመሆኑ የተለያየ ይዘትና አቀራረብ አለው፡፡ ፈቃደ የቃል ግጥሞችን በዓይነት ለመመደብ ምቹ የሆነው መንገድ ብለው ሲያስቀምጡ "በሰው ልጆች ኑሮ ውስጥ የሚከሰቱትን ዐበይት የጋራ ሕይወታዊ ክስተቶች የመከልሰፊያ መመዘኛ ማድረግ አንድ ጥሩ መነሻ ሊሆን ይችላል ብለን የመረጥነው፡፡

" በማለት የሰው ልጅ ሁሉ የሚጋራቸውን እንደ ፍቅር፣ ውዳሴ፣ ሞት፣ ጦርነት ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሂስን በመጥቀስ በነዚህ የጋራ ጉዳዮች በመመራት ቃል ግጥምን መመደብ እንደምንችል ይገልጻሉ።(1991፣89-90) እንግዲህ ቃል ግጥም የሰው ልጆችን ህይወታዊ ክስተቶችንና ዕሳቤዎችን ሁሉ አፋዊ በሆነ ጥበብ የመግለጫ መንገድ ነው ማለት ይቻላል።

### 2.2.2 የቃል ግጥም ባህርያት

ቃል ግጥም እንደ ስነ-ቃል ዘርፍነቱ የተለያዩ ባህርያት አሉት። ዘሪሁን "ስነቃል ሁለት ዋነኛ ባህርያት አሉት"(1992፣22) በማለት ክዋኔና ተለዋዋጭነትን ያነሳሉ ። ክዋኔ ለስነ ቃል መፈጠሪያውም ሆነ መተላለፊያ መንገዱ ነው። በክዋኔ ወቅት አዳዲስ ቃል ግጥሞችም ሆኑ ሌሎች ስነ ቃሎች የመፈጠር አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው። ሁለተኛው ተለዋዋጭነት ነው። አንድ ቃል ግጥም ተፈጥሮ በቃል ይከወናል። በዚህ ጊዜ አንድ አድማጭ ይህን የሰማውን ቃል ግጥም በሌላ አጋጣሚ ሊከውነው ይችላል። ቃል ግጥም ከአንድ አካባቢ ወይም ከአንድ ባህል ወደ ሌላ ባህል ሲሸጋገር ተለዋዋጭነት ይታይበታል። ምክንያቱም እንደ ጽሁፍ ግጥም እንዳለ የመቆየቱ ሁኔታ ላያጋጥመው ይችላል። ተለዋዋጭነቱም በከፊል የቃላት፣ የሀረጋት፣ የስንኝ ወይም የዐረፍተ ነገር ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሆን ይችላል።(1992፣25) ከዚህ ተነስተን የግዕዝን ቅኔ ስንመለከተው ቃላዊነቱ፤ በክዋኔ የታጀበ መሆኑ፣ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ ሊደረስ መቻሉ ፤በየዕለቱ አዳዲስ ቅኔ መቅረቡ ተለዋዋጭነቱን ያሳያል ይህም ማለት የግዕዝ ቅኔ ዛሬ የቀረበው ተደግሞ አይባልም "የቅኔ ቋንጣ የለውም" እንደሚባለው በየዕለቱ አዲስ ሆኖ ይቀርባል። እነዚህ ዋና ዋና ባህርያት ቅኔን የስነ-ቃል ዘርፍ ከሆነው ቃል ግጥም ውስጥ ያስመድበዋል።

### 2.2.3 ቃል ግጥምና የግዕዝ ቅኔ

ቃል ግጥም ቃላዊ የሆነ ጥበብ ሲሆን የሰው ልጆችን እምነት፣ ባህል፣ ፖለቲካ፣ ፍልስፍና በአጠቃላይም ሰዋዊ የሆኑ ዕሳቤዎችን የሚዳስስ ሰፊ የሆነ አፋዊ ጥበብ በመሆኑ የግዕዝን ቅኔ በቃል ግጥም ውስጥ ሊያስመድበው ይችላል። ቃል ግጥም ደራሲው ብዙውን ጊዜ አለመታወቁ፣ በቃል የሚተላለፍ መሆኑ እና የቃል ግጥም አደራረሱም ሆነ መተላለፊያው እንዲሁ በልማድ እንጂ በትምህርት የሚገኝ ባለመሆኑ የግዕዝ ቅኔ ግን ጉባኤ ተዘርግቶለት መምህር ተሰይሞለት ደረጃ በደረጃ የሚማሩትና በብዙ ውጣውረድ ተፈትነው የሚያልፉበት መሆኑ ከቃል ግጥም ጋር ሊመደብ አይችልም በማለት ፈቃደ "አደራረሱ፣አከዋወኑ እና

ተስተላልፎው በቃል ይሁን እንጂ የግዕዝ ቅኔ ህዝባዊ የሚባል አይደለም። ከዘመኑ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ባህል ጋር ተያይዞ ከምሁራን ለምሁራን በንግግር ሳይሆን በተለየ የትምህርት ቋንቋ ተደርሶ የሚከወን ነው ።"(1991፣85) በማለት የግዕዝ ቅኔ የስነ ቃል ዘርፍ ከሆነው ቃል ግጥም ጋር ሊመደብ እንደማይችል ይገልጻሉ።ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ የቅኔ ድርሰት ቃላዊ ጥበብ መሆኑን "የቅኔ ድርሰት አፋዊ ጋዜጣ፣ አፋዊ መጽሄት፣ አፋዊ ጥሑፍ ወይም አፋዊ ማስታወቂያ ወይም መተቻ ነበር ማለት ይቻላል"።(ዜና ማርቆስ ፣1994፣8) ሲሉ ይገልጻሉ።

የግዕዝ ቅኔ ምንም ቃላዊ ቢሆን ደረጃ በደረጃ ከፊደል እስከ ዳዊት ከዳዊት መድገም ወደ ዜማ ከዜማ ወደ ቅኔ በሂደት የሚማሩት ነው። በዚህ መልክ የሚማሩት የቅኔ ዕውቀት ምንም ቃላዊ ቢሆንም በሰምና ወርቅ የበለጸገ በግልጽ የታወቀ ደራሲ ያለው ጥበብ ነው።

ቃል ግጥምን ያየን እንደሆነ ለመደረስም ሆነ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለመተላለፍ ጊዜ ተወስኖላቸው ቦታ ተመቻችቶላቸው እንደ ቅኔ በትምህርት የሚሰጥ ሳይሆን ቃላዊ በሆነ መልኩ ከአንዱ አካል ወደ አንዱ አካል እንዲሁም ከቦታ ቦታ የሚተላለፍ ነው።እንግዲህ ቅኔ እንደቃል ግጥም ሁሉ በቃል መደረሱ፣ አፈጣጠሩ ቅጽበታዊ መሆኑ፣በክዋኔ መታጀቡ፣ ተግባሩም የሰውን ልጅ ፍላጎት፣ተስፋ፣ምኞት፣ሀዘንና ደስታ፣ዓለምን እንዲሁም ተፈጥሮንና የመሳሰሉትን መግለጹ፣ያለው የሥነ-ግጥም ባህሪ ከቃል ግጥም ውስጥ ያስመድበዋል።

### 2.2.4 የግዕዝ ቅኔ ምንነት

የግዕዝን ቅኔ ምንነት የተለያዩ የሙያው ሊቃውንት የተለያየ ብያኔ ሰጥተውት እናያለን። እነ ኤልያስ "ቅኔ ማለት ቀነየ ገዛ፣ተቀነየ ተገዛ ከሚለው አንቀጽ የወጣ በገጸ ንባብ ብዙ ቃልን የሚያሰባስብ ዘር ሲሆን ትርጓሜው የገዥና የተገዥን ምልክት የሚያሳይ ሰዋሰው፥ መሰላል፥ መመላለሻ ማለት ነው።"(1992፣16) የሚል ብያኔ ሰጥተውታል። አለማየሁ ሞገስም ስለ ቅኔ"ቀነየ ተቀነየ- ተቀኘ ዘመረ በምስጢርና በስልት ተናገረ የሚለው ግሥ ጥሬ ዘር ስለኾነ ምስጢር የተጎናጸፈ መዝሙር ማለት ነው።"(1950፣117) በማለት ይገልጻሉ። ቅኔ የሰው ልጅ ተመራምሮ እና ከአዕምሮው አፍልቆ የሚያቀርበው ድርሰት መኾኑንም አድማሱ እንዲህ በማለት ይገልጹታል "ቅኔ ሰው ከራሱ አንቅቶ ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋና ላቅርብ ባለ ጊዜ ምሳሌ መስሎ ምስጢር አሻሽሎ ግጥም በመግጠም የልቡናውን ዕውቀት የአዕምሮውን ርቀት የሚገልጽበት የዕውቀቱን ደረጃ የሚያስታውቅበት የሰሚንም ልቡና የሚያነቃቃበትና የሚያራቅቅበት ድርሰት ማለት ነው"(1963፣9) ከነዚህ ሊቃውንት እንደምንረዳው ቅኔ

ምርምርን የሚጠይቅ አዲስ ሀሳብ የሚፈልቅበት የሰዎችም የዕውቀት ደረጃ የሚለካበት ጥበብ እንደኾነ ነው። ሌላው ስለ ግዕዝ ቅኔ ምንነት ከጻፉ ሊቃውን አንዱ የኾኑት ዜና ማርቆስ ቅኔን እንዲህ በማለት ይገልጹታል።"ቅኔ የቅኔ ሊቃውንት በመንፈሳዊም ኾነ በስጋዊ ሐሳባቸውን የሚገልጡበት የምርምርና የፍልስፍና ድርሰት ነው።" (1964፣2) ቅኔ ምንጩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ይሁን እንጅ ሊቃውንቱ የሚደርሱት በሃይማኖት ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን የሰው ልጆችን ህይወት በሙሉ የሚዳስስ አዕምሮንም ወደፍልስፍና የሚመራና የሚያመራምር ጥበብ መሆኑን እንረዳለን።

የግዕዝ ቅኔ ተራ ግጥም ሳይሆን በሚስጥር የተሞላ ጥበብ መሆኑን አፈወርቅ "ቅኔ እንደማንኛውም ግጥም ቤቱን ማስያዝ ብቻ ሳይሆን ምስጢር፣ሰምና ወርቅ ኅብር ያለው ነው። "(1997፣26) በማለት ይገልጻሉ። ከግዕዝ ቅኔ ውጪ ያሉት ግጥሞች ብዙውን ጊዜ ነጠላ ትርጉም ያላቸውና ማንኛውም አንባቢ በቀላሉ ሊረዳቸው የሚችላቸው ናቸው። የግዕዝ ቅኔ ግን በውስን ስንኞች የተለያዩ ሚስጥራዊ ሀሳቦችን ያዘለ ድርሰት ሲሆን ትርጓሜውንም በቀላሉ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። ይህ ትርጓሜን የሚሻ ድርሰት ህሊናን በተመስጦ የሚመጥቅ መሆኑን ሊቁ አድማሱ ጀንበሬ እንዲህ ይገልጹታል። "ቅኔ ሕዋሳተ አፍን ሕዋሳተ ውስጥን ለህሊና አስገዝቶ በተወሰነ ቁርጥ ሀሳብ የሚታሰብ ስለሆነ ቅኔ ተብሏል። ይኸውም ሊታወቅ በቅኔ ሚስጥር ልቡ የተነካ ሰው ቅኔ በሚያስብበት ጊዜ በፊቱ የሚደረገውን ነገር እያየ አያይም፣እየሰማ አይሰማም።" ከሊቁ ሀሳብ እንደምንረዳው ቅኔ ልዩ የጥበብ ፣ የምርምር፣ የተመስጦ እና በምስጢር የሚራቀቁበት  የሰውን ልቡና የሚገዛ  ጥበባዊ ሀብት መሆኑን ነው። "ቅኔ ማለት ቅኚት ማለት ነው። የበገና ቅኚት በድኅንጻው አማካይነት ድንቅ ቃናን እንደሚሰጥ እንዲሁም ቅኔ የኅሊና ቅኚት ኾኖ በሠምና ወርቅ ስሞች ጥምረት መንፈስን የሚያረካ ምስጢርን ይሰጣል ።ስለዚህ ቅኔ ስሌት፣ ቆጠራ፣ ግራት፣ ግዛት ምስጋና፣ ምስለት...በሚሉ ነገሮች ይተረጎማል።"(ስርግው፣2010፣1) በማለት የግዕዝ ቅኔን ጥበባዊነት እና ዜማዊነቱን፣ በሚስጥር የበለጸገ፣ የተለያዩ ዕሳቤዎች በአንድነት የሚይዝ መሆኑን ይገልጻሉ።እንግዲህ ይህ ታላቅ ፍልስፍናዊ ጥበብ በብዙ ውጣውረድና ድካም የሚገኝ ጥንታዊ የዕውቀትና የፍልስፍና ድርሰት ከሐይማኖቱ ባሻገር መልካሙን ማሞገሻ፣ እኩይ የሆኑ ምግባራትና እሳቤዎችን መንቀፊያና መተቻ የሆነ ቃላዊ ጥበብ መሆኑን "ቅኔ መሳፍንቱ፣ የሴት ወይዘሮው፣ ነገስታቱና ጳጳሳቱ ህዝቡን በበጎ አስተዳደር ሲመሩ የሚሞገሱበትና የሚወደሱበት፣ ሕዝቡን በአስተዳደር ሲበድሉ ደግሞ የሚወቀሱበት የሚዘለፉበትና የሚመከሩበት ድርሰት ነው።" (ዜና ማርቆስ ፣

1994፣8) ሲሉ ይገልጻሉ። ከሊቃውንቱ ሃሳብ እንደምንረዳው የግዕዝ ቅኔ ሀሳብ የሚራቀቅበት ታላላቅ ነገስታትን ጨምሮ እስከ ተራው ህዝብ ድረስ እንደየተግባራቸው የሚሞገሱበትና የሚነቀፉበት እረቂቅ ዕሳቤዎች የሚገለጡበት ሰፊ የጥበብ ባህር መሆኑን ነው።

### 2.2.5 የግዕዝ ቅኔ አጀማመር

የግዕዝ ቅኔ በማን እና መቼ ተጀመረ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አዳጋች ቢሆንም የተለያዩ ምሁራን ያቀረቧቸውን የተለያዩ ታሪካዊ ማስረጃዎችን ለማየት ተሞክሯል። የግዕዝ ቅኔን ጀማሪ ማርዬ "የቅኔ ፈጣሪው (ጀማሪው)ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ ይታመናል። ይሁን እንጂ ለቅዱስ ያሬድ ልዩ ልዩ ድርሰቶች መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ እንደመኾኑ መጠን የቅኔ ድርሰቱም መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ይታመናል።"(2006፣49) በማለት ይገልጻሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ያሉ የዳዊት መዝሙርና መሀልዬ መኃልይ የሚባለው የሰለሞን መጽሐፍ ልክ እንደቅኔው ሁሉ ትርጓሜ የሚያሻቸውና ሚስጥር አዘል በመኾናቸው ለቅዱስ ያሬድ ቅኔ እንደመነሻ መሆናቸውን ያመላክታሉ። ስለቅኔ አጀማመር የተለያየ ሀሳብ እንዳለ እነ ኤልያስም እንዲህ ይገልጻሉ።

> የቅኔ አጀማመር በቅዱስ ያሬድ ነው። ሆኖም መልክ አበጅተው በስርዓት ደንግገው ቤት ሰጥተው በቁጥር ወስነው ያሁኑን የቅኔ ውበት የሰጡት ሐዊራ ፥ መንክራ ፥ እስክንድራ ፥ ፓኦድራ ፥ አቢዳራ ይባላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ዋድሎች በበኩላቸው ቅኔን የደረሰው ዮሐንስ ገብላዊ ነው ሲሉ ጎንጆች ደግሞ ተዋነይ ነው ይላሉ።ሌላም እንዲሁ ደቀ እስጢፋ ነው የሚሉ አሉ።ዮሐንስ ገብላዊ የነበረበትም ቦታ በወሎ ክፍለ ሀገር በአማራ ሳይንት በታቦር ተራራ ነበር።ታዲያ ይህ ዮሐንስ ገብላዊ የተባለው ፊት ብዙዎችን እንዳስተማረ አብነት አድርጎ ያወጣውና በእግሩ የተካው አባ ወልደገብርኤል የተባለውን መነኩሴ ነው። አባ ወልደገብርኤል ደግሞ ራሱን አስመስሎ በሞያ የወለደው ሠምረ አብን ነው።ሠምረ አብ በሚያስተምርበት ጊዜ ጉባኤ አስፍቶ ደቀመዛሙርት አብዝቶ ያስተምር ስለነበር...(1992፣16-18)

የቅኔ ጀማሪ ማንነት ላይ የሚነሳው የተለያየ ሀሳብ ገብረ ዮሐንስም የቅኔ ጀማሪን በተመለከተ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሁለት የተለያዩ ዘገባዎች እንዳሉ በመግለጽ አንደኛው ሀሳብ ዮሐንስ ገብላዊ ሲሆን እሱ ያስተማራቸው እየተተካከ ወልደማርያምንና ተዋናይን በእውቀት እንደወለዱ የሚገልጽ ታሪክ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወደግሪክ ሄዶ ፍልስፍናን በመማር ቅኔን የፈለሰፈውና በጎጃም ቅኔን ያስፋፋው ደቀ እስጢፋ እንደኾነ የሚገልጽ ሀሳብ ነው።(1992፣28-

29) ከላይ ያየናቸው ሊቃውንት የቅኔ ጀማሪ ማነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተለያየ እሳቤ እንዳለ ቢያሳዩም ሁሉም ግን ቅኔ አሁን ያለበት ደረጃ ያደረሱት በየዘመኑ የነበሩ የተለያዩ ሊቃውንት ቢሆኑም ጀማሪው ግን ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ።ይህንን አስመልክተው አፈወርቅ "የያሬድ ቅኔ ቤተኛም ቢሆን ቤት አልባም ቢሆን ጉት ግጥም ነው። ሆኖም በዚህ በታላቅ ስራው በዜማው ድርሰት ውስጥ ቅኔን በማስገባቱና በማዋሀዱ የቅኔን ሙያ አጎላው ርግጥ ከርሱ በኃላ የተነሱ ሊቃውንት የያሬድን ፈለግ ተከትለው የዠመረውን ስራ አስፋፍተዋል።ይህ ግን ከቅኔ ቀደምት መስራቾች ዋነኛው ከመሆን አያግደውም " (1980፣ 3) በማለት ቅኔ አሁን የያዘውን ቅርጽ እንዲይዝ በርካታ ሊቃውንት የየራሳቸውን አስተዋጾ ቢያበረክቱም ጀማሪው ግን ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ በአጽንዖት ይገልጻሉ። ይህንን ሀሳብም በመደገፍ ማርዬ "በአጠቃላይ ቅኔን ቅዱስ ያሬድ ከፈጠረው በኃላ በየዘመናቱ የተነሱ ሊቃውንት ዜማ ልኩን እየመጠኑና እያራቀቁ ዛሬ ካለበት ደረጃ አድርሰውታል። "(2006፣59) በማለት ይገልጻሉ። በአጠቃላይ የግዕዝ ቅኔ በማን ተጀመረ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተደረገው ምርምር የቅኔ ጀማሪው ቅዱስ ያሬድ ይሆናል ከሚል አጠራጣሪ መልስ ባለፈ እንግጠኛ ሆኖ ለመናገር አለመቻሉን ያሳያል።

### 2.2.6 የቅኔ የሐሳብ ምንጭ

ቅኔ በሰው ልጆች አዕምሮ ተጸንሶ የሚወለድ እንደመሆኑ ባለቅኔው ቅኔን ለመድረስ የተለያዩ እውቀቶች ሊኖሩት ያስፈልጋል። ይህም ማለት ቅኔ የሚቀኘው አካል ውሎ አድሮ አስቦና አሰላስሎ የሚጽፈው ሳይሆን ሁኔታው ቅኔ መቀኘትን የሚጠይቅ በሆነበት አጋጣሚ ሁሉ አዕምሮ በፍጥነት የሚደርሰው በመሆኑ በተለያየ ዘርፍ ላቅ ያለ ችሎታ ያስፈልገዋል። እነዚህን የቅኔ የሀሳብ መነሻዎችን ማርዬ ቅኔያዊ የዕውቀት ፈጠራ በተባለው መጽሐፋቸው በዝርዝር ገልጸዋቸዋል። እነዚህም በተወሰነ መልኩ እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

አንድ ሰው ቅኔ ለመቀኘት የቋንቋ እውቀት ያስፈልገዋል ይህም ማለት ከዘወትራዊው ንግግር በላቀ ሁኔታ አመስጥሮና አራቆ መቀኘትን ስለሚጠይቅ የቋንቋውን ስርዓት ማወቅ የግዴታ ይሆናል።ማርዬ ስለቋቋ ዕውቀት አስፈላጊነት ሲገልጹ "በግዕዝ ቋንቋም ኾነ በሌላው ለመቀኘት የቋንቋውን ስርዓት ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል።ለምሳሌ የግስ አረባብና የቃላት አጠቃቀም፣የቁጥር ልክ፣የቅርብና የሩቅ፣የሴትና የወንድ ልዩነትን ልብ ማለት ይገባል።"(2006፣61) ከጽሑፉ እንደምንረዳው የቋንቋውን ሰዋሰው ማወቅ ሐሳብን በተለየ መንገድና ጥበብ ለመግለጽ ጠቃሚ እንደሆነ ነው። ሌላው ለቅኔ መሰረት የሚሆነው የሃይማኖት ትምህርት ዕውቀት ነው። ቅኔ

ሃይማኖታዊ ብቻ ባይሆንም ብዙ ጊዜ የሚቀርበው ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን መሰረት አድርጎ በመሆኑ ባለቅኔው ጥልቅ የሆነ የሃይማኖት እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ ቅኔ የሃይማኖት ትምህርት ዕውቀት እንደሚያስፈልገውም ማርዬ"ብዙው የቅኔ አገልግሎት በቤተክርስትያን ስለሚከናወን አንድ ሰው መሰረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ብቻ ማወቅ ሳይሆን ቅኔው የሃይማኖቱን እምነት እና ቀኖና የማይቃረን መሆን አለበት፡፡"(2006፣63) ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ቅኔ ለመቀኘት ሌላው መሰረት የበዓላት እና የታሪክ ዕውቀት ነው፡፡ ባለቅኔው ብዙውን ጊዜ የሚቀኘው ሃይማኖታዊውንና ሰዋዊውን ጉዳይ አስማምቶ በመሆኑ ከእምነት አንጻር የቅዱሳንን ታሪክ እና በየዕለቱ የሚታሰቡ በዓላትን ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ከመንፈሳዊው ዓለም ውጭ ደግሞ በዓለም፣በሀገር እንዲሁም በአካባቢ የተከሰቱ ታሪካዊ ጉዳዮችን በማወቅና በመመርመር አስተባብሮ ለመቀኘት እነዚህ ዕውቀቶች መሰረታዊ ናቸው፡፡

ሌላውና አራተኛው የቅኔ ምንጭ የቅኔ ቀመር እውቀት ነው፡፡ ስለቅኔ ቀመር ዕውቀት አስፈላጊነት ማርዬ "ቅኔ የራሱ ቀመር አለው፡፡ ይኸንን ቀመር ወይም መጠን ከዜማውና ከሚቀርብበት ወቅት(ጊዜ) ጋር አስተባብሮ ማወቅ ግድ ነው፡፡ አንድ ሰው ቅኔ ለማቅረብ ሲነሳ ቅኔው ጉባኤ ቃና ወይም መወድስ መኾኑን መወሰን አለበት ፡፡" (2006፣65)ይህ ማለት የሚቀርቡት ቅኔዎች ከቅኔ አይነቶች ውስጥ በአንዱ የሚመደቡ መሆን ስላለባቸው ባለቅኔው የሚያቀርበውን የቅኔ ቀመር ለይቶ ማመቅ መቻል አለበት፡፡ ለቅኔ የሐሳብ ምንጭ የሆነው አምስተኛው ጉዳይ  የወቅታዊ ሁኔታ ግንዛቤ ነው፡፡ ባለቅኔው በሚቀኝበት ወቅት በዙሪያው ያለውን ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ጉዳዮች በመቃኘት በእነዚህ ላይ ተመስርቶ ቅኔውን ያቀርባል፡፡የወቅታዊ ሁኔታን አስፈላጊነት ማርዬ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡"አዕምሮ ቅኔን ሲያመነጭ የሚያገናዝባቸውና ለቅኔው መነሻነት የሚጠቀምባቸው ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም ደስታና ሐዘን፣ሹመትና ሽረት፣ሰላምና ጦርነት፣ ጥጋብና ረሀብ የመሳሰሉ ክስተቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ክስተቶች ለቅኔ እንደዋና ምንጭ ይወሰዳሉ፡፡"(2006፣65) እነዚህ ከላይ የተዳሰሱት የቅኔ የሐሳብ ምንጮች ባለቅኔው ምንያህል አዋቂ እና ተፈጥሮንም ሆነ ዙሪያ ገባውን መመርመር መቻል እንዳለበት ያመላክታል፡፡

### 2.2.7 አርእስተ ቅኔ

የግዕዝ ቅኔ አይነቶች የተለያዩ ሲሆኑ የልዩነታቸው መሰረትም ከቅኔዎቹ መጠንና ከሚያተኩሩበት ርዕሰ ጉዳይ እንደሆነ የሙያው ሊቃውንት ይግልጻሉ፡፡ ስለቅኔ አይነቶች ማርዬ "ቅኔን ለዜማ እንዲመች አድርጎ መጥኖ ማቅረብ ግድ ስለሆነ ከመጠንና ከሚያተኩሩበት ርዕሰ

ጉዳይ አንጻር የቅኔ አይነቶችን ከፋፍሎ ማየት ብዙ የተለመደ ነው። በመጠንና በትኩረት ያላቸውን ልዩነት ስንመለከት በዋናነት ዘጠኝ የቅኔ ዓይነቶች አሉ። ከነዚህ ውስጥ ደግሞ አንዳንዶቹ ሁለትና ሦስት ዓይነት ያላቸው ስላሉ በአጠቃላይ አስራ ሰባት ቅኔዎች አሉ ማለት ይቻላል። "(2006፣38) በማለት ይገልጻሉ።

## 1. ጉባኤ ቃና

ይህ ቅኔ ሁለት ስንኝ (ቤት) ያለው ሲሆን የመለኮትና የትስብዕት ምሳሌ ነው። ስንኞቹ ከሚኖራቸው መጠን አንጻር አጭር ጉባኤ ቃና (ሐረጉ አጭር የሆነ)እና ረጅም ጉባኤ ቃና(ሐረጉ ረጅም የሆነ) ከሚዜሙበት ዜማ ስልት አንጻር ደግሞ ዕዝል ጉባኤ ቃና እና ግዕዝ ጉባኤ ቃና ተብለው ስለሚከፈሉ አራት አይነት ጉባኤ ቃና ቅኔዎች አሉ ማለት ይቻላል። ዕዝልም ሆነ ግዕዝ ጉባኤ ቃና ረጅምና አጭር ሊሆን ይችላል። ጉባኤ ቃና ስያሜውን ያገኘው ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው በቃና ዘገሊላ መታሰቢያ ዕለት (ጥር 12 ቀን) በመሆኑ ነው የሚሉ አሉ። መጀመሪያ ሁለት ቤት ስንኝ ኖሮት ሸዋ ውስጥ ቃና በሚባል ቦታ በተካሄደ ጉባኤ ላይ ስለተደረገ ነው የሚልም አለ።አይ ከዚህ ይልቅ የቅኔ (ጉባኤ) ቃና የሚባለው የቅኔን ጣዕም ለማመላከት ነው የሚሉም አሉ።ያም ሆነ ይህ ሁለት ስንኝ ብቻ ያለው መሆኑ ለተማሪ ጥናት የቀና (የተመቸ) ነው። ስለሆነም ተማሪው ሁሉ የቅኔ ልምምድ የሚያደርገው ጉባኤ ቃና ቅኔ በማጥናትና በመቁጠር የቅኔ አፍ መፍቻ ነው ማለት ይቻላል።(ማርዬ፣2006፣41)

## 2. ዘአምላኪየ

ዘአምላኪየ የቅኔው ተማሪ አምላኪየ አምላኪየ (መዝ 62፣1) የሚለውን መዝሙር አዚሞ የሚመራው በመሆኑ ዘአምላኪየ ተብሏል። ዘአምላኪየ ቅኔ በመጀመሪያ ቤትና በመጨረሻው ቤት ጉባኤ ቃና ሲሆን በመካከለኛው ሁለተኛ ቤትና ሐረግ ልዩ ነው። ይኽም ልዩ ሐረግ በአነባበቡ ኂደት መሰረት መንደርደሪያ ይባልኣል። የቁልቁለት መንገድ ኂያጅን ወደታች እንደሚያንደረድረው ኹሉ አነባበቡ ግፊት ያለው ስለኾነ ነው። ቤቱ ሦስት መሆኑ የሦስትነት ምሳሌ ሲኾን የቤቱ ቀለም /ፊደል/ አለመለወጡ ያንድነት ምሳሌ ነው። ሐረጉ ከእነመንደረደሪያው ዐምስት ይሆንኣል። ከሦስቱ አንዱ አካል ዐምስቱን ክፍላተ ሰማይ አልፎ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱ ምሳሌ ነው።(ስርግው ፣2010፣13)

## 3. ሚበዝኁ

ሦስት ቤት ነው። ይኸውም በመወድስ አደራረስ የሚቀኙት ቅኔ ነው።ሚበዝኁ የተባለበት ምክንያት እግዚኦ ሚበዝኁ እለይሣቅዮኒ በሚለው መዝሙር የሚገባ ስለሆነ ነው።(ጎሩይ፣ 1918፣6)

## 4. ዋዜማ ቅኔ

ይኸ ቅኔ በአምስት ቤቶችና በዘጠኝ ሐረጎች ተወስኖአል። ቤቱ የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ ሲኾን፣ ሐረጉ የዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላዕክትና ጌታ በዘጠኝ ሰዓት ደምንና ውኃን የማፍሰሱ ተምሳሌት ነው። ትርጉሙ ወይ(ዜማ) ማለት ነው።ምክንያቱም የሚዜምበት የዜማ ስልት ለዛና ጣዕም ያለው አራራይ ስለሆነ ነው። ይሁን እንጂ ዋናው በዓል እንደነገ ሊሆን እንደዛሬ ጧት ሲቀደስ፣ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ቀደም ብሎም በኃላም፣ በሰባት ሰዓት ሲቀደስም ደግሞ ከሦስት ሰዓት ጀምሮ የሚዘመረው የበዓሉ ነክ መዝሙር ዋዜማ ይባልኣል። በዚኽ ጊዜ ትርጉሙ የበዓሉ መግለጫ /መግቢያ/ ማለት ይሆንኣል።(ስርግው ፣2010፣13 )

## 5. ሥላሴ ቅኔ

ሥላሴ ቅኔ ቤቱ ስድስት ሲሆን ምሳሌነቱም የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ነው። መንደርደሪያና ምድፊያ አለው። ዜማው ሁልጊዜ ዕዝል ነው። ቅኔውም የአበው (የሽማግሌዎች) ቅኔ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ለአዋቂዎችና ለታላላቅ ሰዎች ነው። የስላሴ ቅኔ የሚቀርበው በዋዜማ ክስተትና አርያም አደራረስ፣ በጸሎተ ሰለስቱ ደቂቅና በይትባረክ እግዜብሔር አምላክ አበዊነ ጊዜ ሰብህዎ በሚለው መዝሙር ነው። ሥላሴ የተባለበት ምክንያት "ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ"በሚለው በጸሎተ ሰለስቱ ደቂቅ ድርሰት እየገባ የሚነገር ስለሆነ አምላከ አብርሃም፣ አምላከ ይስሐቅ፣ አምላከ ያዕቆብ እያሉ ሦስትነትን የሚገልጸውን እየዘመሩ ስለሚጀምሩትሥላሴ የሚለው ስያሜ ተሰጥቶታል።(በላይነህ፣1999፣52)

## 6. ዘይዕዜ ቅኔ

ዘይዕዜ ቅኔ ብዙ ጊዜ ስለንጉሥ ክብር ይቀርባል። ዘይዕዜ የተባለውም ከዳዊት መዝሙር "ይዕዜ ትስዕሮ ለገብርከ" በማለት ስለሚጀምር ነው። ዘይዕዜ ቅኔ አጭርና ረጂም ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ረጂሙ ዘይዕዜ አምስት ቤት አለው (የአምስቱ አዕማደ ሚስጥር ምሳሌ ነው)፣

ዜማው ግዕዝ ነው። አጭሩ ዘይዕዜ ሦስት ቤት ሲሆን "ተሰሃለኒ እግዚኦ በከመ እበየ ሳህልከ " የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ስለሚጀምሩት "ሳህልከ" ይባላል፣ ዜማውም አራራይ ነው። (ማርዬ፣2006፣42)

## 7. ሣህልከ ቅኔ

ሣህልከ የተባለው ቅኔ በሦስት ቤቶችና በዐምስት ሐረጎች የተወሰነ ድርሰት ሲኾን፣ የቅኔው ይዘትም በሀገሪቱ ሰላምና በሕዝቧ ደኅንነት ላይ ያተኩራል። ይኸም ማለት ማንኛውም ባለቅኔ ይኽን ቅኔ ሲቀኝ ቅኔው ስለሀገሪቱ ሰላምና ስለ ሕዝቧ ደኅንነት ማውሣት አለበት ማለት ነው። ምክንያቱም "ዝንጀሮ የመቀመጫዬ ይቅደም" አለች እንደሚባለው ምሳሌ ኹሉ፣ ከኹሉ በፊት ስለሀገር ሰላም ማሰብና መጸለይ የሚገባ በመሆኑ ነው። ቤቱ ሦስት መሆኑ የሀገሪቱ ሰላም አጠባበቅ በጦር ሰዎች፣ በሕዝብና በመንፈሳዊያን፣ በእነዚህ በሦስት ወገኖች ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያስረዳል። ሐረጉም ዐአምስት መሆኑ ይኽን ቅኔ ወደሚቀኘው ባለቅኔ ቀርቦ የሚመራው ተማሪ ከቅኔው በፊት በየጊዜው በፈረቃ የሚያዜማቸው ዐምስት የምዕራፍ ጸሎቶች አሉና በእነርሱ ተምሳሌት ነው። ስለዚኽም ሣህልከ ማለት፣ይቅርታህ፣ሰላምህ፣ፀጥታህ ለመንግሥታችን፣ለሀገራችንይሁን ማለት ነው። ይኸውም "መቅድመ ኅሡ ሰላማ ለብሔር እስመ በሰላመ ብሔር ይከውን ንብረትክሙ። /በቅድሚያ የአገርን ሰላም ሹ (ፈልጉ) አኗኗራችሁ በሀገር ሰላም ነው እና" ብሎ የአርማንያ ሊቀ ጳጳስ ጎርጎርዮስ በተናገረው መሰረት ነው። (ስርግው፣2010፣15-16 )

## 8. መወድስ ቅኔ

ይኽ ቅኔ በመወድስ አወራረድ ከመዝሙር እስከ ፍታሕ ሊተ ባሉት የዜማ አባባል ደረጃዎች በስምንተኛው ደረጃ በፍታህ ሊተ (መዝ 42፣1) ስለሚገባ በስምንት ቤቶችና በዐሥራ ስምንት ሐረጎች ተወስኖአል። ስለዚኽም ዐፄ እስክንድር በእሑድ ቀን በስምንተኛው ሰዓተ ሌሊት መጥተው ባለስምንት ቤት መወድስና ባለዘጠኝ ቤት ኵልክሙ ተቀኝተውኣል በማለት ይተርክኣል። ሐረጉ ዐሥራ ስምንት ሲኾን ፣ዐሥሩ መዓርጋት ፣ሰባቱ በሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስትያን ይመሰላሉ። ስምንተኛው በዋጋ ሰጪው ይመሰልኣል። መወድስ ቧሔ የሚባል ሐረግ አለው። መወድስ ቅኔ **ለዐለም** በሚል ነገር መክፈሉ የዓለመ ሥጋና የዓለመ ነፍስ አምሳል ነው። የባለቅኔው ተመሪው **ፍታህ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ** የሚለውን

መዝሙር እያዜሙ ወደ ባለቅኔው ቀርቦ ስለሚያዜመው መወድስን ፍታህ ሊተ የሚሉም አሉ። (ስርግው ፣2010፣16)

## 9. ኰልክሙ

**ኰልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ** (መዝ 46፣1) በሚል መዝሙር ዜማ ስለሚገባ **ኰልክሙ** ተብሎኣል። ኰልክሙ በዘጠኝ ቤቶችና በኻያ ሐረጎች ተወስኖአል። ጌታ በዘጠኝ ሰዓት ነፍሱን ከሥጋውው ለይቶ **ኰልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ**የተባሉትን የማዳኑ ምሳሌ ነው። ሐረጉም የኻያው ዓለማት ምሳሌ ይሆንኣል። "እጋዜ ዓለም በእራኁ /ዓለምን በመዳፉ የጨበጠ/" የተባለ ጌታ በእነዚህ ይመሰገንኣልና። በመወድስ የተወሣው ቧሔ ሐረግ በኵልክሙም አለ። (ስርግው ፣2010፣16)

## 10. ክብር ይእቲ

ክብር ይእቲ ግዕዙም ዕዝሉም አራት ቤት ነው። ይኸውም በቅዳሴ ጊዜ ድርገት ከመውረድ አስቀድሞ የሚቀኙት ቅኔ ነው። ክብር ይእቲ የተባለበት ምክንያት ባለቅኔው ይኸን ቅኔ ተናግሮ ሲጨርስ መዘምራኑ ተቀብለው አንድ ጊዜ ከዘለቁት በኋላ ባለቅኔው ክብር ይዕቲ ዛቲ ለኵሉ ጻድቃኑ ብሎ የሚሰግድ ስለሆነ ነው። (ጎሩይ፣1918፣7)

## 11. ግዕዝ እጣነ ሞገር

ይኽ ቅኔ በሰባት ቤቶችና በአሥራ ሦስት ሐረጎች የተወሰነ ነው። ትርጓሜው የማሳረጊያ/የመጨረሻ/ ዕጣን ማለት ነው። ምክንያቱም ዕጣን የሚታጠንባቸው ጊዜያት ሰባት ስለሆኑና በሰባተኛው ዕጥናት ጊዜ ይኽ ቅኔ ስለሚነገር ነው። ቤቱ ሰባት መሆኑ ስብዐ ለዕለትየ እሴብሐከ (መዝ. 118፣164) እንዲል በሰባቱ ጊዜያት የሚመሰገነው ጌታ ስለዓለም ቤዛ መሞቱን ያስረዳል። ሐረጉ ዐሥራ ሦስት መሆኑ፣ ጌታ ዐሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል የመቀበሉ ምሳሌ ነው።(ስርግው ፣2010፣18)

## 12. ዕዝል ዕጣነ ሞገር ቅኔ

ይኽ ቅኔ በአሥራአንድ ቤቶችና በአሥራ ስምንት ሐረጎች ተወስኖአል፣ ከግዕዙ ዕጣነ ሞገር የሚለየው በቤቶቹና በሐረጎች ተጨማሪዎች ሲኾን፣ ዐሥራ አንዱ ቤቶች ፣ በመስቀል የተሰቀለውን በዐሥራ አንድ ሰዓት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ከመስቀል አውርደው ገንዘው

የመቅበራቸው ምሳሌ ነው:: ዐሥራ ስምንቱ ሐረጎች የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መራጭ ጌታ በስድስት ሰዓተ መዓልት የመሰቀሉ ምሳሌ ነው:: ግዕዙም ዕጣነ ሞገርና ዕዝሉ ዕጣነ ሞገር የሚዜሙት የዕለቱ ዝማሬ ከተባለ በኋላ ነው:: የቅኔው ኹሉ መጨረሻ እንደመሆናቸው በቅዳሴ መጨረሻ ላይ እንዲነገሩ ተደርጎኣል:: (ስርግው ፣2010፣18)

## 13. አሠረ ንጉሥ

አሠረ ንጉሥ ከዚህ በላይ እንዳስረዳን በግዕዝና በዕዝል እጣነ ሞገር ከመንደርደሪያው ቀጥሎ የሚገባ ቅኔ ነው:: አሠረ ንጉሥ የተባለበት ምክንያት ለነገሥታት ምስጋና ብቻ እንጂ የበዓል ቅኔ ባለመሆኑ ነው:: በቀድሞ ዘመን ለነገሥታት ምስጋና ብቻ እንጂ ለሌላ ሰው ይህን የምስጋና ቅኔ ማቅረብ ክልክል ነበረ ይባላል::(ጎሩይ፣1918፣8)

### 2.2.8 የግዕዝ ቅኔ መንገዶች

የግዕዝ ቅኔ መንገዶችን በተመለከተ የተለያዩ በዘርፉ ያሉ ምኹራን የተለያየ ቁጥር በመጥቀስ በርካታ እንደኾኑ ይገልጻል:: ስርግው (ዶ/ር) የግዕዝ ቅኔ መንገዶች ቅፅ ፩ መጽሐፋቸው የግዕዝ ቅኔ መንገዶች 653 ሲኾኑ በዚህ መጽሐፍ ያቀረቧቸው ደግሞ 310 የቅኔ መንገዶችን ነው :: ከነዚህ 310 የቅኔ መንገዶች ይኹኑ እንጂ አውራ የሚባሉት ዋና ዋና መንገዶች ስምንት እንደሆኑ ይገልጻሉ::(2010፣ 27):: አፈወርቅም (አለቃ) ስለ ቅኔ መንገድ ሲግልጹ "የቅኔ ጎዳና ከሺ በላይ ሲኾኑ በጉባኤያት የሚነገሩት 300 ናቸው ::"(1997፣42) በማለት የቅኔ መንገዶች በርካታ እንደኾኑ ይገልጻሉ:: ላዕከማርያም "ጉዳያቸውን ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት ይዘታዊ ትንተና "በሚል በ2010 ዓ.ም ባቀረበው ጥናት ላይ እንዳስቀመጠው የግዕዝ ቅኔ መንገዶች ላይ የተለያየ አመለካከት መኖሩን ይገልጻል:: አንደኛው አመለካከት አንደኛ ሠምና ወርቅ ኹለተኛ ብሂል ብሂል፣ ሦስተኛ ጎዳና ብለው በሦስት ዓበይት ክፍሎች እንደከፈሏቸው ይገልጻል:: ሌላው አመለካከት ደግሞ መቶ አሥራ ሰባት የቅኔ መንገዶች እንዳሉ የሚገልጽ ነው:: እንደ ላዕከማርያም አገላለጽ እነዚህ በርካታ ቁጥር ያላቸው የቅኔ መንገዶች አንዱ ከአንዱ የሚመሳሰል በመኾኑ ሰፊ ልዩነት ያላቸውን አስራ አራት የቅኔ መንገዶችን በመለየት ለነሱ ማብራሪያ ሰጥቷል:: ይህ ጥናትም ላዕከ ማርያም የለያቸውን የቅኔ መንገዶች የሚከተል ይሆናል::

## 1. ተራ ምሳሌ (ሠምና ወርቅ)

በቅኔ ውስጥ ሠምና ወርቅ ኾነው የሚነገሩበት ቃላት በተራ ወይም በተርታ ጎን ለጎን ተሰልፈው ሲታዩ አሰካኩ ተራ ምሳሌ ይባላል፡፡ (ኪዳነ ወልድ ፣1948፣160)

## 2. ኅብር መንገድ

ለሰምና ለወርቅ ያላንዳች አድልዎ የሚያስተባብር ሰም በቅኔው ውስጥ ሲኖር ኅብር ይባላል ፡፡ ይኸውም የኅብረት የጋራ ማለት ነው፡፡ ሰምና ወርቅ ሲለዩ ለሁለቱም የደረሰ ቃል መኾን አለበት ፡፡ ሰምና ወርቅ ባልና ሚስት ሲኾኑ ኅብር ልጅ ማለት ነው፡፡ (አለማየሁ፣1950፣121)

## 3. ውስጠ ወይራ

ውስጠ ወይራ በዘይቤው አወጣጥ ውስጡ ወይራ የኾነ /በውስጡ ወይራ ያለው ዘይት ማለት ሲኾን የሰዋሰው ነገር በዚኽ የተሰየመበት ምስጢር እንዲኽ ነው፡፡ መለኞች አትክልተኞች ዘይቱን ፈልፍለው ወይራውን በፍልፍሉ ውስጥ አግብተው ያጣምሩና ያዳቅሉትኣል፡፡ ስለዚኽ አንድ ይኾኑና፣ ከውስጡ ወይራ ጥንካሬ ሲገኝ ከውጪ ዘይት ጣዕም ይወልድኣል፡፡ በአንጻሩም ወይራው በዘይቱ ውስጥ ተሸፍኖ በዘይቱ እንደሚሰጠው ኹሉ፣ በሠም ዘርፍ ባለቤት የተሸፈነ ነው፡፡ የወርቅ ዘርፍ በተናባቢ ሙሻ ዘርና በለ ሙሻ ዘር ከሠም ዘርፍ ባለቤት ጋር ተጣምሮ ወርቅን ያስገኛኣልና፣ ለዚኽ ነው፡፡ (ስርግው፣2010፣88-89)

## 4. ዝምድ መንገድ

ወርቅ ቀድሞ ሰም ተከትሎ ከወርቅ ዘርፍ ላይ ሲወድቅ ነው፡፡(አለማየ፣1950፣121)፡፡ እንደ ኅብር እና እንደ ውስጠ ወይራ የቃላት ቁጠባ ባይኖረውም ዝምድ ከውስጠ ወይራ ይልቅ ግልጽ በመኾኑ ተወዳጅ መንገድ ነው፡፡ ምሳሌ፦ "ክርስቶስ ኅብስት ተሠርዐ በመስቀል መሶበ አይሁድ "ይህ አካሄድ ዝምድ የተባለበት ምክንያት ወርቁ ከራሱ ይልቅ ለሰሙ አድልቶ የራሱን ዘርፍ ስለሰጠው ኹለቱ ነገሮች የተፈቃቀሩና የተዛመዱ መኾናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡"(ሀብተ ማርያም 1963፣200)

## 5. ዐይነ ውሀ (ልብሰ ወርቅ)

ይህ ስያሜ የተወሰደው መልክን ወይም ጥላን በውሀ ውስጥ ከማየት ጋር በማመሳሰል ነው። ለምሳሌ ውሀን በአንድ ሰፊ ዕቃ አድርገን ከወለሉ ላይ አስቀምጠን ከውስጡ ብንመለከት የቤቱን ጣራ እንመለከታለን ። ሌላም ብዙ ነገር እናያለን። ነገር ግን እጃችንን ከውሀው ውስጥ ብንከተው ምንም የምንጨብጠው ነገር የለም። እንዲኹም በዚህ ዐይነት ቅኔ ውስጥ በተነገሩት ጥቂት ቃላት አማካይነት ያልተነገሩትና ሊኖሩ የሚያስፈልጉት ቃላት ኹሉ ወለል ብለው ስለሚታዩ አካሄዱ ዐይነ ውሀ ተብሎ ተሰይሟል።(ሀብተ ማርያም፣1963፣200)

## 6. ሠም ለበስ

በልብስ ተሸፍኖ የተቀመጠ ወይም የተኛ ሰው በትክክል ማንነቱ ባይታወቅም ሰው መኾኑና ሕጻን ወይም ትልቅ መኾኑ እንደሚታወቅ ኹሉ እንዲሁም በዚህ ዐይነቱ የቅኔ መንገድ ምንም ሰሙ ወርቁን ቢሸፍነው ወርቁ ከውስጡ መኖሩ ይታወቃል፤ ነገር ግን በትክክል ይህ ነው ለማለት ያስቸግራል።(አለማየሁ፣1950፣126)

## 7. ጽድቅ መንገድ

ጽድቅ መንገድ ማለት ሙያዊ ቴክኒክ የጎደለው ማለት ነው። ይኸውም ሠምና ወርቅ ኅብር የሌለው እውነቱን(ታሪኩን) ብቻ በቅኔ መልኩ የሚያቀርብ ነው።(አለማየሁ፣1950፣126)

## 8. ጉራማይሌ(ፍርንዱስ)

ይህ የቅኔ መንገድ ግዕዝ እና አማርኛ እኩል በእኩል በቅኔው ውስጥ እየተቀላቀሉ የሚቀርቡበት አካኼድ ነው።(አለማየሁ፣1950፣126)

## 9. ሠም ገፌ

ይህ የቅኔ መንገድ የሽማግሌ ጭውውት ወይም የብልኅ ሰው ምክር ይመስላል። የተጣላን የሚያስታርቅና ጥፋተኛን የሚገስጽ ሰው ንግግሩን በምሳሌ እንደሚጀምር ኹሉ በዚህም ቅኔ ውስጥ ባለቅኔው ቅኔውን በምሳሌ ይጀምራል። በዚህ አካሄድ ውስጥ ማስተዋል የሚገባው በምሳሌ መጀመርንና ከምሳሌውም በርከት አድርጎ መለገሱን ነው። ሠም ገፌ የተባለበትም ምክንያት የሰሙን ታሪክ በቅድሚያ በመተረኩ ነው።(አለማየሁ፣1950፣126)

## 10. ወርቅ ገፊ

በዚህ ዐይነት ቅኔ ውስጥ ባለቅኔው በቅኔው መጀመሪያ ላይ አንድ ዐሳብ ይሠነዝራል። ከዚህ በኃላ እስከ ቅኔው መጨረሻ ድረስ የዐሳቡን ልክነት ለማስረዳት ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እያስገባ ቅኔውን ይጨርሳል።(አለማየሁ፣1950፣126)

## 11. ፍላጻ (የቀስት ጦር)

ይህ መንገድ ከቃላቱ የአቀማመጥ ለውጥ በስተቀር በንግግር ጣዕም ረገድ ፍላጻና ዝምድ የሚሰጡት አገልግሎት ተመሳሳይ ነው። ብያኔውም የሠም ባለቤት ከወርቅ ዘርፍ ተናቦ እየቀደመ የወርቅ ባለቤት ሲከተል ፍላጻ ይባላል። አሰካኩም "ክርስቶስ ኅብስት ተሠርዐ በመሶበ አይሁድ መስቀል" "መስቀል" የሚለው ቃል በዝምድና አካሄድ ይዞት የነበረውን ስፍራ ለቆ፣ ተስፈንጥሮ፣በመጨረሻ ላይ ሄዶ እንደቆመ ማስተዋል ይገባል።ፍላጻ ያሰኘውም ይኸው ግብሩ ነው።የፍላጻ ጥቅም አንድ ቅኔ በዝምድ መንገድ ቤት ለመምታት፣ዜማ ለማስተካከል ሲያስቸግር ለመለወጫ ኾኖ ማገልገል ነው።(አለማየሁ፣1950፣126)

## 12. ሠረዝ መንገድ

በጀመሩበት ከሚጨርሱት የቅኔ መንገዶች አንዱ ሠረዝ የተባለው ነው። በዚህ አይነት የቅኔ መንገድ ውስጥ ባለቅኔው በቅኔው መጀመሪያ ላይ ስለኹለት ወይም ስለ ሦስት ነገሮች የሚናገር መሆኑን ይገልጣል ። ከዚያ በኃላ ስለእያንዳንዱ በየተራ ያትታል።(ኪዳነ ወልድ ፣ 1948፣167)

## 13. ውስጠ ዘ መንገድ

ውስጠ ዘ ማለት በውስጡ ዘ ያለበት ቃል ማለት ነው። ዘ የተባለው የግዕዝ አገባብም ሲፈታ "የ" ማለት ይኾናል። ውስጠ ዘ ከአንድ ግስ ከሚወጡ የቃል ዘሮች (ዘምድ ዘር፣ባዕድ ዘር ወዘተ) ውስጥ አንዱ ነው።(ኪዳነ ወልድ ፣1948፣167)

## 14. አንጻር መንገድ

ይህ የቅኔ መንገድ ከሰም ገፊ ጋራ ተመሳሳይ ነው። ኾኖም በሠም ገፊ ውስጥ ለወርቁ ተመሳሳይ ወይም አፍራሽ ኾኖ የሚገባው ሠም ተረትና ምሳሌን የመሰለ ወይም ሕይወት የሌለው ነገር ሲኾን፣ በአንጻር መንገድ ግን ብዙውን ጊዜ ሠም ኾኖ የሚገባው እውነተኛ ታሪክ

ነው። አንጻር ቅኔዎች ለመቀኘት በቅዱሳት መጻሕፍትና በታሪክ እንዲሁም በህገ ፍጥረትና በሥነ-ፍጥረት ሰፊ እውቀት ያስፈልጋል። (ኪዳነ ወልድ ፣1948፣170)

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ስለ ግዕዝ ቅኔ ምንነት የዘርፉ ሊቃውንት የሰጡትን ብያኔ በማምጣት ለመዳሰስ ተሞክሯል። በመቀጠልም ስለ ግዕዝ ቅኔ አጀማመር፣ ጀማሪው ማነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሊቃውንት ያቀረቧቸው የተለያዩ የታሪክ ማስረጃዎች ተዳሰዋል። የቅኔ አይነቶች እና የቅኔ መንገዶችን በመዘርዘር ስለምንነታቸው ከሙያው ሊቃውን በቀረበው መሰረት ተብራርቶ ቀርቧል።

## 2.3. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

ይህ ክፍል ለዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በመሆን የሚያገለግሉ የፍካሬና እና የግለተረክ ንድፈ ሀሳቦች ላይ ማብራሪያ የተሰጠበት ነው። እነዚህ ሁለት ንድፈ ሀሳቦች በማዕቀፍነት የተመረጡበት ምክንያት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለጥናቱ የተመረጡት ሴት የቅኔ መምህራኑን የህይወት ታሪካቸውን አስተማሪ በሆነ መልኩ ማቅረብና፤ቅኔዎቻቸውን ደግሞ ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳሉ የሚለውን መመርመር በመሆኑ ነው። እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፎች ደግሞ የነገረ ፍካሬ እና የግለተረክ ንድፈ ሀሳቦች ናቸው።

### 2.3.1 ግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ (Personal narrative theory)

የሰው ልጆች በዚች ምድር ላይ በኖሩበት ከልጅነት እስከ ዕውቀት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ሁሉ ታሪክን እየፈጠሩ ይሄዳሉ። ታሪኩንም በማዋቀር ስለራሳቸው፣ ስለማህበረሰባቸው እና ስለሀገራቸው ይተርካሉ። ግለተረክ ንድፈ ሀሳብም ይህንን የሰው ልጆች ኹነት ስርዓታዊ በሆነ መልኩ መንገሪያ ነው። ቴዎድሮስ ትረካን (Narration) "ታሪክ መንገርን ወይም ታሪክ ማቅረብን ይመለከታል" በማለት ይገልጹታል።(2001፣261)

"ተረክ ታሪክን የመተረክ መንገድ ሲሆን ይኸም በታሪክ ቅደም ተከተል ፣በልብ ወለድ ወይም በዕውነተኛ ክስተቶች ላይ የመናገር ተግባር ነው። "(Barbara Culatta እና Carol Westby፣ 2016፣1)በማለት ይገልጻሉ። ተረክ በሰው ልጆች የተፈጸሙና ሊፈጸሙ የሚችሉ ድርጊቶችና ሁነቶች በተፈጸሙበት የጊዜ ቅደም ተከተል የሚገለጹበት ዘዴ ነው። እንዲሁም Catherine Kohler Riessman የግለተረክ ንድፈ ሀሳብ የህይወት ታሪክን እና ማህበረሰብን ማብራሪያና ማሳያ

ነው በማለት ያስረዳል።(2000፣5) በግለሰብ ደረጃም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ የተፈጸሙ ተግባራት በርካታ ቁም ነገሮች ስለሚኖራቸው ለሌላው አካል አስተማሪ የሚሆኑትና የማህበረሰቡንም ሆነ የግለሰቡን ማንነት ለመረዳት ምልዑ በሆነ መልኩ መረጃ እንዲሰጥ ተሰንዶ መቀመጥ አለበት።

ከላይ ከተነሱት ጥቅሶች ሀሳብ እንደምንረዳው የሰው ልጆች በህይወት ያካበቱትን ልምዳቸውን እና በራሳቸው ላይ የተፈጠሩ የታሪክ ኹነቶችን በታሪክ ቅደም ተከተል ይተርካሉ። ታሪካቸውን በሚተርኩበት ወቅትም ገጠመኞቻቸውን፣ገጠመኞቻቸው የፈጠሩባቸውን ስሜት፣ ያካበቱት ልምድ እና ዕውቀት፣በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ቦታ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸው መስተጋብር ጎልቶ የሚታይ ይሆናል። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት የቅኔ መምህራኑ የሚኖሩት ከማህበረሰቡ እና ከተማሪዎቻቸው ጋር እንደመሆኑ የራሳቸውን ታሪክ ከመንገርም ባለፈ በተዘዋዋሪ ስለማህበረሰቡ፣ስለቅኔ ተማሪዎቻቸውና ስለቅኔ ትምህርቱ፣ ስለሴት የቅኔ ተማሪዎች ህይወት እንዲሁም ስለሚያልፉበት ውጣውረድ፣ ማህበረሰቡ ለሴት የቅኔ መምህራንና ተማሪዎች ከወንዶች በተለየ ያለው አተያይ ምን እንደሚመስል መመልከት ይቻላል። ስለዚህ በግለ ተረክ ጥናት ግለሰብን በምናጠናበት ጊዜ በተዘዋዋሪ የዚያን ማህበረሰብ ማንነት፣ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ የአኗኗር ባህል፣ ያለውን መስተጋብር እንዲሁም አጠቃላይ የማህበረሰቡን እንቅስቃሴ መረዳት ያስችላል።

Labov, William እና Joshua Waletzky" የግል ልምምድን በጊዜ ቅደም ተከተል የሚዛመዱ የትረካ ክፍሎችን የመገንባት ዘዴ ነው። አክለውም ስለተረክ የግለሰቦችን የታሪክ ኹነት በአንድ የጊዜ ሰሌዳ ለመተረክ በቀላሉ የምንገልጽበት ዘዴ ነው።"(1967, 13) በማለት ያስረዳሉ።

የህይወት ታሪክን በምንተርክበት ወቅት ባለታሪኩ በተለያየ ጊዜና ቦታ ያከናወናቸውን የተበታተኑ የታሪክ ሁነቶች በተከናወኑበት የጊዜ ቅደም ተከተል ሂደቱ ተጠብቆ ይገለጻል። ይህ የሰው ልጅ ከልደት ጀምሮ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ሲያልፍ ያከናወናቸው ተግባራትና የተከሰቱ ገጠመኞች ዕረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ ስለሚሆኑ በተደራጀ መልኩ ተተርከው ካልተቀመጡ በስተቀር አስተማሪ ፣ጠቃሚና መረጃ ሰጪ የሆኑ በርካታ የግለሰብ ታሪኮች ባክነው ይቀራሉ። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት ሴት የቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክ ማለትም ብዙም ባልተለመደውና ለሴቶች ክልከላ ያለበት በሚመስለው የቅኔ ሙያ ላይ ያሉት እነዚህ መምህራን ከተማሪነት እስከ መምህርነት ሲደርሱ ያሳለፉት በርካታ የህይወት ልምድ ፣ገጠመኞቻቸው እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የሚያከናውኑት ተግባር አስተማሪና መረጃ ሰጪ

በሆነ መልኩ ተተርኮ ቢቀርብ በተለይም በቅኔው ሙያ ሴቶች መኖራቸውን፤ ሴቶቹ የቅኔውን ሙያ መማርም ሆነ ማስተማር እንደሚችሉና ክልከላም እንደሌለባቸው እና የመማሩም ሆነ የማስተማሩ ሁኔታ ምን እንደሚመስል መረጃ ሰጪ ይሆናል።

ግለ ተረክ ለምን ይጻፋል ለሚለው ጥያቄ Chris Ingraham ምላሽ ሲሰጡ "ግለተረክ ከጽሑፋዊ ተግባቦቶች መካከል አንዱ በመሆኑ እውነታው ከተገለጸ ለህዝብ ታሪክን ይነግራል።"(2017፣56)

የህይወት ታሪክ በወጉ ካልተተረከ በስተቀር ሊታወቅ ወይም ሊታይ አይችልም። ስለዚህ በሌሎች እንዲታውቅ መተረክ ያስፈልገዋል። በተጨማሪም የታሪኩ ባለቤቶች ታሪካቸውንና የህይወት ገጠመኞቻቸውን እንዴት ባለ ሁኔታ ይተርካሉ፤ የቅኔ ዕውቀታቸውን እንዴት ተማሩት፤ እንዴትስ የቅኔ እውቀታቸውን ለተማሪዎቻቸው ያስተምራሉ፤ አሁን ያለው ተማሪ የቅኔ ትምህርት አቀባበሉና ፍላጉቱ ምን ይመስላል፤ የሚሉትን ጉዳዮች በግለ ተረክ ትረካ ወቅት ማሳየት ይቻላል። በመሆኑም የግለ ተረክን ንድፈ ሀሳብ በመከተል ስለ ሴት የቅኔ መምህራን የቅኔ ዕውቀትና ሙያ የበለጠ ለማወቅና ለመረዳት የህይወት ታሪካቸውን ማጥናት ያስፈልጋል።

ይህም ማለት የዚህ ጥናት ትኩረት ስለሆኑት ሴት የቅኔ መምህራን ማንነት፣ የቅኔ እውቀት ትምህርታቸው፣ ቅኔ የመቀኘት እና ተማሪዎቻቸውን የማስተማር ብቃት ለመረዳት የህይወት ታሪክን ማጥናት የበለጠ ስለጉዳዩ ያለንን የዕውቀት አድማስ እንዲሰፋ እንዲሁም ብዙ ያልተለመደውን ሴት የቅኔ መምህርነት ሙያ በሌሎች እንዲታወቅና ተግባራዊ እንዲሆን ያደርገዋል። ምክንያቱም የቅኔ ዘራፊው ከሚቀኛቸው ቅኔዎች ውስጥ ልናገኛቸውና ልንረዳቸው የማንችላቸውን የባለቅኔዎቹን የጥበብና የእውቀት ከየት መጣነት፣ ወደዚህ የዕውቀት ዘርፍ የገቡበትን ሁኔታ፣ ይህን ጥበብ የሚያስተላልፉበትን መንገድ … ወዘተ በህይወት ታሪካቸው ውስጥ እናገኛቸዋለን።

Matthew A. Hawkins and Fathima Z. Salee እንደሚሉት ግለተረክ ሲዘጋጅ መሟላት ያለባቸው የተረክ ደረጃ ብለው በመጥቀስ ሦስት ጉዳዮችን ያነሳሉ። እነዚህም አንደኛ ተረኩ የተሳሰረ መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ሲሆን ሁለተኛው ተረኩ በሌሎች አካላት የሚታይ በመሆኑ በተግባር የተኖረና እውነተኛ መሆን አለበት ሦስተኛው ደግሞ በጥናቱ ውስጥ የህይወት ታሪኩና ትረካው የተዋሀደ መሆኑ መታየት አለበት በማለት ይገልጻሉ።

> Storytelling produces stories that draw from an individuals overarching narratives this argument has three key assumptions. First, the stories told must have a connection with, at least, apersonal narrative (polkinghome, 2007). Second, the story must be connected to a lived experience or stem from a story the individual heard, but it cannot simply be to fantasy. Third the connection between the story and the narrative is intelligible to the researcher. (2018፣209)

ግለተረክ የግለሰቦች ታሪክና ይህም የባለታሪኮችን አጠቃላይ ህይወት የሚኖሩበትን ማህበረሰብ፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ የሚይስቃኝ በመሆኑ የታሪክ ኹነቱ በአግባቡ የተዋቀረና እውነተኛ መረጃን በመያዝ ገላጭ በሆነ መልኩ መቅረብ አለበት:: የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት የቅኔ መምህራኑ ከቅኔ እውቀታቸው በተጨማሪ ያለፉበት የህይወት ጉዞና እያከናወኑ ያሉት ተግባር በውል ያልተገለጠ በመሆኑ ታሪካቸውና ተግባራቸው ይታወቅ ዘንድ ከልደታቸው ጀምሮ ያለፉበትን የህይወት ጉዞ በአሁኑ ወቅትም እያከናወኑ ያሉት ተግባር በተለይም በቅኔው ሙያ እያበረከቱ ያለው አስተዋጾ ከፍተኛ በመሆኑ እና ይህም መልካም ዓርዐያ እና አስተማሪ በመሆኑ በግለተረክ ንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍነት የሁለቱን ሴት የቅኔ መምህራን የህይወት ታሪክ አስተማሪና መረጃ ሰጪ በሆነ መልኩ ይቀርባል:: እንዲሁም እነዚህ የቅኔ መምህራን የህይወት ታሪካቸውን እንዴት አቀናጅተው ይተርካሉ የሚለውን የሚመለከት በመኾኑ ይኽንን ንድፈ ሀሳብ ተጠቅሜአለኹ:: ተራኪዎቹ የህይወት ታሪካቸውን ሲናገሩ ልምዳቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ እምነታቸውን፣ ዓላማቸውን እና የአኗኗር ዘይቤያቸውን አብረው ይገልጻሉ:: ስለዚህ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ስለሚጠናው ሰው አጠቃላይ ሁኔታ በሚገባ ለማወቅ ይረዳል ማለት ነው::

### 2.3.2 ነገረ ፍካሬ

ይህ ጥናት የቅኔ መምህራኑን የግዕዝ ቅኔያት ይዘት የሚመረምር በመሆኑ ነገረ ፍካሬን በንድፈ ሀሳብነት ይጠቀማል:: የግዕዝ ቅኔያት በአንድ ነጠላ ትርጉም የማይቆሙ ይልቁንም የተለያዩ ምስጢራትን የያዙ በመሆናቸው እና የእነዚህን ቅኔዎች ይዘት ለመመርመር ደግሞ የነገረ ፍካሬ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ነው::

"ነገረ ፍካሬ የመረዳት እና የመተርጎም ጽንሰ-ሀሳብና ፍልስፍና ነው:: ትርጓሜ ትርጉሙን ለማብራራት ወይም ለመገንባት የምንሰራበት የግንዛቤ ዘዴ ነው:: ዋና ግቡም እንደ ጽሑፍ ፣

ቅርሶች ፣የንግግር ቃላት ፣ልምዶች እና ዓላማዎች ትርጉም ያላቸው ቁሶች ትክክለኛ ግንዛቤ መፍጠር ነው።" ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው በቃል የሚነገሩ፣ በጽሑፍ የሰፈሩ እንዲሁም ሥዕልና ቅርጻ ቅርጾችን ብዙ ጊዜ መልዕክታቸውን ላንረዳ እንችላለን። ይህም ማለት ዕሳቤያቸውን ለመገንዘብ ትርጓሜ ያሻቸዋል ማለት ነው። የነገረ ፍካሬ ንድፈ ሀሳብም ጸናን የሆኑ ጉዳዮችን ለማፍታታትና ለመረዳት ተመራጭ ነው። በተለይም የግዕዝ ቅኔ ሃይማኖትን፣ ፍልስፍናን፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ  በአጠቃላይም የሰው ልጅ ዕሳቤዎች ጥበብን ተላብሰው በምልዐት የሚቀርቡበት ሙያ ነው። ነገር ግን እነዚህ ጉዳዮች በግልጽ የተቀመጡና በቀላሉ ልንረዳቸው የምንችላቸው ባለመሆናቸውና ባለቅኔውም አመስጥሮ የሚያቀርበው በመሆኑ በጥልቀት መመርመርን የሚሹ ናቸው።የዚህ ጥናት የትኩረት አካል የሆኑት የቅኔ መምህራኑን ቅኔያት ይዘት የሚተነትን በመሆኑ እና ቅኔያቱም የያዙትን እረቂቅ ሀሳብ አፍታቶ ለማሳየት ይህ የነገረ ፍካሬ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ነው ።

Nicolas ስለ ትርጓሜ ሲገልጹ "ትርጓሜ ሁልጊዜ የበለጠ ወይም የተለየ ሊኾን እንደሚችል እና በሌላ መንገድ እንደሚገለጽ ጊዜያዊ ውስንነትም እንደሌለው ይገልጻሉ።"(2006፣204) ዛሬ በተቀኘው ቅኔ እረክቶ ህሊናውን አያሳርፍም፤ የተቀኘውንም ቅኔ ደግሞ አይቀኘውም  በቅኔ ቤት ባህል ባለቅኔው ዛሬ የተቀኘውን ቅኔ ነገ ደግሞ አይለውም አዲስ ቅኔ ይቀኛል እንጂ ይኽንንም የቅኔ ተማሪውም ኾነ የቅኔ መምህሩ የሌላን ሰው ቅኔ ደግሞ ማቅረብ ነውር በመሆኑ በየዕለቱ አዳዲስ ቅኔ እንዲቀኝ ያስገድደዋል። በአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪው የሚያልፍባቸው ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤት እና መጽሐፍት ቤት የሚባሉ አሉ። እነዚህ ትምህርቶች ደረጃ በደረጃ የሚሰጡ ሲኾኑ ወደ ትርጓሜ ቤት መጻሕፍትን ለመማር የሚሄድ ተማሪ ቅኔን ያጠናቀቀና በቅኔ ዕውቀት የበሰለ መሆን አለበት። ምክንያቱም የመጸሐፍት ቤት ትምህርት የተለያዩ የመጻሕፍት ምስጢር የሚመረመርበት በመኾኑ የቅኔ ትምህርት ደግሞ የአዕምሮን አስተውሎት የሚያሰፋና የሚያመራምር ስለሚያደርግ ነው። ከዚህ የምንረዳው ቅኔ በሚስጥር የተሞላና ረቂቅ ጥበብ መኾኑን ነው። ባለቅኔውም በዙሪያው ያሉ ነገሮችን አራቆ በአዲስ ዕይታና መልክ ያቀርባቸዋል ።ይኽንን ለመረዳት ደግሞ ነገረ ፍካሬ ወይም ትርጓሜ ዋነኛ መሳሪያ ነው።

Nicolas Davey እንደሚሉት "ትርጓሜ ጽሑፎች እራሳቸውን በራሱ ትርጉም በሚተካው ቀኖናዊነት ማየት አለባቸው"(2006፣187) ይኽ ማለት ጽሑፎችንም ኾነ ሌሎች ነገሮችን ለመተርጎምና ለመረዳት በምንጥርብት ጊዜ በትርጓሜ ሰበብ ከመሰረታዊው ጽንሰ ሐሳብ

መውጣት እንደሌለብን ለመግለጽ ነው:: በቅኔ ቤትም ሊቃውንት ቅኔ ሲቀኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን በየዕለቱ የምታስባቸውን ቅዱሳን፣ ነገረ ሐይናኖትን፣ ነገረ ቅዱሳንን እና ታሪካቸውን በጥቅሉም በሐይማኖታዊ ጉዳዮች መሰረትነት ለምስጋና፣ ለውዳሴ፣ ለትምህርት ወርቁን በሰሙ አልብሰው ያቀርቡታል:: ምንጊዜም የቅዱሳንን ታሪክ ለክፉ በመስጠትና የሐይማኖቱን ዶግማ በመጣስ ቅኔ አይቀኙም:: ቅኔያትን በምንተረጉምበት ወቅትም ባለቅኔው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ትክክለኛ ዕሳቤና መልዕክት መረዳትና ለቅኔው መነሻ የሆነውን የታሪክ እውቀት ማወቅን ይጠይቃል:: ይህ ካልሆነ ግን የባለቅኔው ሚስጥር ባክኖ ይቀራል አልያም ተፋልሶ ያመጣል ማለት ነው:: Nicolas " The human word is, indeed, essentially incomplete (TM, 425). It is in such incompleteness that the resonance anddepth of the word becomes possible."(2006፣187) የሰው ቃል በእርግጥም በእውነቱ ያልተሟላ ነው:: የቃላቱ ትክክለኛነትና ጥልቀት ሊኖር የሚቻለው በእንደዚህ አይነት ትርጓሜ ነው:: በመተርጎም ሂደት ነገሮችን ለመግለጽ ብንፈልግም ሁሌም ግን የተገለጡ አይሆኑም:: ባለቅኔው ዕሳቤዎቹን የሚገልጠው በቋንቋ አማካኝነት ነው:: ይኹን እንጂ ቋንቋ ኹሉንም ዕሳቤዎች የመግለጥ አቅም አይኖረውም:: ይህ የተሟላ የሚሆነውና ፍጹም ወደሆነ ዕውቀት የሚሄደው በትርጓሜ ነው:: የዚህ ጥናት ዓብይ ትኩረት የሆኑት የቅኔ መምህራኑ ቅኔያቶች ትርጓሜን የሚሹ በመሆናቸው በዚህ የፍካሬ መንገድ ተተንትነው የሚቀርቡ ይሆናል::

### 2.3.3 የሁለቱ ንድፈ ሐሳቦች ትስስር

የግለተረክና የፍካሬ ንድፈ ሐሳብ በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን ንድፈ ሐሳቦቹ በተናጠል ማለትም ግለተረክ ንድፈ ሀሳብ የባለቅኔዎቹን ታሪክ ለማጥናት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የፍካሬ ንድፈ ሀሳብ ደግሞ ቅኔዎቻቸውን ለመፈከር አገልግሏል:: በግለተረክ የሚጠናው የመምህራኑ ታሪክ በሚጠናበት ወቅት ስለ ቅኔ ትምህርት አሰጣጥ፣ በቅኔው ትምህርት ቤት ሴቶች ምን ሚና አላቸው፣ የማህበረሰቡን አስተሳሰብና አመለካከት፣ የአኗኗር ሁኔታ መረዳት ይቻላል:: በፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ደግሞ ቅኔዎቻቸውን ሰብስቦ በመተንተን የሚያነሱትን ጉዳይ ማሳየት ነው:: በዚህም ሁለቱ ንድፈ ሐሳቦች በመደጋገፍ በአንዱ የማይገኘውን መረጃ በሌላኛው ይገኛል:: ይህም ማለት በተረኩ የሚገለጸው የመምህራኑ የህይወት ታሪክ በቅኔዎቻቸው ውስጥ የማይገኙትን የመምህራኑን የልደት፣ የአስተዳደግ፣ የትምህርት ሁኔታ፣ የትምህርቱን ሂደት፣ የተማሩባቸው ቦታዎችና ገጠመኞች፣ ለትምህርታቸው ማህበረሰቡ ያለው አስተዋጾ እንዲሁም አሁን ያሉበትን ሁኔታ ግልጽ ያደርጋል:: በግለተረኩ የማይገኙት የባለቅኔያቱ ከልደት ጀምሮ

ያለውን የአስተዳደግ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣የቅኔ ትምርቱን መቼ፣ የትና ከማን እንዴት ተማሩት፣ማህበረሰቡ ለነሱ ያለው ዕይታ ምን ይመስላል፣ ወደ ቅኔ ማስተማሩ ሙያ እንዴት ገቡ የሚሉ ጉዳዮችን ለማጥናት የሚያገለግል ሲሆን በፍካሬ ንድፈ ሀሳብ ደግሞ የመምህራኑ ቅኔያቶች የሚያነሷቸው ሀይማኖታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ምን ምን ዓይነት ዕሳቤዎችን ይገልጻሉ፣በቅኔያቱ ጎልተው የሚሰሙ ድምጾች ምን ምን ናቸው ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል።ስለዚህ እነዚህ ሁለት ንድፈ ሀሳቦች አንዱ የአንዱን ክፍተት በመሙላት ጥናቱን ሙሉ ያደርጉታል።

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የቅኔ መምህራኑ የህይወት ታሪክ

በዚህ ምዕራፍ የእማሆይ አመተ ማርያም አሰፋና የእማሆይ ኅሪት ደባስ ከልደት ጀምሮ አስተዳደጋቸውን፣ የትምህርት ሁኔታቸውን፣ የተማሩባቸውን ቦታዎች፣ አሁን  በምን ሁኔታ እያስተማሩ ይገኛሉ የሚሉት ጉዳዮች ቀርበዋል። በዚህ የመምህራን ታሪክ ውስጥ ከታሪኩ ባለቤቶች በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ማለትም የቅኔ መምህራኑ መቼ ተወለዱ?፤ አስተዳደጋቸው እንዴት ነው?፤ ይህንን የቅኔ ትምህርት ለመማር ምን አነሳሳቸው? ትምህርቱንስ የት የት ተማሩት?፤  በሚማሩበት ወቅት ያለፉባቸው ውጣ ውረዶች ምን ይመስላሉ?፤ከተማሩስ በኂላ ወደማስተማሩ ሙያ እንዴት ገቡ?፤ ሴትነትና የቅኔ ትምህርት እንዴት ይታያል?፤ በሚያስተምሩበት ወቅት የማህበረሰቡ አቀባበል ምን አይነት ነው፤ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዴት ነው፤ የሚሉት ጉዳዮች ተብራርተው ቀርበዋል። ይህ የመምህራኑ ታሪክ አንድም በቅኔዎቻቸው ውስጥ የማይገኙትን ከላይ የተዘረዘሩ ጉዳዮችን ለመረዳት ያስችላል። አንድም የግለሰብም ሆነ የማህበረሰብ ታሪክ ሊታወቅ የሚችለው ከልደታቸው ጀምሮ ያለፉባቸው የህይወት ጉዞዎች፣ እያከናወኗቸው ያሉ ድርጊቶች ቅደምተከተላዊ በሆነ መልኩ በጽሑፍ ተሰንደው ሲገኙ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት የእማሆይ አመተ ማርያም አሰፋን እና የእማሆይ ኅሪት ደባስን የህይወት ታሪክ በተናጠል አቅርቧል።

### 3.1 የእማሆይ አመተ ማርያም የህይወት ታሪክ

እማሆይ አመተ ማርያም አሰፋ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን እናርጅ እናውጋ ወረዳ ኩሬ ኪዳነ ምህረት በምትባል አካባቢ ከአባታቸው ከአቶ አሰፋ እጅጉ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሙኒት አድገህ በ1968 ዓ.ም ጥቅምት 16 ቀን ተወለዱ። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢያቸው በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የቀለም ትምህርት ጀመሩ። ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ከቤተሰቦቻቸው መኖሪያ ቤት በመራቁ ምክንያት ትምርታቸውን ማቋረጥ ግድ ሆነባቸው። በዚህ ሁኔታ እያሉ በ1977 ዓ.ም በሀገሪቱ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት በእናርጅ እናውጋ ወረዳ የከብት መኖ ወይም ግጦሽ እና ውሃ ጠፋ። የእማሆይ አመተ ማርያም አባት የሆኑት አቶ አሰፋም በርካታ ከብቶች ስለነበሯቸው እነሱን ለማትረፍ አቸፈር ወደተባለ በድርቁ ወዳልተጎዳ ቦታ የተወሰነውን የቤተሰብ አባላት እማሆይ አመተ ማርያምን ጨምሮ ከብቶቻቸውን ይዘው ይሄዳሉ። በዚህ ወቅት አቶ አሰፋ አቸፈር ሳይደርሱ መንገድ ላይ

ባልታወቀ ምክንያት በድንገት ይሞታሉ፡፡ እማሆይ አመተማርያም አባታቸውን ቢያጡም ወደአቸፈር በመሄድ በ1978 ዓ.ም ፓዊ ወረዳ ቀጠና ሁለት መንደር 26 በሚባል ቦታ የተቋረጠውን ትምህርታቸውን እንደአዲስ በመጀመር ከ1978 እስከ 1983 ዓ.ምድረስ እስከ ስድስተኛ ክፍል ተማሩ፡፡ ትምህርት ቤቱ ከስድስተኛ ክፍል በላይ ስለማያስተምር ካሉበት ሥፍራ የአምስት ሰዓት የእግር ጉዞ ተጉዘው ሰባት ወረዳ በሚባል ቦታ እስከ 1985 ዓ.ም ድረስ ተምረው ስምንተኛ ክፍል አጠናቀቁ፡፡ እማሆይ ወደ ዘጠነኛ ክፍል ሲያልፉ ትምህርት ቤቱ እስከ ስምንት ብቻ የሚያስተምር በመኾኑ ቻግኒ ወደሚባል ቦታ በመሄድ ትምህርታቸውን ቀጠሉ፡፡

ቻግኒ ሳሉ አንዲት እናት የቤተክርስትያን ትምህርት ሲያስተምሩ በማየታቸው ተማርከው ልቡናቸው ወደመንፈሳዊው ዓለም በማዘንበሉ ለሁለት ዓመት ያህል መንፈሳዊውንም ዘመናዊውንም ትምህርት ጎን ለጎን እየተማሩ ቆዩ፡፡ ወደ አስራአንደኛ ክፍል እንዳለፉ ግን ዘመናዊውን ትምህርት ሙሉ ለሙሉ አቁመው ወደ መንፈሳዊው ትምህርት ገቡ፡፡ እማሆይ አመተ ማርያም ወደመንፈሳዊው ዓለም እንዲያዘነብሉ ያደረጋቸውን ዋና ምክንያት እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡፡

"የሁለት አመት ህጻን እያለሁ ቤተሰቦቼ በአልባሳትና ጌጣጌጥ አስውበው ቤተክርስትያን ይዘውኝ ይሄዳሉ፡፡ ከዛም ከህጻናት ጋር ስጫወት ያደረኩት ጌጣጌጥ በድንገት ይጠፋል፡፡ ሰውነቴ በሙሉ በህማም ተመታ፡፡ በዚህ ምክንያት አባቴ እኔን ለማዳን በየገዳማቱ ይዞኝ ቢሄድም ድነትን ላገኝ አልቻልኩም፡፡ ነገር ግን እዛው እናርጅና እናውጋ ወረዳ አካባቢ ጀር ገብርኤል የሚባል ገዳም ይዞኝ ይሄድና እንዲህ ሲል ይሳላል፤"የልጄ ጤና ከተመለሰና ከህመሟ ከዳነች ግብር አድቃቂ ኾና ቤተክርስትያንን ታገለግላለች እንጂ ወደ ዓለማዊ ህይወትና ኑሮ አትገባም" በዚህ ምክንያት እኔም ከህመሜ ተፈወስኩ፡፡ አባቴም ለእናቴ ይቺን ልጅ እስከመጨረሻው በመንፈሳዊውም ኾነ በዘመናዊው ትምህርት እንድትገፋ እንጂ ወደዓለማዊ ህይወት እንዳትገባ ብሎ አደራ አላት፡፡ "(ቃ/መ ጥር 23/2012)

በ1987 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ እማሆይ የመደበኛውን ትምህርት ሙሉ ለሙሉ አቁመው መንፈሳዊውን ህይወት ለመጀመር ሲወስኑ መጀመርያ የተጓዙት ወደ እናርጅ እናውጋ ወረዳ ነበር፡፡ በዚህ ወረዳ ደብረ ወርቅ ወለተ ሀና በሚባል የሴቶች ገዳም በመሄድ ገዳማዊ ህይወትን ሀ ብለው ጀመሩ፡፡ ገዳማዊ ህይወቱን ሲጀምሩ በዕድሜ ያልበሰሉ ስለነበሩ በወቅቱ የነበሩት የገዳሙ መነኮሳያት እማሆይ አመተ ማርያምን “ልጅ ናት በዚህ እድሜዋ የገዳማዊ ህይወትን መጀመር የለባትም” ብለው ተቃወሙ፤ ምክንያቱም ወደዚህ ህይወት ለመግባት ከራስ ውሳኔ

ባሻገር የገዳማቱን አስተዳዳሪና የመንፈሳዊ አባቶችን ይሁንታ ማግኘት ግዴታ ነው። እማኾይ አመተ ማርያም ግን ተስፋ ባለመቁረጥ ህልማቸውን እውን ያደርጉ ዘንድ በዓላማቸው ጸንተው ሱባኤ በመግባት በጸሎት ፈጣሪያቸውን ሲጠይቁ ቆዩ። የእማሆይን መንፈሳዊ ጥንካሬ ያዩት ገዳማውያኑም ጥያቄያቸውን ተቀብለው ከገዳሙ እንዲቀላቀሉ ፈቃድ ሰጧቸው። በዚሁ ወለተ ሀና ገዳም ውስጥ የሚኖሩ እማሆይ እናቴ (ወለተ ማርያም) የተባሉ መነኩሲት ለምነና የሚሄዱትን መነኮሳት የሀይማኖት ትምህርት እና ግዕዝ ቋንቋ ያስተምሩ ነበር። እማሆይ አመተ ማርያምም ይህን እድል በመጠቀም በስመ አብ ብለው ጀምረው፣ ውዳሴ ማርያምን ፣ አንቀጸ ብርሀንን፣ ትምህርተ ህወሀትን  እና ህማማተ መስቀሉን ተማሩ። እማሆይ አመተ ማርያም በአንድ ቀን በስመ አብ ብለው ጀምረው ፀሎተ ሃይማኖት ገብተው አደሩ። እማሆይ እናቴም የእማሆይ አመተ ማርያምን የትምህርት አቀባበልና የአዕምሮ ፍጥነት ሲመለከቱ"ፀሎተ ሃይማኖት ይጎትታል አመት ይባላል አንቺ ግን በአንድ ቀን ያዝሽ ስለዚህ የበለጠ መማር አለብሽ" በማለት ወደሌላ ሰፊ ጉባኤ ቤት እንዲሄዱ መከሯቸው። እማሆይ አመተ ማርያም እንደሚሉት "እማሆይእናቴ አንቺ ወደፊት ቅኔ ትማሪያለሽ ጉባኤ ዘርግተሽም ታስተምሪያለሽ መጽሀፈ ትርጓሜ ትማሪያለሽ በማለት በትምህርት እንደምቀጥል ትንቢት ተናገሩ" (ቃ/መ ጥር 24/2012)

እማሆይም የመምህራቸውን ምክር ተቀብለው በትምህርት ለመግፋት ጉዟቸውን ቀጠሉ። በወለተ ሀና የሴቶች ገዳም በነበራቸው የሁለት አመት ቆይታ ገዳማውያኑ የእማሆይን ትህትና፣ ታዛዥነትና እውቀት ተመልክተው የገዳሙ እመምኔት (አስተዳዳሪ) እንዲኾኑ ቢፈልጉም እማሆይ አመተ ማርያም ግን በነበራቸው የትምህርት ፍቅር “በዚህ የልጅነት እድሜዬ መማር እንጂ እንዴት የገዳም አስተዳዳሪ መኾን እችላለሁ?” በማለት በተደጋጋሚ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ሳይኾኑ ቀሩ። በዚህ ወቅትም የዲማዋ እማሆይ ኀሪት ወደ ወለተ ሐና የሴቶች ገዳም በመምጣታቸው ከእማሆይ አመተ ማርያም ጋር ተዋወቁ።

እማሆይ አመተ ማርያምና እማሆይ ኀሪት ያላቸው የትምህርት ዓላማ ተመሳሳይ በመሆኑ የቅኔ ትምህርት ለመጀመር ወደ ዲማ ሄዱ። በወቅቱ በነበሩት መምህር ዘሚካኤል ጉባኤ ቤት ትምህርት ለመጀመር ሲዘጋጁ  መምህሩ የተሻለ እንዲማሩ ደቦዛ ሚካኤል ወደሚባል ቦታ ለትምህርት የመጡ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ጽፈው ላኳቸው። ደቦዛ በምስራቅ ጎጃም ዞን በደባይ ጥላት ግን ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ቦታ ነው። ደቦዛ ሄደውም የቅኔ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ እያሉ የደቦዛው መምህር ሰሎሞን ለብሉይ ትምህርት ወደአዲስ አበባ ለመሄድ

ስለተነሱና በእሳቸው ወንበር ተተክቶ ጉባኤውን የሚያስቀጥል መምህር ባለመኖሩ ምክንያት ጉባኤው ተፈታ። እነ እማሆይ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ በዚያው አካባቢ እነጋትራ ሀና የሚባል ገዳም አስተዳዳሪ የደቦዛ ሚካኤልን ጉባኤ መፈታትና የመምህሩን ለትምህርት መሄድ በመስማታቸው እንዲሁም የሁለቱን ሴት የቅኔ ተማሪዎች ታሪክ በመስማታቸው ወደ እነጋትራ ሀና መጥተው ለቀለብም ሆነ ለማንኛውም ነገር ሳያስቡ እንዲያስቀፅሉ ላኩባቸው (አስቀጻይ ማለት ከመምህር ዝቅ ያለ የተወሰነ እውቀት ያለው ከሱ ዝቅ ያሉትን ተማሪዎች የሚያስተምር ማለት ነው)። ሆኖም እነ እማሆይ ወደ እነጋትራ ሳይሄዱ ከዲማ "እንድትመጡ" የሚል መልዕክት ስለተላከባቸው በቀጥታ ወደ ዲማ ሄዱ። በዚህ ጊዜ ዲማ ላይ ስድስት መቶ የሚደርስ ተማሪ ያላቸው መምህር ዲበኩሉ የተባሉ መምህር ነበሩ። እነ እማሆይ አመተ ማርያምም ጉባኤውን ተቀላቅለው መማር ጀመሩ። በርካታ ተማሪዎች ባሉበት በዚህ ሰፊ ጉባኤ የነበሩት ሁለቱ ሴቶች ነበሩ። የቅኔውን ሰምና ወርቅ እየተማሩ ባለበት ሰዓት ከባህር ዳር ሰላም አርጊው ከሚባል ገዳም ወልደ ጊዮርጊስ የተባሉ "የውስጠ ዘ ቅኔ"[1] አዋቂ መምህር "ዲማ ላይ ሁለት ሴቶች አሉ እነሱን ታስተምራለህ ብሎ እግዚአብሔር ልኮኛል" ብለው መጡ። እኒህ መምህርም የገዳሙን አስተዳደር አስፈቅደው ለሴቶቹ ቦታ ለይተው እንዲያስተምሩ ተፈቀደላቸው። የተወሰነ ጊዜ እንደተማሩም ከመምህሩ ጋር የነበራቸው የመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ስላልነበረና ከመንፈሳዊ ህይወታቸው ጋር ስላልተስማማ ከኒህ መምህር ጋር ለመለየት ተገደዱ። እማሆይ አመተ ማርያም እንደሚሉት "መምህሩ ሲያስተምሩ ጥሩ ቢሆንም በመማር ማስተማሩ ወቅት ለኛ ከነበራቸው አባታዊ ፍቅር የተነሳ ጠጋ በሉ እያሉ ቀረቤታውን በጣም ስላበዙብን እኛ ደግሞ ለመንፈሳዊ ህይወታችን አልተመቸንም ስለዚህ ከሳቸው ጋር ሳንቀጥል ቀረን።" በዚህ ሁኔታ ከመምህሩ ጋር የጀመሩት ትምህርት ቢቋረጥም ተመልሰውም ከወንዶቹ ጋር በመቀላቀል ቅኔውንም፣ ሀዲሳቱንም፣ ትርጓሜውንም መማሩን ቀጥለው በተከታታይ ከ1990 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ለአምስት አመት ያህል ቆይተው ተማሩ።

እማሆይ አመተ ማርያምና እማሆይ ኅሪት ከ1988 ዓ.ም ጀምረው እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ የአመክሮ ቆብ በማድረግ ቆይተዋል። የአመክሮ ቆብ ማለት አንድ መናኒ ገዳማዊ ህይወትን ለመኖር ይህንን ዓለም ትቶ ወደ ገዳም ሲገባ የሚያደርገው ነው። ይህ የአመክሮ ቆብ ከመነኮሳት ቆብ የተለየ እና ምንኩስናን እስኪቀበሉ የሚያደርጉት ነው። መናኒው የምንኩስናን እና የገዳማዊ ህይወትን እየተማረ የሚቆይበት ጊዜ ነው። እነ እማሆይም ይህንን የአመክሮ ጊዜ

[1] ከባለቅኔው ውጭ የቅኔውን ሚስጢር በቀላሉ ሊፈታው የማይችለው የቅኔ አይነት።(እማሆይ አመተማርያም)

አሳልፊው በ1991 ዓ.ም  እማሆይ ኅሪት በ24 ዓመታቸው፤እማሆይ አመተ ማርያም በ23 ዓመታቸው ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም በየኔታ ብዙ  ምንኩስናን ተቀብለዋል:: እማሆይ የምንኩስናን ህይወት ሲገልጹ

"ምንኩስና ከባድ አደራ ነው:: በባህርያችን ታጋሽ እና ጠንቃቃ መሆንን ይጠይቃል:: በወቅቱ ምንክኩስናን ከተቀበልን በኂላ ለብዙ ጊዜ ያለሰው አንንቀሳቀስም ነበር:: ይህ የተቀበልነው አደራም ከዚህ አለም ተድላ ደስታና  ውጥንቅጥ ተለይተን ለዚህ ዓለም ነገር ህሊናችንን ገድለን እንድንኖር ነው:: እኔ ወንድሞቼ ሲያገቡ፣ ሲወልዱ፣ ክርስትና ሲያስነሱ፣ ዓመት በዓል ሲሆን ሂጄ አላውቅም ምክንያቱም የተቀበልኩት አደራ ታላቅ እና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው በመሆኑ ከዚህ አለም ተድላና ደስታ መለየትን ይጠይቃል::" (ቃ/መ ጥር 24/2012 )

በአብነት ትምህርት ቤት ህይወት ውስጥ አንዱ ፈተና በለጋ ዕድሜ ከቤተሰብና ከአካባቢ እርቆ መማሩ ነው:: ተማሪዎቹ በቁርጥ ውሳኔ ከቤተሰብ ከተለዩ በኂላ የዕለት ጉርሳቸውን የሚያገኙት የሄዱበትን ሀገር ሀገሬ፤ ማህበረሰቡንም ቤተሰቤ ብለው በየመንደሩ እየዞሩ "በእንተ ስማ ለማርያም" እያሉ ቁራሽ በመለመን ነው:: ይህ ደግሞ ከገዳሙ እርቀ መሄድን፤ በየመንደሩ መዞርንና የውሻን ጩኸት መታገስን የሚጠይቅ በርካታ ፈተናዎች ያሉበት ነው:: ቁራሽ እየዞሩ መለመን የመንገድ እርቀትና የተለያዩ ፈተናዎች ያሉበት በመሆኑ ለሴቷ የተመቸ አይደለምና ብዙውን ጊዜ የሚለምኑት ወንድ ተማሪዎች ናቸው:: እነ እማሆይ አመተ ማርያምም እንደወንዶቹ እንደፈለጉ ተዘዋውረው መለመን ባይችሉም በአካባቢው ያሉ ማኅበረሰቦች የእነ እማሆይን ታሪክ በመስማታቸው እንደልጆቻቸው በመቁጠር ከሩቅም ከቅርብም ስንቅ የሚሆናቸውን ነገር በአህያ እየጫኑና በሸክም ከተለያየ አካባቢ ያመጡላቸው ነበር:: ከአካባቢው ማህበረሰብ በተጨማሪም አዲስ አበባ የሚኖሩ መዓዛ ድንግል የተባሉ እናት የእነእማሆይን ታሪክ በመስማት ለሁለቱም ሀያ አምስት ብር በድምሩ ሀምሳ ብር በየወሩ ከ1989 እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ ለስምንት ዓመት ያህል ይልኩላቸው ነበር:: ይህ የማህበረሰብ ማነህ?፣ ከየት መጣህ? ሳይል እንደልጁ ቆጥሮ የአብነት ተማሪው መጥቶ ከደጁ ሲቆም ቤቱ ያፈራውን ያለስስት እየለገሰ  ማህበረሰባዊ ሀላፊነቱን በመወጣት ተማሪዎችን ለቁም ነገር ሲያበቃ ኖሯል:: ይህ የማህበረሰብ ደግነት እስከምን ድረስ  እንደነበር እማሆይ ሲገልጹ

"ትዝ ይለኛል አንድ ጊዜ እማሆይ ኅሪት ለምለም እንጀራ አማረኝ ስትለኝ ያንን ለማግኘት ወደ መንደር ለልመና ስሄድ  አንድ ቤት ላይ ስደርስ ውሻ አስደነገጠኝ  ከዛም ፈርቼ ተመለስኩ::

ለካስ ውሻውን ፈርቼ ባዶ እጄን ስመለስ  የቤቱ ባለቤት አይታኝ ኖሯል እንጀራውን አጥፋ አጥፋ ይዛልን መጣች::"(ጥር24/2012)

ይህ ልማድ አሁንም ድረስ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በገጠሩ አካባቢ ያለ ተግባር ነው። እነ እማሆይ ቅኔውን የተማሩት ከወንዶቹ ጋር በመሆን ስለነበረ ከማህብረሰቡ በተጨማሪ ወንዶቹ ተማሪዎች ከለመኑት ቁራሽ ያካፍሏቸው እንደነበር ይገልጻሉ። ይህም በአብነት ትምህርት ቤት ያለውን መረዳዳትና መተዛዘንም ያሳያል።

እነ እማሆይ እንዲህ ባለ ሁኔታ ሀዲሳቱንም የቅኔውንም ትምህርት ተምረው በቅኔ እውቀት ብቁ በመሆናቸው ለማስመስከር ወደ ጨጎዴ ተጓዙ። ጨጎዴ በምዕራብ ጎጃም ዞን በቋሪት ወረዳ የሚገኝ ሥፍራ ነው። በዚህ ሥፍራ የኔታ ያሬድ የተባሉ  በቅኔው ሙያ አንቱ የተባሉ የቅኔ መምህር አሉ። ማንኛውም የቅኔ ተማሪ በየጉባኤው ቤት ከመምህር መምህር ዞሮ የተማረውን ዕውቀት ማስመስከርና ብቃቱን ማረጋገጥ አለበት ። በሌላ አገላለጽ የብቃት ማረጋገጫ ማዕከል ሄዶ ማረጋገጥ አለበት ማለት ነው። እማሆይ አመተ ማርያምም በየገዳማቱ እና በየጉባኤ ቤቱ ከመምህር መምህር ዞረው የተማሩትን የቅኔ ትምህርት በዚህ የብቃት ማስመስከሪያ ተቋም ጨጎዴ የኔታ ያሬድ ላይ በመሄድ ብቁ መሆናቸውን አስመስክረዋል። ያስመሰከረ ሰው ደግሞ ጉባኤ ዘርግቶ እሱም በተራው ደቀመዛሙርትን ማፍራት አለበት። እማሆይ አመተ ማርያም ግን ለመማር ከነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ፍትሀ ነግስትን ለመማር ተነሱ ። እማሆይ ፍትሀ ነገስት ለመማር የነበራቸውን ፍላጎት እንዲህ ይገልጹታል።

"በወቅቱ ገንዘብ ስለሌለኝና የሚሰጠኝም ስላልነበረ እንዲሁም ፍትሀ ነገስቱን የመማር ፍቅር ስለነበረኝ ልብሴን ሺጨ በዘጠና አምስት ብር የፍትሀ ነገስት መጽሀፍ ገዝቻለሁ" (ቃ/መ ጥር 24/2012)

እማሆይ አመተ ማርያም  ለመማር ከነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ መጽሐፍ ገዝተው ፍትሀ ነገስቱን ለመማር ሲነሱ መምህራቸው “ከዚህ በኋላ የተማሩትን ማስተማርና ደቀመዛሙርትን ማፍራት እንጂ መማር ይበቃዎታል” አሏቸው። በመምህራቸው ቅር የተሰኙት እና ያልጠበቁት የገጠማቸው እማሆይ አመተ ማርያም  የመምህራቸውን ትዕዛዝ ሳይቀበሉ ለትምህርት ወደ ምስራቅ ጎጃም ቀራንዮ መድሃኔ ዓለም አቀኑ። በዚያም መሪጌታ መላከ መላዕክት ተስፋ ስላሴ ከተባሉ መምህር የዋሸራ እና የውስጠ ዘ ቅኔ እና የቅኔውን ሰዋሰው መማር ቀጠሉ። ትምህርቱንም እንደጨረሱ በ1998 ዓ.ም “ባህር ዳር ተክለ ሃይማኖት መጥተው

እንዲያስተምሩ” የሚል ደብዳቤ ከቤተክርስትያኑ አስተዳደር ደረሳቸው:: እሳቸውም ጥያቄውን ተቀብለው ወደ ባህር ዳር ተክለሀይማኖት አመሩ:: ነገር ግን ቦታው እንዳሰቡት ለሳቸው መንፈሳዊ ህይወት የተመቸ አልነበረም:: የቦታውን ምቹ ያለመሆን ተናግረው ለመሄድ ሲነሱ በአካባቢው የነበሩ አባቶች በወቅቱ ሊቀጳጳስ ወደነበሩት አቡነ  በርናባስ ይዘዋቸው ይሄዳሉ:: በዚህ ወቅትም እማሆይን ይዘዋቸው የሄዱት አባቶች እማሆይን ቅኔ እንዲቀኙላቸው ይጠይቋቸዋል እማሆይም ቅኔያቸውን ያቀርባሉ:: አቡነ በርናባስም የእማሆይን ዕውቀት እና ችሎታ እንዲሁም ሴት የቅኔ መምህር መገኘቱን በማድነቅ ከባህርዳር ሳይሄዱ አቡነ ገሪማ የሚባል የሴቶች ገዳም ስላለ እዚያ ሴቶችን እንዲያስተምሩ ጠየቋቸው:: እማሆይም የታላቁን መንፈሳዊ አባት ትዕዛዝ በማክበር ወደአቡነ ገሪማ የሴቶች ገዳም ሄደው ሴቶችን ማስተማር ጀመሩ:: ነገር ግን የነበሩት ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ስላልነበራቸው ለተወሰነ ጊዜ ቆይተው አሁን ወደሚያስተምሩበት የባህር ዳር ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ተጓዙ:: የዚህ ካቴድራል አስተዳዳሪ እማሆይን ቅኔ እንዲያስተምሩ የጠየቁበትን አጋጣሚ እንዲህ በማለት ያስታውሱታል::

"በወቅቱ የባህር ዳር ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴደራል ውስጥ ያስተምሩ የነበሩት መምህር በመሄዳቸው ምክንያት ጉባኤው ተቋርጦ ስለነበር በወቅቱ የነበሩት የገዳሙ አስተዳዳሪ አባ ሀይለማርያም ወደ እሳቸው እንድመጣ አዘዙኝ::  በታዘዝኩት መሰረት ወደ ቤተክርስትያኑ ሄጄ ወደ ቢሯቸው ስገባ በጣም የገረመኝን ነገር ተመለከትኩ ይኸውም የቅኔ ሊቋ የእማሆይ ገላነሽን ትልቅ ፎቶ ተቀምጧል:: በአግራሞት ፎቶውን እያየሁ ሳለ አባ ሀይለ ማርያም እማሆይ ይህንን ፎቶ አየሽው እማሆይ ገላነሽ ናት:: የሷን ፎቶ እዚህ ያስቀመጥኩት ለምን እንደኾነ ታውቂያለሽ:: እማሆይ ገላነሽ ታላቅ የቅኔ ሊቅ ነበረች ነገር ግን በእግሯ የተተካ ሴት የቅኔ ሊቅ ባለመኖሩ እያዘንኩ ዘወትር ስወጣና ስገባ ፎቶዋን አተኩሬ እያየኹ እማሆይ እባክሽ ሰው ውለጂ እንዳንቺ ዓይነት ሊቅ ፍጠሪ እላት ነበር በማለት ካጫወቱኝ በኋላ ልጅ ጠርተው የእማሆይ ገላነሽን ፎቶ አንሳው ብለው አስነሱት:: ምክንያቱም እስከዛሬ እማሆይ ገላነሽን ሰው ውለጂ እያልኳት ነበር አሁን ግን ሰው ወልዳለች በማለት ሴት የቅኔ ሊቅ እንዲፈጠር የነበራቸውን ጉጉት ነገሩኝ :: እኔ ግን ይህ ቤተክርስትያን መሀል ከተማ ላይ  በመሆኑ ለመንፈሳዊ ህይወቴ  ምቹ አይሆንም ስላቸው የኛን ህይወት ተመልከቺ እዚህ ቦታ እረጂም እድሜ ስናሳልፍ ምንም የኾነው ነገር የለም"ሀጢአት ካልሄዱባት አትመጣም" በማለት ከተማ መኖር በራሱ ለመንፈሳዊ ህይወት ችግር እንዳልኾነ አስረዱኝ :: እኔም በሀሳባቸው ተስማምቼ ለማስተማር ወሰንኩ:: በዚህ ጉባኤ

ዘርግቼ ቅኔ እንዳስተምር በተጠየኩበት ወቅት ህጻናትንም እንዳስተምር ስጠየቅ እኔም ጌታ እንኳ "ኢትክልዎሙ ለህጻናት ይምፁ ሀቤየ እስመ ሎሙ ኒየቲ መንግስተ ሰማያት፤ ህጻናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው መንግስተ ሰማያት እደነሱ ላሉት ናትና" በሎ ተናግሯልና። ስለዚህ ህጻናትንም አስተምራለሁ ብዬ ተስማማሁ።" (ጥር 25/2012)

እማሆይ በባህር ዳር ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ማስተማር እንደጀመሩ አብዛኞቹ ተማሪዎች ወንዶች ነበሩ። ጉባኤው እየሰፋ ሲሄድ ግን ሴት ተማሪዎችም መምጣት ጀመሩ። ቦታ እስኪጠብ ድረስ ተማሪ መጉረፍ ጀመረ። እማሆይ አመተ ማርያም ጉባኤያቸውን አስፍተው በሚያስተምሩበት ሰዓት የእማሆይን ትጋትና ዕውቀት የተመለከቱት የቤተክርስትያኑ አስተዳዳሪ የሆኑት አባ ሀይለማርያም ለእማሆይ አመተ ማርያም አንድ ሀሳብ አቀረቡላቸው። ይኸውም ቀን ቀን ተማሪዎቻቸውን እያስተማሩ ማታ ማታ የመደበኛውን ትምህርት እንዲማሩ ነበር። እማሆይ አመተ ማርያም የቀደመ ታሪካቸውን ማለትም ወደ መንፈሳዊው ህይወት ሳይገቡ እስከ አስረኛ ክፍል ተምረው ወደ አስራአንደኛ ክፍል አልፈው የተውትን ትምህርት ሳይናገሩ በውስጣቸው ይዘውት ነበር። ነገር ግን አባ ሀይለማርያምም በተደጋጋሚ እንዲማሩ ሲጠይቋቸው እማሆይም ወደ ምናኔው ሳይገቡ የመደበኛ ትምህርት ተማሪ እንደነበሩና ከአስረኛ ወደ አስራአንደኛ ክፍል እንደተዛወሩ የአለማዊው ትምህርት ከመንፈሳዊው ጋር የማይጣጣምና የሚቃረን መስሏቸው እንደተውት ነገሯቸው። አባ ሀይለማርያምም በዚህ ሁኔታ በመደነቅ በፍጥነት የትምህርት ማስረጃቸውን አምጥተው ትምህርታቸውን ከማስተማሩ ጎን ለጎን እንዲቀጥሉ አዘዟቸው።

እማሆይም የመማር ፍላጎት ስለነበራቸውና እያስተማሩ የመማሩን ፈቃድ ከአስተዳዳሪው በማግኘታቸው ብሎም መንፈሳዊ ህይወት የመደበኛውን ትምህርት ከመማር እንደማያግድ ስለተረዱ የአስተዳዳሪውን ሐሳብ በመቀበል ቀድሞ ሲማሩ ከነበሩበት ከቻግኒ የትምህርት መሸኛቸውን አስመጥተው ባህር ዳር ከተማ “ኢትዮጲስ” በሚባል የርቀት ትምህርት ተቋም ትምህርታቸውን ጀመሩ። እሳቸው የተማሩት በቀድሞው የትምህርት ስርዓት ከአስር ወደአስራ አንደኛ ክፍል እንዳለፉ ቢሆንም እንደገና ወደ ዘጠነኛ ክፍል ተመልሰው መማሩን ቀጠሉ። የአስረኛ ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተና ተፈትነው ወደ መሰናዶ የሚያስገባ ነጥብ አመጡ። እማሆይ ግን “ብሉ ናይል” ኮሌጅ ተቋሙ ከሚሰጠው የትምህርት መስኮች የሚፈልጉትን መርጠው መማር እንደሚችሉ የነጻ ትምህርት እድል ሲሰጣቸው መሰናዶ ገብቼ ከምማር ኮሌጅ ገብቼ ብማር ይሻላል በማለት በዲፕሎማ መርሀ ግብር በኮፕሬቲቭ አካውንቲንግና ማኔጅመንት

ቀጥለው ቀን ቀን ተማሪዎቻቸውን ቅኔ እያስተማሩ ማታ ማታ እሳቸው እየተማሩ በከፍተኛ ውጤት አጠናቀቁ። በመቀጠልም በአድማስ ዩኒቨርስቲ በቢዝነስ ማኔጅመንት በዲግሪ ተመርቀዋል። "ትምህርት ማብቂያ የለውም" ብለው የሚያምኑት እማሆይ አመተ ማርያም የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ባመቻቸላቸው የትምህርት ዕድል በቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት በ2010 ዓ.ም የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል። በአሁኑ ወቅትም በ2012 ዓ.ም ባገኙት የትምህርት ዕድል በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በግዕዝ ቋንቋ በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር እየተማሩ ይገኛሉ።

ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በዚሁ በባህር ዳር ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ሴትም ኾኑ ወንድ ተማሪዎችን ንባብ፣ ቅኔ፣ ወንጌል፣ ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያም፣ መልክዐ ማርያም፣ መልክዐ ኢየሱስን ያስተምራሉ። እሳቸው ያስተማሯቸው አንድ ሴትና አንድ ወንድ በቅኔው ሙያ አስመስክረው በአሁኑ ወቅት ጉባኤ ዘርግተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ። እማሆይ በአሁኑ ወቅት ሰላሳ ሁለት የሚደርሱ በካቴድራሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆነው የሚማሩ ወንድ የቅኔ ተማሪዎች ያሏቸው ሲሆን ዳዊት የሚማሩ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ሴት ተማሪዎችም አሉ። ይህ ጥናት በተደረገበት ወቅት ሴት የቅኔ ተማሪዎች የሉም። ነገር ግንከዚህ በፊት እንደነበሩ እማሆይ ይናገራሉ። ወንዶቹ የቅኔ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ከቤተሰብ እርቀው የመጡ በመሆናቸው እንደጥንቱ የቆሎ ተማሪ በየመንደሩ በመሄድ ስመ እግዜብሄርን ጠርተው ቁራሽ ለምነው የሚማሩ ናቸው። ሴቶቹ ግን ዙረው ለመለመን ስለሚያስቸግራቸው ከቤተሰብ ስንቅ ይዘው በመምጣት ትምህርታቸውን ይከታተላሉ። የአኗኗር ሁኔታቸውን በተመለከተ ደግሞ እንደጥንቱ የቆሎ ትምህርት ቤት የሳር ጎጆ ሳይሆን እንደነገሩ በቆርቆሮ የተሰሩ ሰፋፊ ቤቶች ውስጥ ሶስት አራት ሆነው በአንድ ይኖራሉ። እነዚህ ተማሪዎች በቋሚነት በክረምትም ሆነ በበጋ ሙሉ ጊዜያቸውን ለቅኔው ትምህርት ሰጥተው የሚማሩ ሲሆኑ በክረምት ወቅት መደበኛው ትምህርት ሲዘጋ በርካታ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርስቲ የሚማሩ ተማሪዎች እንደየደረጃቸው ሲማሩ ክረምቱን ያሳልፋሉ። በዚህ ወቅት ታዲያ ተማሪዎቹ ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡ በመሆናቸው የማደሪያ ችግር እንደሚገጥማቸው ይናገራሉ። እማሆይ ይህንን የተማሪዎች የመኖሪያ ችግር ለመቅረፍ ህንጻ እንዲገነባላቸው ካቴደራሉን ቢጠይቁም እስካሁን ምላሽ እንዳላገኙ ይናገራሉ። ነገር ግን ባሉት ቤቶች ውስጥ አቻችለው ያስተምራሉ። ተማሪዎችም አዲስ እንግዳ ተማሪ ሲመጣ በትህትናና በፍቅር ተቀብለው በማስተናገድ ተሳስበው ይኖራሉ።

በምልከታዬ ወቅት እንዳስተዋልኩት እማሆይ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነትና ቀረቤታ እንደ እናትና ልጅ ነው። እማሆይ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ተማሪ ሳሙኤል ሲገልጹ

"እማሆይ ለእኛ እንደናታችን ናቸው። እኛ ከተለያየ ቦታ ነው ለመማር የመጣነው ለምሳሌ እኔ የመጣሁት ከዳንግላ አካባቢ ነው። ከጎንደር የመጣ አለ ከመንዝ አካባቢ የመጣ አለ እና ቢሆንም ሁላችንም ተቻችለን ነው የምንኖረው ። ወጣቶች ስለሆንን እናጠፋለን፤ በትምህርቱም አንዳንዴ ችላ እንላለን እሳቸው ግን እየተቆጡ እየመከሩ ይዘውናል። ተማሪውም እሳቸው ያዘዙትን ይሰራል። በቤተ ክርስትያኑ አንዳንዴ ስራ ሲኖር በእሳቸው በኩል ስንታዘዘ እንሰራለን ። በይሰሞን እራሱ አንቺ እንዳየሽው ይህንን የሽንትቤት ቁፋሮ እማሆይ ገንዘብ ከሚያወጡ ብለን እየቆፈርን ነው ያለነው። አንዳንዴ ሲቸግረን እማሆይ ያሳለፉትን ውጣ ውረድና ችግር በመንገር አይዟችሁ በርቱ ይሉናል። እኛም ከቤተሰብ ተለይተን ስንመጣ እግዚሀርን አምነን ከፈጣሪ በታች መምህራችንንና የአካባቢውን ማህበረሰብ ተስፋ አድርገን በመሆኑ የሳቸውን ምክርም ይሁን ቁጣ እንቀበላለን። በማስተማሩም በኩል እማሆይ በጣም ጎበዝ ናቸው፤አንድ ስህተት እንኳ አያልፉም። "(ቃ/መ ጥር 25/2012)



ምስል 1. የእማሆይ አምተማርያም ተማሪዎች ቅኔ ሲቀኙ

## 3.2 የእማሆይ ኀሪት ደባስ የህይወት ታሪክ

እማሆይ ኀሪት ደባስ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በእነማይ ወረዳ በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ አካባቢ ልዩ ስሙ ቤተ መስቀል በሚባል አካባቢ ከአባታቸው ከአቶ ደባስ ገሰሰ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ እናትነሽ አስናቀ በ1967 ዓ.ም ተወለዱ። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢያቸው በሚገኝ ቤተ መስቀል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርት ጀመሩ። የአስር አመት ህጻንና የሁለተኛ ክፍል ተማሪ እያሉ የእናታቸው አባት የሆኑት አቶ አስናቀ ወርቁ አረፉ። በዚህ ወቅትእማሆይ ኀሪትም አብዝተው በማልቀሳቸው ምክንያት ዓይናቸውን ታመሙ። ቤተሰቦቻቸውም ሀዘን ላይ ነበሩና ለልጃቸው ህመም ትኩረት ሰጥቶ ወደ ህክምና የወሰዳቸው ሰው ባለመኖሩ ህመሙ ተባብሶ ከትምህርታቸው አስቀራቸው። በዚህ ምክንያትም በጨቅላ እድሜያቸው ከእኩዮቻቸው ተነጥለው ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ። የልጃቸውን ተጫውተው ሳይጠግቡ ከጓደኞቻቸው ተነጥለው ከትምህርት ተለይተው ብርሃናቸው አደጋ ላይ መውደቁን መመልከት ያሳዘናቸው አባት "ከዚህ በኋላ ሌላ ዓለም የለኝም" በማለት ከቢቸና ከተማ አቅራቢያ ከምትገኝ ጮለሚት ማርያም ገዳም ፀበል ለማስጠመቅ እና ፈውስ ለማግኘት ይዘዋቸው ሄዱ። ለተወሰነ ጊዜ እንደቆዩም ህመሙ ተሻላቸው።

የልጃቸው ዓይን መዳን ያስደሰታቸው አባት ከጮለሚት ገዳም ልጃቸውን ይዘው ወደ መኖርያ ቀያቸው ቤተ መስቀል ይመለሳሉ። የልጃቸው ብርሃን መመለስ ደስታው ሳያልቅ በሄዱ በአምስተኛ ቀናቸው ተመልሶ ዓይናቸው ይታመማል። የልጃቸው ተመልሶ መታመም ያሳሰባቸው አባት በድጋሚ ወደ ጮለሚት ማርያም ገዳም በመሄድ ብዙ ጊዜ ቢያሳልፉም የዓይናቸው ህመም ሊታገስላቸው አልቻለም። እማሆይ ኀሪት ዓይናቸው ሙሉ ለሙሉ ባይጠፉም (የተወሰነ ያይላቸው ስለነበር) መደበኛውን ትምህርት ባለመማራቸው ተስፋ ሳይቆርጡ በገዳሙ ውስጥ ከነበሩ መምህር ከበስመ አብ ጀምረው ነአኩተከ፣ ፀሎተ ሀይማኖትን መማር ጀመሩ።ነገር ግን ቦታው ከቤተሰብ ራቅ ያለ በመሆኑ እና እማሆይም ገና ሕፃን በመሆናቸው ምክንያት ለአንድ ዓመት ያህል እንደቆዩ በትምህርቱ ብዙም ሳይገፉ ተመልሰው ወደ ትውልድ መንደራቸው አቀኑ።

ዲማ ቅኔን እና መጻህፍትን ተምረው ቤተ መስቀል የመጡ የአጼት ሰው መርጌታ ተከስተ ብርሃን ብሬ የተባሉ ሰው ነበሩ። እማሆይ ኀሪትም ከመርጌታ ተከስተ ብርሃን ውዳሴ ማርያምን፣ አንቀ ፀብሃንን፣ መልክዐ ኢየሱስን፣ መልክዐ ማርያምንና ዳዊትን ጨምሮ

የሀይማኖት ትምህርት ተማሩ። ቀጥለውም የውዳሴ ማርያምን አንድምታ በመማር ላይ ሳሉ የእማሆይን ልበ ብርሃንነት የተመለከቱት መርጌታ ተከስተ ብርሃን ቅኔ እንዲማሩ ይመክሯቸዋል። እማሆይም በመምህራቸው ሀሳብ ተስማምተው ቅኔን ለመማር ግስ በማጥናት ቅኔ እየቆጠሩ መንገር ጀመሩ። ለቤተሰቦቻቸው የመጀመሪያ ልጅ የሆኑት እማሆይ ኅሪት በለጋ እድሜያቸው ታናናሽ እህትና ወንድሞቻቸውን የመያዝና የተለያየ ስራ የማገዝ ሃላፊነት ስለተጫነባቸው ትምህርታችውን በአግባቡ መከታተል አልቻሉም።በተጨማሪም የሳቸውን በሃይማኖት ትምህርት የመግፋትና ቅኔን ለመማር መጀመራቸው ከአባታቸው በስተቀር ዘመዶቻቸውም ሆኑ የአካባቢው ማህበረሰቦች አለመቀበላቸውን እንዲህ በማለት ይገልጹታል።

"በአብነት ትምርት ቤት የተለመዱት ወንዶች በመሆናቸውና እኔም ትምህርቱን ስጀምረው ሌላ ሴት ተማሪ ስላልነበረ በወቅቱም ደርግ ሁሉንም ህብረተሰብ እንዲማር ይቀሰቅስ ስለነበረ ሁሉም የአካባቢው ማህበረሰብ ልጆቹን ወደዘመናዊው ትምህርት ነበር የሚልከው። በዚህ ምክንያት ይቺ ልጅ የሀይማኖት ትምህርት ተምራ መቅደስ ውስጥ ገብታ ልትቀድስ ነው ወይስ ምን ልትሆን ነው ያለቦታዋ አስገብተው የወንዶችን ሙያ የሚያስተምሯት  እያሉ ቤተሰቦቼን ያሚቸው እና ይቃወሚቸው ነበር። ነገር ግን አባቴ እንድማር ይፈልግ ስለነበር የማንንም ሀሳብ ሳይሰማና ያለውን የሌሎችን ሰዎች ጫና ታግሶ በትምህርቴ እንድገፋበት በተወሰነ መልኩም የተሻለ ቢሆንም በቤተሰብ ውስጥ እኔ የመጀመሪያ ልጅ ስለሆንኩ ታናናሾቼን የመያዝ፤ቤት ውስጥ ስራ የመስራት ሃላፊነት ስለተጫነብኝ የተጀመረው ትምህርቴ ተቋረጠ።"(ቃ/ለ ጥር 15/2012)

መርጌታ ተከስተ ብርሃን በተማሪያቸው የትምህርት መስተጓጎል በማዘን እና የቤተሰቦቻቸውን የግንዛቤ ችግር ተመልክተው እማሆይ በትምህርቱ እንዲገፉ በማሰብ ስንቅ አዘጋጅተው ወደ ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም አስጠፍተው ለቤተሰቦቻቸው ሳያሳውቁ ይዘዋቸው ይሄዳሉ። ዲማ ከደረሱ በኋላም እማሆይ ኅሪትን እዛው ለሚኖሩ አክስታቸው አደራ ሰጥተው ዲማ በሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም የቅኔ፣ የሀዲሳት እና የፍትሀ ነገስት መምህር የነበሩት የኔታ ዘሚካኤል ጋር ትምህርታቸውን እንዲማሩ አደራ ሰጥተዋቸው ወደ ሀገራቸው አዴት ሄዱ። እማሆይም የቅኔ ትምህርታቸውን መከታተል ጀመሩ። ሆኖም ትምህርቱን ብዙም ሳይገፉ ታናሽ እህታቸው በመሞቷ ምክንያት  ወደቤተሰቦቻቸው ሄዱ።

እማሆይ ወደ ዲማ ሳይመለሱ የጀመሩትን ትምህርት ለመቀጠል በ1987 ዓ.ም ወደ እናርጅ እናውጋ ወረዳ ደብረ ወርቅ ማርያም በመሄድ ሰፊ ጉባኤ ከነበራቸው የኔታ ከብካብ ከሚባሉ

መምህር ያቋረጡትን የቅኔ ትምህርት ቀጥለው መማር ጀመሩ። በዚህ ወቅትም ከባህርዳሯ እማሆይ አመተ ማርያም ጋር ተዋወቁ። ለሶስት ዓመት ያህልም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ እንደቆዩ በአሁኑ ወቅት አክሱም ጽዮን ቅኔን እያስተማሩ ያሉት እማሆይ ህይወት ደቦዛ ሚካኤል በሚባል ቦታ እያስተማሩ እንደሆነ ይሰማሉ። በዚያ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ወደ ደቦዛ ሚካኤል ቢሄዱም የቅኔ መምህሯ እማሆይ ህይወት በጉባኤ ቤቱ እና በቤተክርስትያኑ ውስጥ በተፈጠረ ችግር ቦታውን ለቀው ሊሄዱ በመሆናቸው እንዳሰቡት ባይሳካላቸውም በሌሎች አስቀጻዮችች ትምህርቱን ቀጠሉ።

በቅኔ ቤት አስቀጻይ ማለት ከመምህር ያነሰና በእውቀት ብዙ ያልበሰለ አንዳንድ ጊዜ መምህሩን ተክቶ የሚያስተምር በመሆኑ በመምህር መማር አለብኝ በማለት እንደገና ተመልሰው ወደ ዲማ የኔታ ዘሚካኤል ዘንድ ይሄዳሉ። ዲማ የኔታ ዘሚካኤል ጋር ሀዲሳት የተማሩ ሊቀ ሊቃውንት ሰሎሞን የተባሉ ወደ ደቦዛ ሚካኤል ሊያስተምሩ ሲሄዱ እማሆይም መምህሩን ተከትለው ወደ ደቦዛ በመመለስ የቅኔውን ትምህርት ቀጠሉ። እማሆይ እንደሚሉት ብዙውን የቅኔ ትምህርት የተማሩት ደቦዛ ሚካኤል ከእኚሁ መምህር ነው። ለአንድ ዓመት ያህል እንደተማሩ መምህሩ ብሉይን ለመማር ወደ አዲስ አበባ በመሄዳቸው ምክንያት ጉባኤው ተፈታ። እማሆይ ጎሪትም ተመልሰው ወደ ዲማ በመሄድ ከየኔታ ዘሚካኤል ትምህርታቸውን መከታተል ጀመሩ። ነገር ግን የእማሆይ ልቡና እረፍት አልነበረውምና አሁንም ወደ ሌላ ጉባኤ ቤት ለመሄድ ወስነው ሲነሱ የኔታ ዘሚካኤል " እዚሁ ይማሩ እንጂ ከዚህ በኋላ የትም መሄድ አይቻልም" አሏቸው። በዚህ ጊዜ እማሆይ የአመክሮ ቆብ አድርገው የቆዩ በመሆናቸው ከእማሆይ አመተ ማርያም ጋር በመሆን ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከየኔታ ብዙ በ1991 ዓ.ም ምንኩስናን ተቀበሉ።

እማሆይ የቅኔውን ትምህርት በማቆም ሀዲሳትን መማር ጀመሩ። ሀዲሳቱን ተምረው እንደተመረቁ "እስካሁን የለፋሁበትን የቅኔ ትምህርት ማስመስከር አለብኝ" በማለት ወደ ጨጎዴ ተጉዘው ከ1994 እስከ 1997 ዓ.ም ቆይተው የተማሩትን የቅኔ ትምህርት የበለጠ በማዳበር በቅኔው ሙያ ብቁ መሆናቸውን ከሊቀ ሊቃውንት ያሬድ አስመስክረው ወደ ዲማ ተመለሱ።

እማሆይ በቅኔው ሙያ ማስመስከራቸውን የሰሙ የተለያዩ ገዳማት አስተዳዳሪዎች ለመምህርነት ስለፈለጓቸው ወሎ፣ ባህርዳርና አዴት አካባቢ ደብዳቤ በመጻፍ ለገዳሙ ጥያቄ አቀረቡላቸው። ይህን ያዩት የኔታ ዘሚካኤል ዲማ ላይ እንዲያስተምሩ በማሰብ ገዳማቱንና የአካባቢውን ማህበረሰብ በመሰብሰብ ካወያዩ በኋላ ለእማሆይ የመኖሪያ ቤት እና ለማስተማሪያ የሚሆን ጉባኤ ቤት በመስራት ቅኔ እንዲያስተምሩ ተደረገ።

እማሆይ ኀሪት በ1997 ዓ.ም የማስተማር ተግባራቸውን ሲጀምሩ ሴት የቅኔ ተማሪዎች አልነበሩምና ወንዶችን ብቻ በማስተማር ነበር ። ሆኖም በዚህ ጊዜ የነበሩት ሌላው የቅኔ መምህር ደስተኛ አልነበሩም፤ ምክንያቱም ተማሪዎች በእማሆይ የማስተማር ብቃት እየተማረኩ ወደ እሳቸው ይሄዱ ነበር። በዚህ ምክንያት እማሆይ ህጻናትን እንዲያስተምሩ ቢደረግም ቅሬታው መቆም ስላልቻለ ሴቶችን ብቻ እንዲያስተምሩ ተደረገ። በወቅቱ ሴት የቅኔ ተማሪዎች ባለመኖራቸው እማሆይ ኀሪት ቢከፉም ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ሴቶችና ወንዶችን ቀላቅለው ማስተማር ጀመሩ።

እማሆይ ኀሪት በ2006 ዓ.ም የማስተማር ስራቸውን አቁመው በቤተ ክህነት ባገኙት ፈቃድ መፅሐፈ ሊቃውንትን ለመማር አዲስ አበባ ወደምትገኘው ታዕካ ነገስት ባዕታ ለማርያም ገብተው ከ2007 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ትምህርቱን ሲከታተሉ ቆዩ። ነገር ግን ጤና በማጣታቸው የጀመሩትን ትምህርት አቋርጠው ወደ ቀደመ ስፍራቸው በመመለስ ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ቅኔ የማስተማሩን ተግባር ቀጠሉ። በአሁኑ ሰዓትም ሴት ተማሪዎችን ብቻ የሚያስተምሩ ሲሆን ሰላሳ አምስት የሚሆኑ ሴት ተማሪዎች አሏቸው። ከነዚህ ውስጥ ሀያ አምስት ያህሉ ማህበረ ቅዱሳን በሚባለው ተቋም የገንዘብ ድጎማ ይደረግላቸዋል። ከተማሪዎቻቸው አብዛኞዎቹ ከጎንደር አካባቢ የሚመጡ ሲሆኑ የአካባቢው ተማሪዎች ብዙም እንደሌሉ ይገልጻሉ። በክረምት ወቅት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በመምጣት በዕረፍት ጊዜያቸው መጥተው ይማራሉ፤ የተወሰኑት ደግሞ በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው የተማሩትን የቅኔ ትምህርት ዲማ በመምጣት ለማጠናከር ይማራሉ። ነገር ግን በመጠለያ ዕጥረት ምክንያትም ከተለያየ አካባቢ ቅኔን ለመማር የሚመጡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ፤መጠለያ ቢኖር ጉባኤው ሊሰፋ እና ከአሁኑ የበለጠ ተማሪ ሊመጣ እንደሚችል ተስፋ ያደርጋሉ። እማሆይ ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት፤የጠበቀ ቁርኝትና ፍቅር እንዲህ ይገልጹታል፦

"ተማሪዎቼ ለኔ ልዩ ናቸው እነሱም ያላቸው ፍቅራቸው መናገር ያቅተኛል። ያላቸው ነገር የተለየ ነው።"(ጥር 8/2012)

ተማሪዎቹም ከእማሆይ ጋር ያላቸውን የእናት እና የልጅ ፍቅርና የጠበቀ ግንኙነት ተማሪያቸው የሆነችው ወለተ ስላሴ እንዲህ ትገልጸዋለች።

በአንድ ወቅት ከጀርመን ሀገር የመጡ የእማሆይን ታሪክ ሰምተው ወደ ዲማ በመምጣት ገዳሙን እንዲሁም የወንዶችን እና የኛን (የሴቶችን) ጉባኤ ቤት ስንማር በማየታቸው በተለይም

እማሆይ እኛን ሲያስተምሩ አብረው ቁጭ ብለው በመመልከታቸው በጣም አደነቁ ። ይህንን የሀገሬን የቅኔ ትምህርት ቤት ጉዳይ በተለይም የሴቶችን የቅኔ ዘረፋ ጉዳይ በደንብ መተዋወቅ አለበት። እማሆይም እውቅናና ክብር ማግኘት ስላለባቸው ከሚመለከተው አካል ጋር ተነጋግሬ ከዚህ የበለጠ ክብር እንዲያገኙ አደርጋለሁ አሉ። በዚህ ጊዜ ተማሪው በሙሉ ብድግ ብሎ እኛ ማንንም አንፈልግም እየመጣችሁ አትረብሹን እማሆይን ከወሰዳችኹ ማን አለን እኛ ቢርበንም ቢጠማንም ችለን እንማራለን ካልኾነም እኛ ብንሄድ እንኳ አቅምና እረዳት ያለው መማር ስለሚችል እየመጣችሁ እሳቸውን እንወስዳለን እያላችሁ ጉባኤው እንዲፈታ አታድርጉ። ብሎ ሁሉም ተማሪ ሲያለቅስ እሳቸውም አብረው አልቅሰው ይቅርታ እኔ እሳቸውን ለማስተዋወቅ እንጂ በክፉ አስቤው አይደለም በማለት የተማሪውንና የእማሆይን ጥብቅ የኾነ ግንኙነት እና ፍቅር አድንቀው ድጋፍ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተው ሄዱ። በተለያየ ጊዜም እንደዚሁ እማሆይን ሌላ ቦታ እንውሰድ እያለ ስለሚመጣ ነው። እና ተማሪው የእማኾይ ነገር ጭንቁ ነው ።እሳቸውም ለተማሪው በጣም ነው የሚሳሱት ማለትም ስንቅ ሲቸግረን እንኳ ከራሳቸው ቀንሰው ይሰጡናል። እንኳን እኛ ተማሪዎቻቸው የዲማ ሰው (የአካባቢው ሰው) እራሱ እማሆይ ከዚኽ እንዲኼዱ አይፈልግም።(ቃ/መ ወለተ ሥላሴ ጥር 10/2012)

ይህ እንግዲህ እማሆይ ኀሪትና ተማሪዎቻቸው ያላቸውን ቅርበትና ፍቅር የሚያሳይ ሲሆን ለተማሪዎቹ እረጅሙን የአብነት ትምህርት ቤት ህይወት ያለውን ውጣ ውረድ ሳይሰላቹ በትዕግስት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋቸዋል። ለመምህሯም ኑሮው ምቹ ባልሆነው የአብነት መምህራን ህይወት ደስ ብሏቸው እውቀታቸውን እንዲያስተላልፉ ያደርጋቸዋል።

ስለ እማሆይ ኀሪት ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም የወንዶች ቅኔ መምህር የሆኑት መርጌታ አለማየሁ ዳኜ ሲናገሩ

“እማሆይ ኀሪት በጣም ጠንካራ ናቸው። በሴት አቅም በዛ ላይ ከአለም ብርሃን የተከለከሉ በመሆናቸው፤(የቅኔ ትምህርት አንቺ አታውቂውም እንጂ ትንሽ ከበድ ይላል) በዛላይ ከቤተሰብ እርቆ ከሀገር ሀገር ዞሮ ከተለያየ መምህር የሚማሩት በመሆኑ ለሳቸው ከበድ ይላል፤ ቢሆንም ይህን ሁሉ ውጣ ውረድ አልፈው እዚህ ደርሰዋል። እኔ እማሆይን ከልጅነታቸው ጀምሬ አውቃቸዋለሁ በጣም ጠንካራ ናቸው። የቅኔ ትምህርት ለሴት ትንሽ ይከብዳል ብዙ ጊዜ ተማሪው ከቤተሰብ ስንቅ ስለማያገኝ መንደር ለመንደር ዞሮ ቁራሽ ለምኖ ነው ትምህርቱን የሚማረው ስለዚህ ለሴት ያስቸግራል። እንደምታይው ያው አሁን እኔ ወንዶችን አስተ ምራለሁ እሳቸው ሴቶችን ያስተምራሉ አንዳንድ ጊዜም ሴቶቹን ወደኛ ይዘዋቸው በመምጣት

እዚህ ቅኔ ይቀኛሉ ። ተማሪውም አገሬውም ማለት የዲማ አካባቢ ሰውም በጣም ይወዳቸዋል። አንዳንዴ በአንዳንድ ጉዳይ ከዲማ ሲወጡ ጥለውን ሊሄዱ ነው በማለት ይጨነቃሉ። እሳቸውም ዲማን ከለቀቁ ጤና አይሰጣቸውም ስለዚህ ሌላ ቦታ መሄድ ቢፈልጉም ያው እስካሁን አሉ።" (ቃ/መ ጥር 15/2012) በማለት እማሆይ ኅሪት ከተማሪዎቻቸው እና ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት እንዲሁም ጥንካሬያቸው ይገልጻሉ።



ምስል 2. የእማሆይ ኅሪት ተማሪዎች በትምህርት ላይ

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የቅኔ መምህራኑ የህይወት ታሪክ በቅደም ተከተል የቀረበ ሲሆን። መረጃውም ሁለቱ መምህራን ቅኔ በሚያስተምሩበት የተለያየ ስፍራ በመገኘት ታሪኩን ሙሉ ሊያደርጉ የሚችሉ መረጃዎችን በሚያስገኝ መልኩ ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተብራርተው ቀርበዋል። የህይወት ታሪኩም መምህራኑ የት ተወለዱ?፤ እስተዳደጋቸው እንዴት ነበር?፤ ወደ ቅኔው ትምህርት እንዴ ገቡ?፤ ሴትነትና የቅኔ ትምህርት እንዴት ይታያል?፤ ለትምህርታቸው የቤተሰብና የማህበረሰብ አስተዋፆ እንዴት ነበር?፤ አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል የሚሉ ጉዳዮች የታዩ ሲሆን በነዚህ ጉዳዮች መሰረትነትም የቅኔ መምህራኑ እማሆይ አመተ ማርያምና እማሆይ ኅሪት በገጠራማው የሀገሪቱ ክፍል ተወልደው በለጋ እድሜያቸው ወደ መደበኛ ትምህርት የገቡና ተመሳሳይነት ባለው አጋጣሚ ወደ ቅኔው ትምህርት ያዘነበሉ አብዛኛውን የቅኔ ትምህርትም አብረው የተማሩ እና ረጅም አመታት

አብረው ያሳለፉ መሆናቸው፤ለቅኔ ትምህርቱ የነበረው የቤተሰብና የማህበረሰብ አስተዋፆን በተመለከተ የእማሆይ አመተማርያም ቤተሰቦች ወደ ቅኔው ትምህርት ለመግባት በጎ አመለካከት የነበራቸው ሲሆን የእማሆይ ጎሪት ቤተሰቦች ግን ከአባታቸው በቀር ሌሎቹ የቤተሰቡ አባላት በጎ አመለካከት ያልነበራቸው መሆኑ፤ በሩቅም ሆነ ቅርብ የነበረው ማህብበረሰብ ግን የቅኔ ትምህርቱን ጀምረው እስኪጨርሱ እንደቤተሰብ ሆኖ እንደሚደግፋቸው በጥናቱ ለማየት ተችሏል፡፡ የቅኔ ትምህርት ከቤተሰብ እርቆ፤ ከመምህር መምህር ተዘዋውሮ፤ ቁራሽ ለምኖ፤ ረዘም ላለ ጊዜ የሚማሩት በመሆኑ ለሴት ልጅ ምቹ ባይሆንም እነዚህ የቅኔ መምህራን ግን ይህን ሁሉ ውጣ ውረድ አልፈው አሁን ተተኪ በማፍራት ላይ እንደሚገኙ በጥናቱ ለማየት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የቅኔ ትንተና

ይህ ምዕራፍ የጥናቱን ግብ ለማሳካት ከሁለቱ መምህራን የተሰበሰቡት ቅኔያቶች በፍካሬ ስልት ተተንትነው የቀረቡበት ነው። እነዚህ ቅኔያቶች መምህራኑ በተለያየ አጋጣሚና ሁኔታ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተመስርተው የተቀኟቸው ናቸው። እነዚህንም ቅኔያቶች መምህራኑ ካሉበት ቦታ በመሄድ የተሰበሰቡ ሲሆን ከእነዚህ ቅኔያቶች መካከል ለትንተና የተመረጡት ሰላሳ ሦስት ቅኔዎች ሲሆኑ ስምንት የግዕዝ ቅኔ ዓይነቶች ናቸው። እነዚህም ጉባኤቃና፣ ዘአምላኪየ፣መወድስ፣ ዘይእዜ፣ ሥላሴ፣ ሚበዝኁ፣ ኀንጌሃ፣ ዋዜማ የተባሉ ቅኔያቶች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ ጉባኤ ቃና የተሰኘው የቅኔ ዓይነት ሰፊውን ቁጥር ይወስዳል። በዚህ ምዕራፍ የቀረቡት ቅኔያቶች በመጀመሪያ ማህበራዊ ቀጥሎም ፍልስፍናዊ በመጨረሻም ሐይማኖታዊ ዕሳቤ ያላቸው ቅኔያቶች እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተፈርጀው ተፈክረዋል።

በዚህ ጥናት ውስጥ ተሰብስበው የተተነተኑት የመምህራኑ ቅኔያቶች ፈርጀ ብዙ የሆነውን የነገረ ሰብዕ ጉዳዮችን የያዙ ማህበራዊ፣ ፍልስፍናዊ ሐይማኖታዊ ቅኔያቶች ሲሆኑ ሊቃውንቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የታዘቡትን፣ የኖሩትን፣ ያዩትንና የሰሙትን በመተቸት፣በመምከር ፣ በማሞገስ ማህበረሰባቸው መልካሙን እንዲጠብቅ እና እንዲያስቀጥል በጎ ያልሆነውን ልማድ እንዲያስወግድ ከፍ ባለ ጥበባዊ መንገድ ይናገራሉ። በፍልስፍናዊው የሰውን ልጅ ምኞትና ፍላጎት ይገልጻሉ እንዲሁም እረቂቅ የሆነውን ሞት ይሞግታሉ፤አምላክን ይጠይቃሉ፤ በነገረ ሐይማኖቱ በኩልም እንዲሁ ነገረ ቅዱሳንን፣ ነገረ ትንሳኤን፣ ነገረ ድህነትን በአጠቃላይም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ አስተምህሮ ያሉ ጉዳዮችን ወርቁን በሰም አልብሰው አራቅቀው ይቀኛሉ። በዚህ መሰረት አስራ ስምንት ማህበራዊ ጉዳዮችን፤ አምስት ፍልስፍናዊ ጉዳዮችን ፤አስር ሐይማኖታዊ ጉዳዮችን የያዙ ቅኔያቶች እንደሚያነሱት ርእሰ ጉዳይ በፍካሬ ስልት የያዙትን ምስጢራዊ ዕሳቤና መልዕክት ከተለያዩ ታሪካዊ ፣ ሀይማኖታዊ እና የተለያዩ አስረጂዎችን በማምጣት ተተንትነው ቀርበዋል።

### 4.1 ማህበራዊ ጉዳይ

ማህበራዊ ጉዳይ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለና የተለመደ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት ያለው በዕለት ከዕለት የሚከወን ድርጊት እና ዕሳቤ ነው። ማህበራዊ ጉዳይ በውስጡ በርካታ

ውስብስብ ዕሳቤዎችን የያዘ ነው። የዚህን ጥናት ዓብይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የጥናቱ ትኩረት የሆኑት የቅኔ መምህራኑ የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸውን ቦታው ድረስ በመሄድ እና በመሰብሰብ የተካሄደ በመሆኑ በመስክ ከሚካሄዱ ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚመደብ ነው። በዚህ ክፍልም ከሁለቱ የቅኔ መምህራን የተወሰዱ ጉዳያቸውን ማህበራዊ ያደረጉ አስራ ስምንት የሚሆኑ ቅኔያቶች ተተንትነዋል። መምህራኑ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን በቅኔያቶቻቸው ውስጥ የሚገልጹ ሲሆን በቅኔያቱ ትርጓሜ ትንታኔ ሂደትም የግዕዝ ቅኔ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰጥ የትምህርት ዘርፍ ቢሆንም ከሐይማኖታዊው ጉዳይ ባሻገር የሰው ልጆችም የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ የሚመለከት እና ሰዋዊ የሆኑ ዕሳቤዎች የሚራቀቁበት እንደሆነ ለማሳየት የሚያስችሉ ቅኔያት ተፈክረው ቀርበዋል።

### 4.1.1 ስለምክር

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

አብዛኄ ወይኑ ጌጋይ ዘውገ ዘሰለጳድ ቆሬ።

ተገንጽለ ግበ ዘአልባ ፍጥረተ አሮን ዝማሬ[2]።

**ትርጉም፦** በደል ወይኑን የአበዛ የሰለጳድ *ሥጋ የሥጋ* ወገንተኛ የሚሆን ቆሬ።

የደገኛ አሮን ፍጥረት ምስጋና የሌለባት ጉድጓድ ተገለበጠ (ወደቀ)።

የቅኔው ወርቃዊ መልዕክት ታሪኩ በኦሪት ዘፀአት ላይ የምናገኘው ነው። እስራኤላውያን በግብጽ በባርነት በሚኖሩበት ዘመን ንጉሱ ፈርዖን በእስራኤላውያን ላይ በደል ይፈጽምባቸው ነበር። ያለዕረፍት በማሰራት ነፍሰ ጡር ሴቶችን ሳይቀር ጭቃ እያቦኩ እዚያው እንዲወልዱ በማድረግ እስራኤላውያን ላይ ግፍ በማብዛቱ በእሱና በሀገሩ ላይ ቁጣ (መቅሰፍት) በመጣበት ጊዜ በባርነት የያዛቸውን ህዝቦች እንዲለቅ በተለያዩ መቅሰፍቶች ቢመከርም እስራኤላውያንን አለቅም በማለት አገዘዙን አጽንቶ ሲያስጨንቃቸው በሙሴ መሪነት እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ለመውጣት ወደ ከነአን ሲጓዙ የኤርትራ ባህር ለሁለት ተከፍሎ በደረቅ ምድር ተሻግረዋል። ልቡ የደነደነው ፈርዖን እስራኤላውያን ላይ ባርነት አጽንቶ ለመኖር ሲል

---
[2]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

ከነሠራዊቱ  ሲዘምትባቸው እስራኤላውያንን ያሻገረች ባህር ፈርዖንን አስጥማዋለች ::ይኸው ታሪክ በዚህ ቅኔ ውስጥ በመምጣት ምክርንና ተግሳጽን አለመስማት የሚያስከትለውን ውድቀት ላማስተላለፍ ቀርቧል ::

ከማህበራዊ ጉዳይ አንጻር ሲታይ አንዳንድ ሰው አስካሪ የሆኑ መጠጦችን አብዝቶ የሚጠጣ አለ። አንድ ሰው በሱስ ወይም በልማድ፣ በብስጭት ፣በወቅታዊ ችግር እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች አብዝቶ የሚጠጣ ይሆናል። ይህንን አመሉንም እንዲተው ቢመከር እንኳ አሻፈረኝ በማለት በመጠጥ ሱሱ ይገፋበታል በዚህም ምክንያት ስራን በአግባቡ ያለማከናወን ፣ትዳርንም ሆነ ኑሮን መምራት ያለመቻል ሀላፊነትን ያለመሸከም ችግሮች ይገጥሙታል።

ማህበረሰቡም አብዝተህ አትጠጣ አትስከር ብሎ ሲለው ያልሰማውን ሰው "ምከረው ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው" በማለት ሰውዬውን እንደእብድ በመቁጠር ማህበረሰቡ ከሚሰጣቸው ሃላፊነቶችና የክብር ቦታዎች በመለየት ማህበረሰቡ ራሱ ያገልለዋል። አብዝቶ የሚጠጣ ወይም ሰካራም ሰው ከማህበረሰቡ መገለል ብቻ ሳይሆን የመጠጡ ብዛት ኑሮውንና ስራውን አስትቶ የመጠጥ ምርኮኛ ስለሚያደርገው መጨረሻው በተለያዩ በሽታዎች ተይዞ ህይወት ማጣትን ያስከትላል። በቁሙም ከመጠጡ ብዛት እራሱን መቆጣጠር ስለሚሳነው ለሰው ልጅ ከማይገባ ስፍራ በየቆሻሻውና በየጉድጓድ፤ "የአሮን ፍጥረት ምስጋና የሌለባት ጉርጓድ" ውስጥ ይወድቃል በማለት  በብዙ ተግሳፅ ያልተመለሰውና ያልተመከረው ፈርዖን መጨረሻው እንዳላማረው ሁሉ የበዛ መጠጥም እንዲሁ ከክብር ያጎድላል፤ ማንነትን ያሳጣል፤ በሰዎች ዘንድ ያስነቅፋል፤ ከፍ ሲልም እንደ ልበ ደንዳናው ፈርዖን ህይወቱን እንደሚያሳጣው "ወይኑ ያበዛ ፈርዖን" በሚሉት የቅኔው ቃላት የበዛ መጠጥ የሚያስከፍለውን ዋጋ እየገለጹ የሰው ልጅ መጠጥን ማብዛት እንደሌለበት ቢጠጣ እንኳን በልክና በአግባብ እንደሆነ ባለቅኔዋ  ምክር አዘል የሆነ ቅኔ ተቀኝተዋል።

**ቅኔ ፪ ጉባኤ ቃና**

እምከዊኖተ ሰብእ በኩር ከዊኖተ ገብር እንስሳ።

ነዋ ይኄይስ ቀቢረ ቆማ አበሳ[3]።

**ትርጉም፦**

ሰው አለቃን ከመሆን አገልጋይ እንስሳን መሆን።

---

[3]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

እነሆ በደል ሴትዮን በቁሚ ለመቅበር ይሻላል።

በቅኔው የተላለፈው ሠማዊ መልዕክት በደልን ለማጥፋት ሰው ከመሆን ይልቅ እንስሳ መሆን ይሻላል የሚል ነው። እንስሳን እንስሳ ቢያጠፋው በደል ሆኖ አይቆጠርበትም። እንስሳት ቢያጠፉ ወይም ቢበድሉ በወንጀል አይጠየቁም።የሰው ልጅ ግን ላጠፋው ጥፋትና በደል ተጠያቂ ይሆናል። ወርቃዊ ክፍሉ ደግሞ ስልጣን ወይም አለቅነት የሰው ልጆችን ሊጎዳ የሚችል ስለሆነ ከአለቅነት ይልቅ አገልጋይ ሰራተኛ መሆን እንደሚበልጥ የሚገልጽ ነው። ሰው አለቃ ሲሆን ስልጣኑን ለማጽናትና ለመጠበቅ ሲል በሱ ተቃራኒ የቆሙትንና በሀሳብም ሆነ በግብር የማይመስሉትን ለማስወገድ ይጥራል። በዚህ የተነሳም በደልን ይፈጽማል። "ሹመት ሺሞት" እንዲሉ ሹመት ሲያገኝና አለቃ ሲሆን በበደል ላይ በደልን እየጨመረ በህሊናው የሞተ ይሆናል። በሌላ መልኩም የሰው ልጅን በእኩል ማስደሰትና ሀሳቡን መፈጸም አዳጋች በመሆኑ አለቃ ሁኖ በሚመራበትና በሚያስተዳድርበት ቦታ ላይ ያሉ ሰዎች ጋር መቀያየም ይፈጠራል። ከዚህም በተጨማሪ ሀላፊነት በአግባቡ ካልሰሩበት እዳ በመሆኑ ጥንቃቄና ታማኝነትን የሚጠይቅ ትልቅ ተግባር ነው። ሰዎች ግን ብዙ ጊዜ አለቅነትን ይመኛሉ በተለያየ መንገድም የተመኙትን ስልጣንና ወንበርም ሲያገኙ "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል"የሚለውን ብሂል ተግባራዊ ለማድረግ ይሯሯጣሉ። በቀደመው ዘመን በተለይም በቤተክርስትያን አካባቢ ለአለቅነት ሲፈለጉ ጥለው ይሸሹ ነበር። በአሁኑ ሰዓት ግን በቤተ ክህነትም ይሁን በቤተ መንግስት አለቃ ለመሆን ስልጣን ለመያዝ እና በያዙት ስልጣን ሌሎችን ለመቅጣት፤ የኔ የሚሉትን ለመጥቀምና እራሳቸውን ለማገልገል የማያደርጉት ጥረት የለም። ሥልጣን ለማግኘት ሲሉም የሰው ልጅን ህይወት የሚቀጥፉም አሉ። ይህ ሁሉ ግን እራስ ወዳድነትና ስግብግብነት እንጂ ለሀገርና ለወግን የሚጠቅም ተግባርን ለመፈጸም አይደለም።

ሰው ለከት የሌለውን ፍላጎቱን ለማሟላት፣ ዕውቅና ለማግኘትና ሰዎችን ለመበቀል ሲል አለቅነትን ይሻል። ነገር ግን ከባለስልጣን ይልቅ አገልጋይ ወይም ሰራተኛ የሆነው ሰው በዕውቀቱ፣ በጥበቡ፣ በሙያው እና ባለው አቅም ሁሉ ለማህበረሰብም ሆነ ለሀገር ታላላቅ ተግባራትን መፈጸም ይችላል። ባለቅኔዋም "በደል ሴትዮን በቁሚ ለመቅበር" በሚለው ስንኝ ከጥፋት ለመራቅና፤ ሰውን ላለማስቀየም፤ መልካም ስራን ለመስራት፤ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚጠቅም ተግባርን ለመፈጸም፤ ከህሊና ባርነት ነፃ ለመሆን ከአለቅነት ይልቅ አገልጋይ መሆን፤ ሰራተኛ መሆን፤ በተማሩት ትምህርትና ዕውቀት ሀገርና ወገንን ማገልገል እንደሚበልጥ አመስጥረው ገልጸዋል።

**ቅኔ ፫ ዘይእዜ**

ዘመደ ከበሮ ኢትሑር ኀበ ከበሮ ባህታዊ።
አመ ቦአ ወአመአተወ ወርሀ ፆም ማህየዊ።
እስመ ኢይትናገር ህቅ ለሊሁ ምስሌሁምስለ መኑመ ዜናዊ[4]።

**ትርጉም፦** የከበሮ ዘመድ አትሁን(ዝም አትበል አውራ) ፆም ሲገባ ከበሮ
ስለማይመታ ዝም ይላል እንደባህታዊ ይመንናል።
የፆም ወር ገብቷል ወይም ፆም ተጀምሯልና።
ከበሮ ፈጽሞ ዝም ሊል ነው።

ሰው ምግብ ሲያንቀው ህቅ እንደሚል ከበሮም ዝምታ ህቅ አደረገው ፆም ነውና። የቅኔው ወርቃዊ ሀሳብ በኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ስርዓት ዓብይ ፆም ተብሎ በሚታወቀው የፆም ወራት ከበሮ አይመታም። በአቢይ ፆም ወራት ሰውን ወደፈጣሪ የሚያቀርቡ ከስጋዊ ሀሳብ ይልቅ ወደመንፈሳዊው ዓለም የሚስቡ የበገና ዝማሬዎች ይዘመራሉ። በፆም ወራት ከበሮ ጭብጨባ እና እልልታ አይኖርም ። ባህታዊ ይህን ዓለም ትቶ እንደሚመንን ከበሮም በፆም ወራት ከአገልግሎት ይታቀባል። ወደ ሠማዊው ትርጉም ስንሄድ አንዳንድ ሰው በሁሉም ጉዳይ ላይ ዝምታን ይመርጣል። ሀሳቡን ከመግለጽ፣ተናግሮ ከማሳመን ተከራክሮ ከመርታት ይልቅ አንደበቱን ቆልፎ ይቀመጣል። ሰው ካልተናገረ ማንነቱ ፣እውቀቱ፣ በውስጡ ያለው ሀሳብ በግልጽ ሊታወቅ አይችልም። ከዚህም ሌላ  የሰው ልጅ ከሌሎቹ ፍጥረታት ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች ቀዳሚው በቋንቋ አማካኝነት መናገር መቻሉ ነው። ነገር ግን  ሰዎች በተፈጥሯቸው አልያም በሁኔታዎች ዝምተኛ  ይሆናሉ። ይህም በተለያየ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ከነዚህም ውስጥ ነገሬ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል፣ "ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባም" እንደሚባለው ከንግግር በኃላ ሊመጣ የሚችልን ቅጣትና ውግዘት በማሰብ እንዲሁም የንግግር ልምድ ያለመኖር ሰዎችን በዝምታ እንዲሸበቡ ሊያደርግ ይችላል።ይህ የንግግር ልምድ ያለመኖር የሚመጣው ብዙውን ጊዜ ከቤተሰብ አስተዳደግ ጋር ተያይዞ ነው። ምክንያቱም በቤተሰብ ውስጥ ልጆች እንዲያወሩ አይፈቀድላቸውም። እንዲያውም ሊያወሩ ሲሞክሩ እንደልጅነታችሁ ቀስ ብላችሁ እደጉ በሚል ያሸማቅቋቸዋል። የንግር ልምዳቸውንም እንዳያዳብሩ ያደርጓቸዋል። ይህ ደግሞ በወደፊቱ ህይወታቸው ላይ ሀሳብን የመግለጽ ችግር እንዲገጥማቸው በሰው ፊት ሀሳባቸውን እንዳይገልጹ ያደርጋል።

[4]የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

"ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል" እንዲሉ ሰው ካልተናገረ የሚፈልገውን ማግኘት ስለማይችል በመናገርና ለሰዎች ሀሳባቸውን በማስረዳት የሚፈልጉትን ነገር በቀላሉ ለማግኘትና ከሰዎች ጋር ለመግባባት ይቸገራሉ፡፡ ሀሳቡን በውስጡ አምቆ ለሱ የሚገባውን ሌሎች ንግግር አዋቂዎች ሊወስዱበት ይችላሉ፡፡ ሰው ካልተናገረ ከሌሎች ሰዎች ጋር መግባባት ይሳነዋል፡፡ አለፍ ሲልም እገሌኮ ዝጋታም ነው በማለት ከማህበረሰብ ጋር ጠንካራ መስተጋብር እንዳይፈጥር ያደርገዋል፡፡ ባለቅኔዋም በዝምታ የተዋጠውን ሰው ምን እንደከበሮ ዝም ትላለህ ተናገር ሀሳብህን ግለጥ ሲሉ "የከበሮ ዘመድ አትሁን(ዝም አትበል አውራ) ከበሮ የጾም ወራት ገብቶ ከአገልግሎቱ ካልታቀበ በስተቀር ዝም እንደማይል የሰው ልጅም በቋንቋ የመናገር ጸጋ የተሰጠው ከመሰሎቹ የሰው ልጆች ጋር እንዲግባባ መናገር ባለበት ሰዓትና ጉዳይ ላይ እንዲናገር በመሆኑ ማህበራዊ ኑሮን ለመኖር መናገር የግድ ያስፈልግሃልና መናገር አለብህ በማለት ይገልጻሉ፡፡ ማህበረሰቡም "ዝምታ ለበግም አልበጃት" በማለት ዝም ያለ ሰው እንደሚጎዳና የፈለገውን እንደማያገኝ ንግግርም ለሰው ልጆች አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

### 4.1.2 ስለስንፍና

**ቅኔ፩ ዋዜማ**

ሶበበዝኑ ወፈድፈዱ ፈፀምተ ፈቃዱ ሀካይ ዘገብረ ሀካይ ዘመነ፡፡
ተመነየ ፈጣሬ እሙንቱ ዘውገ ያሬድ ደይነ፡፡
ጎልያድ ፈርዖን መምለኬ እሙንቱ ዘኮነ፡፡
እሙንቱ ይረዱ ዘአስተአየነ፡፡
ግብረ ቆሬ ላዕላዌ ካህነ[5]፡፡

**ትርጉም፦** የገብረሀካይ ዘመን በዚያ ጊዜ የሀካይ ፈቃድ ክፋትን የሚፈጽሙ ፈጽመው በበዙ ጊዜ፤
የክፉዎች ፈጣሪ በፈታሪ ዘንድ የያሬድ አመስጋኝ ወገን ገብር ሀካይ የጎልያድና የፈርኦን ደይንን ተመኘ፡፡
የጸና የሆነ የእነሱ መመለኪያ ወርቅ አነሱ ከአገልጋይ ላዕላዌ ክርስቶስ ተለይተው የቆሬ ስራን የገመገመበት ወደ እዚያ እነሱ ይወርዱ ዘንድ የዘመዶቹ ጎልያድ እና ፈርኦን ግምጋሜ ቅጣትን ተመኘ፡፡

[5]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

የቅኔው ወርቃዊ ሀሳብ በተሰጠው መክሊት ስላልተጠቀመው ሰነፍ አገልጋይ የሚገልጽ ነው፡፡ በቅኔው ውስጥ ጎልያድና ፈርዖን በንጽጽር የመጡ ሲሆን ጎልያድና ፈርዖን የተሰጣቸው ስልጣን፣ሀብትና ጉልበት በመልካም ሳይጠቀሙበት በመቅረታቸው መጨረሻቸው ውድቀትና ጥፋት እንደሆነው ሁሉ ገብረ ሀካይም በተሰጠውን መክሊት ባለመጠቀሙና ጌታውን በመወንጀሉ ምክንያት ፈርዖንና ጎልያድ ላይ የደረሰው ቅጣት አግኝቶታል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ሃያ አምስት ላይ እንደተገለጸው ሦስት አገልጋዮች የነበሩት አንድ ባለጸጋ ለሦስቱም አገልጋዮቹ ለአንዱ አምስት ለአንዱ ሁለት ለሦስተኛውም ገብረ ሀካይ ለተባለው አገልጋዩም አንድ ሰጥቶ ሁሉንም ነግዳችሁ አትርፉችሁ ቆዩኝ በማለት ወደ ሩቅ ሀገር ይሄዳል፡፡ እነዚህ አገልጋዮችም ከገብረ ሀካይ በስተቀር በተሰጡት ልክ ወተውና ወርደው በመስራት አትርፈው ጌታቸው መጥቶ ሲጠይቃቸው በታማኝነት ቀረቡ፡፡ ከጌታቸው የተቀበሉትምን አስረክበው ለሽልማት በቁ፡፡ ይህ ገብረ ሃካይ የተባለ ሰነፍ አገልጋይ ግን ነግዶ እንዲያተርፍ የተሰጠውን ገንዘብ መሬት ውስጥ ቀብሮ በማቆየት ጌታው መጥቶ ሲጠይቀው አንተ ያልዘራኸውን የምታጭድ ያልደከምክበትን የምትሰበስብ ክፉ መሆንህን ስላወኩ ይኸው ገንዘብህን ቀብሬ ቆይቼ አሁን አወጣሁት በማለት ያችን የተቀበላትን ገንዘብ ሳያተርፍ ለጌታው አቆየ፡፡ በገብረ ሀካይ ተግባርና ንግግር የተበሳጨው ባለፀጋም መከራ ወዳለበት ጉድጓድ እንዲጥሉት አሽከሮቹን አዘዘ፡፡ ወደ ሠማዊው ጉዳይ ስንሄድ ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ሰነፍ የሚባሉ ሰዎች አሉ፡፡ እንደማንኛውም ሰው በተፈጥሮ፣በልምድና በትምህርት ያገኙትን እውቀት ወይም ሙያ ተጠቅመው ከራሳቸው አልፈው ለሀገርና ለወገን መትረፍ ከፍ ሲልም ክብርና ሽልማት ማግኘት ሲችሉ እውቀትና ችሎታቸውን በውስጣቸው ይዘው ምንም ተግባር ሳይፈጽሙ ይኖራሉ፡፡

ሰነፍ ሰው ማህበረሰቡም ይነቅፈዋል፡፡ ሰው ለመኖር ፍላጎቱን ለማሟላት ፣የተሻለ ነገር ለማግኘት ባለው አቅምና ዕውቀት ተጠቅሞ ስራን ይሰራል ይህ ካልሆነ ግን በስንፍናው ምክንያት ከሰው በታች ሆኖ ለመኖር በራሱ ይፈርዳል፡፡ አንዳንድ ሰው ባለኝና በተሰጠኝ ነገር ሰርቼ ልጠቀም ሀገርና ወገኔን ልርዳ ከማለት ይልቅ እኔ ይህን አልሰራም ይህን አልችልም በማለት የተሰጠውን እውቀትና ችሎታ ሳይጠቀምበት ትኩስ ሀይሉና ጥሬ ጉልበቱ እንዲሁ አባክኖ ይቀራል፡፡ እኩዮቹ ወጥተው ወርደው ባገኙት ነገር ለራሳቸው ሲደሰቱ በሰዎች ዘንድም ከበሬታ ሲቸሩ ሰነፉ ሰው ግን የሰው እጅ ተመልካች በሰው ጀርባ ተንጠልጥሎ የሚኖር ይሆናል፡፡ በሰዎች ዘንድም የተጠላና የተነቀፈ ይሆናል፡፡ የሰው ልጅ ልዩ ልዩ ስጦታ ያለው

ሲሆን ትጉ የሆነው የተሰጠውንና ችሎታውን ተገንዝቦ በተግባር በማዋል ሲጠቀም ሰነፉ ደግሞ የተሰጠውን ችሎታና አቅም በመቅበር ባለው ነገር ሳይሰራ ባክኖ ይቀራል፡፡ ባለቅኔዋም ማህበረሰቡ ለሰራተኛ ሰው ያለውን ክብርና ለሰነፍ ሰው ያለውን አሉታዊ የሆነ አመለካከት እና በስንፍናው የሚያገኘውን ውርደትና መከራ እንዲሁም የሰው ልጅ ባለው ችሎታና አቅም መስራት እና ማትረፍ እንዳለበት ይናገራሉ፡፡

### 4.1.3 ስለሰው ልጅ ከዳተኝነት

**ቅኔ ፩ መወድስ**

*ለመኑ ሀለየ እግዜአብሔር ተድላ ዓለማት ዓለመ እምድኅረ ፈጠረ ለነ፡፡*

*አኮኑ ህድግዎ ወመንንዎ ይብለነ፡፡*

*ወቦኑ ለእንስሳት ዘከረ ለሊሁ ወሀለየብነ፡፡*

*ቅድመ ኢሳይያስ ነቢይነ ውስተ አዕምሮ አማን አምጣነ እንስሳት ይሄይሱነ፡፡*

*ዓለምሂ ለእመ ተርፈ ኢያህዝነነ ፍጡነ፡፡*

*አምጣነ ሀሳር ወቅጥቃጤ ፍኖተ ሰናክሬም ዓለምነ፡፡*

*ወመፍትው እግዚእ ዓለመ ( ከመ ያድህነነ) ለነ፡፡*

*አምጣነ ለሊሁ መቅድመ ኩሉ ዓለምነ ወርስትነ*[6]*፡፡*

**ትርጉም፦** እግዚአብሔር የዓለምን ደስታ ለማን አሰበ?

የዓለምን ደስታ ለእኛ ከፈጠረ በኋላ ተውትና ናቁት ይለናልና፤

በውኑ ለእንስሳቶች አስታወሰና አሰበን፤

በነቢያችን በኢሳይያስ ፊት በእውነተኛ ዕውቀት እንስሳቶች ይበልጡናልእና ዓለምም ቢቀርአያሳዝነንም፤

የሰናክሬም መንገድ (ዓለማችን) ሀሳር ስቃይ ነውና፤

ጌታም ዓለምን ያስተወን ዘንድ ተገቢ ነውና፤

ከሁሉ በፊት እርሱ ዓለማችን እና ርስታችን ነውና፡፡

የቅኔው ወርቃዊ ጉዳይ አምላክ የሰውን ልጅ ከምድር ፍጥረታት ሁሉ አልቆና አክብሮ ቢፈጥረውም የሰው ልጅ ግን ውለታውን እንደረሳና ፈጣሪውን እንዳሳዘነ የሚገልጽ ነው፡፡የሰው ልጅ ከመፈጠሩ በፊት የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ ከፈጠረ በኋላ ነው ሰውን የፈጠረው፡፡ ወደ ምድር ከመጣም በኋላ በምድር ላይ ባሉ ፍጥረታት ላይ ስልጣን ተሰጥቶት ነበር በዳዊት

---

[6] የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

መዝሙር  አርባ ስምንት ከቁጥር አስራ ሁለት ላይ እንደተገለጸው"ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አላወቀም ልብ እንደሌላቸው እንስሶችም ሆነ መሰላቸውም" ከክብሩ በመውረድ እንስሳዊ ባህሪን እየተላበሰ የማይገባውን ተግባር በመፈጸም ባለውለታውን ፈጣሪ አሳዘነ። የሰው ልጅ ከክብሩ ማነስና አምላኩን እረስቶ ወደ ኀጢያት በመጓዙ ምክንያት ፍጹም የሆነው ፈጣሪ ሰውን በመፍጠሬ ተጸጸትኩ እስከማለት አድርሶታል።

ወደሠማዊ ሀሳቡ ስናመራ በሠሙ የተነገረው የማህበረሰቡ ጉዳይ ነው። በማህበረሰቡ ኑሮ ውስጥ ሕይወትን ለመምራት የሚያስፈልጉ ጉዳዮች አሉ። እነዚህን ነገሮች ሁሉም ሰው ሁሉንም ሊያሟላ አይችልም አንዱን ሲያሟላ ሌላው ይጎድልበታል በመሆኑም የሌለውን ካለው ተውሶ እያሟላ ኑሮውን ይቀጥላል። ስለዚህ የጎደለንን ከጎረቤትም ሆነ ከዘመድና ጓደኛ ለማግኘት ጠባይን ማሳመርና የተዋለልንን ውለታ ማሰብ ግድ ይላል።

ሰው በዚች ምድር ላይ ሲኖር በሁሉ ሙሉ ሊሆን አይችልምና የሌሎች ሰዎች ድጋፍና እርዳታ ስለሚያስፈልገው በአንድ ወቅት የተዋለለትን ውለታ አስታውሶ መመለስና መልካም ማድረግ ሲገባው በተቃራኒው ሆኖ ይገኛል ለዚህም ነው ማህበረሰቡ " ሰውን ያመነ ጉም የዘገነ፣ ሰው ማመን ቀብሮ ነው" እያለ የሰውን ልጅ ከዳተኝነትና አይጨበጤነት የሚገልጸው። ውለታን የማያስብ ሰው የመረዳዳት መንፈስን ስለሚጎዳ ከሌሎች ጋር ያለው የግንኙነት መስመሩ የሻከረ ይሆናል። ማኅበራዊ መስተጋብሩም የላላ ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ ማኅበራዊ ፍጡር ነውና ለመኖር የግድ ሌሎች ስለሚያስፈልጉት የተዋለለትን ውለታ ሳይረሳ በተቻለው አቅም ውለታውን እያሰበ መኖር ይጠበቅበታል። ባለቅኔዋም የሰው ልጅ የተደረገለትን ነገር የተዋለለትን ውለታ የሚረሳ መሆኑን አምላክ እንደሰው ልጅ ያከበረው አልነበረም ሰው ግን ውለታውን ይረሳል በማለት የውን ልጅ ከዳተኝነ በማሳየት ተቀኝተዋል።

### 4.1.4 ስለቅጣት

**ቅኔ ፩ ሚበዝኁ**

ምስጢረ ሥላሴ ወላድ እምዘጉባኤኪ ጠፍአ ቃለዚአኪ ሰማዒ።
ኢሰማዔ ቃልኪ ለኪ ዘፍትሐአሮን ቅጽኢ።
ውእቱ ልሙደ ዘንተ አምጣነ ኢይትኤዘዝ ድኅረ ነጋሜ አዕምሮ ገዛኢ[7]።

**ትርጉም፦** የሥላሴ ወላድ ምስጢር ሆይ ያንቺን ቃል የሚሰማሽ ከጠፋ፤
ያንቺን ቃል የማይሰማውን በአሮን ፍርድ ቅጭ፤

[7] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

የገኸ ዕወቀት ነጋሽ ከዚህ በኋላ አይታዘዝምና እሱ ያንን ለምዶ

አይታዘዝምና።

የቅኔው ወርቃዊ ጉዳይ  እውቀት እና ምስጢር የሚራቀቀው በጉባኤ ቤት ነው። ከጉባኤ ውጪ እውቀት ወይም ምስጢር አይገኝም የሚል ነው። ሠሙ ሰው ከስህተቱ ይመለስ ዘንድ የጥፋት ተግባሩን እንዲተው ከጅምሩ መገሰጽ እንደሚገባው የሚገልጽ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ልጆቻቸውን አብዝተው ከመውደዳቸው የተነሳ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ የሚፈጽሟቸውን መልካምም ይሁን መጥፎ ተግባራት እሰይ አበጀህ በማለት ያሳድጋሉ። ልጆቹም መሆን የሚገባቸውን ሳይሆን በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰብ ዘንድ የሚያስነቅፍ ሰብዕናን እያዳበሩ ይሄዳሉ። ምክንያቱም ከህጻንነታቸው አልተቀጡምና ከጥፋት ስራችሁ ተመለሱ ቢባሉ የሰውን ሃሳብ የሚቀበሉ እና የሚመለሱ አይሆኑም። "እናቴ የእንቁላሌ ጊዜ በቀጣሽኝ ኖሮ" እንዳለው ሁሉ ገና በትንሹ መመለስ ካልቻልን ትላልቅ ጥፋቶች ሲፈጸሙና አልታዘዝም ባይነት ሲመጣ ለመመለስ አስቸጋሪ ይሆናል። በማህበረሰብም ሆነ በሀገር ደረጃ በደል የሚፈጽሙ አካላት ገና ከጅምሩ ከዕኩይ ምግባራቸው እንዲመለሱ ቢቀጡ እና ቢገሰጹ ከፍ ወዳለው ጥፋት አይሸጋገሩም። ነገር ግን ከጅምሩ የሚሰራውን ስህተት እየታየና እየተሰማ ዝም ከተባለ በኋላ ለመመለስ ከባድ ይሆናል። ስለዚህ አንድ ልጅ ሲያጠፋ ከመነሻው መቀጣት አለበት ምክንያቱም የሰራው ስራ የማይገባ መሆኑን እንዲያውቅ ያደርገዋል። ሲያድግም በተሰማራበት ስራ ሁሉ ታማኝና ሙያውን አክባሪ በመሆን ያደገበትን ቤተሰብና ማህበረሰብ ያስመሰግናል። በተቃራኒው ሆኖ እንደጠማማ ዛፍ ተጣሞ ካደገ በኃላ ላስተካክልህ ቢሉት ስለማይመለስ "አሳዳጊ የበደለው" እየተባለ ቤተሰቡን ሲያስወቅስ ይኖራል።

ቅጣት አንድ አካል ላጠፋው ጥፋት ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እና በአግባቡ የሚሰጥ መሆን አለበት ይህ ካልሆነም ግን የራሱ የሆነ ደካማነት አለው ።ይኸውም በውሃ ቀጠነ የሚቀጣውም እንዲሁ እያጠፋ እንደሚታለፈው የሰብዕና መጓደልን ያስከትላል። ምክንያቱም ይህ በትንሹም በትልቁም የሚቀጣው ልጅ የሚያዳብረው ሰብዕና ፈሪ፤ ሁልጊዜም የጥፋተኝነት ስሜት የሚሰማው ይሆናል። ስለዚህ አንድ ህጻንም ሆነ ተማሪ የተጣመመ ማንነትን እንዳያዳብር ሳይበዛም በተቃራኒው ደግሞ ልቅም ሳይሆን  በአግባቡ መቀጣት አለበት። ባለቅኔዋም በጉባኤ ቤት ውስጥ ለመምህሩ የማይታዘዘውንና በትዕቢት የተወጠረውን ተማሪ በማንሳት "የገኸ ዕወቀት ነጋሽ ከዚህ በኃላ አይታዘዝምና እሱ ያንን ለምዶ አይታዘዝምና። "በሚለው ስንኝ በጊዜ ካልተቀጣና ካልታረመ በኃላ ለመመለስ አስቸጋሪ እንደሚሆን ይገልጻሉ። አሁን አሁን ቅጣት

እየቀረ የመጣ ይመስላል:: ቤተሰብም ሆነ መምህራን ልጆችን መቅጣት ሲያስነቅፋቸው ይታያል:: ነገር ግን በተለይ ልጆች በፈጸሙት ጥፋት መጠነኛ ቅጣት ሊቀጡ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም በወቅቱ ካልተቆነጠጡ ልጆቹ እያደጉ በመጡ ቁጥር በቀላሉ የማይገሩ ፤እናት አባትን የሚሳደቡ፤ መምህሮቻቸውን የሚያንጓጥጡ፤ ታላላቆቻቸውን የማያከብሩ ከፍ ሲሉም ሀገርንና ወገንን የሚበድሉ ይሆናሉ::

### 4.1.5 ስለእድሜ

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

እዝራ ወሔኖክ ለመልከ ጼዴቅ አብትሩ::
በደኃራዊት ዘመን ዘኢነጸሩ ነጸሩ[8]::

**ትርጉም፦** የመልከ ጼዴቅ ወገኖች የሆኑ ዕዝራና ሄኖክ ሰዎች፤
በመጨረሻው (በኋለኛው ዘመን) ዘመን አይተውት የማያውቁትን አዩ
መቆየት ደህና ነውና::

የቅኔው ወርቃዊ ሀሳብ ዕዝራና ሄኖክ አሁን በሕይወተ ሥጋ ተሰውረው ቢኖሩም በኋላ ዘመን ማለትም በዓለም ፍጻሜ ወደ ምድር መጥተው ያላዩትን ሞት እንደሚያዩ እና መከራን እንደሚቀበሉ የሚገልጽ ነው:: አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ የሚለው አምላካዊ ቃል ይፈጸም ዘንድ የሰው ልጅ ትንሽም ሆነ ትልቅ ሁሉም በሞት ምክንያት ወደ አፈር ይገባል:: እዝራና ሔኖክ እንዲሁም ሌሎችም ቅዱሳን ከቅድስናቸውና ካላቸው የመንፈሳዊ ህይወት ደረጃ አንጻር ሞትን ሳያዩ በብሔረ ህያዋን ተሰውረዋል:: የአምላክ ቃል የማይሻርና የማይለወጥ በመሆኑ እነዚህ በህይወተ ሥጋ የሚኖሩ ቅዱሳን በኋለኛው ዘመን ወደ ምድር መጥተው ሞትን ይቀበላሉ:: ባለቅኔዋም እነዚህ ቅዱሳን አይተውት የማያውቁትን ሞት እንደሚያዩ ሞትን እንደማንኛውም የሰው ልጅ እንደሚቀምሱ በቅኔያቸው አመስጥረው ተናግረዋል::
ወደ ሠማዊ ትርጉሙ ስንመለስ እድሜ ያገኘ ሰው ብዙ ያያል የሚል ነው:: በማህበረሰቡ ውስጥ ወጣት ሲሞት ገና ምንም ሳያይ ተቀጠፈ ይባላል:: በተቃራኒው ደግሞ እድሜ ባይጠገብም እረጅም ዘመን ኖሮ እድሜውን ጠግቦ የሞተ እንደሆነ እሱኮ ብዙ አይቷል ይባላል:: "እድሜ መስታወት ነው ሁሉን ያሳያል" እንዲሉ እድሜ አግኝቶ የቆየ ሰው ያላየውን ያያል፤ ያልሰማውን ይሰማል:: ቀዳሚው ምርቃትም እኮ እድሜ ይስጥህ ነው:: ሄኖክና እዝራ በመጨረሻው ዘመን የሰው ሁሉ እጣ የሆነውን እና እነሱ ያላዩትን ሞት እንደሚያዩ ሁሉ የቆየ

[8]የአማሆይ ኀሪት ቅኔ

ሰውም  በዚህ ዓለም ላይ የሚፈጸሙ ሁነቶችን ለማየት እና ለማከናወን ይችላል። ወጣቱ ትዳር ይዞ ለመውለድ፣ የወለደውን ለማሳደግ፣ ልጆቹን ለቁም ነገር ለማድረስ በምድር ላይ የሚፈጸሙ ተግባራትን ለማከናወን መቆየት እድሜ ማግኘትን ይጠይቃል። "ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ"የሚባለውም እኮ እድሜ ሰጥቶት ሁሉን ለማየት የበቃ ሰው ነው እንዲህ ነው እያለ መናገር የሚችለው በስማ በለው ሳይሆን በጊዜና በቦታ ተገኝቶ ማየት ስለሚገባ ነው። የሰው ልጅ በህይወት ለመቆየት፤ መጪውን ለማየት፤ በልቡ የሰነቀውን ተስፋ ለማሳካት እድሜን አብዝቶ ይፈልጋል ይመኛታልም። በመሆኑም ለዕድሜው መቆየት ስለሚጓጓ ህመም በተሰማው ቁጥር ሀኪም ቤት ይሄዳል፤ እንደየ እምነቱ ያድነኛል ይፈውሰኛል ብሎ ያመነበትን ሁሉ ያደርጋል። ይህ እንግዲ የሰው ልጅ ለመኖር በምድርም ላይ ቆይቶ ሁሉን ለማየት ስለሚጓጓ ነው። ባለቅኔዋም መቆየት መልካም ነው ሁሉን ያሳያል ሲሉ ተቀኝተዋል።

### 4.1.6 ስለዕውቀት

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

ጉባኤ ቃና ባዕል ከመ አብርሃም ከዋኒ።
አልበሰኒ ልብሰ አእምሮ እንተለኩሉ ይሤኒ[9]።

**ትርጉም፦** እንደ አብርሃም ሃብታም (ደግ) የሆነ ጉባኤ ቃና፤
ለሁሉ የሚያምር የሆነ እውቀት ልብስን አለበሰኝ።

የቅኔው ወርቃዊ ጉዳይ እውቀት ነው። አእምሮ እውቀት ማለት ነው። አእመረ አወቀ ከሚለው ግስ የወጣ ነው። እውቀት የሰው ልጆችን ያስከብራል፣ ያስመሰግናል፣ ሹመትና ሽልማትን ያሰጣል። የሰው ልጅ ከአካባቢው እና ከማህበረሰቡ እንዲሁም በተለያዩ የትምህርት ተቋማት ገብቶ በተወሰነ የሙያ መስክ ላይ በመማርና በማወቅ ለራሱም ኾነ ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ሲያከናውን እውቀት አለው አዋቂ ነው ይባላል። እውቀት ያለው ሰው ተናግሮ ማሳመን ተከራክሮ መርታት ይችላል። በዚህ ቅኔ ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናውቀው አብርሃምና ጉባኤ ቃና ተመሳስለው ቀርበዋል። ሰሙ አብርሃም ባዕል ነው። በደግነቱ የሚታወቀው አብርሃም ቤቱን ከመንገድ ዳር በመቀለስ የወጣ የወረደውን ሁሉ እየተቀበለ ቤት ለእንግዳ ብሎ የሚያስተናግድ ሰው ነው። አብርሃም ከደግነቱ እና እንግዳ አብዝቶ በመቀበሉ ምክንያት አምላክን በሰው አምሳል ለማስተናገድ የበቃ ነው። የሰው ልጅ ደግነት ሲነሳም አብርሃም ቀድሞ ይጠራል። "እንደ አብርሃም ሃብታም (ደግ) የሆነ ጉባኤ ቃና"። የሚለው ስንኝ እንግዲህ

[9] የእማሆይ ኀሪት ቅኔ

አብርሃም ወደቤቱ የመጣውን ሁሉ ያለልዩነት ተቀብሎ አብልቶና አጠጥቶ እንደሚመልሰው ሁሉ ጉባኤ ቃና ለፈለጋት ወደ መገኛዋ ወይም ወደ ቤቷ ለመጣ ሁሉ ትንሽ ትልቅ ሳትል ማእዷን ዕውቀትን ዘርግታ ያለስስት ብሉልኝ ጠጡልኝ በማለት የሰውን ልጅ በጥበብ ታረካለች፡፡ ጉባዔ ቃና (እውቀት) ለፈለጋት ሁሉ ደግ ናት፡፡ ትገኛለችና በማለት ባለቅኔዋ ጉባዔ ቃናን የፈለጋት ያገኛታል ድንቁርናን አስወግዳ ጥበብን ታላብሰዋልች በማለት ገልጸዋል፡፡

ወደ ሠሙ ትርጓሜ ስንመጣ እንደ አብርሃም የተባለ ባለጸጋ ሰው ነው፡፡ ባለጸጋ ሰው ነዳያንን እንዳይበርዳቸው ልብስ መደረቡን ማልበሱን መናገር ነው፡፡ ባለጸጋ በሃይማኖታዊም ሆነ በሰብዓዊ ዕሳቤ አማካኝነት ካለው ላይ አካፍሎ ለታረዙት ያለብሳል፡፡ ሃይማኖተኛው ብታረዝ አልብሰሽኛል የሚለውን የአምላክ ጥያቄ ለመመለስና የጽድቅ ስራ ለመስራት የታረዙትን ያለብሳል፡፡ ሰብዓዊያን ከሆነ ደግሞ ከሞት በኂላ ያለውን ጽድቅ በማስብ ሳይሆን እንዲሁ የህሊና ዕርካታ ለማግኘት ሲል ነዳያንን ያለብሳል፡፡ በዘመናችንም ሁለቱንም አካላት እናገኛለን፡፡

### 4.1.7 ስለሚዜ ክቡርነት

**ቅኔ፩ ጎንጄሃ**

አሚነ ወክህደተ ለኒቆዲሞስ ገዛእቶ፡፡
ኒቆዲሞስ ነጋሜ ጥበቡ አኅደሮሙ ቤቶ[10]፡፡

**ትርጉም፦** የኒቆዲሞስ ሚዜዎች አሜን እና ክህደትን፤
በጥበቡ የነገሠ ኒቆዲሞስ ከቤቱ አሳደራቸው፡፡

ወርቁ ኒቆዲሞስ ክህደትና ሃይማኖትን በአንድነት እንደያዘ የሚያሳይ ነው፡፡ ታሪኩን በመጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ሦስት ላይ ተገልጾ እንደምናገኘው ኒቆዲሞስ የአይሁድ አለቃና የኦሪት አዋቂ ሲሆን አይሁዳዊያን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመወንጀል በሚመክሩበት ጊዜ ቀን ቀን ከነሱ ጋር ይመክራል፤ እንዴት የአይሁድ አለቃ የኦሪት ምሁር ሆኖ ከክርስቶስ ይማራል መባልን በመፍራት ትምህርቱም እንዳይቀርበት በመፈለግ ሌሊት ሌሊት ከክርስቶስ እግር ስር ቁጭ ብሎ ሲማር ያድራል፡፡ እነዚህ ሁለት የተቃረኑ ተግባሮች በኒቆዲሞስ ይከናወናሉ በማለት ያስረዳል፡፡ ሰሙ ደግሞ የማህበረሰቡን ሚዜ አክባሪነት ያሳያል፡፡ በኢትዮጵያ ባህል ሚዜ ክቡር ነው፡፡ሚዜ የሙሽራው የቅርብና የልብ ጓደኛ ሲሆን በሙሽራውና በቤተሰቦቹ ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ሰው ነው፡፡ ሚዜ ሲመረጥም እንዲሁ የተገኘው ሰው ሁሉ ሳይሆን የሙሽራውን ጉድለት የሚሞላ፤ከሰርጉ ጅማሬ እስከ ፍጻሜ ድረስ ከፊት የሚቆም፤

[10] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

ሙሽራው የሰርጉ ዕለት አምሮ እንዲታይ የሚያደርግ ነው፡፡ የሙሽራው ቤተሰብም በሰርጉ ወቅት ከሚቀርበው ድግስ ጀምሮ የተለየ መስተንግዶ ይደረግለታል፡፡ ሚዜ ሰርጉ ከመድረሱ በፊት ጀምሮ ስለሰርጉ ጉዳይ ከሙሽራው እኩል ደፋ ቀና ሲል ከርሞ የሰርጉ ዕለትም ከሙሽራው ጎን በመቆም ሙሽራውን አድምቆ ሰርጉን ያሳልፋል፡፡ የሰርጉ ዕለት ካለፈ በኋላም ሌላው ሰርገኛ ወደየቤቱ ሲሄድ ሚዜ ግን ከሙሽራው ጋር በደስታ ይቆያል፡፡

### 4.1.8 ስለኢትዮጵያ

**ቅኔ ፩ ሥላሴ**

ወላድ ኢትዮጵያ ፈጣሬ ጥሙቃን ወኢጥሙቃን፣ ሀላዌ መንበሩ መቅደስ
ዘርዓያዕቆብ ወጎሬ፡፡
ታበጽህ እደዊሃ ዘንስኣዝማሬ፡፡
እስከነዛቲ ትረከብ ባዕለ ብዙኂን ፈጣሬ፡፡
ሲሳየ ውሉዳ በኢስዋሬ፡፡
ወሀበ ውሉዳ ኢይምጻእ መርገመ ቆሬ፡፡
ዘአልቦቱ ዘክርስቶስ ፍሬ[11]፡፡

**ትርጉም፡-** ኢትዮጵያ እናት ጎሬ የተባለ ያዕቆብ በያዕቆብ ወገን የሰው ልጆች ዘንድ፤
በመቀመጫው ቤተመቅደስ የሚኖር የተጠመቁ ክርስትያኖችንና ያልተጠመቁ
ምስጋናን የተቀዳጁ  እጆቿን ፤
ህዝቦችን ወደ ፈጠረ አምላክ ተዘረጋለች፤
ምስጋናን የተቀዳጁ የእሷ እጆቿን ትዘረጋለች፤
ከፈጣሪ ባለጸጋ ያለመሰወር የልጆቿን ሲሳይ ምግብን ያቺ እስከምታገኝ ድረስ
የክርስቶስ ፍሬ ጽድቅ የሌለው፤
ቆሬ የቆሬ መርገም መከፋፈል ወደ ልጆቿም እንዳይደርስ እጆቿን ወደ ፈጣሪ
ትዘረጋለች፡፡

የቅኔው ወርቃዊ አመስጥሮ ባለቅኔዋ በባህር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴደራል ቤተክርስትያን መጋቢት አስራ ስድስት ቀን በ2012 ዓ.ም በቅዳሴ ሰዓት ካህናት ስለኢትዮጵያ በሚማልዱበት ጊዜ ባለቅኔዋ ስለ ኢትዮጵያ ቅጽበታዊ በሆነ መልኩ የተቀኙት  ሲሆን ቅኔውም ኢትዮጵያ የተለያዩ ሕዝቦች፣ የተለያየ መልክ፣ ባህል፣ ዕምነት፣ በርካታ ቋንቋዎች

[11] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

በአጠቃላይም ብዙ ዓይነት መገለጫ ያላቸው ህዝቦች መገኛ ናት። እነዚህ ህዝቦችም በአንዲት ኢትዮጵያ በምትባለው ቤታቸው የሚኖሩ ናቸው። ባለቅኔዋ የኢትዮጵያ የብዙ ህዝቦች እናት እንዲሁም እነዚህ ህዝቦቿ በአንድነት በፍቅር እንዲኖሩ እጆቿን ወደፈጣሪ ዘርግታ ትለምናለች የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በማምጣት ነው የገለጹት። "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዜብሔር ትዘረጋለች"(መዝሙር፣67፣31) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን በጸሎቷ ለህይማኖቱ አማኞችም ሆነ ላልሆኑት ጸሎት ታደርሳለች። "ቆሬ የቆሬ መርገም መከፋፈል ወደ ልጆቿም እንዳይደርስ እጆቿን ወደ ፈጣሪዋ ትዘረጋለች"። በሚለው የቅኔው ስንኝ መልካም ያልሆነው ክፋት፤ ፀብና መለያየት በተለይም በአሁኑ ሰዓት ያለው በብሔር መከፋፈል ተወግዶ በፍቅርና በአንድነት ጸንታ እንድትኖር ያለማቋረጥ ወደ ፈጣሪዋ የምታቀርበውን ልመና የሚገልጽ ነው

የቅኔው ሰማዊ ክፍል ደግሞ እናትን የሚመለከት ሲሆን እናት በመልክም ሆነ በባህሪ የተለያዩ ልጆችን ትወልዳለች። ልጆች ምንም ከአንድ ማህፀን ቢወለዱም በአንድ ጣራ ስር ቢያድጉም የተለያየ መልክና ባህሪ ይኖራቸዋል። እነዚህ የተለያዩ ልጆች እናታቸው ክፉ ደግ ቀይ ጥቁር፣ አጭር ረጅም ሳትል ያለልዩነት በፍቅር አሳድጋ ለቁም ነገር ታበቃለች። በኑሯቸው የተሻሉና ባለጸጎች እንዲሆኑም በመሻት ፈጣሪዋን ትማጸናለች። በቤት ውስጥ የልጆቹ አባት ቢኖርም ከልጆች ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያለው ግን ከእናት ጋር ነው። አባት በቤት ውስጥ የጎደለውን ቢሞላም ለልጆቹ መኩሪያና መመኪያ ቢሆንም የእናትን ያህል ሊሆን ግን አይችልም። እናት ለልጇ ስትል እራሷን መስዋዕት አድርጋ ታሳድጋለች ለወግ ለማዕረግ ታበቃለች ማህበረሰቡም "እናት ሳለች አጊጥ ጀንበር ሳለች እሩጥ" የሚል ብሂል አለው። እናት ማጌጫ መክበሪያ ናትና እናትህ በህይወት እያለች ተማር፣ ኑሮህን መስርት፣ ማድረግ ያለብህን ነገር አድርግ ሲል ነው።

**ቅኔ ፪ ዘአምላኪያ**

ኢትዮጵያ ጸውአት ለብእሴ ዘአሃ ዐቢይ።
ከመኢይልክፍ ቅጽረ ቤታ ጸላኢ እኩይ።
እስመ በምሴት ተርህው አናቅጸ ቤታ አባይ[12]።

**ትርጉም፦** ኢትዮጵያ ወደ ዐብይ (ዐባይ) ተጣራች፤

[12]የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

ጠላት ድንበሯን እንዳይደፍር፤

በምሽት በሮቿ (የአባይ ግድብ) ተከፍተዋልና።

የዚህ ቅኔ ወርቃዊ ጉዳይ ሀገር የተባለችው ኢትዮጵያ ዐባይን ትጣራለች። ይኸውም ጠላት ድንበሯን እንዳይደፍረው ተከብራ እንድትኖር ሲሆን በሌላ በኩል ታላቁ የአባይን ወንዝ ለሀገሩ ባዳ ሆኖ የሌሎች ሀገሮች ብቻ ሲሳይ ሆኖ እንዳይቀር ዓባይም ለኢትዮጵያውያን በረከት ይሆን ዘንድ ገድቦ ለሀገር ጥቅም ለማዋል የቀደሙት የኢትዮጵያ ነገሥታት ቢያቅዱም በተለያየ ምክንያት ሀሳባቸው ተሳክቶ በዘመናቸው አባይን ገድበው መጠቀም ባይችሉም  አኹን ባለው ትውልድ ግን ሀሳቡ ወደ ተግባር ተቀይሮ የአባይ ግድብ እየተሰራ ይገኛል። ባለቅኔዋም አባይ እስካሁን ለሀገር መዋል ሲገባው የባዕዳን ሲሳይ መሆኑንና አሁን ግን ዘግይቶ ግድቡ መጀመሩን  "በምሽት በሯ(የአባይ ግድብ) ተከፍቷል" በሚለው ስንኝ  ይጠቅሳሉ። ነገር ግን ለብቻ የመጠቀም አባዜ የተጠናወታቸው ሀገሮች ኢትዮጵያ ዓባይን ገድባ እንዳትጠቀም በተለያየ መልኩ የተጀመረው ግድብ ከፍጻሜ እንዳይደርስና የሀብቷ ተጠቃሚ እንዳትሆን በርትተው እየሰሩ ይገኛሉ።  እነዚህ የሀገር ጠላቶች ድንበር ጥሰው እንዳይገቡ ሉኣላዊነቷን እንዳይደፍሩ የተጀመረው የዓባይ ግድብም ከፍጻሜው እንዲደርስ  መንግሥት መጠበቅ አለበት። ለሀገር ክብር እና ደህንነት ዋና ተጠሪው በስልጣን መንበር ላይ ያለው መንግሥት ነውና በማለት በቅኔያቸው አመስጥረው ተናግረዋል ።

ሰማዊ ፍቺውን ስንመለከተው በኢትዮጵያ ስም የተጠራችው ሴት በምሽት በሯን ከከፈተች ጠላት መጥቶ አደጋ ያደርስባታል። ብቻዋን የምትኖር ሴት በጊዜ (በብርሃን) ወደቤቷ ገብታ በሯን ካልዘጋች ጨለማውን ተገን አድርጎ ጠላት ይመጣባታል የሚል ነው።

### 4.1.9 ስለሴትነት

## *4.1.9 1 ስለሴትነትና እናትነት*

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

ተመየጢ ሔዋን ኀበ እምኪ ገነት።

እስመፀልአተኪ ለኪ ሀማተ ሲኦል እሳት[13]።

**ትርጉም፦** ሄዋን ሙሽራ ሆይ ወደ እናትሽ ገነት ተመለሽ፤

የባለቤት ሲኦል ሀማት እሳት አንቺን ጠልታሻለችና።

[13] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

ወርቁ ረቂቅ የሆነውን የሲኦል ቅጣት የሚያሳይ ሲሆን አዳምና ሄዋን አታድርጉ የተባሉትን በማድረጋቸውና የአምላክን ሕግና ትዕዛዝ በመተላለፋቸው ምክንያት ከቀደመ መኖሪያቸው ከገነት ተባረው ወደሲኦል ተጥለዋል። በአምላክ ምህረትና በተከፈለላቸው ዋጋ ከሲኦል ዕሳት ነፃ ወጥተው ወደ ቀደመ ቦታቸው ወደ ገነት ተመልሰዋል። ሔዋንም ከሚያቃጥላት የሲኦል ዕሳት ነጻ ወጥታለች። ሰሙ ማህበራዊው ጉዳይን ማለትም በትዳር ውስጥ ያለን የአማትና ምራት ያለመስማማትን የሚያሳይ ነው። የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ከሚያልፍባቸው የህይወት ጉዞዎች ውስጥ አንዱና ትልቁ ጉዳይ ትዳር ነው። ትዳር ለአቅመ አዳም በደረሰ አንድ ወንድ እና ለአቅመ ሄዋን በደረሰች አንዲት ሴት መካከል የሚፈጸም አብሮ የመኖር ውሳኔ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ አስር ላይ እንደተገለጸው "ወንድ እናትና አባቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላታል ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ"። ለምንድን ነው (ሴቷ አባትና እናቷን ትታ ያልተባለው) ሚስቱን በማለት ትዳር ከቤተሰብ ተለይቶ በሁለቱ ተጣማሪዎች አንድ አካልነት የሚመሰረት ነው። በሚመሰረተው ትዳር ውስጥም ዋናዎቹ ባልና ሚስቱ ናቸው። ነገር ግን የሁለቱም ጥንዶች እናትና አባት እንዲሁም ዘመድ አዝማዶች ትዳራቸው ውስጥ በተለየ መልኩ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይችላል። አንዳንዱ ሙሉ ለሙሉ የባልና ሚስቱን የኑሮ ሁኔታ መቆጣጠር ያምረዋል። አዳንዱም እንዲሁ በተወሰነ መልኩ ብቻ እንደቤተሰብ ግንኙነት በማድረግ የልጆቻቸው ትዳር እንዲሞቅና እረጅም ጉዞን እንዲጓዝ በተለያየ መልኩ ድጋፍ ያደርጋል።

ባልና ሚስት ተስማምተው ቢኖሩም እንኳን ሚስትና የባል እናት ወይም አማት ብዙውን ጊዜ አይስማሙም። የአማትና ምራት ጸብ ሲከርም አማት ልጇን ሚስትህን ካልፈታህ ሞቼ እገኛለሁ እረግምሃለሁ ልትል ትችላለች። በተለይ ኑሯቸው ከባሏ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት የሚኖሩ ከሆነ ዕለት ዕለት መገናኘት ስለሚኖር ጸቡ የበለጠ የከረረ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የሚመሩት ሰላማዊ የነበረው ትዳር መረበሽ ይጀምራል አለፍ ሲልም ይፈርሳል። የአማቷ ጭቅጭቅ የሰለቻት ሚስትም ትዳሯን ትታ ወደ እናቷ ቤት ትመለሳለች። ይህ ከአማት ጋር ያለው አለመግባባት ጎልቶ የሚታየው በሴቶቹ በሚስትና በባል እናት ላይ ነው። በወንዶቹ ላይ ቢኖርም ማህበረሰቡ የሚያጎላው የሴቷን በመሆኑ "አማትና ምራት ሳይፋቀሩ ወደ መሬት" ብሎ ይናገራል። ባለቅኔዋም የሄዋንን ረቂቅ ከሆነው ከሲኦል ቅጣት ነጻ መውጣት እና ወደቀደመ ክብር መመለስን በመግለጽ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የአማትና ምራት ያለመዋደድ አለፍ ሲልም የሀገር መሰረት በሆነውን ትዳር መስለው አመስጥረው ገልጸዋል።

**ቅኔ ፪ ሚበዝሁ**

እሙ ለቂርቆስ አንጌቤናዊት ፅንስት ወርሃ ምንዳቤ ዘሉኪዮስ።
በውስተ ቤታ አሚን እስከነ ይበፅ ዘቂርቆስ።
ማእረሪሁ ለገድል ወላዴዘቦ ሰማዕት ተርጓሜ መጥባሂት ሀዲስ[14]።

**ትርጉም፦** የቂርቆስ እናት አንጌቤናዊት የንጉሥ ሉኪዮስ ችግር ምንፍቅና በችግር
ምንፍቅና ጊዜ የተቸገረች ናት፤
ሀዲስ ሰይፍን የሚተረጉም ሰማዕት የሰማዕት ሽማግሌ ገድል፤
የገድል ሽማግሌ አዝመራ የሚሆን ቂርቆስ የቂርቆስ ተክል ፍሬ፤
በሃይማኖት ቤቷ እስከሚደርስ ድረስ የተቸገረች ናት።

የቅኔው ወርቃዊ ክፍል ቤተክርስትያን በሰማዕትነት የምታስባቸው ሰማዕቱ ቂርቆስና የእናቱ ቅድስት ዕየሉጣን ታሪክ ሲሆን የቂርቆስ እናት ቅድስት እየሉጣ በዘመኑ የነበረው ንጉስ ሃይማኖታችሁን ካዱ እኔ ለማመልከው ስገዱ ባላቸው ጊዜ ልቧ ለሁለት ተከፍሎ ተጨንቃ ነበር። ነገር ግን ህጻኑ ቂርቆስ የያዘውን እምነት በልቡ በማጽናት እናቱ ጨክና ሐይማኖቷን እንድትጠብቅ ፈጣሪውን በመማጸን እናቴ ሆይ ጽኚ ብሎ እስኪያበረታት ድረስ በጥርጥር ተጨንቃለች። ነገር ግን ልጇ ካጸናት በኃላ በጥርጥር የተከፈለው ልቧ ተመልሶ በሐይማኖቷ ጸንታ እስከሰማዕትነት ደርሳለች። የቅድስት እየሉጣ ጭንቀት ከእናትነት ጋር የሚናበብ ነው።

ሠሙ ባለቅኔዋ እናት ለልጇ ምን ያህል እንደምትጨነቅ ገልጸውበታል። እናትነትን ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "እናት" "የወለደች ሴት ከወለደችው ጋር ባላቸው የተዛምዶ ግንኙነት የምትጠራበት ቃል፣ የመሪነት፣ የአስተዳዳሪነት፣ የሞግዚትነት፣ የደግነት፣ የሩሁሩህነትና የፍቅር ተምሳሌት ናት"።(1948፣225) በማለት ይገልጹታል። እናት ልጇን በደግነት አሳድጋ ለቁም ነገር እስኪደርስ ድረስ ትጨነቃለች ብዙ ታስባለች መሰዋዕትነት በመክፈል የልጇን ከቁም ነገር መድረስ በጉጉት ትጠብቃለች። እናት እሷ ሳትማር ልጇን ታስተምራለች፤ እሷ እየበረዳት ለልጇ ትደርብለታለች፤ እሷ ተዋርዳ ልጇ በክብር እንዲኖር ትጥራለች "ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች" እንደሚባለው ሁሉ ለልጇ ስትል የማትቀበለው መከራ የለም። ልጇ አድጎ ለቁምነገር እስኪበቃ ድረስ እራሱን ችሎ ኑሮውን መምራት እስኪችል ድረስ እናት ዘወትር ስለልጇ አብዝታ ታስባለች። ልጅ ለአቅማዳም ደርሶ ራሱን ቢችልም ለእናቱ ምንጊዜ ልጅ ነውና እናት ማሰቧ አይቀርም። ለዚህም ነው ”እናቴ ባለችኝ ሳይሆን ሚስቴ ባለችኝ አውለኝ" የሚባለው ሚስት ባሏ

[14] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

ሲዘገየባት እና ሲያመሽባት በጥርጣሬ መንፈስ ከሌላ ሴት ጋር እየማገጠ ነው ትላለች፡፡ እናት ግን በተቃራኒው ልጁ ችግር ገጥሞት ነው፤መከራ ደርሶበት ነው እንጂ በጤናው አይደለም በማለት አብዝታ ስለልጇ ትጨነቃለች፡፡ እንግዲህ የእናት ለልጇ መጨነቅ ከጽንሰት ጀምሮ ልጇ ካደገ በኋላ የሚያቆም ሳይሆን እስከ ህይወቷ ፍጻሜ የሚዘልቅ ነው እንጂ፡፡

### *4.1.9.2 ስለሴት ልጅ ተወዳጅነትና አስፈላጊነት*

**ቅኔ ፩ ዘአምላኪየ**

*መንክራት አእኑስ በላዕለ ስምዖን ፀማዳ፡፡*

*ለድንግል ወላዲተ ዘቦ ለመንክር ወልዳ፡፡*

*ይትሌዓላ ስምዖን አኮኑ ክቡረ ተግባሮን እንግዳ*[15]፡፡

**ትርጉም፦** *ድንቃድንቅ ሴቶች የአድናቆት ንግስት ልጇ ክርስቶስን፤*

*የወለደች የድልግል ማርያም አገልጋይ ስምዖን፤*

*በስምዖን አገልጋይ ዘንድ ክፍ ከፍ ይላሉ፤*

*ስምዖን ደገኛ በስራቸው እንግዳ ዘንድ የከበረ ነውና።*

ወርቁ የስምዖን በላዔሰብእ ታሪክ ሲሆን በላዔ ሰብእ ሰባስምንት ነፍሳትን የበላ ሰው ሲሆን በዚህ ሀጢያቱ ምክንያት ወደሲኦል የመውረድ ዕጣፋንታው የነበረ ቢሆንም በሴቷ ድንግል ማርያም አማላጅነት ምክንያት ከቅጣት ተርፏል፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ተዓምረ ማርያም የተባለ መጽሐፍ ላይ እንደተጻፈው በላዔሰብ የሰውን ልጅ ገድሎ እንደአውሬ ሲበላ ኖሮ ከእለታት አንድ ቀን እንደልማዱ ሰው አግኝቶ ሊበላው ሲሄድ በቁስል የተመታ በመሆኑ ተጠይፎ ሊሄድ ሲል ስለማርያም ውሃ አጠጣኝ ብሎ ሲማጸነው ከያዘው ውሃ ያቀምሰዋል፡፡ ይህ የደግነት ስራው እንደዋጋ ተቆጥሮለት በሞት በተወሰደ ጊዜ ከአምላክ ፊት ለፍርድ ሲቆም ከሰባ ስምንት ነፍስ ይልቅ ያቺ በድንግል ማርያም ስም የዘከራት ጥሪኝ ውሃ ታስባለት ከቅጣት አምልጧል፡፡ ሠማዊ ጉዳዩ ደግሞ ሴቶች በማርያም ወዳጅ በሆኑ ሰዎች ዘንድ የከበሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ሴት የክብር ቦታ አይሰጣትም ፣ለሀላፊነት አትታጭም በየትኛውም ስፍራና ሁኔታ ላይ ወንዱ ነው ቀዳሚ የሚሆነው፡፡ በቤተሰብ ውስጥም ወንድ ልጅ እንዲማር ይደረጋል የተለያየ የሞራል ድጋፍ ይደረግለታል ከህጻንነቱ ጀምሮም እሱ የበላይ እንደሆነ ይነገረዋል፡፡ በተቃራኒው ሴቷ ግን የወንድ ልጅ ታዛዥ እንደሆነችና ይህንንም አምና እንድትቀበል ተደርጋ ታድጋለች፡፡ ይህ አስተሳሰብም አብሮ ያድግና ወንዱ በሴቷ ላይ

---

[15] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

የበላይነት ስሜቱን ያንጸባርቃል በተግባርም ያሳያል። "ሴት በማጀት ወንድ በችሎት" በማለት ማህበረሰቡም የሴትን ሚና አሳንሶ ሴት ክብር የማይገባት ከሰው ያነሰች ፍጡር አድርጎ ይመለከታታል። እንዲያውም አባታችን አዳም በሄዋን ምክንያት ነው ከገነት የተባረረው ከክብር የጎደለው በማለት ሴትን እንደጥፋተኛ ይቆጥራል።

የሴት ልጅን ተፈጥሮ እንደደካማ በመቁጠርና በማሳነስ "ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ" በሚለው ብሂሉ አንድም የሴትን እውቀት አሳንሶ የማየትና የወንድን ያህል ልታውቅ አትችልም የነገሩ ሁሉ መቋጫና ማሰሪያው የወንዱ ሀሳብ እንደሆነ ያምናል። አንድም የሴቷን አቅምና ችሎታ ይክዳል። ይህ ዕሳቤም ወንዱ ሴቷን ከኔ እኩል ናት ምንም የሚጎድላት ነገር የለም ብሎ እንዳያስብ ያደርገዋል። ባለቅኔዋም ይህንን የተሳሳተ የማህበረሰብ አመለካከት ለሀይማኖታቸው የተገዙ ቅዱሳን በተባሉ ሰዎች ዘንድ ሴቶች የክብር ቦታ አላቸው። ምክንያቱም ቅዱሳን በሄዋን ምክንያት አዳም ከገነት ቢወጣም በድንግል ማርያም አማካኝነት አዳም ወደ ቀደመ ክብሩ ትመልሷልና በሴት ምክንያት ድህነትን አግኝተናል ብለው ቅዱሳን ሴቶችን ያከብራሉ በማለት ይገልጻሉ።

**ቅኔ ፪ ጉባኤ ቃና**

መለኮት ዕድ እንበሌሃ ለእንተ ሀና ወለት።
ኢይክል ይንበር ውስቴታ ለዘሐነፀ? ትስብእት[16]።

**ትርጉም፦** መለኮት ወንድ ልጅ ያለ ሀና ሴት ልጅ(ያለድንግል ማርያም)፤
በሠራት ቤት ውስጥ ይኖር ዘንድ አይችልም።

የቅኔው ወርቃዊ ሀሳብ ከሶስቱ አካል አንዱ ወልደ እግዜብሔር የሰውን ልጅ ለማዳን ወደዚህ ምድር ሲመጣ ለእናትነት የመረጣት  የቅድስት ሀናን ልጅ ቅድስት ድንግል ማርያምን እንደሆነ የሚገልጽ ነው። ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክ ሰውን ለማዳን ወደዚህ ምድር ሲመጣ የማዳኑ ምክንያት ትሆነው ዘንድ የመረጣት ሴት ናት።

ወደ ሠማዊ ጉዳይ ስንመለስ ወንድ ልጅ ቤት ቢሰራ ሀብት ቢያፈራ ያለ ሴት ልጅ ህይወቱ ሙሉ ሆኖ ሊኖር አይችልም የሚል ነው። በማህበረሰቡ ዘንድ ሴት ልጅ ዝቅ ተደርጋ ትታያለች በኑሮ ውስጥ ያላት አስተዋጾና አስፈላጊነት ብዙ አይስተዋልም።  ባለቅኔዋ ግን "ያለ ሀና ሴት ልጅ በሰራት ቤት ውስጥ ይኖር ዘንድ አይችልም" ሲሉ ወንድ ልጅ ያለሴት ልጅ መኖር እንደማይችል ነው የገለጹት። በማህበራዊው፣ በምጣኔ ሐብታዊው እንዲሁም በፖለቲካዊው

[16]የእማሆይ ጎሪት ቅኔ

ጉዳይ ላይ ታላላቅ ተግባራትን የፈጸሙ በጦር ሜዳ ሳይቀር ጠላትን በግንባር የተፋለሙ ሴቶች ቢኖሩም እውቅና አይሰጣቸውም ጎልቶ የሚሰማው የወንዱ ብቻ ነው። አባዊ ስርዓቱም ለራሱ የክብር ስፍራ በመስጠት ለሴቷ ክብር እንደማይገባት በተለያየ መልኩ ያንጸባርቃል።

በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ትዳር ትልቁ የህይወት ሽግግር ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድም ከፍ ያለ ስፍራ የሚቸረው ነው። ትዳር የቁም ነገረኝነት መለኪያ፤ ለማህበራዊ ሀላፊነት መታጫ፤ መከበሪያ ነው። ትዳር ያልመሰረተ ከሆነ ግን ብዙ ጊዜ የተናቀና ቁምነገር የማይገኝበት ተደርጎ ይቆጠራል ። ትዳር መስርቶ ህይወቱን በወጉ መምራት አልቻለም በሚል ማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ሀላፊነቶች አይታጭም በተቃራኒው የተገለለ ይሆናል። ለዚህ ታላቅ ተቋም መሰረቷ ሴት ናት።በቅኔው ውስጥ "ያለሐና ሴት ልጅ፣ በሰራት ቤት ውስጥ ይኖር ዘንድ አይችልም። "በሚል የተገለጸው ሠማዊ መልዕክትም ወንድ ልጅ ምንም ያህል ጠንካራ ቢሆን ያለሴት ልጅ በዚህ ዓለም ላይ ሙሉ ሆኖ ሊኖር አይችልም የሚል ነው።

**ቅኔ ፫ ጉባኤ ቃና**

ብእሴ ምድረ ሰዶም ነድ ኢትመንን እደ ሰሎሜ ብእሲተ።
አምጣነ ብእሲት እምከ ገሞራ እንተ ተወለድከ አንተ[17]።

**ትርጉም፦** የሰዶም የምድር ወንድ እሳት የሰሎሜ እጅ እጅ ሴትን አትናቅ፤
አንተ የተወለድክባት እናትህ ገሞራ ሴት ናትና።

የቅኔው ወርቃዊ ጉዳይ የቅድስት ድንግል ማርያም አክስት የሆነችው ቅድስት ሰሎሜ ድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና ጸንሳ ሳለች በድንግልና መጽነሷን አላምንም ሴት እንዴት በድንግልና ልትጸንስ ትችላለች ካላየሁ አላምንም ብላ እጇን ወደ ማህጸኗ ስታስጠጋ እንደተቃጠለች የሚገልጽ ነው። ወደ ሰማዊው ሀሳብ ስንሄድ ሴትን አትናቅ የወለደችህ ሴት ናትና የሚል ነው። በማህበረሰብ ውስጥ ሴት ልጅ እንደውለታዋና ተግባሯ የወንድ ልጅን ያህል ክብር አይሰጣትም ። እውነታው ግን ወንድ ልጅ ያለሴት ልጅ ስኬታማ ህይወት ሊኖረው አይችልም። ወደዚህ ምድር ቢመጣ በሴት፣ አምጣ ወልዳና ጡቶቿን መግባ ብታሳድግ ሴት ሆና ሳለ የሴት ልጅ ውለታ ግን በተቃራኒው ሆኖ ይስተዋላል። ሀገር የሚመሩ ነገስታትን፣ ለችግሮች መፍትሄ የሚያፈልቁ ምሁራንን፣ ለሀገር እና ለወገን አለኝታ የሆኑ ጀግኖችን የሚወልዱ ሴቶች ቢሆኑም አባዊው ስርዓት እነሱን ዝቅ አድርጎ ከማየት አይመለስም።

[17] የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

አባወራው እንኳ ሚስቱ ሴት ልጅ አከታትላ ከወለደች ይከፋዋል ወንድ ልጅ ሲወለድ የሚሰማው ደስታ አይሰማውም እንዲያውም "ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ የት አለ ንግዱ" በማለት ሴት መውለድን እንደኪሳራ ይቆጥረዋል።

በተለያዩ መስኮችም ሴት ልጅ የምትፈጽመውን ተግባር እውቅና ከመስጠት ይልቅ ሲንቅና ሲያንኳሽሽ ይስተዋላል። አሁን አሁን ለሴቶች የተሻለ ነገር ቢኖርም በቀደመው ዘመን ግን ሴትን ከወንዱ እኩል ሰው ናት ብሎ አምኖ የተቀበለ እስከማይመስል ድረስ ጭቆናና መድሎ ሲፈጽምባት ኖሯል። ማህበረሰቡም ባልና ሚስት በትዳር ወልደው ያሳደጉት ልጅ ባለጌ ሲሆን ሴቷ እንዲባልግ ያደረገችው ይመስል "የሴት ልጅ" በማለት የእናትነት ክብሯን ያኮስሱታል። በልጁ የአስተዳደግ ችግርም ከወንዱ ይልቅ ሴቷን ተጠያቂ ያደርጋል። ባለቅኔዋም ሴትን ልጅ የሚሳደበውን የሚያጣጥለውን አባዊ ስርዓት የገነነበት ማህበረሰብ ሴት ልጅ እናትህ ናትና አትናቃት ይልቁንም አክብራት በማለት ምክርና ተግሳጽ አዘል ቅኔያቸውን አመስጥረዋል።

### *4.1.9.3 ስለሴት ልጅ ጀግንነት*

**ቅኔ ፩ሚበዝሁ**

ተመውኦ አፅራር ዘፈነ ኢትዘፍን እንከ ጣይቱ ዘውገ አርሴማ።

እስመ ላእለ ርእሳ ፀአነት ተርቢኖስሀ አስኬማ።

ጣይቱ ብፅእት እንተ ሐረያ በክብር መስፍነኤርሞን ፊማ[18]።

**ትርጉም፦** መንፈስ ቅዱስ ፤በክብር የመረጣትና የአርሴማ ወገን፤ የሆነች ብፅእት ጣይቱ

የጠላት መሸነፍ ዘፈንን እንንግዲህ አትዘፍንም፤

የኤርሞን አለቃ ጊዮርጊስ ቆብን ከራሷ ላይ አድርጋለችና(ጭናለችና)።

የቅኔው ሠማዊ ጉዳይ ለእግዚአብሔር ያደሩ ቅዱሳን ዘፈንን አይዘፍኑም የሚል ሲሆን። ቅዱሳን የዚህን ዓለም ተድላ ደስታ በመተው እራሳቸውን ለፈጣሪያቸው በማስገዛት የሚኖሩ በመሆናቸው የጽድቅ ስራ ካልሆነው የሰይጣን ስራ ሁሉ የተለዩ እና እሱንም ድል የነሱ ናቸው። ወርቃዊው ሀሳብ ደግሞ እቴጌ ጣይቱ የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት በመያዝ ጠላትን ድል ነስታለች የሚል ነው። የሴቶች እኩልነትና ነጻነት ባልታወጀበት፤ ዓለም በስልጣኔ ባልተራቀቀችበት ዘመን ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ በወረረ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ ከአጼ ሚኒሊክ ጋር በመሆን አመራር በመስጠት በወቅቱ የነበረውን ህዝብ በማጀገን አብረው አድዋ ላይ በመዝመት የኢጣልያ ጦር ድል እንዲነሳ ከፍተኛ አስተዋጾ የነበራቸው

[18] የእማሆይ ኀሪት ቅኔ

ታላቅ ሴት ናቸው። "የሴት ብርቱ ታሰኛለች አንቱ" እንደሚባለው አጼ ሚንልክ በመላው ዓለም ለሚገኙ ጥቁር ህዝቦች ኩራትና የነጻነት ፋና የሆነውን የአድዋ ድል በአሸናፊነት ለመፈጸም ያበቃቸው ከእሳቸው የአመራር ጥበብ ባሻገር በወቅቱ ከነበረው የህዝብ አንድነትና ጀግንነት እንዲሁም የዕቴጌይቱ ጥበበኛነትና ብልሀት የተሞላው አመራር ሰጭነት መሆኑን የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። ተክለጻድቅ መኩሪያ አጼ ምኒሊክና የኢትዮጵያ አንድነት በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ ስለእቴጌ ጣይቱ ብልህ የአመራር ሰጪነት ሲገልጹ "እቴጌ ለወታደሮቻቸው ወደ ምሽጉ ገብቶ ለመዋጋት እንደዚህ ለበዛችሁት ጦር የምሽጉ መንገድ ጠባብ ስለሆነ ከጣሊያኖቹ መድፍና ጥይት የበለጠ እርስ በርሳችሁ ትገዳደላላችሁ። ስለዚህ ሄዳችሁ ጣልያኖቹ ውሃ እንዳይቀዱ ምንጩን ጠብቁ" (1983፣285)። ማለታቸውን ጠቅሰው የእቴጌይቱን ብልሀት ገልጸዋል። የሴት መላ ስጠኝ እንዲሉ እቴጌ ጣይቱ ጣሊያኖቹ ከጦር ውጊያ በተጨማሪ ውሃውን በመቆጣጠር በውሃ ጥም እንዲያልቁና ሀይላቸው እንዲዳከም በማድረግ ለጦርነቱ ድል የበኩላቸውን አስተዋጾ አድርገዋል።

ከእያንዳንዱ ስኬታማ ወንድ ጀርባ ጠንካራ ሴት አለች እንደሚባለው ከታላቁ ንጉስ ከአጼ ሚኒሊክ ጎንም ብልኀ ጣይቱ አለች። ባለቅኔዋም ታሪክ በክብር የሚዘክራቸውንና ዓርአያ የሆኑትን ጀግና ሴት በቅኔያቸው በማምጣት አመስጥረው ገልጸዋል።

**ቅኔ ፪ ጉባኤ ቃና**

አንስተ ሀገር ለብዋ ኢትዮጵያዊተ ጣይቱ።
ከመአክረየቶሙ ዝህረ ለኀያላነተ ሀገር እስፍንቱ[19]።

**ትርጉም፦** የሀገር ሴቶች ኢትዮጵያዊት የምትሆን ጣይቱን አስታውሱ፤
ስንቶቹን ኃያላኖች መቃብር እንዳስቆፈረቻቸው።

የቅኔው ወርቃዊው ጉዳይ እቴጌ ጣይቱ "ሴትና ድስት ወደማጀት" የሚለውን አስተሳሰብ ጥሳ ወደ ጦርነቱ በመዝመት የጀግንነት ተግባር መፈጸሟንና የኢትዮጵያ ሴቶች እቴጌ ጣይቱን አርዓያ እንዲያደርጉ የሚያሳስብ ነው። ንጽጽሩ በሀገራችን ያለው የአባዊ ሥርዓት የበላይነት ሴቶችን ደካማ አድርጎ የሚመለከት ሲሆን ሴቷም ይህንን አምና እንድትቀበል የሚያደርግ ነው። በአስተሳሰብም ሆነ በተግባር የወንዶች የበላይነት ባለበት ሀገርና ማህበረሰብ ውስጥ ሴቶችን አሳንሶ ከማየት ባለፈ እንደሰው የማይቆጠሩበት ሁኔታ ይኖራል። ከአወንዱ እኩል ተግባራትን የማትከውን፣ የሽንፈት ማሳያ እና መጠሪያ ተደርጋ ትወሰዳለች። ይህ ስር የሰደደ

[19]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

የሴቷን ሰውነት የሚክድ ዕሳቤ ሴቶቹ እራሳቸው እኛኮ አንችልም ወንዶች ናቸው ጠንካሮች ወደሚል ድምዳሜ እንዲደርሱ ያደርጋቸውና ታላላቅ ከሚባሉ ሀገራዊ ጉዳዮች፣ከትምህርት መስክ፣በአደባባይ ከሚከወኑ ተግባራት እራሳቸውን ያገላሉ። ነገር ግን ይህንን ሁሉ የአስተሳሰብና የተግባር ተፅዕኖ ተሻግረው ታላላቅ ተግባራትን የሚፈጽሙና ታሪክ የሚሰሩ ዕንስቶች አሉ። ከነዚህ ሴቶች መካከል ደግሞ ታሪክ በክብር የሚዘክራቸው እቴጌ ጣይቱ አንዷ ናቸው። እቴጌ ጣይቱ በ1888 ዓ.ም ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ከንጉሠ ነገሥቱ ከአፄ ሚኒሊክ እና በወቅቱ ወደጦርነቱ ከዘመተው ኢትዮጵያዊ ጀግና ጋር በመሆን ለጦርነት የተሰለፉ እና ለሀገራቸው ነጻነት ተዋግተው ለአሁኑም ይሁን ለመጭው ትውልድ አርዓያ የሚሆኑ ጀግና ናቸው።

ባለቅኔዋም እኒህን ጀግና ሴት ከታሪክ ጠቅሰው በማምጣት የፈጸሙትን ተጋድሎ፣ለሀገራቸው ነጻነት የዋሉትን ውለታ በማስታወስ ጠላትን ያስጨነቁትን ጣይቱን ተመልክታችሁ እሳቸውን አርዓያ ምሳሌ አድርጋችሁ እንደሳቸው ሁኑ። ማህበረሰቡ ዝቅ አድርጎ ቢያያችሁም እንደደካማ ቢቆጥራችሁም እናንተ ግን የሰዎች ልበ ሙሉነት በሚፈተንበት የጦርነት አውድማ ላይ ለመጋደል ቆርጠው የወጡትን ጣይቱን ተመልከቱ። የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ተከትላችሁ አትድከሙ። እሳቸው ጀግና እንደሆኑ እናንተም ጀግና ሁኑ ደካሞች አይደላችሁምና በማለት ይናገራሉ።

## 4.2 ፍልስፍና

ፍልስፍናዊ ጉዳይ የሰው ልጅ ተፈጥሮን፣ በዙሪያው ያሉ ጉዳዮችን፣እውነትን የሚፈልግበት፣ ዕረቂቅ የሆኑ እሳቤዎችን የሚመረምርበትና ምላሽ ለማግኘት የሚጠይቅበት ጥልቅ የሆነ የዕውቀት ዘርፍ ነው። የሰው ልጅ አዕምሮ ምንጊዜም ከመጠየቅ አይቦዝንም በዚህ ተፈጥሯዊ ባህርይውም ለተለያዩ ጉዳዮች ምላሽ ያገኛል፤ መፍትሄ ይፈልጋል። እነዚህን ፍልስፍናዊ ጉዳዮችንም በተለያዩ መንገዶች ይገልጣቸዋል። ከነዚህ መገለጫ መንገዶች አንዱ የግዕዝ ቅኔ ነው። የግዕዝ ቅኔ ከሐይማኖታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ባሻገር ለሰው ልጅ አዕምሮ ጸናን የሆኑ ዕሳቤዎች የሚቀርቡበት፣ ማህበረሰቡ እውነት ብሎ ያጸደቃቸው ጉዳዮች የሚመረመሩበር ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት የመምህራኑ ቅኔያትም ፍልስፍናዊ ጉዳዮችን ያነሳሉ። ከቅኔያቶች ውስጥ አምስት ያህል ፍልስፍናዊ ጉዳዮችን የያዙ ቅኔያቶች ተፈክረው ቀርበዋል።

### 4.2.1 ስለሰው ልጅ ፍላጎት
**ቅኔ ፪ ስላሴ**

ይስማዕ አውያተ መኑ እግዚአ ለነፍስ እምአ አግብርተ ዓለም ታህቲት

ባህታዊ ወመተባለ አማሌቅ ባዕዱ::

ለጾም እግዚአ ኢያሱ ለእፅብት ፈቃዱ::

እንዘ ይእስእሎ ወሥጋ ዝናባተ ፀል ይረዱ::

አሀዱ አማሌቅ እስመ አሐዱ::

ባህታዊ ፀሀዬ በይነስኩርንዱ::

ይስዕሎ ምስለ ሊቅ ወልዱ[20]::

**ትርጉም፦** የነፍስ ጌታ ጾም ይሄ የማንን ጩኸት ይስማ ከታችኛው ዓለም እስላምና ክርስትያን፤

ከነዚህ ፈቃዱ የምታስደንቅ የኢያሱ ጾም ጌታ፤

ይህንን አንዱ እስላም ስጋና ወተት ዝናቦች እንዲዘንቡ ሲለምነው፤

አንዱ ባህታዊ ከሊቅ ልጁ ጋር ስለሽንኩርት ፀሀይን ይለምነዋል ማንንይስማ::

የቅኔው ወርቃዊው ጉዳይ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኖች በጾም ወቅት ከስጋና ከወተት(ከጥሉላት) ሲከለከሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ግን ስጋና ወተት እንደሚመገቡ የሚገልጽ ነው::

ማህበራዊው ጉዳይ የሰው ልጅ ፍላጎት የተለያየ መሆኑን የሚገልጽ ነው:: ሰው የተለያየ ሀሳብና ፍላጎት ስላለው አንዱ አንድ ነገር ሲፈልግ ሌላው ደግሞ ሌላ ይፈልጋል:: ለአንዱ ርካሽ የሆነው ነገር ለአንዱ ውድ ይሆናል:: ዝናብ ያገኘ በፀሀይ እጦት ይቸገራል ፀሀይ ያገኘ ደግሞ ዝናብ በማጣት ይቸገራል:: ሁሉም የየራሱን ፍላጎት ለማግኘትና ለመርካት ሲል ብዙ ይደክማል፤ ይወጣል ይወርዳል ያቻለውን ሁሉ ያከናውናል ከአቅሙ በላይ የሆነውን ደግሞ ይሰጠኛል፤ ያደርግልኛል ወደሚለው አምላኩ ልመናን ያቀርባል:: በቅኔ ውስጥ "ማንን ይስማ" የሚሉት ቃላት የሰውን ልጅ የተለያየ ፍላጎትና የማያባራ ጥያቄውን ወደ አምላኩ እንደሚያቀርብ የሚገልጹ ናቸው:: የዝናብ ዕጦት በድርቅ ምክንያት የሰውን ልጅ መሰረታዊ ፍላጉት የሆነውን ምግብ የሚያሳጣ ከባድ ችግር ነው:: እንዲሁ በዝናብ እረስርሳ የተሰጣትን ያበቀለች ምድር ቡቃያው ለፍሬ ይበቃና ይበስል ዘንድ ፀሀይ ታስፈልጋለች:: ነገር ግን የዝናብና የፀሀይ መገኛ

[20] የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

ወቅታቸው የተለያየ በመሆኑ በአንድ ጊዜ አንድ ላይ ሊገኙ አይችሉም። ዝናብ ተገኝቶ ፀሀይ ላይገኝ ይችላል። ሁሉም ነገር ተማልቶ ባለመገኘቱ ምክንያት የሰው ልጅ ሁል ጊዜም ከመጠየቅ አይቦዝንም እንደጠየቀና እንደፈለገ ህይወቱ ታልፋለች እንጂ።

የሰው ልጅ ፍላጎት የተለያየ በመሆኑ እና ለመኖር የሚያስፈልጉት ነገሮችም የተለያዩ በመሆናቸው ለአንዱ የበዛው ለአንዱ እያነሰ አልያም ከነጭራሹ እየጠፋ ይቸገራል። አንዱ ሀገርና ህዝብ በዝናብ ብዛት ሲቸገር ሌላው ሀገርና ህዝብ ደግሞ በበዛ ፀሀይ በበረሀ ይሰቃያል ሁሉም ነገር ተሟልቶና ተመቻችቶ ስለማይገኝ። የእያንዳንዱ ግለሰብ ፍላጎትም እንዲሁ ነው ። ሀብት የሌለው ሀብትን ይሻል፤ ሀብት ኖሮት ጤና በማጣት የተቸገረው ጤናውን ይለምናል፤ ልጅ የሌለው ልጅ ይለምናል። የሰው ልጅ በራሱ ልፋትና ጥረት አልሳካ ያለውን ከአቅሙ በላይ የሆነውን ነገር ለማግኘት ይሰጠኛል ወደሚለው አምላኩ ይለምናል። ባለቅኔዋም የሰውን ልጅ የተለያየ ፍላጎት በማምጣት ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ ተሟልቶ እንደማይገኝ እና ሰውም የተለያየ ፍላጎቱና ጥያቄው ሊገታ እና ሁሉንም በአንዴ አሟልቶ ሊያገኝ የማይችል በመሆኑ ፈጣሪ የማንን ጨኸት ይስማ ሲሉ ሁሉን የሚችለውን አምላክ የደካማውን የሰውን ልጅ ባህሪ አላብሰው የሰውን ልጅ የተለያየ ፍላጎትና ጠያቂነቱን አሳይተውበታል።

### 4.2.2 ስለሞት

**ቅኔ ፩ ዘአምላኪየ**

> *አንተ ሞት አምጻኤ ብዙኅንሣር።*
> *ምንት ዘይፀንአከ በሰማይ ወምድር።*
> *እስመተአደውከ ለኤልሳዕ አበተዋሕዶ ክቡር*[21]

**ትርጉም፦** ብዙ ሀሳር የምታመጣ ሞት ሆይ፤

የሰማይና የምድር አምላክ ክርስቶስ የከበረ የተዋህዶ አባት ኤልሳን ተደፋፍረኸዋልና፤

የሰማይና የምድር ሰው በሰው ዘንድ የሚቀይህ ምንድን ነው።

የቅኔው ሰማዊ ክፍል ሰውን የማያከብር ደፋር ሰውን የሚመለከት ነው። አንዳንድ ሰው በዕውቀታቸው፣ በስራቸው እንዲሁም በዕድሜያቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ አንቱ የተባሉትን ሰዎች በመናቅ ከክብር ዝቅ አድርጎ ያቃልላቸዋል። ደፋርና ባለጌ ለሰማይና ለምድር

[21] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

የከበዱ ታላላቅ ሰዎችን ከማክበር ይልቅ አቃሎ የሚያይና ክብራቸውን ዝቅ የሚያደርግ ባለጌ በመሆኑ ማህበረሰቡም "ባለጌን ተነስ አይሉትም" በማለት ታላላቆችን የማያከብር ባለጌን መተው እንጂ እንዲህ አድርግ ማለት አያስፈልግም በማለት ይገልጻሉ። ባለቅኔዋም ሰዎችን የሚደፋፈረውን፣ ለሰዎች ክብር የማይሰጠውን ባለጌ ሰው መጨረሻህ ምን ይሆን በማለት ይገልጹታል። የቅኔው ወርቃዊ ክፍል ደግሞ የሞትን ደፋርነት እና ጨካኝነት የሚገልጽ ነው። ሞት ምግባረ ቢስ በሆነው ሰው ተመስሎ የቀረበ ሲሆን ባለጌ ታላላቆችን እንደማያከብር ሁሉ በዕውቀት የላቁ፣ በስራቸው የተከበሩ፣ በጀግንነታቸው የተፈሩ፣ ነገስታት ቢሆኑ ባለስልጣን ከሞት አያመልጡም ሞት ባለጸጋ ብሎ አይፈራም ደሃ ብሎም አዝኖ አይተውም ሁሉንም ይወስዳቸዋል ደፋር ነውና።

ባለቅኔዋ ይህንን ቅኔ የተቀኙት የሰሜን ጎንደር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕአቡነ ኤልሳ ባረፉ ጊዜ ነው። ብፁዕ አቡነ ኤልሳ ታላቅ የሃይማኖት አባት እና ደግ ህዝብን የሚያጽናኑ በመሆናቸው ለሁሉም እኩል የሆነው ሞት በእሳቸውም ላይ በደረሰ ጊዜ ረቂቅ የሆነውን ነገር እንዴት ደፋር ነህ እንዴትስ እሳቸውን ያህል ታላቅ ሰው ትወስዳለህ በማለት ሞት የሚሰጥህ ቅጣት ወይም የጥፋት ዋጋህ እንዴት የከፋ ይሆን ትልቅ ሰው ደፍረሃልና ሲሉ ሞትን እየወቀሱ የተከበሩትን የተዋህዶ አባት ሽማግሌውን አቡነ ኤልሳን ወስደሃልና ለእሳቸውም ልትራራላቸውና ልትምራቸው አልቻልክምና በማለት እረቂቁን ሞት ተናግረውታል። የሰው ልጆች ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጆቻቸው፣ የሚወዷቸውና የሚያከብሯቸው ምንግዜም ከጎናቸው እንዲለዩ በተለይም ደግሞ በሞት እንዲወሰዱባቸው አይፈልጉም ነገር ግን ይህ ተፈጥሯዊ ግዴታ ሁሉንም የሰው ልጆች ታናሽ ታላቅ ሳይል በፈለገው ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ እገሌን ውሰድ እገሌን ተው ብሎ ክልከላ ማድረግ አይቻልም። ይህ በመሆኑም ሰዎች የሚወዱትንና የሚያከብሩትን ሰው ከጎናቸው በሞት ሲነጠቁ ሀዘናቸው ከባድ ይሆናል። ባለቅኔዋም በጣም የሚያከብሯቸውና የሚወዷቸው ታላቁ አባት አቡነ ኤልሳዕ በድንገት ሲያርፉ የተሰማቸውን ሀዘን እና ለእርሳቸው የነበራቸውን ክብርና ፍቅር የገለጹት የሞትን ጭካኔ እንዲሁም እኒህን ታላቅና የተከበሩ ሰው በመድፈሩ ቅጣቱ ምን ይሆን በማለት የሰው ልጆችን ሁሉ ህልውና ነጣቂውን ሞት መጨረሻህ ምንድን ነው ሲሉ በቅኔያቸው ይጠይቁታል ።

**ቅኔ ፪ ሥላሴ**

አንተ አማኑኤል መፍቀሬ ሰብእምድር ወኢዮር ለወልድከ ሞት

እመከመፈጠርከሙ እንጋ፡፡

ውእቱ አምጣነ ለመደ ዜና ሰብእ ሥጋ፡፡

እንዘ ተፈጥሮቲ መቅድመ ለዓቂበይእቲ ሕጋ፡፡

ለሔዋን እም ምልዕተ ጸጋ፡፡

ዘዕዝራ ወሔኖክ ዘኀድጋ፡፡

ለዓለም ዘተመልአት ንትጋ[22]፡፡

**ትርጉም፦** አንተ የምድርና የሰማይን ሰው የምትወድ አማኑኤል ሆይ፤

ሞት ልጅን እንዴት እንደፈጠርከው እንጃ፤

እሱ የሰው ወሬ ስጋ የለመደ ነውና፤

የናት ሔዋን ህግን ማክበር አስቀድሞ ተፈጥሮ ሲሆን፤

ኀዶሎነትን የተመላች ዓለምን የተዋት የዕዝራና የሄኖክ ስጦታ ይህን የተመላች፤

የእናት ሔዋን ህግን ለማክበር ተፈጥሮው ሲሆን ሞት ልጅ ወሬ ስጋን ለምዷልና

እንዴት እንደፈጠርከው እንጃ፡፡

ሠሙ የሚያመለክተው ወሬ የለመደን ወሬኛ ሰውን ነው፡፡ በወርቃዊው ክፍል ግን ባለቅኔዋ የክርስቶስ አምላክን ሞት በማንሳት ሞት ለምን አስፈለገህ በማለት ይጠይቃሉ፡፡ ሞት የሰውን ልጅ ሁሉ የሚያሸንፍና ከመኖር ወደ አለመኖር የሚለውጠውን ሃይል እንዴት ፈጠርከው ለምንስ ሞት ተፈጠረ በማለት በተለይም የአምላክን ሞት ያነሳሉ፡፡ በክርስትና አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሰውን ልጅ ለማዳን አምላክ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱና በሶስተኛው ቀን መነሳቱ ተገልጿል፡፡ ባለቅኔዋም ሞቼ አድንሀለሁ ከሚል ይልቅ ሳይሞት ማዳን ይችል የለምን? ይላሉ ምክንያቱም አምላክ ነውና ሁሉን ማድረግ ስለሚችል ነው፡፡ ሞትን የፈጠርከው አንተ ሆነህ ሳለህ የሰውን ልጅ እንዲገድል ለምን ፈቀድክለት አንተስ ሞትን ድል መንሳት እየቻልክ መሞትህ ለምን አስፈለገ እያሉ አምላክን ይሞግታሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አስራ ስድስት ላይ "ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሶስተኛውም ቀን ይነሳ ዘንድ እንዳለው ለደቀመዛሙርቱ ይነግራቸው ጀመረ" የሚለውን ቃል መነሻ

[22]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

በማድረግ አሸናፊ የሆነውን ሞት ድል መንሳትህ እንደማይቀር እያወክ ለምን ሞትክ ለምን የሰው ልጆችን ስጋ ሲበላ ኖረ ይህን እንዴት ፈጠርከው እያሉ ይጠይቃሉ፡፡

በሌላ ገጽታ በቅኔው የፈጣሪ ትህትና ይደነቅበታል፡፡ አምላክ በመለኮቱ ህያው እና ሁሉን ማድረግ የሚችል ሆኖ ሳለ ሞትን መቅመሱ ለፈጠራቸው ፍጥረታት ታዞ መገኘቱ አስደናቂ ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ አስተምህሮ አምላክ ስጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር ሲመጣ አንድም የሰውን ልጅ ለማዳን አንድም አርዓያ ሆኖ አድርጉ ከማለቱ በፊት አድርጎ በማሳየት ለማስተማር ነው፡፡ በቃል ብቻ ይሁን ከማለት ይልቅ ለአምላክነቱ የማይገባውን በከብቶች በረት መወለዱ፣ እንደህጻናት እያለቀሰ ማደጉ፣ የሰው ልጆችን ስቃይ መቀበሉ፣ በሰዎች እጅ መገረፉ ሁሉ ትህትናን ማስተማሩ ነው ባለቅኔዋም አንድም አምላክ ሆኖ ሞን ማሸነፍ እየቻለ ለምን መሞት አስፈለገው በማለት አምላክን ይጠይቃሉ አንድም ሁሉን የሚችል ሆኖ ሳለ እንደ ታናሽ ሰው ዝቅ ብሎ መታዘዙን ያደንቃሉ፡፡

**ቅኔ ፫ ጉባኤ ቃና**

አዳም ወሔዋን ኢወለዱ እንበለ ኤልያስ ወልደ፡፡

ለኀይል ሞት እስመ ኢወሀበ እደ[23]፡፡

**ትርጉም፦** አዳምና ሔዋን ከኤልያስ በቀር መች ልጅ ወለዱና፤

ሁሉን ለአሸነፈው ለጉልበተኛ ሞት እጅ አልሰጠምና፡፡

ታሪኩ በዘመነ ኦሪት የነበረው የነብዩ ኤልያስ ሲሆን እንደ ሰው ልጆች ሁሉ የስጋ ሞት ሳያገኘው ወደ ብሄረ ህያዋን ማረጉን የሚገልጽ ነው፡፡ "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ" የሚለው አምላካዊ ቃል ሁሉንም የአዳም ልጆች የሚመለክት ቢሆንም በመልካም ምግባራቸውና ሐይማኖታቸው የተነሳ ህያውነትን ተጎናጽፈው ስጋቸው አፈር ሳይነካው የሞትም ሀይል ሳያሸንፋቸው የሚኖሩ አሉ፡፡ ኤልያስም ከነዚህ ህያዋን የሚደመር ነው፡፡ ወደ ሰሙ ጣጣ ስንመለስ ግን የሰው ልጅ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ በተባለው አምላካዊ ቃል መሰረት ሁሉም የአዳም ዘር ሞት በተባለው ባለስልጣን ይወሰዳል፡፡ ከአዳም ጀምሮ ሁሉም የሰው ልጆች በሞት ተሸንፈው ወደ መቃብር ወርደዋል፡፡ ምንም በዚህ ምድር ላይ በዕውቀት፣ በሀብት፣ በስልጣን የታወቁና ብዙ ዝና ያላቸው ሰዎች ሁሉም በነበር አልፈው በሞት ተወስደዋል፡፡ ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ የነበረ አንድም የሰው ልጅ የለም፡፡

---

[23] የእማሆይ ኀሪት ቅኔ

የሰው ልጅ ለአፈር እንደተሰራ ሞትም የማይቀር የመጨረሻ ዕጣ እንደኾነ "ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከሞት የሚቀር የለም" የሚለው ምሳሌያዊ ንግግር ሞት ለሰው ልጆች ሁሉ የሚደርስ ዕጣ የህይወት ጉዞን የሚገታ ሀይል እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ሰዎች በሚያከናውኑት ተግባር፣ ባላቸው የስልጣን ከፍታ፣ እንዲሁም ዝናና ሀብት ፈራሽ ገላን የተሸከሙ በሞት የማይወሰዱ ዘላለማዊ መስለው ቢታዩም እነዚህ ነገሮች ግን ከሞት የሚያስጥሉ ባለመሆናቸው ተሸናፊ ሆነዋል፡፡ ባለቅኔዋም "አዳምና ሔዋን ከኤልያስ በቀር መች ልጅ ወለዱና" በሚለው ስንኝ በሀይማኖቱ ቅዱሳን ተብለው በፈጸሙት ሐይማኖታዊ ተጋድሎና የጽድቅ ስራ በፈጣሪ ከተመረጡት ከነኤልያስ ውጪ አለም ከተፈጠረ ጀምሮ የሰው ልጅ ሁሉ ሞት በተባለው ዕረቂቅ ሃይል እንደሚሸነፍ፤ ምንም ጅግና ቢሆን በሞት ግን የማይሸነፍ እንደሌለ በዚህ ምድር ላይም ዘላለማዊ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

### 4.2.3 የአምላክን ፍርድ የሚሞግት

**ቅኔ፩ መወድስ**

ያስተዐብይኑ ባዕል እግዚአብሔር ዐበይተ ሀኤት ሀገር ዐበይተ ኀጥአን፡፡  
ዓይነ ዚአሁ ኀሩየ መትሕተ ኢያንበሬስ ደይነ፡፡  
ኀበ ኀበ ይነብር ኩነኔሁ ወኅሩየ በኢርውናሁ ኄራነ ኄራነ፡፡  
አምጣነ ያነብር መንበረዛ ማርያም ድንግል እንተ ኢያሱ ሰፈነ፡፡  
ደብረዘይትሂ ነጋሤ ጊዜ ዘዘያበድር ጻድቃነ፡፡  
ኃጥአነ ኃጥአነ ወጻድቃነ ቅዱሳነ፡፡  
ቁጻሬገሀነም ኀጉለ እንተያደክም ፍጡነ፡፡  
ወሕብስተ ጽድቅ አማናዊት መንግስተ ሰማይ መካነ፡፡  
አኮኑ ቅሩብ እደ ዚአሁ አማነ[24]፡፡

**ትርጉም፡** እግዚአብሔር ባዕለጸጋ የአበላልጣልን ወይስ ያዳላልን?  
የክፉት ሀገር ታላላቆች ኃጢያተኞችን በራሱ ዓይን ዓይቶ መርጦ መርጦ  
ከኢያንበሬስ በደለኛ በታች ደይን በደይን ስለግዛቱ ሲያስቀምጥ  
በቸርነቱ መርጦ ደጋጎችን ግን ይህች የሆነች ጥብቅ ማርያም የማርያም ወንበር  
ክብር በክብር ወንበር ያስቀምጣልና፡፡

---

[24]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

የጊዜ ንጉስ ደብረ ዘይትም ደጋጎችን የሚመርጥ ፈጣሪ ፍርድ ሴትዮ ከፍርድ
ሴትዮ ጋር ያጡ የሆኑ ሀጢአተኞች ለሀጢያተኞች ሽማግሌዎች ፈጥኖ
የሚያደክም የገሀነም ጥሬ ጥፋት ጥፋት ጥሬን ሲያቀርብ ፤
ለእውነተኞች ቅዱሳን ደግሞ የእውነተኛይት ጽድቅ ሴትዮ እንጀራ ክብርን
ከመንግስተ ሰማይ ቦታ እውነተኛ የሚሆን የራሱ እጅ በእጅ ያቀረበ አይደለምን።

የቅኔው ወርቃዊ መልዕክት አምላክ በዕለተ ምጽዐት የሚሰጠውን ፍርድ የሚጠይቅ ነው። የዓለም ፍጻሜ በሚመጣበት ጊዜ የሰው ልጅ በአምላኩ ፊት ቆሞ ፍርዱን ይቀበላል። በዚያን ጊዜ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 እንደተገለጸው አምላክ በደብረ ዘይት ሲገለጥ መልካም የሠሩ ፤እንደ ትእዛዙና ህጉ የኖሩ፤ ወዳጆቹንና ባለሟሎቹን ይፈርድላቸዋል። ኑ እናንተ የአባቴ ብሩካን ዓለም ሳይፈጠር ያዘጋጀሁላችሁን መንግሥቴን ውረሱ ብሎ ወደ ዘላለማዊ እረፍት ይጠራቸዋል። ሕግና ትዕዛዙን አፍርሰው ለፈጣሪ ሳይገዙ የኖሩትን ደግሞ በተቃራኒው እናንተ ጎጥኣን ከኔ እራቁ በማለት ወደ ዘላለማዊ ቅጣት እንዲሄዱ ይፈርድባቸዋል። ባለቅኔዋ አምላክ በአምላክነቱ ሁሉን ማድረግ ይቻለዋልና ሐጥያተኞቹ ከክፉ ስራቸው እንዲመለሱ፣እንደጻድቃን በጎ ህሊናና መልካም ምግባር እንዲኖራቸው ማድረግና የሱ ወዳጅ እንደሆኑት ቅዱሳን ማድረግ እየቻለ ለምን ዝም ይላቸዋል በማለት ፈጣሪ ሁሉንም የሰው ልጅ እንደ ህጉና ትዕዛዙ እንዲኖር ቢያደርገው ኖሮ ሐጢያተኛ የሚባል አይኖርም ወደ ሲኦል የሚወርድ የዲያብሎስ ባሪያ የሚሆን ሰው አይኖርም ነበር ሲሉ ለሰው ልጆች በማዘን አምላክን ይጠይቃሉ።

ወደ ሰሙ ትርጉም ስንመለስ በዚህ ዓለም የሰው ልጆችን አድሎአዊነት የሚያሳይ ነው። በለጸጋ ለወዳጅ ዘመዱ፤ ሀብትና ንብረት ላለው ያደላል። ባለጸጋ በተሰጠው ሀብትና ንብረት ድሆችን ከመርዳት ለአቅመ ደካሞች ከመቆም ይልቅ በሀብት የሚመስሉትን ፤ውለታውን የሚመልሱለትን በመመልከት ላለው ያደላል። ሰው ከሰው ያበላልጣል ደሀውን ለመርዳት ለቡ አይፈልግም በማለት የሰውን ልጅ አድሎአዊነት ይናገራሉ።

## 4.3 ሃይማኖታዊ ጉዳይ

ሃይማኖት ከሰው ልጆች ሥጋዊ ዕይታ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን በማመን ተቀብለው የሚጓዙበት ነው። እነዚህን ረቂቅና ጸናን የሆኑ ሐይማኖታዊ ጉዳዮች አካል ነስተው ለሰው ልጅ ህሊና ቅርብ በሆነ መልኩ በግዕዝ ቅኔ ይቀርባሉ። ቅኔም መፈጠሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ቤተክርስትያን በመሆኑ ባለቅኔዎችም መሰረታዊ የሆነ የሃይማኖቱ እውቀት ያስፈልጋቸዋል። በዚህም በቅኔያቱ ውስጥ ነገረ ሃይማኖትን፣ ነገረ ቅዱሳንን፣ ነገረ ድህነት፣ህያውነትን የመሳሰሉት ጉዳዮች ይቀርቡባቸዋል። በዚህ ክፍልም ከመምህራኑ የተሰበሰቡ አስር ቅኔዎች በፍካሬ ጎዳና ተተንትነው ቀርበዋል።

## 4.3.1 ህያውነትን የሚገልጹ

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

ፍሡሐን ሔኖክ ወሱቱኤል ሕፃናተ ኤዶም እም።

እስመ አስተየቶሙ ኤዶም ለእሉ ሀሊበ ኅርየት ላሕም[25]።

**ትርጉም፦** የእናት ኤዶም ሕፃናቶች ሔኖክና ሱቱኤል ደስተኞች ናቸው።

ሔኖክና ሱቱኤልን እናታቸው ኤዶም የመምረጥ ላም ወተትን አጠጥታቸዋለችና።

የቅኔው ሠማዊ ክፍል የሚያመለክተው ህፃን ልጆች እናታቸው የጡቷን ወተት ስታጠጣቸው ደስተኞች፣ ሳቂታና ተጫዋቾች ይሆናሉ የሚል ነው። ወርቁ ግን ዘላለማዊነትን የሚገልጽ ሲሆን በሃይማኖት አስተምህሮም የሰው ልጅ ሞትን አሸንፎ ዘላለማዊነትን ወይም ህያውነትን ይጎናጸፋል። ይህ ህያውነት ግን እንደሌሎቹ የስጋ ሞትን ካስተናገዱ በኃላ ሳይሆን ሞትን ሳይቀምሱ ከነስጋቸው ህያው ሆነው የመኖር ምስጢር ነው። በሃይማኖት የሰው ልጅ በመልካም ምግባሩና ተጋድሎው ቢሞትም እንኳ ህያዊት ነፍሱ ከቅጣት አምልጣ ወደ ዘላለማዊ ህይወት ትሸጋገራለች። በሌላ አንጻር ደግሞ በሰሩት የተለየ የጽድቅ ተግባር ምክንያት አምላክ የመረጣቸው እንደሌላው የአዳም ልጅ የስጋ ሞትን ሳይቀምሱ ከዚህ ዓለም ኑሮ በመለየት በብሄረ ህያዋን ያኖራቸዋል። ባለቅኔዋም ሔኖክና ሱቱኤል በጽድቅ ስራቸው ወደ ሞትን ሳይቀምሱ ወደ ብሔረ ህያዋን እደተነጠቁ ገልጸዋል።

---

[25] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

### 4.3.2 ስለትንሳኤ

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

*አንተ ወልድ ኮናኔ አዳም ጸላኤ።*

*ቀተልከ አውደዘዘሔዋን መንገኒቅከ ትንሣኤ[26]።*

**ትርጉም፦** *የአዳም ገዢ ወልድ አንተ ሆይ፤*

*የሔዋን አደባባይ ሲታል ከዚህ በጠበንጃህ ትንሳኤ*

*ጠላት ዲያብሎስን ገደልክ።*

*ሠሙ* አንዳንድ ሰው ጠላቱን በአደባባይ ማለትም ሰው ባለበትና በግልጽ ቦታ በመሳሪያ ይገለዋል። ወርቁ የኢየሲስ ክርስቶስን ትንሳኤ የሚገልጽ ነው። ታሪኩ የሰው ልጆች አባት እና እናት የሆኑት አዳም እና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት የተነሳ ከገነት ተባረው ከነልጅ ልጆቻቸው በሲኦል መከራ ይቀጡ ነበር። አምላክም አዳምና ሔዋንን ወድቃችሁ ቅሩ ሳይል ፀፀታቸውንና መስዋዕታቸውን ተመልክቶ አዳምን ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሀለሁ ብሎ ቃል ኪዳን በገባለት መሰረት ሰው የሆነው አምላክ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደህጻናት ካደገ በኋላ ከአይሁድ እጅ መከራን ተቀብሎ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ተሰቅሎ ሞቶ ተነስቶ መቃብርን ድል ነስቶ የአዳምን ጠላት ዳቢሎስን ተበቅሏል። "በጠበንጃህ ትንሳኤ ጠላት ዳቢሎስን ገደልክ" ማለት የክርስቶስ ትንሳኤ እንደጠመንጃ ሆኖ የአዳምን ጠላት ዳቢሎስን ገሎታል ማለት ሲሆን የአዳምና የሔዋን መገኛ ሲኦል በክርስቶስ ትንሳኤ ድል ተነስቷል ማለት ነው። ባለቅኔዋም በዕምነቱ ውስጥ ያለውን የክርስቶስን ትንሳኤ ማለትም ሚስጥረ ትንሳኤን በቅኔያቸው ገልጸዋል።

### 4.3.3 የአምላክ ትንሳኤ ለቅዱሳት አንስት መገለጥ

**ቅኔ ፩ ዘአምላኪየ**

ለቀቢሮተ ወልድ ይብፅሓ አመዘወልደ አብ ሞት።

ይረውፃ እንዘይፀርሓ ቅዱሳት አንስት።

ወበከዋላሆን እደው አዛቦ ለታኦጎሎስ አሀሰት[27]።

---

[26]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

[27]የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

**ትርጉም፦** በአብ ልጅ ሞት ጊዜ ወልድ ሟችን ለመቅበር ይደርሱ ዘንድ፤

ቅዱሳት አንስት እየጮሁ ይሮጣሉ።

በኃላቸውም የታኦኅሎስ ጭራን የያዙ ወንዶች ይሮጣሉ።

የቅኔው ሠማዊ ጉዳይ በገጠሩ የሀገራችን ክፍል ሰው ሲሞትና መልዕክተኛ ሲላክ ሴቶች እየጮሁ ከፊት ከፊት ሲሮጡ ወንዶች ደግሞ ከኂላ እንደሚከተሉ የሚያመለክት ነው። ወደ ወርቁ ስንሄድ የክርስቶስን ትንሳኤ ቀድመው ያዩት ቅዱሳት አንስት ናቸው የሚል ነው። በቅዱስ ማርቆስ ወንጌል በምዕራፍ አስራ ስድስት ላይ ተገልጾ እንደምናገኘው የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ ለማየት የተመረጡት ሴቶች ነበሩ። ይህንን በሃይማኖቱ የከበረ ምስጢር ቀድመው በማየትና ለኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ለነበሩት ሐዋርያትም የተናገሩት እነዚሁ ሴቶች ነበሩ። በማህበረ ባህሉ ሴቶች ዝቅ ተደርገው የሚታዩ፤ ወንዱ ማሰብም ሆነ መስራት የሚችለውን ነገር ሁሉ መስራትም ሆነ ማድረግ የማይችሉ ተደርገው የሚታሰቡ ናቸው። በሃይማኖቱም በሔዋን ምክንያት ሴቶች የተገፉ ነበሩ። ይኸውም የሰው ልጆች አባት የሆነው አዳም ከገንነት የተሰደደው ከእርሱ አትብሉ የተባሉትን የገነት ፍሬ በሔዋን ምክንያት በመብላቱና ትዕዛዙን በማፍረሱ ነው። በዚህም ለሰው ልጆች ሁሉ በስቃይ እንዲኖሩና ሞት እንዲፈረድባቸው ሆኗል። ይህ ሁሉ የሆነው ቀድማ የሰይጣንን ምክር በሰማችውና አዳምንም ባሳተችው በሔዋን ምክንያት በመሆኑ እና በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ ሦስት ቁጥር አሥራ ሶስት ላይ እንደተገለጸው እሷንም ፈጣሪ ስለረገማት ነው። ነገር ግን አምላክ የሰውን ልጅ በይቅርታው ለማዳን ስጋ ለብሶ በድንግል ማርያም አማካኝነት ወደዚህ ምድር ሲመጣ የነበረባቸው እርግማንና ነቀፌታ ተወግዶ ሴቶች ተከብረዋል። ምክንያቱም በታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናገኘው አምላክ ወደዚህ ምድር ሲመጣ ለእናትነት የተመረጠችው ሴት ናትና። በልደቱ ሴትን እንዳከበረም በትንሳኤውም ከወንዶች አስቀድሞ ለሴቶች ትንሳኤውን ገልጧል ይህም የሴትን ልጅ ክብር ከፍ የሚያደርግ ነው። ባለቅኔዋም ሴቶች የአምላክን ትንሳኤ ከሐዋርያት ቀድመው ለማየት የተመረጡ መሆናቸውን በመግለጽ በሃይማኖቱ በኩል ምን ያህል እንደከበሩና ምስጢረ ትንሳኤን ያህል ታላቅ ነገር ቀድሞ ለማየት ቅዱሳት አንስት እንደተመረጡ በቅኔያቸው ገልጸዋል።

## 4.3.4 ስለዕርገት

**ቅኔ ፩ ሚበዝኑ**

ተበቋኢተ ወልድ ማኅረፅ ኀረቤተ ሰማይ ምድር ለሰማይ ኀረቤታ፡፡
በቢህሎተ ወልድ ማህረፅ ተመይጠኪ ፀውአታ፡፡
እምሀበ ጸታ ለምድር ሰማይ ወምድር ለፈጠረ ሰማይ ፆታ[28]፡፡

**ትርጉም፦** ወፍጮ ወልድን የምትጠቀም የሰማይ ኀረቤት ምድር፤
ይህቺ ሰማይ ኀረቤቷን ወፍጮ ወልድ ተመለሰልሽ ብላ ጠራቻት፤
ሰማይ ለምድር ወገኗ ከመሆኗ የተነሳ ምድርም ለሰማይ ወገኗ ከመሆኗ የተነሳ፡፡

የቅኔው ሠማዊው ሀሳብ የማህበረሰቡ ጉዳይ ነው፡፡ በማህበረሰብ ኑሮ ውስጥ ጉርብትና አለ፡፡ በጉርብትና ውስጥ አንዱ የአንዱን ጉድለት እየሞላ የሌለው ካለው ኀረቤቱ እየተዋዋሰ ኑሮውን ይቀጥላል፡፡"ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ኀረቤት" እንዲሉ በማህበረሰብ ውስጥ ጉርብትና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ከስጋ ዝምድና በላይ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት ነው፡፡ በጉርብትና ውስጥ የመተጋገዝ እና የመረዳዳት ጉዳይ ስላለ በአንዱ እቃ በጋራ በየተራ እየተዋዋሱ በመተሳሰብ እንደሚጠቀሙ የሚያሳይ ነው፡፡ ወደ ወርቃዊው ጉዳይ ስናመራ የኢየሱስ ክርስቶስን እርገት የሚገልጽ ነው፡፡ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ዓበይት በአላት ተብለው ከሚከበሩት ውስጥ አንዱ እርገት ነው፡፡ እንደ ቤተ ክርስትያኒቱ አስተምህሮ አምላክ ሰውን ለማዳን በስጋ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሰው በምድር ላይ በመመላለስ ስርዓትን ከፈጸመ በኃላ በመስቀል ተሰቅሎ በስጋ በመሞት በትንሳኤ በመነሳት በእርገት ወደ ቀደመ ክብሩ ወደ ሰማይ አርጓል፡፡ ባለቅኔዋ ጌታ መጀምሪያ ከሰማይ ወደ መሬት ወደ ድንግል ማርያም መውረዱን ሰማይ ለምድር መንገሯ በኃላም በዕርገቱ ከምድር ወደ ሰማይ መውጣቱን ምድር ለሰማይ ነገረቻት ብለው በመጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ ሃያ አራት ላይ የተነገረውን የጌታን እርገት አመስጥረው ገልጸውታል፡፡

[28]የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

### 4.3.5 ስለአማላጅነት

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

ማርያም ብእሲት ለስምዖን አቃቤ ኤዶም ገነታ፡፡

ከመኢትየውሆ ዘሲኦል ለዝንቱ እስመ ትምዕዶ በቤታ[29]፡፡

**ትርጉም፦** ማርያም ሴትዮ የገሮዋ ኤዶም ጠባቂ ስምዖንን፤

የሲኦል መከራ ዘማ እንዳታታልለው በቤት ምህረቷ ስምዖንን ፤
እሱን ትመክረዋለች እኮ፡፡

ለሠሙ አንዳንድ በዓለም ባሉ ዘማውያን ምክንያት የተጠበቁ የዋህ ሰዎች እንዳይሰናከሉ ማርያም የተባለችው ሴትዮ ትመክረዋለች የሚል ነው፡፡ ለወርቁ ስምዖን በላኤ ሰብ በድንል ማርያም አማላጅነት ከሲኦል መዳኑን የሚያመለክት ነው፡፡ በተዓምረ ማርያም እንደተገለጸው ስምዖን ሰባ ስምንት ሰዎችን የበላና ይንን ግብሩን የሚገልጽ መጠሪያ ያለው በላኤ ሰብዕ ከባህሪው ውጪ የሆነውን እንደ ዱር አራዊት የሰውን ስጋ በመብላት የሰባ ስምንት ሰዎችን ሕይወት ያጠፋ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ ምንም ጨካኝ ቢሆን ትንሽ ርህራሄ አይታጣበትምና የሚበላው ሰው ፍለጋ ላይ ባለበት ሰዓት  በቁስል የነደደ ሰው ስለማርያም ውሃ አጠጣኝ ሲለው አጠጥቶታል፡፡ የሰው ልጅ ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከሞት የሚቀር የለምና ይህ በግብሩ የሚጠራው በላዔ ሰብዕ እለተ ሞቱ ደርሶ ከሞተ በኃላ በአምላክ ፊት ለፍርድ ሲቀርብ ያቺ ጥርኝ ውሃ እንደ ትልቅ ዋጋ ተቆጥራ በድንግል ማርያም አማላጅነት ከሲዖል መከራ ነጻ ወጥቷል፡፡ ባለቅኔዋ የድንግል ማርያምን አማላጅነት የብላዔ ሰብዕን ከዘላለም ቅጣት መዳን በቅኔያቸው አመስጥረው አቅርበውታል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ቅድስት ድንግል ማርያምን በአማላጅነቷ ስለሚያምኑና ይህ የስምዖን በላዔ ሰብዕ የድህነት ታሪክ ተዘውትሮ ስለሚነገርና የበዛው ሀጢያቱ በምልጃዋ በመሻሩ ምክንያት ድንግል ማርያምን የበላዔ ሰብዕ አማላጅ በማለት ይጠሯታል፡፡ ባለቅኔዋም ቅድስት ድንግል ማርያም ስምዖን በላዔ ሰብዕን አማልዳ ምህረትን አሰጥታዋለች ከሲዖልም አድናዋለች በማለት ገልጸዋል፡፡

---

[29] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

### 4.3.6 ስለቅዱሳን ተዓምር

**ቅኔ ፩ መወድስ**

አልቦ ሀሰት በደብረ ድማህ በከመ አልቦሙ ሀሰት ብሔረ ብፁዓን ወገነት።
ብሔረ እዝራ ወሄኖክ እንተ ኢሃሎ ሀሰት።
ለእመ ሰዳዲት ወለእመ ውሉድ ለጻዲቅ ተከስተ ብርሃን ምቋሙ በጽሃት።
ወጽዋዑኒ ለማቴዎስ ህላዌ መነኮስ ዋህድ ቅድመ መነኮሳት ሰማዕት።
ለንጉሥሂ ሠራዊቱ ዘኢትዮጵያ ቅድስት።
ማየደብረ ድማህ ከመይስትዩ ለእመፈቀደሰራዊት።
ማየ ኮኩህ አንቅሃት ዘሰረቀ ብርሃን ጸሎት።
ድህረ ህልፈቱ ለተክለ አልፋ በትረተክለ አልፋ ተናገረት።
እስመብእሴ እግዚአ ኮነ ስማ ዘሔኖክ ሕይወት[30]

**ትርጉም፦** ዲማ በሚባል ቦታ ውሸት የለም የተባረኩ ህዝቦች ሀገር ስለሆነ፤
በእዝራ እና ሄኖክ ሀገር ውሸት የለም ወይም አይታወቅም፤
ፃድቃን ለሆኑት ለተሰደዱትም ለተወደዱትም ብርሃን ተገልጦላቸዋል።
ከመነኩሴዎች ቀዳሚ የሆነ ማቴዎስ መነኩሴ ጽዋ፤
የቅድስት ኢትዮጵያ የንጉስ ሠራዊት (የዲማን ውሃ ሠራዊቱ እንዲጠጡ )፤
የውሃው ድምጽ ለጥዋት(ፀሐይ ስትወጣ ) ለፀሎት ይቀሰቅሳቸዋል።
ተክለ አልፋ ከሞተ (ከአረፈ) በኃላ የሱ በትር (መቋሚያ) ተናገረች።
ስሟ የሄኖክ ሕይወት ሆኗልና።

በሰሙ የተገለጸው ዲማ በተባለው ቦታ ሀሰት አይነገርም ምክንያቱም የዲማ ህዝቦች ለፈጣሪያቸው የተገዙ ስለሆኑ የሚል ነው። የቅኔውን ወርቃዊ ጉዳይ ስንመለከት በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም በአስራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በገዳሙ የነበሩ ቅዱሳንን ተዓምር የሚገልጽ ነው። ተኣምር እንደ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት "በቁሙ ታምር ታምራት ድንቅ ምልክት እንደ ነቢያት እንደ ሐዋርያት በእግዜር ኀይል በክርስቶስ ስም ካልኾነ በቀር ማንም ሰው ሊሰራው የማይችል ልዩ ድንቅ ጉድ ብርቅ የኾነ አምላካዊ ስራ"።(1948፣ 228)በማለት ይተረጉሙታል። ተኣምር ከሰዎች አቅምና ችሎታ በላይ የሆኑ ነገሮች በፈጣሪ ሀይል ሲፈጸሙ ሲሆን ፈጻሚው አካል በፈጣሪው የተመረጠ ልዕለ ሰብዕ ነው። ይህ ልዕለ ሰብ

---

[30] የእማሆይ ኀሪት ቅኔ

በህይወት እያለ ድንቅ ድንቅ ተኣምራትን ያከናውናል፤ ከዚህ ዓለም ከተለየ በኋላ በሱ ስም የተለያዩ ተኣምራት ይከናወናሉ፡፡ በዚህ ቅኔ ውስጥ የቀረቡት ተኣምራትም ልዕለ ሰቦቹ ወይም ቅዱሳኑ በይህወተ ስጋ ከተለዩ በኋላ የተፈጸሙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የአባ ማቲዎስ ተዓምር ነው፡፡ አባ ማቲዎስ ለዲማ አምስተኛው መምህር የነበሩ እና በገዳሙ ታላላቅ ታምራትን ያደረጉ አባት ናቸው፡፡ ተኣምሩም የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም አጭር ታሪክ በሚለውና በመምህር ወልደ ኢየሱስ መቅጫ በተጻፈው መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው "የገዳሙ ማህበር በየማዕረጋቸው ተቀምጠው በአንድ ቤት ይበሉ ይጠጡ ነበር፡፡ ከእለታት በአንድ ቀን እንደተለመደው በአንድነት ሲመገቡ ሳለ አንዱ መንፈሰ ስስት አድሮበት ጠጥቶ አልጠጣሁም አለ፡፡ ሊቀ ረዱም የአባታችን ጽዋ ይመስክርብን አለውና መስክርልን ቢሉት በእኔ አንድ ጠጥቷል ብሎ መሰከረ፡፡(2009፣11) ባለቅኔዋ ይህንን የአባ ማቲዎስን ጽዋ ምስክርነት በመጥቀስ ነው በዲማ ላይ ውሸት የለም ሲሉ ቅኔ የተቀኙ፡፡

ሁለተኛው የቅኔው ሀሳብ ደግሞ የአባ ተክለ አልፋን ተዓምር የሚገልጽ ሲሆን ይህም አባ ተክለ አልፋ በዚሁ በዲማ ገዳም የነበሩ መምህር ሲሆኑ በቅኔው ላይ እንደተገለጸው እሳቸው በሚኖሩበት ዋሻ ሰው አልነበረምና ከዚህ አለም ባረፉ ጊዜ መቋሚያቸው እንደሰው አፍ አውጥታ ለገዳሙ መነኮሳት ማረፋቸውን ተናግራለች፡፡ "ሲያርፉም ለገዳሙ መነኮሳት መቋሚያቸው እንደተናገረች ገድላቸው ይናገራል በሚጸልዩበት ዋሻ ሰው አልነበረምና" (2009፣ 13) ባለቅኔዋም ሰፊ የሆነውን የቅዱሳንን ገድል በቅኔያቸው አምጥተው ገልጸዋል፡፡

### 4.3.7 ሄሮድስ ስላስፈጃቸው የኢየሩሳሌም ህጻናት

**ቅኔ ፮ ጉባኤ ቃና**

በዘሞተ ወልደ ሶልያና ኢትህዝኒ ሰይፍ፡፡
እስመ ያእክሉኪ ደቅ ወውእቶሙ አዕላፍ[31]፡፡

**ትርጉም፦** ሰይፍ ሴትዮ ሆይ በሞተው በማርያም ልጅ አትዘኚ፤
ያሉ ልጆችሽ ይበቁሻልና እነዚህም ዕልፍ ናቸውና፡፡

የቅኔው ሠማዊ ሀሳብ በልጇ ሞት ምክንያት በሀዘን ውስጥ ያለችን እናት የሚያጽናና ነው፡፡ ከብዙ ልጆች መካከል አንዱን በሞት የተነጠቀች እናት ልጆቿ ብዙ ናቸውና በሞተው አላዝንም አትልም በመሆኑም አብዝታ ታለቅሳለች፡፡ የሚጽናናው ሰው ግን ሌሎቹን ልጆች በመመልከት ተጽናኚ በሞተው ልጅሽ አትዘኚ እያለ ይመክራታል፡፡ ወደ ወርቃዊው ጉዳይ ስንመለስ የኢየሱስ

---

[31]የእማሆይ ኅሪት ቅኔ

ክርስቶስን ስደትና የቤተ ልሄም ህጻናት በሄሮድስ ሰይፍ ማለቃቸውን የሚግልጽ ነው። የቅኔው ታሪክ በማቲዎስ ወንጌል በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልጾ እንድምናገኘው ሰባሰገል በሄሮድስ ዘመን በቤተልሔም የተወለደውን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማየት እና ለመስገድ ከምስራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣታቸውን ሲሰማ የተወለደው ኢየሱስ ምድራዊ ንጉስ ነው መንግስቴን ይገዳደረኛል ብሎ በማሰቡ ምክንያት ለማጥፋት  ሄሮድስ ካያችሁት በኃላ እኔም እሰግድለት ዘንድ በእኔ በኩል ተመለሱ አላቸው ሰባ ሰገልም ባዩት ራዕይ ምክንያት ወደ ሄሮድስ ሳይሄዱ መንገዳቸውን ቀይረው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ሄሮድስም ሰብአ ሰገል እንዳታለሉት በተረዳ ጊዜ በቤተ ልሄም ያሉ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ህጻናት በሙሉ በሰይፍ ፈጃቸው። በዚህ ወቅት ሄሮድስ የመንግስቴ ተቀናቃኝ ያለውን ኢየሱስ ከተገደሉት ህጻናት መካከል አልተገኘም ምክንያቱም ኢየሲስ ክርስቶስ በእናቱ ጀርባ ላይ ሆኖ ወደ ግብጽ ምድር ተሰድዶ ነበርና። ባለቅኔዋም በቤተልሄም አስራ አራት እልፍ የቤተልሄም ህጻናት ሲፈጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አለመገደሉን ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ተነስተው አመስጥረውታል።

### 4.3.8 ስለሰው ተፈጥሮ

**ቅኔ ፩ ጉባኤ ቃና**

እሳት ወማይ ባህርዮሙ ለሰብአ ገሞራ ወኖኅ።
ይትበሀሉ ሕዝብ ምስጢራተ ቅኔ ብዙኅ[32]።

**ትርጉም፦** የገሞራና የኖህ ሰዎች ባሕርያቸው እሳትና ውሃ ነው።
የበዛ ቅኔ ፈጣሪ ምሥጢራቶች ሕዝቦች ይባባላሉ።

ሠሙ የሰው ልጅ በተናደደ ጊዜ እሳት ይሆናል፣ ይቆጣል፣ ስሜታዊ በመሆን እሳታዊ ባህሪን ያሳያል። ወዲያው ደግሞ ንዴቱ ሲለቀው እና ሲረጋጋ ደግሞ ይቀዘቅዛል ውሃ ይቀዘቅዛልና የውሃነት ባህሪ ይታይበታል። የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ሁሉ እነዚህ የእሳትነትና የውሃነት ባህሪያት ሲፈራረቁበት ይኖራሉ። እነዚህ ባህርያቱም የሰውን ልጅ ሥነ ፍትረት ከእሳትና ውሃ መፈጠሩን የሚያስረዱ ናቸው የሚል ነው። ወርቃዊ ሀሳቡ ደግሞ በሥነ-ፍጥረት  የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ከአዳም ጀምሮ ከፈጣሪው የታዘዘውን ትዕዛዝ በማፍረስ በደልን እየፈጸመ በተለያዩ ጊዜያት ቅጣት ደርሶበታል። ከነዚህ ቅጣቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱት በኖሕ ዘመን የነበሩትና ሰዶምና ገሞራ በሚባሉ ከተሞች የነበሩ ሰዎች ናቸው ። በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ ስድት ላይ  እንደተገለጸው በኖሕ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች

---

[32]የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

ሀጢያት በማብዛታቸው ምክንያት በኖህ አማካኝነት ከሀጢያታቸ እንዲመለሱ ቢነገሩም ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ጻድቅ የነበረው ኖህ ከቤተሰቦቹ ጋር ሲተርፍ በዛ ዘመን የነበሩ የሰው ልጆች በሙሉ በጥፋት ውሃ አማካኝነት አልቀዋል። በዚሁ በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ አስራ ዘጠኝ ሎጥ ከሁለቱ ልጆቹ ጋር በመሆን ሲተርፍ ሌሎቹ የሰዶምና ገሞራ ሰዎች በአጢያታቸው ምክንያት እሳት ከሰማ ወርዶ አጥፍቷቸዋል። የሰው ልጆች ስነ-ፍጥረት ከአራቱ ባህርያተ ስጋ እና ከሦስቱ ባህርያተ ነፍስ የተፈጠረ ነው። እነዚህም እሳት፣ ውሃ፣አፈር እና ነፋስ ናቸው። ባለቅኔዋም የሰው ልጅ ከእነዚህ ነገሮች የተፈጠረው የሰው ልጆች በገዛ ክፉ ስራቸው ምክንያት የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ባህርያቸው ወይም ተፈጥሮአቸ በእሳት ሲጠፉ የኖህ ዘመን ሰዎችም በውሃ ጠፍተዋል በማለት ቅኔያቸውን አመስጥረዋል።

### 4.3.9 ስለኀጢያት

**ቅኔ ፩ ዋዜማ**

ይእቲ ሞአባዊት ዘመነ ቀኖና ዘወልድ ዘታስተጋብእ አበሳ።
ዘጢሮስ ዘርዓሙአባዊ ዘግዘፍ ሮሳ።
ማህደሪሀ ባሶረ መብዝኄብዙኅ ተውዳሳ።
ከመትግበር ዝኮ ዘይትዋቀሳ።
እስመዛቲ ኀልየት አበሳ[33]።

**ትርጉም፦** ያቺ የሆነች ሞአባዊት የወልድ ክረምት የቀኖና ዘመን በዚያ ዘመን ጊዜ፤
የልጅ ድንዳኤ ወገን የሚሆን የሞአባዊ የዘር ጢሮስ በደል ሀብትን
የምትሰበስብ ናት።
ምስጋናዋ የብዙ ብዙ የሆነላት ወደ ቤት ስጋዋ ሀብትን የሰበሰበች ናት።
በወገኖቿ በላተኞች ዘንድ እሷ የሚከራከራትን ታሳፍር ዘንድ እሷ
አስባለችና።

ሠሙ ያልተጠመቁ ክርስትያን ያልሆኑ ሰዎች ሀብትን በመሰብሰብ ስጋቸውን ያደልባሉ። አብዝቶ በመብላትም ስጋቸውን ያገዝፋሉ። ወርቁ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ ላይ እንደተጠቀሰው ሙአባዊያን የተባሉት ከአባታቸው የወለዱት ከሎጥ ሁለት ሴቶች መካከል የታላቋ ልጅ ከአባቴ የወለድኩት ስትል ሞዓብ ብላዋለች። የእርሱ ዘሮችም ሙዓባውያን ይባላሉ። ሙዓባውያን እግዜብሔርን የማያመልኩ ህዝቦች ናቸው። ባለቅኔዋም ክርስትያን

---

[33] የእማሆይ አመተማርያም ቅኔ

ያልሆነችውን ሴት በጾም ጊዜ ሀጢያትን ትሰራለች በደልን ታደርጋለች። መብል መጠጥን በማብዛት በደልን ትፈጽማለች። የሰው ልጅ አብዝቶ ከሚበላ ይልቅ አብዝቶ ቢጾም ራሱን በመግዛት ለሐይማኖቱ ህግና ስርዓት ተገዢ ይሆናል። ሲጾም የተራቡትን፣ የተጠሙትን፣ የታረዙትን በማሰብ ለሰዎች መልካም ማድረግን ይለማመዳል። ለህሊናው በመገዛት ለሰው ልጆች ሁሉ ማሰብ ተግባሩ ይሆናል። መብልና መጠጥን ማብዛት ሰውን ከሰዋዊ ባህሪው ወደ እንስሳነት ይቀይረዋል። የመጀመሪያው ሰው አዳም አጢያት የሰራው አትብላ የተባለውን በመብላት በመሆኑ መብል የበዛ እንደሆነ የሰው ልጆችን አጢያት ወደ መስራት ይገፋቸዋል።

### 4.3.10 ስለጷጉሜ

**ቅኔ ፩ ዘአምላኪየ**

በዋኢየ ይእቲ ግብር ዘዲሜጥሮስ እልመክኑ።
ዘተከሰተ ወዘኢተከሰተ ዘፈጠረ መኑ።
እስመ ለሕፃን ጷጉሜን ቀሰፋ ዘእንበለ ትልሀቅ ቦኑ[34]፣

**ትርጉም፦** የተገለጠውንና ያልተገለጠውን የፈጠረ ዲሜጥሮስ ጌታ፤
በሱ ስራ የሚገባ ማነው።
ሕፃን ጷጉሜን ሳታድግ በዕውነት ቀስፏታልና።

ሠሙ በአምላክ ስራ ማን ሊገባ ይችላል የሚል ነው። ፈጣሪ የፈለገውን ያደርግ ዘንድ ስልጣን ስላለው ለምን ይህን አደረክ ለምን ያንን አላደረክም አይባልም። የወደደውን በፈለገው ጊዜ ሊፈጽም ስልጣን አለው። አንዱ በህጻንነቱ በሞት ይወስደዋል ሌላውን በአፍላ እድሜው በወጣትነቱ ይወስደዋል አንዱን ደግሞ እረጅም እድሜ እንዲኖር ያደርገዋል። ሁሉም የአምላክ ስራ ነውና፤ የሰው ልጅ ይህንን የፈጣሪ ፍርድ ተቃውሞ ማስቀረት አይችልም። ወደ ወርቃዊው ጉዳይ ስንመለከት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ውስጥ የሚገኘውን ባህረ ሀሳብ ወይም የዘመን አቆጣጠር የቀመረው ቅዱስ ዲሜጥሮስንና ጷጉሜን የሚመለከት ነው። ዲሜጥሮስ አስራ ሁለተኛው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ሲሆን ባህረ ሀሳብን ወይም የዘመን አቆጣጠርን በመቀመር በአመት ውስጥ ያሉ ወራትን በመከፋፈል በዓላትና አጽዋማት የሚውሉበትን ቀን የደነገገ ታላቅና ቅዱስ ሰው ነው። ባለቅኔዋም ኢትዮጵያን በዓለም ልዩ ከሚያደርጓት በርካታ ነገሮች አንዱ የሆነውና የአስራ ሦስት ወር ጸጋ ባለቤት ተብላ የምትጠራበትን የዘመን ቀመሯን በማምጣት ሊቁ በዓመት ውስጥ ያሉትን ቀናትና ወራት በመከፋፈል ሰላሳ ሰላሳ አድርጎ

[34]የእማሆይ ኀሪት ቅኔ

ሲያስቀምጥ ጷጉሜን አምስት ቀን ከአራት አመት አንድ ጊዜ አድስት ቀን በማድረግ  ከሌሎቹ አሳነሳት ሳታድግ ቀጫት የሱን ህግ ማን ሊያፈርስ ይችላል በማለት በዓመቱ መጨረሻ ላይ የምትመጣዋን ጷጉሜን እና የዘመንን ቀመር የቀመረውን ዲሜጥሮስን ገልጸዋልን፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በሁለት የሴት ቅኔ መምህራን ላይ የተደረገ ሲሆን ትንታኔው የቅኔ መምህራኑ የህይወት ታሪክና ቅኔዎቻቸው ላይ አተኩሯል። በዚህ መነሻነትም በጥናቱ የእማሆይ ኀሪት ደባስ እና የእማሆይ አመተማርያም አሰፋ የህይወት ታሪክ እና የሚቀኟቸው ቅኔዎች ይዘት የፍካሬ ስልትን በመጠቀም ተተንትኗል። በቅኔያቱ ውስጥ ምን ምን ጉዳዮች እንደሚነሱም አሳይቷል። የጥናቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ የሶስት ዙር የመስክ ቆይታ ቃለ መጠይቅና የምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል። የታሪኩ ባለቤት የሆኑ የቅኔ መምህራንን ታሪክና ቅኔዎቻቸውን፣ የቅኔ ተማሪዎቻቸውን እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ አካላትን የሚመለከቱ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ ሲሆን የቅኔ ማስተማሩ ሂደት ደግሞ ተፈጥሯዊ መቼትን በመጠቀም በምልከታ ተሰብስቧል። መረጃዎቹም በምስልና ድምጽ መቅረጫዎች ተሰንደዋል። በጥናቱ ውስጥ የቀደምት ስራዎች ቅኝት በማድረግ ያነሱትን ጉዳይ፣ ደካማና ጠንካራ ጎኖች፣ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎ በአግባቡ ተፈትሾ ቀርቧል። በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የሚገለጹ የቅኔን ምንነት፣ አጀማመር፣ አይነቶችና መንገዶችን የሚያሳዩ ሀቲቶች የተለያዩ የሙያው ሊቃውንት ያነሱትን ሀሳብ በማምጣት ለማብራራት ተሞክሯል። በንድፈ ሀሳብ ደረጃም ጥናቱ ሁለት ጉዳዮችን ዓላማ ያደረገ በመሆኑ ግለተረክ ንድፈ ሀሳብንና ፍካሬን በማምጣት የንድፈ ሀሳቦችን እሳቤ ብሎም ለጥናቱ የሚያገለግሉበትን ሁኔታ የሚያትቱ ሀሳቦች ተብራርተዋል።

በምዕራፍ ሦስት የጥናቱ አንድ አካል የሆነው የቅኔ መምህራኑ የህይወት ታሪክ ከታሪኩ ባለቤቶች በቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ መሰረት የእያንዳንዳቸው ታሪክ በተናጠል ቀርቧል። በዚህ ክፍል የቅኔ መምህራኑ የትና መቼ ተወለዱ?፤ አስተዳደጋቸው ምን ይመስል ነበር?፤ ወደ ቤተክርስትያን ትምህርት እንዴት ገቡ?፤ ለቅኔ ትምህርታቸው የቤተሰብ ድጋፍ ምን ይመስል ነበር?፤ቅኔውን የት የትና ከማን ተማሩት?፤ የቅኔ ትምህርት ከቤተሰብ እርቆ ከደብር ደብር ከመምህር መምህር ተዟዙሮ ረሀብና ጥሙን ታግሶ ቁራሽ ለምኖ በብዙ ደጅ ጥናት እና ፈተና የሚማሩት እና ለሴት ልጅ ከበድ ያለ በመሆኑ እነዚህ የቅኔ መምህራን ይህን ውጣ ውረድ እንዴት አለፉት?፤ በተማሪነታቸው ወቅት ማህበረሰቡ የነበረው ድጋፍ ምን ይመስል ነበር?፤መምህርስ ከሆኑ በኂላ የተማሪዎቻቸው ሁኔታምን ይመስላል?፤ የሚሉ ጉዳዮች

ተብራርተው ቀርበዋል። በዚህ መሰረትም የቅኔ መምህራኑ ታሪክ በአብዛኛው ቢመሳሰልም ጥቂት የማይባሉ ልዩነቶች እንዳሏቸውም ለማስተዋል ተችሏል። የሚያመሳስላቸው ጉዳይ ሁለቱም የተወለዱበት አካባቢ ተቀራራቢ መሆኑ፤ ወደ ቅኔው ትምህርት የገቡበት አጋጣሚና ሁኔታ፤ የቅኔውን ትምህርት ከልጅነታቸው የመጀመራቸው አጋጣሚ፤ ትምህርቱን አብረው ለብዙ ጊዜ መማራቸው ብሎም አሁን ያሉበት ሁኔታ ነው። ልዩነታቸው ደግሞ እማሆይ አመተማርያም ከቅኔው ትምህርት በተጨማሪ በዘመናዊው ትምህርትም በመግባት እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ዘልቀው ዲፕሎማና በሁለት የተለያዩ የትምህርት መስኮች ዲግሪን ያገኙና አሁንም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን እየተማሩ ያሉ በመሆናቸው ለትምህርት ያላቸው አቋምና ጥንካሬ ልዩ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም ደግሞ እማሆይ አመተማርያም በቅኔው ሙያ ወንዶችንም ሴቶችምን ያስተምራሉ። እማሆይ ኅሪት በመንፈሳዊው ትምህርት ብቻ ተወስነው ያሉና በቅኔው የማስተማር ሂደትም ሴቶችን ብቻ ለይተው ማስተማራቸው ነው።

በታሪኩ ውስጥ የታየው  ጉዳይ አንዱ የአብነት ተማሪው ትምህርቱን ለመማር የሚያደርገው ጉዞና የሚከፍለው መስዋዕትነት ሲሆን። ይህ ጉዳይም በሁለቱ መምህራን የትምህርት ጉዞ ውስጥ ይታያል ። እማሆይ አመተማርያምና እማሆይ ኅሪት በቅኔው ሙያ በቅተው ለመገኘት ከሀገር ሀገር፤ ከደብር ደብር፤ ከመምህር መምህር ተዘዋውረው ረጅም አመታትን ፈጅተው መማራቸው የቅኔ እውቀት በብዙ ውጣ ውረድ እንደሚገኝ ለማየት ያስችላል። ሁለተኛው ደግሞ ዓርአያ ሊሆን የሚችለው የማህበረሰቡን የመረዳዳት እና የሌላውን ሰው ልጅ እንደራሱ አድርጎ የማስተማር ባህል ነው። ይህ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል አሁንም ድረስ ያለ መልካም ተግባር ሲሆን ተማሪው የአብነት ትምህርቱን ለመማር የተወለደበትን ቀዬና ቤተሰቡን በመተው ወደማያውቀው ሀገር ሲሄድ የሚይዘው ስንቅም ሆነ ገንዘብ ሳይኖረው የሚሄድበትን ማህበረሰብ ያስተምረኛል ብሎ በልበ ሙሉነት ጉዞውን ያደርጋል። ማህበረሰቡም “ከየት መጣህ?”፣ “ማነህ?” ሳይል ያለውን እየለገሰ ለቤተክርስትያን፣ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅሙ ሊቃውንትን እንዲፈሩ ያደርጋል። ይህም በታሪኩ ውስጥ የታየ ሲሆን እነዚህ ሴት የቅኔ መምህራን እንደወንዶቹ በየሰፈሩ ዙረው መለመን ባይችሉም እንኳን ታሪካቸውን የሰማ ከሩቅም ሆነ ከቅርብ ስንቅ በመውሰድ፣ አነስተኛ ቢሆንም እንኳ በየወሩ ገንዘብ በመላክ እንደልጆቹ እየተንከባከበ ለቁም ነገር አድርሷቸዋል። ማህበረሰቡን በማስገንዘብና በማስተባበር በርካታ ተማሪዎችን ከየአቅጣጫው ሰብስባ በማስተማር አንቱ የተባሉ ሊቃውንትን ስታፈራ የነበረችውና ያለችው ቤተክርስትያን ወላጅ አልባ ህጻናትን ከሚያሳድጉ የተለያዩ ተቋማት ውስጥ አንዷ መሆኗን

ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በጥናቱ የታየው ሌላው ጉዳይ የቅኔ ተማሪው የእርስ በርስ መተሳሰብ ነው፡፡ ይህም በአብነት ትምህርት ቤት አዲስ ተማሪ ሲመጣ እግር አጥበው ከለመኑት ቁራሽ አብልተው የብቸኝነት ስሜት እንዳይሰማው በማድረግ ያላምዱታል፡፡ ይህም ረጅሙን የትምህርት ጉዞ በትዕግስት እንዲማረው የራሱ የሆነ አስተዋጽዎ አለው ፡፡ በዚህ ጥናት እንደታየው ወንዶቹ የቅኔ ተማሪዎች እነማሆይን ሊርባቸው ይችላል በማለት ለምነው ካገኙት ቁራሽ ያካፍሏቸው እንደነበር በታሪኩ ውስጥ ተገልጿል፡፡ ይህም የተማሪውን የመረዳዳትና የመተሳሰብ ባህል ያሳያል፡፡

በምዕራፍ አራት የመምህራኑን ቅኔያት በመሰብሰብ ሰፊ ትንታኔ ተደርጓል፡፡ ቅኔያቱ በሦስት ዓበይት ርዕሶች የተከፈሉ ሲሆን የመጀመሪያው ማህበራዊ ጉዳይን የሚመለከቱ የሰው ልጆችን ህይወት የሚዳስሱ ስለ ምክር፣ ውለታ፣ ስለእድሜ፣ ስንፍና፣ ስለሚዜ ኩቡርነት፣ቅጣት፣ ስለ ሴትነት፣ እናትነት፣ ስለ ሴት ልጅ ክብር፣ ስለ ሴት ልጅ አስፈላጊነት፣ ስለ ሴት ልጅ ጀግንነት እንዲሁም ስለ ኢትዮጵያ የሚገልጹ ቅኔዎች ተፈክረው ቀርበዋል፡፡ በትንታኔው እንደታየውም ባለቅኔዎቹ የሚኖሩበትን ስርዓተ ማህበርና የሰውን ልጅ የሚመክሩ፣ የሚወቅሱና መልካም ባህሉን የሚገልጹ ብሎም የሰውን ልጅ ማንነትና ባህርይ የማሳየት አቅም ያላቸው ቅኔዎች እንደሆኑ ታይቷል፡፡ ሌላው በቅኔዎቹ የታየው ጉዳይ ሴትነት ሲሆን የቅኔዎቹ ድምጸትም ሴት መከበር አለባት፣ የሴት ልጅ ውለታ ታላቅ በመሆኑ ውለታዋ መታሰብ አለበት፣ ጀግና ናት የሚሉ ናቸው፡፡ በእነዚህ ቅኔዎችም መምህራኑ ሴት ልጅ በማህበረሰቡ አስተሳሰብና ተግባር ውስጥ የተናቀች፣ እንደሰው የማትቆጠር፣ በአባዊው ስርዓት ተጽዕኖ የተጎዳች ሆናለች በማለት በሀይማኖቱ በኩል ከቅዱሳት መጻህፍት የድንግል ማርያምን እና የቅዱሳት አንስትን ታሪክ በማምጣት ሴቶች ምን ያህል እንደተከበሩና ለወንድ ልጅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ ገልጸውባቸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ማህበራዊ ጉዳዮችን የያዙ ቅኔዎች የሰውን ልጅ ህይወት የሚዳስሱ በመሆናቸው የግዕዝ ቅኔ ሐይማኖቱ ላይ ብቻ የሙጥኝ ያለ ሳይሆን ሰዋዊ የሆኑ ታላላቅ ዕሳቤዎች ተራቀው የሚቀርቡበት ጥበባዊ ፈጠራ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሁለተኛው ፍልስፍናዊ ጉዳይ ሲሆን እነዚህ ቅኔዎች የሰውን ልጅ ምኞትና ፍላጎት የሚገልጹ ዕረቂቅ የሆነውን ሞት የሚሞግቱና ሃይለኝነቱን የሚያሳዩ የአምላክን ፍርድ የሚጠይቁ እንደሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡

ሦስተኛው ሐይማኖታዊ ጉዳይን የሚመለከቱ ቅኔዎች ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን በዚህም መልካም ምግባርና የጽድቅ ስራ የሚያጎናጽፈውን ዘላለማዊነትና ህያውነትን የሚገልጹ፣

የአምላክን ትንሳኤ፣ የሰውን ልጅ ድህነት፣ ስለ ቅዱሳን አማላጅነትና ተዓምር፣ ስለ ሰው ልጅ ተፈጥሮ (አፈጣጠር)፣ በሐይማኖቱ ውስጥ ያለውን የሴትን ልጅ ክብርና ለምስጢር መመረጥ፣ ስለ አምላክ ዕርገት እንዲሁም የቤተ ክርስትያንን ዘመን አቆጣጠር የሚገልጹ ቅኔዎች እንደሆኑ ተስተውለዋል። እነዚህ ቅኔዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን የሚገልጹ፣ የሚሰብኩ፣ የሚያስተምሩ ሲሆኑ በዚህም ቅኔ ለመቀኘት የሐይማኖቱን አስተምህሮ መረዳት፣ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ያሉ ታሪኮችን እና ነገረ ቅዱሳንን ማወቅ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ታይቷል።

በአጠቃላይ መምህራኑ በቅኔዎቻቸው ውስጥ ማህበራዊ ጉዳዮች በስፋት እንደሚገለጹባቸው የተስተዋለ ሲሆን እነዚህን ዕሳቤዎች ሲገለጹም ከሐይማኖታዊ ታሪኮች ጋር አጣምረው እንደሚገልጹ ማወቅ ተችሏል። የግዕዝ ቅኔም ሥነ-ጽሑፋዊ ዋጋው ከፍ ያለ በዘይቤ የበለጸገ ለምርምር የሚጋብዝ ጥልቅ የሆኑ ዕሳቤዎች የሚገለጹበት ጥበብ እንደሆነ ታይቷል። በምልከታዬ እንዳስተዋልኩት ቅኔያቱ ቅርጻቸው ቢጠና በተጨማሪም በቅኔ ቤት ያለው ክዋኔ ቢጠና አዋጪ ይመስለኛል።

# ዋቢ ጽሑፎች


ሀብተማርያም ወርቅነህ። *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣1963 ዓ.ም።

ላዕከ ማርያም ብርሀኑ። "ጉዳያቸውን ማህበራዊ ፣ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ያደረጉ የግዕዝ ቅኔያት ይዘታዊ ትንተና"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ፣ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 2010 ዓ.ም፣ ያልታተመ

ማርዬይግዛው። *ቅኔያዊ የዕውቀት ፈጠራ*። አዲስ አበባ፣ ዜድ ኤ ማተሚያ ቤት፣ 2006 ዓ.ም።

ሰሎሞን ተሾመ። *ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ*።አዲስ አበባ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ ፣2007 ዓ.ም።

ስርግው ገላው። *የግዕዝ ቅኔ መንገዶች ቅፅ ፩*። አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣2010 ዓ.ም።

በላይነህደሴ። "የቅኔቆጠራ፣ነገረና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች ውስጥ"።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ፣ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ዓ.ም ፣ያልታተመ።

ተስፋ ጊዮርጊስ ዘደብረ ሊባኖስ(አባ)። *ተዓምረ ማርያም፡ግዕዙና አማርኛው*።አዲስ አበባ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ንጉሰ ነገስት ዘኢትዮጲያ ማተሚያ ቤት፣1924ዓ.ም።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ። *አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት* ።አዲስ አበባ፣ኩራዝ አታሚ ድርጅት፣1983 ዓ.ም።

ቴዎድሮስገብሬ፡፡ በይነ *ዲሲፕሊናዊ የሥነጽሑፍ ንባብ*፡ አዲስአበባ፣ አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001 ዓ.ም ።

ኀሩይወልደ *ሥላሴ*። *መጽሐፈ ቅኔ*። አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1918 ዓ.ም።

አበበ ከበደ። "የመልአከ መልአክ ተስፋ የዋሻራ ውስጠ ዘ የግዕዝ ቅኔና ቅኔው ከሌሎች ቅኔዎች

የሚለይባቸው ባህርያት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ፣ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣1993ዓ.ም፣ ያልታተመ።

አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሀን)። *መጽሐፈ ቅኔ (ዝክረ ሊቃውንት)*። አዲስ አበባ፣ በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፣1963 ዓ.ም።

አፈወርቅ ተክሌ(አለቃ) ።*መጽሐፈ ታሪክ ወግስ*። አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት ፣1997 ዓ.ም።

አፈወርቅ ዘውዴ (አለቃ) ።*ቅኔ ጥበብ አኀማመርና አረማመድ*። አዲስ አበባ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1980 ዓ.ም።

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*። አዲስ አበባ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፣፳፻ ዓ.ም።

ኤልያስ ነቢየ ልኡል(አለቃ) እና ከፍያለው መራሒ (ቀሲስ)። *ትርጓሜ ቅኔ ፈለገ ሕይወት*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም ።

ኪዳነ ማርያም ጌታሁን (መምህር)። *ጥንታዊው የቆሎ ተማሪ* ። አዲስ አበባ፣ በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 1980 ዓ.ም።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም።

ወልደ ኢየሱስ መቅጫ(መምህር)። *የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊ ገዳም አጭር ታሪክ* ። ለታሪክ ማተሚያ፣2008 ዓ.ም።

ዓለማየሁ ሞገስ። *ሰዋስወ ግዕዝ ምስለ ተሰነአወ* ። አዲስአበባ፣ ተስፋ ማተሚያ ቤት፣ 1950 ዓ.ም።

ዘሪሁን አስፋው:: *የስነጽሁፍ መሰረታዊያን*: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣1992 ዓ.ም::

ዜና ማርቆስ እንዳለው:: *ቅኔ ለወጣቶች ቁጥር አንድ*:: አዲስ አበባ፣ ሆራይዘን ማተሚያ ቤት፣ 1994 ዓ.ም::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር::*የግዕዝ ቅኔያት*:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፣1980 ዓ.ም::

ያለው እንዳወቀ::*የምርምር መሰረታዊ መረሆዎችና አተገባበር*:: አዲስ አበባ አልፋ አታሚዎች፣ 1998 ዓ.ም::

ይጌይስ ኃይለ ሚካኤል "የግዕዝ መወድስ ቅኔ":: አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 1975ዓ.ም ፣ያልታተመ::

ይኩኖ አምላክ መዝገቡ:: "በግዕዝ ቅኔ ሰም ውስጥ የሴት ገጸባህርያት ገለጻ":: አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣1997 ዓ.ም ፣ ያልታተመ::

ዮሐንስ አድማሱ "ሰምና ወርቅ" ::አዲስ አበባ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት ጽሑፍ፣1959 ዓ.ም ፣ያልታተመ::

ገ/ዮሐንስ ገ/ማርያም:: *ክፍል አንድ ተቅዋመ ጸዮን ክፍል ሁለት ቅኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን*: አዲስ አበባ፣1992 ዓ.ም::(ማተሚያ ቤቱ አልተጠቀሰም)

ጽጌ አባተ:: "ቅኔያዊ ውርስ"::አዲስ አበባ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍትምህርት ክፍል ዲግሪማሟያጽሑፍ፣1972ዓ.ም ያልታተመ::

ፈቃደ አዘዘ:: *የሥነ-ቃል መምሪያ*:አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ቤት፣1991 ዓ.ም::

ፍቅረ ድንግል፡፡ "ቅኔ መቀኘትና ቅኔ መቁጠር በግዕዝ"፡፡አዲስ አበባ፤የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍትምህርት ክፍል ፤ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤1963 ዓ.ም ፤ያልታተመ፡፡

ፍቅሩ ደመቀ፡፡ "ሥነ-ቃልን ሠም ያደረጉ የግዕዝ ቅኔዎች ይዘታዊ ትንታኔያቸው" ፡፡አዲስ አበባ፤የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ፤ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፤ 1995 ዓ.ም፤ያልታተመ፡፡

Barbara Culatta and Carol Westby. "Telling Tales;Personal Event Narratives and Life Stories".(2016).https;//www.researchgate.net/publication/308710831.

Catherine Kohler Riessman."ANALYSIS OF PERSONAL NARRATIVES".Boston University,Riessman@bu.edu,2000.

Chris Ingraham."The Scope and Autonomy of Personal Narrative".North Carolina State University, Department of Communication ,Campus .2017, Vol. 34(1) 54-74.

Finnegan, Ruth. Oral poetry its Nature,significance and Social Context.London and New York: Cambridge University press, 1977.

KOTHARI.Research Methodology Methods & Techniques.India.New Age Internatinal (P)Limited, Publishers.1990.

Labov, William and Joshua Waletzky."Narrative analysis". Essays on the Verbal and Visual Arts, ed. J.Helm, Seattle: University of Washington Press.1967, pp 12-44.

Matthew A. Hawkins and Fathima Z. Salee. "The omnipresent personalnarrative: story formulation and the interplay among narratives".Journal of Organizational Change Management. Emerald Group Publishing Limited,2012, Vol. 25 No. 2, pp. 204-219.

National Sociery for the Study of Education, https://nsse-chicago.org/Home.asp.

Nicholas Davey. Unquiet Undertanding Gadamer's Philosophical Hermeneutics.State University of New York Press, Albany, 2006.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ
### የመምህራኑ ቅኔያቶች

### 1.1. የእማሆይ አመተ ማርያም ቅኔያቶች

1. ጉባኤ ቃና

ሚ ይገርም ሕፃን ደብረዘይት ምጻት፡፡

አኮኑ ይትዋነይ ለሊሁ በነበልባልዊ እሳት፡፡

2. ዘአምላኪየ

ለዛቲ ዓለም እቤርተእሉ ሥላሴ፡፡

ግብርኪ አኮኑ ይመጽእ ድምሳሴ፡፡

ምንትኑ ይሄይስ ይቤላ ዘመደክርስቶስ ዘሙሴ፡፡

3. ሚበዝኑ

ከመ ከመነፋስ ገብር ወከመ ከመ ገብር ነፋስ ወርኀ ምጽአት ወልድ ገደመ፡፡

ከመ ከመደም ማይ ወማይ ብዙኅን ደመ፡፡

ከመ ከመ  ኑፋቄ ኅጥእ ወከመኅጥእ ዘነቅል መዋዕለ ክርስቶስ ዓለመ፡፡

4. ዋዜማ

አንተ እግዚአኩሉ እምዘገበርካሁ መቅድመ ዘስመዚአከ ነግሠ፡፡

ዘገበርከ ወርኀደብረዘይት መብዝኄ ተውዳሰ፡፡

ነዋ ያጠፍእ መኮንነ ምጽአት ነፋሰ፡፡

ኀበ ኀበ ይብሉ ሕዝብ ዘኢተሞገሰ፡፡

በኩረ ጊዜ ይትቃፀቡ ነፍሰ፡፡

5. ዘይዕዜ

ለይቲ ዓለም ወለተዘቦ እግዚአብሔር ባዕል ዘለከፋሃ ምንትኑ፡፡

መርህበ ህላዌ ለኢህላዌ ግድፍተ መልበሳ ትረውጽ አኮኑ፡፡

እንዘይሬእያ ምጽአት ለእግዚአብሔር መኮንኑ፡፡

ቀዋሜ ነፋሳት አበው ቀረብተ እልመክኑ፡፡

እንተ ያስተጋብእ ሰብአ መብዝኄ ብዙኀ መጠኑ፡፡

6. **ኲልክሙ መወድስ**

ባዕላይ ነፋስ እንተሙስና ረዋጼ፡፡

ዘይሄይስ ብዑላነበኩሩ ሰርገወ ድንጋጼ፡፡

7. **ዘአምላኪየ**

መነ ይኄይሉ ሶምሶን ዘፈጠርዎ ሥላሴ፡፡

አሮን ንቡረ መንበሩ ለምልክዓም ሙሴ፡፡

ለኀያላኒሁ ለኀጉል ነጋሢ ዘአስተዮሙ ድምሳሴ፡፡

8. **ሥላሴ**

ፍቅረ ወሰላመ ሀብታተ ኢሳይያስ ዳንኤል ኖሴዕ መብዝኄ ሥሩአነ ልሳነ ስርዓተ፡፡

ያስተጋብእ ኄረ ሐዋርያ ወላዲ አሰርተ፡፡

አምጣነ ሰላም ወፍቅር ዘኩሉ ሀባታተ ኩሉ መንግሥተ፡፡

እግዚአብሔር ዘመስረተ፡፡

ኀሣሤ ዓለመ እንተ ኢያስተተ፡፡

ያወርሱ ቤተወልድ ቀወምተ፡፡

9. **መወድስ**

ከመ ከመትውልድ ወርቅ ንግሥተ ሀካይ አቢኣ ሀካየ አበዚአሃ አስተዋራዴ

ማሕጸኒሃ ሀኬተ ምህላ ወሀካይ ቡአዴ፡፡

መክሊት ብእሲተ ኄራዊ ወለደት ፍድፋዴ፡፡

ዕቁበስርዓቱ ለማስያስ አቅራቢ ኄራነ ደብረተአምኖ መስገዴ፡፡

አንተሂ ዘርዐያሬድ ዘኢታከብር ወላዴ፡፡

ይኩን ምጉያጸከ ተጽናሰ ተዋሐዴ።

ጉባኤ ቃና ወመወድሰ ልሳናተ ግዕዝ ኢለማዴ።

እስመ ኮንከ አንተ እንዘትመውቅ ነዳዴ።

10.መወድስ

አጋዕዝተ ብሂል ብህለ ሲመተ ምድራዊ ሀካይ ዘፈርያን ወርኀ ተምህሮ ፍትሐ ` እልመክኑ።

አስተዳላዌ ሰናየ ቅኑያነ ተግባር ሥልጣኑ።

ጸታ አስተራትዮስ ጋይዮስ አግናቴዎስ ጸታ አናንያ አኪላስ ካህኑ።

ለዘቴዎፍሎስ ኤወጄኖስመርአንዮስ ታዶስ ወሀቤወቁ ሀካየኪኑ።

ዘማርያማዊት ማርያምሃ አስተዳለውክዎ ቦኑ።

ኀበ ኀበ እብል እኩያነ ተጸወኑ ተጸወኑ።

ጽላሎተበኩሩ ለስምያን ፍሉጣነ ጉየት ባኑ።

ይሴሰዩ ውእቶሙ ተኮርጎኑ ተኮርጎኑ።

አውጽኦተልሣንቤቶሙዘይእቴገሎዘመኑ።

11.ሚበዝኑ

ሕስው ሕስው ብሉየ አዛርያስ ዝኀር ወዐሴ አማኑኤል ሀቤ።

ስቱየ ወይነ ዘሰሎሞን በኩረ ሶቤ።

ብሉየአዛርያስ ዝኀር ወይነ ባኀር ወልደ እስመ ኢሰተይኩ ይቤ።

12.ጉባኤ ቃና

እሩየ  ጤምወስ ነድ መፃጉዐ መፃጉዐ ደዌ መጽንኢ።

ባህቲቶ ውዕየት ክፍለ ኢየሱስ በቋኢ።

13.ዋዜማ

አማኑኤል መርሀዘቦ ሐዲስ ኤዶም መጽሐፈ ዘካርያስ ዘሎ።

መስንዱ ልሳነ ዚአሁ ይተረጉም ኩሎ።

አምጣነ ልሂቅ ውእቱ ምሁራነ ብሉይ ተንጉሎ።

ውስተ ጉባኤሁ ለባላር ዘተጎይሎ።

ጥበባተ ዘይጸውዕ ቃሎ።

14.ሥላሴ

አውገዘ ወአሰሰለ ካህነ ብሉይ ወሐዲስ ዘሙሴ ወጴጥሮስ ዘርዐ ሕዝቅያስ ምናሴ።

ሲዓለ ኢአቃቤ ሕጉ ለውእቱ ሙሴ።

ኅሩያኒሃ ለኤዶም ዘአምረሮሙ ድምሳሴ።

አምጣነካህን ዘውዳሴ።

ዘፈቀደሁ ይፌፅም ዓለመ እሴ።

ዘውገእሉ ሥላሴ ሥላሴ።

15.መወድስ

አማኑኤል ጽንሰ ጽንሰ መቃብር ወላደ አዛርያስ ባላር ጠፍአ ወማሰነ።

ሶበሁ ለከፈት ሆሳዕና ዳዊት ክውነ።

መቃብር ጽንሰተ ፈጣሪ እጼሃ ፋጡነ።

ዘገሠሠት አድመዘበ እንተዘኢክህላ ቶማስ ይመርስሶ ኅሩያነ።

ማኅፀኒሃ ለመቃብር ወላደ አቤል ዘአምነ።

መምለኬ መምለኪ ዘተቀደሰ መቅደሰ ቅዱሳነ።

ቅዱሳኒሃ ለኤዶም ጽንሰ መቃብር መጠነ።

ኅጥአነ ወኄራነ ጸጋመ ወየማነ።

እግዚአብሔር ባዕል ዘአስተዳለዎ መካነ።

16.ክልክሙ መሰድስ

ማትያስ ታያስ ከመ ከመቅብዕ ዘንዕደ።

ወመቅበርት ከመ ከመ ርእሰ ጸዋሪ ክቡደ።

**17.ጉባኤ ቃና**

አንተኑ ማስያስ ቀታሌ ኀይለ ሶምሶን ጸላኤ፡፡

ትቀትል መርህበ ዘሔዋ መንገኒቀከ ትንሳኤ፡፡

**18.ጉባኤ ቃና**

ብሔረ ዓባይ ጥበብ ዘነርላርዮስ ወዕዝራ፡፡

አይቴኑ ዘይብል ብእሲተ በኩረ ያሬድ በኩራ፡፡

**19.ዘአምላኪየ**

አንተኑ ዘመን ሙጻአብርሃነ ወልድ ፍጋኤ፡፡

ታርእየነ ዘኢትዮጵያ ወግእዝ ትንሳኤ፡፡

ናስተበቊአከ ለከ ሕዘበ ሀገር ውዋኤ፡፡

**20.ሚበዝሁ**

እግዚአብሔርግእዝ ከዊኖ ዘባነ ዘዘማርያም ኢትዮጵያ፡፡

ባረከ ሕዝበ ይኩኑ ሐዋርያ፡፡

ዘልሳነ ግእዝ አምላክ ሕዘበ ዓቢይ ሀገር ወዓሌ ምሥጢር ኖትያ፡፡

**21.ዋዜማ**

ስምኡ ወለብኡ ሊቃነ ደብረ ያሬድ ዩኔቨርሲቲ ሶበሁ አብዝኀት ዓለመኩልነ ጻዕቀ፡፡

ለግእዝ ፈጣሬ ሐዲስ ምጽአቱ ዘረቀ፡፡

ከመ ከመ በጽሐ ወአልጸቀ፡፡

መላእክተ አምላክ ያሬድ ዘአስተአፈቀ፡፡

ቅኔያተ ዘዓለም ደቂቀ፡፡

**22.ዘይዕዜ**

ዐበይተ ዛቲ ሀገር ወንኡሳን ወርኀ ትንሳኤ ወልድ ዓቢይ ዘለከፎሙ ምንትኑ፡፡

ኢትዮጵያ መርህ በጽድቅ ውእቶሙ በበጊዜሆሙ እንዘቦ እልመክኑ፡፡

እስመ ያመጽኡ ሞተ መሰውረ አቤል መኮንኑ።

እስከያወርሱ ምድረ እስተአየኑ።

እሙንቱ ባዕዳነ ዘይቀንዮሙ ባኑ።

23.ጉባኤ ቃና

ግእዝ አንተ ወሙሀዘ ጥበብ አእምሮ።

መጽሔተ ሀገር ዓባይ ዕዘቦ እግዚእናከኢብትሮ።

24.ጉባኤ ቃና

ብኄራ ጥበብ ወላዲተ ሐዲስ ፈጠረ።

ለሰላም ካምፓስዩኒቨርሲቲ ዘተገብረ።

25.ጉባኤ ቃና

አንተ ያሬድ እስትግቡእ እምኅበ አልቦ ቀለመ።

ጉቡአነ ሕልፈት ግብርከ ኢታህጥአነ ሰላመ።

26.መወድስ

ኦ ትዕግስት ወሰላመ ጊዜ ወፍቅረ ትሕትና ዘታኦስ አናግደ ጳውሎስ ሐዋርያ።

ሀልኡ እመ ወራዙተ ውሉደ ማሕፀና ዋሕድና ምስካያ።

እንዘትባርኩ መሳቅለ ዘእደተአምኖ ካህን ምሉዐ ቡራኬ ሲሳያ።

ኢትዮጵያ እቤርተ ጽድቅ እንተ ሰብአ ግብፅ ጸራልያ።

ትኩት ዝኮ ዘንግሥተ ዓለም አርኣያ።

ይብድሩ ተፋቅሮ ወተሳልሞ ዘአክሶስያ።

ዘምጽአተ ዐቢይ አምላክ ለኢትዮጵያ ነቢያ።

27.ጉባኤ ቃና

ኦ ወላድ ወላዴ ዘቦ ትንሳኤ።

እስኩ ፀውኢ ኀይለ ኃያላን ጉባኤ።

**28.ጉባኤ ቃና**

አይቴ ንጸወን ሕዝበ ተዋሕዶ ኩልነ፡፡

ኤልሳዕ ኦመተዋሕዶ እስመወድቀ ብነ፡፡

**29.ዘአምላኪየ**

አንተ ሞት አምጻኤ ብዙኅ ኀሣር፡፡

ምንት ዘይፀንአከ ዘሰማይ ወምድር፡፡

እስመ ተአደውኮ ለኤልሳዕ አበተዋሕዶ ክቡር፡፡

**30.ሚበዝሁ**

ለቀለመወርቅ ወኤልሳዕ አበወዓባይ ቤቴል ንግሥተ ውእቱ ተዋሕዶ፡፡

ለከፎሙ ምንት ደብረ መላልኤል ሀይዶ፡፡

እስመይትቃደሙ ሞተ ሩፀተ እግሩ ለአቤል ኖላቂ ሕልፈት ተዘምዶ፡፡

**31.ዋዜማ**

ልጉክት ዘኤልሳዕ ምሉአንጽሕና ወክብር ስቴያተ ዕዝራ ሐታቲ፡፡

ኀምዘሞት እንተ ሥጋ ሙሴ ኀምዘ አቤል ባቲ፡፡

እምከመነበቡ ቅደመ ነቢየ አማኑኤል ኬልቲ፡፡

ወርኀ አስተንግዶ አንጋ ዘኢመዋቲ፡፡

በኩረ ዘቦ አብርሃም ከባቲ፡፡

**32.ዘይዕዜ**

ኦ አምላክ ኬንያእሉ ሥጋ ወነፍስ በሥልጣ'ንከ አሐቲ፡፡

አምሣለ ቀዳማይ አልዓዛር አንስኦ እንስከ ኬለ ኤልሳዕ በኩረ ዛቲ፡፡

አምጣነ አልቦቱ አምሳለ ኤልሳዕ በኩረ ዛቲ፡፡

ቃለተዋሕዶ 'ንግሥት ዘመበ መሰሀቲ፡፡

ዘደኅሪተ ተፍፃም ዘጽድቅ መንግስተ አማኑኤል ኬልቲ፡፡

**33.መወድስ**

እስኩ ንቴክዝ ሕዝበሃይማኖት እምነገረ ሕልፈት ዶርነ አበወሃይማኖት ወቅድስና።

አምጣነ ኀጥአይነንሕነ ለተዋሕዶ መካና።

ወ'ንስክዮ እምአመክህነ ለዘአቤል ኅትና።

ጾርነ ሞተ ስጋ አሶት ኀይልከ ወአንሠረ ዘትሕትና።

ጳጳሳቲሃ ሠራዊቲሃ ለቤተክርስትያን መባልና።

ጸልዩ ጸሎታት እስከነታስኡ በኩረዮና።

መዋቴ ሃይማኖት ዘታያስ ፈጣሬ ኤልሳዕ ልዕልና።

ወታምጽኡ ተናዝዞ ተከዝቋ ሥጋ ራሔል ዘቅድሞና።

ቅውማኒክሙ ቃለ ዘወላዴ ጴጥሮስ ፍና።

**34.ዘይእዜ**

ማርያም ንግሥት ዘመነ ፍዳ ዘነያ አሀዘት ነቢያቲሃ ሱባኤ።

ዘመነ ምስፍና ለደብረዘይት ሶበሀልቀ በሊኦተ ሥጋ ዘድንግል ጉባኤ።

አቅደመ ወልድ ኢይብጻህ ዘትንሳኤ።

ረዋጼ መቅበርት አላዛር እንበለ ምማኤ።

ብሂሎተከሃ ወዝየ እንተ አብዝሀ ጽዋኤ።

**35.ጉባኤ ቃና**

ሚጠት ግዕዝ ያዕቆብ ኢትዮጵያ እንተ ከነዐን መካነ።

ስማ ተስፋ ቶማስ ዮሴፍ መንግስተ ሰማይ ኮነ።

**36.ዘአምላኪየ**

አንትሙ ህዝብ ዘልሣነ ግዕዝ እልመክኑ።

አውፅው ተስካረ ግዕዝ ዘሀሎ ስልጣኑ።

በውሂብ ፍት አፍቅሮ ሀገር ካህኑ።

37.መወድስ

አንተኑ ግዕዝ ሀራሴ አዕምሮ እምነ ተናነቢ ትርጓሜ ገራህት ወእምነ ሰዋሰው ዓለም ህሬ፡፡

ለእንተ ደከምከ አንተ አመተማርያም ዝማሬ፡፡

ፈጥሪከ ቃለመወድስ ይበሎ ለፍሬ፡፡

ወይቀቦ እም አኩይ በረደ ይሁዳ ወባኦስ (ወታኦስ) ልቡሳነ ሀኬት እስከደሬ፡፡

ለእክልከሂ ቅኔ ያሬድ ዘመነ ረሀብ ፍካሬ፡፡

ሰረገላ ናዳብ ዮስዶ እም አዲስ አበባ እስከነ ትግሬ፡፡

ዘሰብአ ጎንደሬ አጥፍአ ረሀበ ፈሮን ወቆሬ፡፡

ኢትራወጽ ዘጎጃሜ ወይሲጦ ለጎንደሬ፡፡

ዝማሬ ማርያም ባዕልተ አጥፋዕተ ሀጉል ስዋሬ፡፡

38.መወድስ

አንትሙ ሕዝበ ዘቤተመንግስ ከመሕዝባ ለቤቴል ደብረሀተታ ኩርጓኔ፡፡

በውስተማራኪ ዓለም ምልዕተ ጥበብ ብያኔ፡፡

ለግዕዝ እግዚአብሔር ዘፈጠረ ቅኔ፡፡

እስኩመ ሰብህዎ በሚሕበርክሙ ልብ እንተሀተታ ክዋኔ፡፡

አንተሂ ቃለ ግዕዝ ፈጣሬ ዘሊቅ ምጣኔ፡፡

ተፈሣህ ምስለኩሉ ወተናበብ አሀተኔ፡፡

ሕዝበ ዩኒቨርስቲ ዓለም ቅቡዓነ አሚን ከልበኔ፡፡

አምጣነ ለመድኪ ተናብቦ እንዘ ያቀርበኮ በውሳኔ፡፡

ወእሙንቱሂ ቀርቡከ እንበለ አሀቲ ምናኔ፡፡

39.መወድስ

ሰላም ወፍቅር ሠራዊተ ዘቦ አብርሃም አብ መንበረ ማዕምራን ይነግሱ፡፡

አምጣነ አብርሃም ሊቅ መብዝሔ ብዙህ ተውዳሱ፡፡

ለቶቤል ተጻራሬ እሉ አፍለሶ እምናሱ።

ቃለ ሀይማኖት ለሀገሪትነ ምዕልተ ጥበባት ዘያሬድ ዘወርዘው ተአሚን ይታለሱ።

ጸጋመ ወየማነ ለብዕልናዝ ኢያሱ።

ፍቅረ ወሰላመ ሰራዊተ ያዕቆብ ወአልባሱ ለአብርሃም ሊቅ ለሊቀ አዕላፍ ሞገሱ።

ዘሕዝበ ጽንፈ ባሕር አርጋድያ ተቀደሱ ተቀደሱ።

ወርኀ ሲመተ ዘአብርሃም ሐዳሴ ብዙሃን መንፈሱ።

## 40.ጉባኤ ቃና

ምሁራን ጻድቃን ዐቀብተ ሀገር ወሕዝባ።

ሶበ ላዕለ ሕዝባ ተንሥአ ድንቃዌ ቀታሌኩሉ ጠቢባ።

## 41.ዋዜማ

ማርያም ወሰሎሜ ባሕይታዊያት ዘሳሌም ዓለመ ሠጋሆን ሰይፈ።

መነና እስመይሰምኣ ተሰዶ መጽሐፈ።

ወርኀንግሥናሁ ሄሮድስ ዘብዙኃነ አዕቀፈ።

እመብዝኖ ተድላ ዘሰብእ ዘአስተኀለፈ።

ወልደ አብ ሰብዕና ምዕራፈ።

## 42.ዘአምላኪየ

እስመ እንዘአሚን ድንግል ወለተ ኢያቄም አሐቲ።

ብዙኀ ተግባረ ዚአሃ ቤተሰብእ መዋቲ።

መፍትው ይሕትት ተግባራቲሃ ሐታቲ።

## 43.ጉባኤ ቃና

ኃያላን እደው ኢትመንኑ አንስተ ፈጣሪ ዘሙሴ።

እስመ በአንቀጸን ሀለው ወሀብተ ሀብተ ሰብእ ሥላሴ።

## 1.2. የእማሆ ኅሪት ቅኔያቶች

### 1. ጉባኤ ቃና

ምልዕ ዕለት ዕለት ይእዜ ጉባኤ።

ማዕከለ ምሁራን ተረክበ አኮኑ ሊቀ ዩንቨርስቲ ፅዋኤ።

### 2. ጉባኤ ቃና

ጉባኤ ቃና ተንስአ ወወጠነ ፋና ዩንቨርስቲ ተአውቆ።

ለጉባኤ ቃና መርድዕ ሀዋሪ እስመ ጽንፈ ባህር አልፀቆ።

### 3. ጉባኤ ቃና

መልአከ ፀጋ አባይ አሐዱ በመልዕልተ ጣና መልአክ።

አሐዱ የሀልፍ ዘይቤ በመፅሀፈ አበው ቡሩክ።

### 4. ዘአምላኪየ

ኩሉ ይትመሀር በቃለ መወድስ አቡነ።

እስመ ነስኦ በኑኃ ዘመኑ ዘመንግስት ስልጣኑ።

ቃለ መወድስ አብ ድህረኒ ተስፋ ቅቡጻን ዘኮኑ።

### 5. ሚበዝሁ

ምሁራን አንብቡ ወአጥርዩ ግዕዝ ለትውልደ ጎጃም ስነ ፀሐይ።

መጽሐፍ ዘይብል እም አባይ እስከ አባይ።

አምጣነ አኮ ቀሊል መጽሐፈ ዛቲ ሀገር እንተ ለኩሉ ምስካይ።

### 6. መወድስ

አንጋድ ጥበባተ ፀጋ ባኡ ባኡ ውስተ ማህደሩ ለመልከአም።

እንተ እገሪሁ ተሀስሩ በሀብለ ህዳሴ ግሩም።

አባይ አርዌ ጣና እስመ ሰብአ ጥበባተ ፀጋ ኢያፈርህ ዮም።

ድህረ ተቀነዎ ወተሀፅኦ በእደ እግዚአ አባይ እንተ ሀፀና ጎጃም።

ኢትፍርሂ ነገረ ዝንቱ አርዌ ፅንፈ ባህር አዳም።

ንትናበብ ተናብቦ እለ ተጋባእነ እመ ዓለም፡፡

በይነ ዘከዋኒት ቅድስተ ሀገሪትነ ሰላም፡፡

ከመ ይሰብክ ተናዘዞ እም ንጉሳነ መቀውም፡፡

7. አጭር መወድስ

አልቦቱ ተፅናስ ለልሳነ ግዕዝ ህዳሴ፡፡

ውእቱ አምጣነ ወለደ ብእሲተ ወብእሴ፡፡

8. ጉባኤ ቃና

መፍትው ይሰወጥ ወልደ ማርያም ክርስቶስ፡፡

እስመ በሰሉስ ዕለት ሰጠጣ ለልብሰ መቃብር ሃዳስ፡፡

9. ጉባኤ ቃና

ቅድስተ ቅዱሳን ይእቲ ህንፃ ሥላሴ ሳይዳ፡፡

አምጣነ ተርእያ ተርቢኖስ በዛቲ እስከነፈረስ ፀዓዳ፡፡

10. ጉባኤ ቃና

ንዋየ ብዙሃን ይስእል ወይትወከፍ በስመ ሥላሴ ሠለስቱ፡፡

ህንጻ ደብረ ድማህ ህመም ከዋኒ ዘርዓ ሊቃውንት እስፍንቱ፡፡

11. ጉባኤ ቃና

ሀገሪተ ጴጥሮስ እቀብ ለኢትዮጵያ ንጉሳ

ወተፃረርከ ይግድፋ ፈጣሪ ታህተ እገሪሃ ከኒሳ፡፡

12. ጉባኤ ቃና

አንትሙ ህዝብ እንዘ እንተ ትገድፍ ኩሎ፡፡

ሰምእዎ ለወልደ ትንሳኤ ወአፅምኡ ቃሎ፡፡

13. ጉባኤ ቃና

እስፍንተ ነፀርኩ በዛቲ አመተ ማርያም ዓይንየ፡፡

ምልዕተ አዕምሮ ዘኮነት እንዘቦ በኢትዮጵያ ዕድሜየ፡፡

**14.ዘአምላኪየ**

አንትሙ ህዝብ ዘሀደርክሙ ፌማ።

ሀለይዎ ወተዘከርዎ ለደብርነ ዲማ።

አምጣነ ቅድስት ይእቲ እምኩሉ ወታስተፌስሕ በስማ።

**15.ዘአምላኪየ**

ለዘኖሙ ህዝብ አንቅህዎሙ እምዘሎ።

ይሕንጹ በከመ ለመዱ ለድማህ መርጡሎ።

ወለእመአኮ ፀውኡ አዕርክቶ ለሰማዕተ ልዳ ወሴሎ።

**16.ዘአምላኪየ**

ለቤተክርስትያን መርአት ፀዋኢተ ስሙ እብኖዲ።

አብሰልዋ ለመናፍቃንህ በእሳት ነዳዲ።

እንዘ ፈጣሪሀ ታመልክ ለዛቲ አመ ረከብዋ ዓዲ።

**17.ሚበዝሁ**

መንክር ግብርከ መጋቢ ዓለማት ዘኮንከ አዲስ አበባ አማኑኤል።

እስመ ተወለድከ አንተ እም ኢትዮጵያ ድንግል።

ለድህነተ ኩሉ ዓለም በለቢሰ ስጋ ዘሰብእ ክቡረ ክቡራን አህባል።

**18.ዋዜማ**

አቤሜሌክ ዘሚካኤል ሙስና ማህደሩ ስፋህ ከመ ኢይርዓይ በዝየ።

ሰውረኒ ወኢታርእየኒ ሀጉለ ቤት እኩየ።

ሀበ ሀበ ይቤ ገሀደ ሀበ አምላኩ ጸለየ።

ወጸሎቶሂ ተወክፈ ከመ ተመነየ።

ፈጣሪሁ ዘሰምረ ነቢየ።

19.ሥላሴ

ማርያም ቤተ ጉባኤ ኢየሩሳሌም ደብረ ድማህ ዘእንበለ ዘርዕ ወለደት ትርጓሜ

እግዚአ ወንጌል ሐዲስ።

ሀበ ግብፅ አዲስ አበባ ተሰደት ለፈውስ።

እንዘ ለሊሃ ትከውን ለኩሉ መድኃኒተ ወነፋስ።

እም ቃለ መምህር ኢሳይያስ።

እስመ በላዕሌሃ ተንስአ ሀጉለ ቤት ሄሮድስ።

ዘቀተለ ደቂቀ በናአስ።

20.ዘይእዜ

ኦድንግል ኢትዮጵያ ዘበውስቴትኪ ፆርኪ ዘኢይፀውር አዳሙ።

ምንትኒ ይእሴኒ ስመ ዚአኪ እስመ ለኪ ያስተበፅኡኪ ምሁራን ኩሎሙ።

ወለነፅሮ ኪያኪ ለእለ ጌሰሙ ላእለ ጌሰሙ።

መንጌሎከ ጌሠ ወያስተሃምሙ።

ወሃዲስ ስመኪ በአበ ምሁራን አዕዋሙ።

21.ጉባኤ ቃና

ኦ አይሁድ ምኩራብክሙ አንፅሑ።

እንግዳ ማስያስ ሃቤሃ አምጣነ ይመፅእ ናሁ።

22.ጉባኤ ቃና

ነገሮ ገሀደ ለኤልያስ አምላከ ኤልያስ ቅኔ።

ህማነ ከለዳ ኢያባእ ቀደመ በዘኤልያስ ኩርጓኔ።

23.ዘአምላኪየ

አሐዱ መርድእ እንበለ መጠን ነፀራ።

በዘመፃአት ሀበ ቤተ ዘቦ ኤልያስ እገሮራ።

አምጣነ ኩለሄ ሐዲስ እንታክቲ በዘ ኤልያስ መድበራ።

**24.አጭር መወድስ**

መርደዕ ለምግባረ ሠናይ ዘቆምከ።

አምላክነ ሰዋሰው ቅኔ መና ሠርክ የሀብከ።

**25.ጉባኤ ቃና**

ጉባኤ ቃና ተንስኢ እመንበርኪ አርምሞ።

አምጣነ ሀበኬ መፅአ ንግስታተ ቅኔ አበሞ።

**26.ጉባኤ ቃና**

ሰሎሜ ወዮሴፍ ወሶልያና አርድዕት።

ጊዜሆሙ ዳህነ ኢየማሰኑ በግብት።

**27.ጉባኤ ቃና**

ብሉዕየ መዋዕል ዮሴፍ ኢነፀረ ምንዳቤ ጊጋር ምትረተ።

በፈቃደ አምላክ ረከበ አኮኑ ሀብተ ያዕቆብ ስደተ።

**28.ጉባኤ ቃና**

ይብል ግዮን ሰብአ ኤፌሶን ከኒሳ።

እንበለ መጠን ሰተይኩ ሐሊበ ውሳጤ እንስሳ።

**29.ዘአምላኪየ**

ህፃናተ ሴሎ ሀደጉ ነውረ ኤልያስ ዳህና።

ይብልዑ ኢየሩሳሌመ ሰይፈ ሜሎስ መና።

ምስለ አይረጎሙ ቀርቡ አኮኑ ህፃናተ ሴሎ መዲና።

**30.ጉባኤ ቃና**

ልብሰ በብኑዳ አነመ በኪሮስ ተጋድሎ ስጋ ጠቢበ።

ጠቢበ ጠቢባን ሰማዕት ጠበብተ ስቃይ ምኩራብ።

**31.ጉባኤ ቃና**

ለእንተ ለኪሮስ ኪሮስ አፍቀሮ ደብረ ኤዶላም ወኒሳ።

በብኑዳ ንጉስ ሀውልቱ በአለ ግሩም አንበሳ።

**32.ዘአምላኪየ**

ኮነ ሣዕረ ህዋስ ኪሮስ ባህሁቱ።

ለኪሮስ ህማሙ እስመ ፀንዐ ቦቱ።

በከመ ህሙም ማትያስ ለአማኑኤል ትውክልቱ።

**33.ጉባኤ ቃና**

ብሩክት ይእቲ ጉባኤ ቃና እቤር።

አምጣነ ለአርድት ትውህብ አእምሮ ህብስተ ዚያሃ በክብር።

**34.ዘአምላኪየ**

ህፃነ አንጌቤን ቂርቆስ ዘያፈቅሮ እልመክኑ።

ቀኖተ ምክር ኢየሉጣ ያፀመዕ በእዝኑ።

ኢየሉጣ ለቂርቆስ ወላዱ እንዘ ይቀፅባ በአይኑ።

**35.ጉባኤ ቃና**

ሊቀ ተአምኖ ገብርኤል ኢይትናገር እንተ ዘኢያእምር ህሳዌ።

እስመ ነገሩ እሙን በኃበ ማርያም ሠርዌ።

**36.ጉባኤ ቃና**

ለህንፃ ከኒሳ ጎልያደ ቀተሎ እግዚአ ኬፉ ዳዊት።

ሠለስተ አዕባዕነ እንዘ ይዌሩ በግብት።

**37.ዘአምላኪየ**

መጋቢ ሀዲስ ገብርኤል መጋቤ ብሉዕይ ከዋኒ።

ለብሉይ እንዘ ይፌፅሞ ሀዲስ ወጥአኒ።

እምንበዕናሁ ለሔር መልአከ አሀዱ አዶኒ።

38.ሚበዝሁ

ዘመደ ዘመዱ ለሳዶቅ ዘመደ ሀና ብእሲት ዘመደ ሳሙኤል ተከናሲ።

ዘመደ ሚካኤል ፋኑኤል ገብርኤል አልሆሳሲ።

ኩሎ ይዜኑ ለዛቲ ድንግል ብእሲተ መልክአ ብእሲ።

39.ጉባኤ ቃና

ባእለ አባግዕ ዲዲሞስ ኖላዊ አባግዕ ዘህንድ።

በአውደ ዚአሁ ያዕቆብ አባግኢሁ ለአውድ።

40.ጉባኤ ቃና

ሀገረ ዲዲሞስ ዔው ዘኢተፈቅረ በቤቱ።

ለዲዲሞስ ነጋዴ ህንደኬ ዔወ ህንድ ዘታህቱ።

41.ጉባኤ ቃና

ወልደ ነጎድጓድ ዮሀንስ ዘመነነ አለመ ሄዋን ህልፈተ።

በበሀገሩ ዘረወ ለኩሉ መቃብረ ስጋ ንብረተ

42.ጉባኤ ቃና

ባእታ ለእም ድንግለ ኢያሱ ወሙሴ።

እምነ ደቂቃ ለሳሌም ማህደረ ብዙህ ቅዳሴ።

43.ዘአምላኪየ

ለወለተ ሀና ወሳዶቅ ዘወለድዋ ተስላስ።

ኢያቄም ወሀና ይብልዋ መቅደስ።

በኃበ ብዙሀን ፃድቃን እንተ ከዋኒት አዲስ።

44.ጉባኤ ቃና

ልደተ ዮናስ ነግድ ዘኃበ ቤትኪ መፅአ።

ማርያም በልዕዮ አሀደ በዘወለድኪ ሰብአ።

45.ጉባኤ ቃና

አቡሁ ይመስል ህይወቱ ለቃለ አዋዲ ዘቆመ።

በገዳመ ሰይፍ ዘጊጋር ከማሁ አምጣነ ዘመኖ ፈፀመ።

46.ዘአምላኪየ

አመ ዮም ተገዝመ አርዘ መርአዊ ግዙፍ።

ሀልቁ እንዘ ይወድቁ ኃበ ሞአብ ፀድፍ።

ሀሊብ ወቅብ ወስጋ አሪዊተ ጊዜ ዘፃይፍ።

47.ጉባኤ ቃና

መበለተ ስምኦን ነፋስ ኢትበልዕ ዘእንበለ ማይ ንስቲት።

መና ቅዱሳን ገነተ ውስቴታ ለኪዳነ ምህረት ቤት።

48.ጉባኤ ቃና

መድሎተ አሚን ያነብብ ለነፍሰ ስምኦን እቤርት።

ሚካኤል መምህር ላእከ ማርያም ሠናይት።

49.ዘአምላኪየ

ምስለ በላኤ ሰብእ ህስስ መሬተ ቅዱሳን በዘይት።

ተካየደት ኪዳነ ምህረት ማርያም ንግሥት።

ለበላኤ ሰብእ ተሀብ ገነተ ብዙሀን ሰማዕት።

50.ሚበዝሁ

ከዋኒት ቅድስተ ቅዱሳን ሄራን ማርያም ዘመደ ወልድ።

ሄርት ይእቲ ወርህርሂት ሀገረ ባእድ።

እስመ አራቂተ ኮነት ለዘተባህሰ ስምዖን ዘምስለ እግዚአ ዋህድ።

51.ዋዜማ

ትከውን ከመ እፅ ዘነያ ተተክለት ኃበ ሙሀዘ ማይ ሀዲስ፡፡

ዘታነብብ ህገ ፈጣሪሃ እንተ ስምያን ነፍስ፡፡

ወበበ ጊዜሃ ዘትሁብ ፍሬ እፀ ሙሴ ቅዱስ፡፡

ኢይትነገፍሂ ፍፁመ ቆፅለ ዕፅ ይቡስ፡፡

ዘሀረሶ ሚካኤል ሀራስ፡፡

52.ዘአምላኪያ

ረሀበ ወፅምአ ለባህታዊ አዝማዱ፡፡

እፀ ቃዴስ አማኑኤልሃ ይቀስሙ ወረዱ፡፡

መንገለ ታህታዋቆረቶስ ሀቅለ ምድረ ሳሌም አውዱ፡፡

53.ጉባኤ ቃና

እስፈንተ ደምስስ ወአፀወ ምኩራብ አይሁድ እስፍንቱ፡፡

ምፅአተ አምላክ ህሙም መንፅኢ በሀገረ ሳሌም ታህቱ፡፡

54.ዘአምላኪየ

ሃፃኒተ እሉ አይሁድ ውሉደ ሳሌም ዘፀንአ፡፡

እሞሙ ምኩራበ አይሁድ ትመኒ ሰብአ፡፡

በሀሊ አምላክ አነ አኮኑ በኢየሩሳሌም ተንስአ፡፡

55.ጉባኤ ቃና

መጻጉአ ደዌ ሕፃን እንተ እየእመረ ነፍሰ፡፡

እሳተ መለኮት እቶን በእደዊሁ ገሰሰ፡፡

56.ዘአምላኪየ

መፃጉ ውርዝው በእደ ዚአሁ ቀፀባ፡፡

ለመርዓት ገፀ  መለኮት ሙስና ዘአልባ፡፡

እንዘ ይቀፅባ ጤሜዎስ በአይኑ ለመርዓተ ሙሴ መክበባ፡፡

57.ጉባኤ ቃና

ከንቱ ውእቱ ህላዌ ዓለመ በፅድቁ::

አምጣነ መንፈቁ ያሀዝን እንዘ ይትፌሳሕ መንፈቁ::

58.ጉባኤ ቃና

መአዲ ገሀነም ወመንግሥተ ሰማይ ይፈዲ::

ንዋያተ ጊዜ ሙታነ ከመ ይትወከፍ ዓዲ::

59.ጉባኤ ቃና

እዝራ ወሄኖክ ለመልከ ጼዴቅ አብትሩ::

በዳህራዊት ዘመን ዘኢነፀሩ ነፀሩ::

60.ሚበዝሁ

ኢይዝራኤላዊ ምዕአት ኢይዝራኤላዊ ምዕአት አመቦአ ዘቦአ::

ዘምድረ ዓለም ምኩራብ ኢይትአመን ወድአ::

ኢይዝራኤላዊ ምዕአት እስመ ሀብታቲሃ ለምድር ከመቅፅበት አይን አንስአ::

61.ጉባኤ ቃና

ምንት ውእቱ ህማም ለምድር ሄዋን ዘቀለ ::

ገፃ ለምድር አሀቲ አምጣነ መስለ ቆፅለ::

62.ዘአምላኪየ

በለስ ወወይን ሐዋርያተ ሀቅል ሀቅለ::

ሐሩ እንዘ የሀድጉ ሀገሮሙ ቆፅለ::

በበሀገሩ ያብፅሁ እሙንቱ ሕብስተ እብራስዲ ወንጌለ::

63.ጉባኤ ቃና

ኢበስለ ቂርቆስ ሰዊተ አንጌቤን አውድ::

አስተዳላዊ ገብርኤል ዘያስተዴሉ በነድ::

**64.ዘአምላኪየ**

ፍቅር ኢየሉጣ ወቂርቆስ ለመልአከ ሰማይ አህባሉ፡፡

ብዙሀነ ሰብአ ፅድቀ እዝራ ይስህበ ይቤሉ፡፡

ወራዙተ ፀጋ ገድላት ዘተጋብኡ እምኩሉ፡፡

**65.ጉባኤ ቃና**

ክርስቶስ ሠምራ እቤርት ወተክለ ሀይማኖት አሀዱ፡፡

በትረ ተጋድሎ አሀዙ ወሀቦ ቁልቁሊተ ወረዱ፡፡

**66.ዘአምላኪየ**

ተክለ ሀይማኖት እግርከ ዘጉጋ ተመትሮ አሀዚ፡፡

ከመ ይሁር ገራህተ ዳህና ዘሄኖክ ተካዚ፡፡

ምንትኒ ኢይከል ከመ እግረዘቦ መላዚ፡፡

**67.ዘአምላኪየ**

ሐይማኖተ  ኬፋ ባዕልዘተለአለ ወከብረ፡፡

ወርቀ ሳሌም እስጢፋኖስሀ ውስተ እብን ቀብረ፡፡

መኑመ ሰብእ ለዝኩ ከመ ኢይርክብ ምእረ፡፡

**68.ዋዜማ**

ኩሎሙ ህፃናት ቅድመ ዘካርያስ ጊጋር አእሩገ ሳሌም ውቅሮ፡፡

ኢፈርሁ እንዘ ይትናገሩነገረ ትመትሮ፡፡

አመ ሠምኡ ሳሌም ነገረ ሄሮድስ ኮሮ፡፡

እስመ ሰይፍ ለሳሌም ሀገሮ፡፡

**69.ጉባኤ ቃና**

መስቀለ አላዓዛር ዘአስተሀፀበ ፍጥረተ፡፡

እመቃብሪሃ ተንሥአ ድህረ ተቀብረ ወሞተ፡፡

**70.ጉባኤ ቃና**

ጾመ ኢየሱስ መምህር  መምህር ተፈልጠ ተፈልጠ።

ለመምህር ስባሄ በመቋም ቀጥቀጠ።

**71.ጉባኤ ቃና**

ባርከ ባርከ ማህበረነ ጉባኤ።

ልሳነ ግዕዝ አቡነ መጻኢ እንዘታከብር ፅዋኤ።

**72.ጉባኤ ቃና**

ሰላም በልኒ ፍኖተ ሠላም ድንግል።

እንዘ ትትከሰቲ አንቲ ለዘጉባኤ አካል።

**73.ዘአምላኪየ**

ሕዝበ ተጋብኦ እቀቡ ቃለ ጳውሎስ ልዑለ።

ተዘከሩ መኳንንቲክሙ ዘነገሩ ቃለ።

ዘነገሩክሙ ቅድመ ዘይቤ ለዘተርጎመ ወንጌል።

**74.ሚበዝሁ**

ካህናተ ፀጋ ወክብር በይነ ፈላስያን ጸልዩ ጸሎተንስሐ ጽዋኤ።

ፍኖተ ሠላም ይኩን ፍናገብረ ምድህን ጉባኤ።

ዘቦቱ ይትገበር ለእለ እለቱ ብዙህ ጸሎተ ዘአበው ሱባኤ።

**75.ሚበዝሁ**

ህላዌ ዝንቱ ዓለም ኩሎ ዓለመ ዘያስተሀፅበ በህቁ።

እንዘ መንፈቁ ይትፈስህ እስመ የሀዝን መንፈቁ።

ወአንተ ዳቤር ሀዘነ ልቡና ህድጊ ከመ ካልዓን ይልህቁ።

## አባሪ ሁለት

## ለቅኔ መምህራኑ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ሙሉ ስምዎ ማን ይባላል?
2. መቼና የት እንደተወለዱ አስተዳደግዎን ጨምረው ቢገልጹልኝ?
3. ወደ ቅኔ ሙያ እንዴት ሊገቡ ቻሉ?
4. የቅኔ ትምህርቱንና እውቀቱን የት ሊያገኙትና ሊማሩት ቻሉ?
5. ወደ ቅኔ ትምህርቱ ሲገቡ የቤተሰብ ፈቃድ እንዴት ነበር?
6. የቅኔ ትምህርቱን ሲጀምሩ የነበረዎት አመለካከት ምን ነበር?
7. የቅኔ ትምህርቱ አልከበደዎትም ነበር?
8. እንደሚታወቀው ቅኔ የሚቀኙትም ሆነ የሚማሩት ወንዶች ናቸው ነገር ግን እርስዎ የሴት ቅኔ ዘራፊ ለመሆን እንዴት ወሰኑ?
9. እንግዲህ እርስዎ ቅኔ ከመቀኘትም አልፈው ያስተምራሉ ወደየትኛው ይበልጥ ያደላሉ?
10. በእርስዎ አረዳድ ቅኔ ምንድነው ይላሉ?
11. ከቤተሰብዎ ውስጥ የቅኔ እውቀት ያለው ይኖር ይሆን?
12. የቅኔ ዕውቀቱን ለማወቅ ወይም ለመማር ምን ያህል ጊዜ ፈጀብዎት?
13. በዚህ ደብር ሴቶችን እንዲያስተምሩ ፈቃዱ የማነው?
14. የእርስዎን ቅኔ የማስተማር ጉዳይ የአካባቢው ማህበረሰብም ሆነ በገዳማቱ ውስጥ ያሉ ሊቃውንት እንዴት ያዩታል?
15. የተማሪዎቹ የቅኔውን ትምህርት አቀባበል እንዴት ያዩታል?
16. ምን ያህል ተማሪዎችን ያስተምራሉ?
17. ከተማሪዎችዎ ጋር ያለዎት ግንኙነት ምን ይመስላል?
18. ቅኔዎች በምን አጋጣሚ ይፈጠራሉ?
19. የተማሪዎቹ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዴት ነው?በቃል፣ የትምህርቱ አይነት? በሳምንት ስንት ቀን? ለምን ያህል ሰዓት?
20. ቅኔውን ማስተማር ከጀመሩ ምን ያህል ጊዜ ይሆንዎታል?

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | መኖሪያ ቦታ | የትምህርት ደረጃ | ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | እማሆይ አመተ ማርያም አሰፋ | ሴት | 44 | ባህር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል | የቅኔ መምህርና በግዕዝ ቋንቋ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ | መምህር |
| 2 | እማሆይ ኅሪት ደባስ | ሴት | 45 | ዲማቅዱስጊዮርጊስገዳም | የቅኔ መምህር | መምህር |
| 3 | መርጌታ አለማየሁ ዳኜ | ወንድ | 46 | ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም | የቅኔ መምህር | መምህር |
| 4 | ሳሙኤል አዳነ | ወንድ | 25 | ባህር ዳር ፈለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል | የቅኔ ተማሪ | ተማሪ |
| 5 | ወለተ ሥላሴ ያለው | ሴት | 23 | ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም | የቅኔ ተማሪ | ተማሪ |

## አባሪ ሦስት
የተለያዩ የምስል ማስረጃዎች



ምስል 3. ሴት የዳዊት ተማሪዎች





ምስል 4. እማሆይ አመተማርያም ከቅኔ ተማሪዎች ቅኔ ሲነግሩ



ምስል 5. ተማሪ ልሳኑ ቅኔ ሲነግሩ



ምስል 6. አጥኚዋ ቃለ መጠይቅ ስታደርግ